Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ
Seek Wisdom, Elevate your Intellect and Serve Humanity

# ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአራቱ ሃይማኖቶች የአማርኛ መዝሙራት ግጥሞች


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐግብር

በ

## የማርያምወርቅ ተሻገር

ሰኔ 2015 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

# ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአራቱ ሃይማኖቶች የአማርኛ መዝሙራት ግጥሞች

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐግብር

በ

የማርያምወርቅ ተሻገር

አማካሪ

የወንድወሰን አውላቸው (ዶ/ር)

ሰኔ 2015 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐግብር

# ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአራቱ ሃይማኖቶች የአማርኛ መዝሙራት ግጥሞች

በ

የማርያምወርቅ ተሻገር

አማካሪ

የወንድወሰን አውላቸው (ዶ/ር)

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| ------------------------------- | ----------------- |
| የፈታኝ ስም | ፊርማ |
| -------------------------------- | ---------------- |
| ------------------------------- | ----------------- |

## ምስጋና

ከታናሽነቴ ጀምሮ የረዳህኝና የምትረዳኝ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! ውለታህንና ቸርነትህን ባሰብኩ ቁጥር እደነቃለሁ፤ ስለረዳኸኝም ከልቤ አመሰግንሃለሁ፡፡ እምዬ፣ እናቴ፣ አዛኜ፣ ስደክም ጉልበቴ፣ ሳዝን መጽናኛዬ፣ የመዓልት ምርኩዜ፣ የሌሊት መብራቴ እናቴ፣ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም በእያንዳንዱ የሕይወቴ ጉዞዎች አጠገቤ አለሽና አመሰግንሻለሁ፡፡

ውድ ጊዜህን ሠውተህ ከአጠገቤ የነበርከው በሐሳብ የረዳኸኝ፤ ጋሼ፣ መምህሬና አማካሪዬ ዶክተር የወንድወሰን አውላቸው ስለበጎነትህ አመሰግንሃለሁ፡፡

ጥናቴ እንዲሳካ የበኩላችሁን አስተዋጽዖ ሳደረጋችሁልኝ የማኅበረ ቅዱሳን አገልጋይ ፍቃዱ ምሕረቴ፣ ዘማሪት አዜብ ከበደ፣ ዘማሪት ትንቢት ቦጋለ፣ ዘማሪ በርሱፍቃድ አንዳርጋቸው፣ ዘማሪት ለምለም ከበደ እና መልአከ ገነት በለጠ ይረፉ (ከአሜሪካ) የሚቻላችሁን አግዛችሁኛልና አመሰግናችኋለሁ፡፡

ዑስታዝ አቡበከር አሕመድ፣ ዶክተር ሀሰን ካዎ፣ ደራሲና ጋዜጠኛ ሁሴን ከድር፣ ፕሮፌሰር አደም ካሚል፣ ሙነሽድ አሊአሚን፣ ሙነሽድ አስማማው አሕመድ፣አቶ ዑስማን አደም፣ ነሽዳዎችና መንዙማዎች፣ አጋዥ መጻሕፍትን የት እንደሚገኙ በመጠቆምና አንዳንድ ግልጽ ያልሆኑልኝን ነገሮች በማብራራት ረድታችሁኛልና አመሰግናለሁ፡፡

ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አባ ጴጥሮስ ባረጋ፣ አባ ዳዊት ውብሸት፣ ዘማሪና የአቢይ ዘርዓ ክህነት ተማሪ ራእይ ዮሐንስ፣ ዘማሪት ሐና ዮሐንስ፣ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዘማሪዎችን መዝሙራት ለመሰብሰብ ባደረግሁት ጥረት እናንተ ከጎኔ ባትኾኑ ኑሮ አይሳካም ነበር፤ ስለቀናነታችሁ አመሰግናለሁ፡፡

ዘማሪት ሶፊያ ሽባባው፣ ፓስተር ዘሪሁን ግርማ፣ ጋዜጠኛ ዘካርያስ ብርሃኑ ሊያግዙኝ የሚችሉ ሰዎችን አድራሻ በመስጠት፣ መዝሙራትን በመስጠት፣ ጽሑፎችን በመስጠት ስላገዛችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

በመጨረሻም በጥናቱ ዙሪያ ሐሳብ አስተያየት የሰጣችሁኝ እና የረዳችሁኝን ዶክተር የኔዓለም አረዶንና ዶክተር አራጌ ይመርን አመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫ


አርእስት ገጽ

ምስጋና ... i
አጠቃሎ ... iv
ሙዳዬ ቃላት ... v
ምህጻረ ቃላት ... viii
አበርክቶ ... ix
ምዕራፍ አንድ ... 1
መግቢያ ... 1
1.1.የጥናቱ ዳራ ... 3
1.2.የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት ... 8
1.3. የምርምር ጥያቄዎች ... 9
1.4.የጥናቱ ዓላማ ... 10
1.4.1. አጠቃላይ ዓላማ ... 10
1.4.2. ንዑሳን ዓላማዎች ... 10
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ... 10
1.6. የጥናቱ ወሰን ... 11
1.7. የጥናቱ ዘዴ ... 12
1.8. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ... 12
ምዕራፍ ሁለት ... 16
ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ... 16
2.1. ጽንሰ ሐሳብ ... 16
2.1.1. የመዝሙር ምንነት ... 16
2.1.2. የነሽዳ ምንነት ... 17
2.1.3. የመንዙማ ምንነት ... 18
2.1.4. የመዝሙር ባህሪያት ... 19
2.1.5. የመዝሙር ጠቀሜታ ... 21
2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ... 22
2.3. የንድፈ ሐሳብ ማዕቀፎች ... 26
2.4. የፖለቲካ ምንነት ... 29
ምዕራፍ ሦስት ... 31

የመረጃ ትንትና ........ 31
3.1. ፖለቲካዊ ድምፀት ያላቸው መዝሙራት ........ 31
3.1.1. ዘረኝነትን ኮናኝ መዝሙራት ........ 31
3.1.2. የአንድነት አናጺ መዝሙራት ........ 41
3.1.3. ሃያሲያነ መንግሥት መዝሙራት ........ 49
3.1.4. አጽራረ ኢትዮጵያ በመዝሙራቱ ........ 52
3.2. ሀገራዊ ድምፀት ያላቸው መዝሙራት ........ 60
3.2.1. ሀገረ ታሪክ ዘካሪ መዝሙራት ........ 61
3.2.2. ሀገር ፍቅር አዝማሪ ........ 65
3.3. ማኅበራዊ ድምፀት ያላቸው መዝሙራት ........ 70
3.3.1. ኀሠሣ ይቅርታ መዝሙራት ........ 71
3.3.2. ሴብነትን ገናኟ መዝሙራት ........ 77
3.4. መባያዎች /Motifs/ ........ 78
3.4.1. በኦርቶዶክስ፣ በእስልምና፣ በካቶሊክ፣ በፕሮቴስታንት መዝሙራት ያሉ መባያዎች ........ 79
3.4.2.. በኦርቶዶክስና በእስልምና ብቻ ያሉ መባያዎች ........ 85
3.4.3. በኦርቶዶክስ፣ በካቶሊክ፣ በፕሮቴስታንት መዝሙራት ብቻ ያለመባያ ........ 95
3.4.4. በኦርቶዶክስና በካቶሊክ ብቻ ያለ መባያ ........ 97
3.4.5. በኦርቶዶክስ ብቻ ያሉ መባያዎች ........ 100
ምዕራፍ አራት ........ 112
4.1. ማጠቃለያ ........ 112
4.2. የጥናቱ ግኝት ........ 113
4.3. የይሁንታ ሐሳብ ........ 116
ዋቢ ጽሑፎች ........ 117
አባሪዎች ........ X

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት “ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአራቱ ሃይማኖቶች የአማርኛ መዝሙራት ግጥሞች ውስጥ” በሚል ርእስ የተሠራ ነው፡፡ እነዚህም ሃይማኖቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የእስልምና፣ የካቶሊክ እና የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ መዝሙራት ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን የተመለከቱ ጉዳዮች ተተንትነውበት የተሠራ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ዓላማ አድርጎ የተነሣው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአራቱም ሃይማኖቶች የመዝሙር ግጥሞች እንዴት እንደቀረበ ለመፈተሽ ነው፡፡ ጉዳዩን የተመለከቱ ዝማሬዎችን ሰብስቦ በርእሰ ጉዳዮቻቸው በመበደን ይዘታቸውን እያብራራ አስፍሯል፡፡ ይህ ዓላማ ግቡን እንዲመታ በአራቱም ሃይማኖቶች ውስጥ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የሚያቀነቅኑ መዝሙራት የትኞች ናቸው? ምን ብለው ነው ያነሡት? ምንስ ፋይዳ ነበራቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሣት ጥናቱ የሚፈልገውን መረጃ እንዲያገኝ አድርጓል፡፡ የጥናቱ ወሰንም ጉዳዩን የተመለከቱ መዝሙሮቹ፣ ነሽዳዎች፣ መንዙማዎች ከ1983 ሰኔ እስከ 2013 ነሐሴ የተሠሩትን ያካትታል፡፡ መዝሙሮቹ በተለይ በኢህአዴግና በብልጽግ የአስተዳደር ዘመን የተዜሙ ሲሆኑ በመንፈሳዊ መዝሙር ውስጥ የተለያዩ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ጉዳዮች ውስጥ እንዴት እንደቀረቡ በመተንተን ድምፀታቸውን ያጠና ነው፡፡ በጥናቱ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቀዳማይና ካልአይ የመረጃ ምንጮች ተካተውበታል፡፡ በዋናነት የተጠቀመው የመረጃ ምንጭ በሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ ተጠቅሟል፡፡ ለሰበሰብኩት መረጃ መተንተኛ የንድፈ ሐሳብ ማሕቀፎች ብዬ የተጠቀምኳቸው ተግባራዊ ወይም ጠቀሜታዊ ሲሆን ሁለተኛው ማኅበራዊ ሂስ ነው፡፡ የመተንተኛ ስልቱ ደግሞ የይዘት ትንተና (content analysis) ነው፡፡ የሰበሰብኳቸው 1900 መዝሙራት መካከል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ የሚያጠነጥኑ 49 መዝሙራትን አግኝቻሁ፡፡ ይህም ያነሣሁትን ርእሰ ጉዳይ በቀጥታ ሊያገዝፉልኝ የሚችሉትን ብቻ የተመለከተ ነው፡፡ መዝሙራቱ በአጥኚው ሲቃኙ በመዝሙሮቻቸው የምእመናኑን መሻትና ብሶት፣ ሕዝባቸው እና ሀገራቸው ከፈጣሪያቸው ጋር ያላቸውን የግንኙነት ልሥላሴና ሽክረት በዘመን መንፈስ ውስጥ በልዩ ልዩ ድምፀት ያለ ፍርሃት ገልጸዋል፡፡ መዝሙሮቹ፣ ነሺዳዎቹ፣ መንዙማዎቹ በኢህአዴግ ብልጽግና ሥርዓተ መንግሥት ጊዜ የቀረቡ በመሆናቸው የየዘመኑን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ክሥተቶችን ምን ነበርነትን እና ምን አለነትን ያሳዩ የዘመኑ የሕዝብ ድምፅ ሆነው በጥናቱ አገልግለዋል፡፡

## ሙዳዩ ቃላት

ሀዲስ= ነብዩ መሐመድ ሰአለት ዐለል ወሰላም የተናገሩት ያስተማሩት ያስተላለፉት ትምህርት መልእክት ሥራ የያዘ መጽሐፍ

ህልቅ= ፍጥረት

ሃሌ ሉያ= ዓለምን በአንድነት ቃል የመሠረተውን ክቡርና ምስጉን የሆነውን የነበረውን ያለውንና የሚኖረውን ልዑል እግዚአብሔርን እናመስግን ማለት ነው።

ሐሩር= ከባድ ፀሐይ

መቅራት= ማንበብ መማር

ሙሐባ= ፍቅር

ሠራፐታ= ረኃብ የጸናባት ከተማ

ሩሀ= ነፍስ፣ መንፈስ፣ ሕይወት

ራህመት= ዕዝነት፣ ማዘን

ራህማን= አንተ አዛኝ ሆይ፤

ራደ= ተንቀጠቀጠ፣ ፈራ፣

ሱረትል= ምዕራፍ

ስምዐ= ምስክር

ሶሐባ= ባልደረባ

ሽርክ= መጋራት

ቁር= ብርድ

ብካያ= ልቅሶ

ብፅዕት= ያመነች

ተሰዓት= ዘጠኝ

ታዛ= መጠጊያ

ኑሥራህ= እገዛ፣ እድል፣ የፈጣሪ እርዳታ

ኒዕማ= ጸጋ

ኖላዊ ኄር= ቸር እረኛ

አርሽ= ጥላ የፈጣሪ ዙፋን

አራራይ= በባሕርዩም ልብን የሚመስጥ የሚያራራ አእምሮን ሰብስቦ የመያዝ ዐቅም ያለው ልዩ ዜማ ነው፡፡

አበው= አባቶች

አብርሂ= አብሪ

አኬልዳማ= የደም መሬት

አኺራ= መጪው ዓለም፣ ዘላለማዊ ሕይወት፣ የሰማዩ ሕይወት

አዶናይ= ሁሉን ቻይ

ኢማን= እምነት

ኪታብ= መጽሐፍ

ኪዳን= መሐላ

ዕዝል= ታዛይ ወይም ተደራቢ ማለት ነው። ምክንያቱም ከግእዝ ጋር ተደርቦ አንዳንድ ጊዜም ተቀላቅሎ ስለሚዜም ነው። ዕዝል በዜማ ባሕርዩ ልክ እንደ ግእዙ ሁሉ ማኅዘኒ የሚያሳዝን የሚያስለቅስ አሳዛኝ ማለት ነው።

ወፈቀ= ገጠመ፣ ሰጠ፣ ለገሰ

የመሪባ ውኃ= መራራ ውሃ

ያረቢ= ጌታ ሆይ

ግእዝ= አንደኛ የመጀመሪያ ዜማ ማለት ነው። በባሕርዩም ሲታይ ጠንካራና ለማዜምም ኀይለኛ ሆኖ እናገኘዋለን። በዚህም የተነሣ ሊቃውንቱ ከሌሎቹ ይልቅ ደረቅ ዜማ ወዙ ወይም ቅላጼው ለዛው በቀላሉ የማይያዝ ነው ይላሉ።

ዱንያ= ምድራዊ ሕይወት

ጭረት= ማለት በዜማው መካከል ካለው ንባብ አንዱን የፊደል ዘር ወይም ቃል መጎተት ወይም መሳብ ሲሆን አንገትህን ወደ ላይ አቅንተህ የምታዜመው ማለት ነው።

ድፋት= ማለት ድምፅህንና አንገትህን ወደታች እርግጥ አድርገህ ደፍተህ ትንፋሽህን ወደ ውስጥ እንደመሳብ ብለህ ማዜም ነው።

ጀሊል= ፈጣሪ፣ የልዕልና ባለቤት፣ ጌታ

ጁንድ= ወታደር፣ ሠራዊት

ጸባዖት= የእግዚአብሔር መንበር መገኛ

ጽድቅ= እውነት

ፈሰድ= ብልሹ፣ ከንቱ፣ የማይረባ

## ምህጻረ ቃላት

ሉቃ.= ሉቃስ

መዝ.= መዝሙረ ዳዊት

መ.ነገ.= መጽሐፈ ነገሥት

ማር.= ማርቆስ

ማቴ.= ማቴዎስ

ሰ.ዐ.ወ= ነቢያችን መሐመድ ሰዐለት ወሰላም

ት.ሐጌ.= ትንቢተ ሐጌ

አ.አ.= አዲስ አበባ

ኤር.= ትንቢተ ኤርሚያስ

ኪ.ወ.ክ.= ኪዳነ ወልድ ክፍሌ

ዓ.ም= ዓመተ ምሕረት

ዘፍ.= ዘፍጥረት

ዮሐ.= ዮሐንስ

የሐዋ.= የሐዋርያት ሥራ

ገላ.= ገላቲያ

ጢሞ. ጢሞቴዎስ

ዲ.ን= ዲያቆን

ዶ/ር= ዶክተር

ጴጥ.= ጴጥሮስ

## አበርክቶ

# ለአባቴ አቶ ተሻገር አቻነፍ

## ምዕራፍ   አንድ

## መግቢያ

ይህ ጥናት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአራቱ ሃይማኖቶች የአማርኛ መዝሙራት ግጥሞች ውስጥ ሲሆን፤ እነሱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት፣ የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ናቸው፡፡ ጉዳዩን የተመለከቱ መዝሙሮቹ፣ ነሽዳዎች፣ መንዙማዎች ከ1983 ሰኔ እስከ 2013 ነሐሴ የተሠሩትን ያካትታል፡፡ መዝሙሮቹ በተለይ በኢህአዴግ ብልጽግና  የአስተዳደር ዘመን የተዜሙ ሲሆኑ በመንፈሳዊ መዝሙር ውስጥ የተለያዩ ኢትዮጵያዊነትን  በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ጉዳዮች ውስጥ እንዴት እንደቀረቡ በመተንተን ድምፀታቸውን ያጠና ነው፡፡

መዝሙራት ለጸሎት፣ ለማመስገንና ለመለመን ከማገልገላቸው ባሻገር ሀገራዊ ጉዳዮችን ለማስተላለፍ ያላቸውን ዐቅም ጥናቱ ቃኝቷል፡፡ መዝሙር ምስጋና ብቻ አይደለም፤ በርካታ ጉዳዮችን የሚያስተነትን ነጥብ ነው፡፡ በመዝሙር ፈጣሪ ብቻ አይደለም የሚመሰገነው የፈጣሪ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም፣ መላእክት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ሱሐቦችና የፈጣሪ ምርጦች፣ እንደክብራቸው መጠን ይሞገሱበታል፤ ይቀደሱበታል፤ ሀገርም ትመሰገንበታለች፤ ትቀደስበታለች፤ ሕዝቦቿም ከጥፋት ጋር እንዳይውሉ ፈጣሪያቸውን እንዲያመሰግኑ ይደረግበታል፡፡ (ሰሎሞን፣ 13)

የአማርኛ መዝሙራት ድክመቶችና ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው?፡፡ (በማኅበረ ቅዱሳን፣10) የሚለው መጽሐፍ የመዝሙር ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ አከፋፈል፣ ዐይነቶች፤ ይዘት በአማርኛ የመዝሙር ግጥም ምን እንደሚመስል የሚያስረዱ ነጥቦችን በዝርዝር አቅርቧል፡፡ ሌላው "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና በፕሮቴስታንት እምነት በካሴት እና በሲዲ የወጡ የአማርኛ መዝሙር ግጥሞች ጥናት፡፡ (ዘካርያስ ብርሃኑን፣ 2010፣ 42) (ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ) በማለት ባጠናው ጥናቱ በኢ.ኦ.ተ.ቤ እና በፕሮቴስታንተን እምነት ውስጥ ከአምስት አልበም በላይ ባወጡ ከ1960ዎቹ እስከ 1990 ዎቹ እንዲሁም ከ2000 ዓ.ም. በፊት በማለት ገድቦ አጥንቷል፡፡

ከእነዚህ ቀደምት ሥራዎች በተጨማሪ (ተሾመ ብርሃኑ፣ 31) ከ1983 እስከ 1985 ዓ.ም. የመንግሥት ሽግግር ወቅት፤ የተዘፈኑ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ድምፀቶች (በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች ማሳያ) (ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ) ተሠርቷል። ጥናቱ በዐቢይ ዓላማነት በመንግሥት ሽግግር ወቅትን ተከትሎ የተዘፈኑ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ነክ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ያስተላለፏቸውን ዋና ዋና ድምፀቶች በመተንተን፤ በዘፈኖቹ ግጥሞች ውስጥ የተጠቀሟቸውን ድምፀቶች በመለየት የጊዜውን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እንዴትነት መፈተሽ በሚል የተሠራ ነው። ይኸው አጥኚ የተለያዩ አጥኚዎችን ዋቢ አድርጎ እንደሚያስረዳው

> "Timkhet፣ 2009፣ 2 እና Ashenafi፣ 1976፣289። የሙዚቃ ግጥሞች የአንድን ማኅበረሰብ ሁለንተናዊ አኗኗር፣ ባህል፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ሌሎች መሰል ጉዳዮችን የመግለጽ፣ የማሳወቅና የመሰነድ ዐቅማቸው ከፍተኛ ነው። Geite(1999፣172) "Amharic poems and songs play a significant role in reflecting serious contemporary issues and problems of society, besides their function as entertainment and instruction in the daily lives…" በማለት የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ከማዝናናት ባሻገር በማኅበረሰቡ ውስጥ የላቀ ሚና እንዳላቸውና በየጊዜው ብቅ የሚሉ ማኅበረሰባዊ ችግሮችን የማንፀባረቅ ተግባር እንደሚከውኑ ያብራራሉ።"

በማለት ያስረዳል።

ዘፈኖች ከላይ የተመለከትነውን ዐይነት ሚና ካላቸው፤ መዝሙራት በግጥሞቻችው የሀገር ፍቅርን እና አንድነትን፣ ተቆርቋሪነትን እና አብሮ መኖርን፣ ፈጣሪ ከሀገራቸው ጋር እንዲሆን ቀን እና ሌሊት መለመንን፣ በተከታዮቻቸው ልብ ውስጥ ለመቅረጽ የሚችሉ መሆናቸውን፤ በመከባበር ላይ የተመሠረተች ሀገርን በማጠናከር ሰላምን አስፍኖ ሀገርን ለማስቀጠል መጥቀሙ፤ የሀገርን ፍቅርን በሰዎች ልብ ላይ ለመትከል የሚያግዙ መሆናቸውን እንገነዘባለን።

ይህ ጥናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት፣ የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት የአማርኛ የመዝሙር ግጥሞች ውስጥ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንዴት እንደቀረበ የሚፈተሽበት ብቻ ነው። ጥናቱ በዐይነታዊ የምርምር ዐይነት ሥር ያለውን ገላጭ የአቀራረብ መንገድ ተከትሏል። የመተንተኛ ስልቱ

ደግሞ የይዘት ትንተና (content analysis) ነው፡፡ የመረጃ ምንጮቹ ሁለት ናቸው፡፡ በቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ሥር በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተዘመሩትን ሀገራዊ መዝሙራት ሲሆኑ ደኃራዊ ምንጮቹ ደግሞ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አጋዥ መጻሕፍት ናቸው፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት[1] በአራቱ ሃይማኖቶች የአማርኛ መዝሙራት ግጥሞች የሚለውን ርእስ ስንመለከት ኢትዮጵያ ፈጣሪያቸውን የሚፈሩ ሕዝቦች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ በሦስተኛው የሕዝብ ቆጠራ 1999 ዓ.ም.‹‹73 ሚሊዮን 918 ሺህ 505 ደርሶ እንደ ነበር ይታወቃል፡፡ በዚህም ኦርቶዶክስ 32,138,126፣ ሙስሊም 25,045,055፣ ፕሮቴስታንት 13,746,787፣ ካቶሊክ 536,827 መሆናቸውን›› Ethiopiazare.com (ኅዳር፣ 2001) ጠቅሷል፡፡ ይኼ በፐርሰንት ሲቀመጥ 62.8 በመቶው ወይም 46,421,740 ያህሉ የክርስትና እምነት 33.9 በመቶው ወይም 25,045,550 ያህሉ የእስልምና እምነት ተከታይ፤ ሌሎቹ 3.3 በመቶ መሆናቸውን የቆጠራው ውጤት አመልክቷል፡፡

ይኼ አሃዝ ኢትዮጵያ ሃይማኖት እና ሃይማኖተኞች ያሉባት ምድር መሆኗን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሬቷ የሚኖረው ሕዝብ 96.7 በመቶው ሃይማኖተኛ ነው፡፡ ይኸ ሕዝብ የራሱ ታሪክ፣ ባህል፣ ቅርስ መግባቢያ ቋንቋ አለው፡፡ ሲያገባ የሚሰረግበት፣ ሲሞት የሚቀበርበት፣ ሐዘንና ደስታውን፣ ቅሬታና ድጋፉን የሚገልጽበት ዘመን የማይሽረው ማንነት ያለው ሕዝብ መኖሪያ ናት፤ ኢትዮጵያ፡፡

ኢትዮጵያ ሀገር ናት ሲባል በዓለም መንግሥታት ዘንድ የታወቀ ዳር ድንበር፣ መንግሥት፣ ሕዝብ ያላት፤ ከሌሎች ሀገራት የሚመስላትም ሆነ የሚለያት የራሷ የብቻዋ የሆነ መገለጫ ያላት ምድር ናት፡፡ “ሀገር በታሪክ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በልማድ፣ በተስፋ፣ በደስታና በመከራ ተሳስሮ የሚኖር አንድ ወገን ሕዝብ የሚኖርበት የዓለም ክፍል ነው” ይላሉ፡፡ (ከበደ፣ 72)

እነዚህ ጣራና ግድግዳውን ሰፍተው የያዙ ምሶሶዎች ባይኖሩ ኑሮ አሁን ያለችውን ኢትዮጵያን በዚህ ሁኔታ እኛ እጅ ላይ አትደርስም ነበር፡፡

[1] ታሪኩ፣ 56 አማርኛ ሁሉ ለሁሉ፡፡ በሚለው መጽሐፉ፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚለውን እንደ ስም ስምን

> ሰው ከመሬት፣ ሰው ከአራዊት፣ ሰው ከተፈጥሮ፣ ሰው ከወራሪ ጋር የነበረው ትግል፣ ውጊያና ወዳጅነት፣ ተረት፣ ያወጋው ወግ፣ የፈጠረው አፈታሪክ፣ ያከማቸው ትዝታ፣ ሰው ለመሬቱ፣ ለወገኑና ለእምነቱ የከፈለው መሥዋዕትነት፣ የዘፈነው ዘፈን፣ ያቅራራው ቀረርቶ፣ የፎከረው ፉከራ፣ ያገኘው ድልና የተሸከመው ሽንፈት፣ ያደረገው በደልና የደረሰበት በደል ይኼ ሁሉ ነው ሀገር። መገለጫው ቅርስ መዋሐጃው ባህል፣ መታያው ልብስና መዋቢያው ጌጣጌጥ፣ መገናኛው ቋንቋ፣ መዝናኛው ጭፈራ ማስተማሪያው ተረት... ይኼ ሁሉ ነው ሀገር። (ዳንኤል፣ 19)

ጥናቱ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ ነውና ስለ ሀገር ማንሣት ግድ ይለኛል፤ ስለ ሀገር ሳነሣ ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ መሆኑ ግልጽ ነው።

> በቅዱሳት መጻሕፍት በጥንታውያን የታሪክ ሰነዶችና የሥነ ጥናት ጥናቶች ከታወቁት የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝብና አህጉር መካከል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ቅድሚያ ቦታን ይዘው ይገኛሉ። ኢትዮጵያ የቃሉ ትርጉም ጥቁር ማለት ነው ኤር. 13፡23 በግሪክና በመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲያን አስተሳሰብ ኢትዮጵያ ከግብጽ በስተደቡብ ጥቁር አባይና ነጭ አባይ እስከሚገናኙበት የነበረ ሀገርና መንግሥት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ከ40 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። .... ይሁንና ኢትዮጵያን በሥነ ሰብአ Anthropology ጥናትና ምርምር ከዘር ትውልድ መካከል በፀሐይ ግለት የጠየሙ (the shadow clour of skin) ሆነው የሚገኙ ዘርዐ ትውልድ ሲሆኑ የሚኖሩበትም አካባቢ ከመልካቸው ጋር የተዛመደ መልክ ኢትዮጵያ ተብሎ ተሰይሟል። (ኃይለ ማርያም፣ 61)

ኢትዮጵያዊ፣ ኩሽ፣ አቢሲኒያ፣ ሳባ፣ አኩሱም፣ ሐበሻ፣ ፑንት እየተባለች ትጠራለች። በእነዚህ ሃይማኖቶች በመዝሙር፣ በነሽዳ እና በመንዙማ ውስጥ ስሟ እንደአመችነቱ በልዩ ልዩ ሕብር ተገልጦ ይገኛል።

ሀገሪቱ እና ሕዝቦቿ አንድ ሆነው ሳለ፤ ስሟ ብዙ የሆነበት ምሥጢርም የኋላ ታሪኳ መሆኑን በኢትዮጵያ ላይ ሰፊና ከፍተኛ ምርምር ያደረጉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ (ጎርጎርዮስ፣ 62 ፤ ኃይለ ማርያም፣ 12 ፤ቴዎድሮስ፣ 17)

ኢትዮጵያ ስንል ሕዝቦቿን ተራራውን፣ ባህሉን፣ ጋራው ድንበሩን፣ ትዝታውን፣ ሙሾ እንጉርጉሮውን፣ ሥነ ቃሉን፣ ክውን ጥበቡን፣ ልምዱን እምነቱን ሁሉንም ሃይማኖት፣ ማንነት፣ ባህል፣ ሕዝብ ሸምኖ የያዘውን ገመድ ማለት እንደሆነ ከፍ ብሎ ተጠቅሷል፡፡

ከኢትዮጵያ በመነሣት ኢትዮጵያዊያን የተባሉ ሕዝቦችን ሸምነው እና ገምደው የያዙ የጋራ ሀገራዊ፣ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ የጋራ እሴቶች አሉ፡፡ ሕዝቦቿ እርስ በእርስ ተዋሕደው ተደጋግፈው እንዲኖሩ ያስቻሉ ካስማዎች አሉ፡፡

ለዚህ ፀሐፊ የኢትየዮጵያና የኢትዮጵዊነት ማንነት እና ምንነት መሠረታዊ ጥያቄ የተቀበረው በኢትዮጵያ የመንፈሳዊ ህልውና ላይ እንደሆነ ሙሉ እምነቱ ነው፡፡ ምንም እንኳ መንፈሳዊ እሴቶች የሚባሉት በጣም ጥልቅና ብዙ ቢሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ በጥቅሻ የሚነሡት፤ በተለይ አሁን ያለውን የፖለቲካና የማኅበራዊ ውጥረት በሰላም ለመፍታት አማካኝና ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉት ሦስት መንፈሳዊ እሴቶች ናቸው፡፡ እኒህም ‹‹የሕገ ሕሊና መንፈስ›› ፣ ‹‹የሽምግልና መንፈስ››ና ‹‹የይቅርታ መንፈስ›› (አቤል፣ 12)

ኢትዮጵያዊነት ሲባል ደግሞ ከኢትዮጵያ የተነሣ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ መነሻ ከሌለ መድረሻ የለም፤ የጥናቱ ማጠንጠኛ የሆኑት ኦርቶዶክስ፣ እስልምና፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት የሚዘምሩላት፣ የሚሰብኩላት፣ የሚያቀነቅኑላት ሀገር ኢትዮጵያ ከሆነች ከእርሷ ምድር የበቀሉት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ይባላሉ፡፡

ሀገርን መውደድ ሀገርን ማፍቀር ለሀገር መድከምና መሞት ከእርሷ የተነሣ ነው “**የዘላለማዊቷ** መንግሥት ማኅደርና ባለ አደራ የኾነችውን ኢትዮጵያን፣ ከእርሷ የተነሣ ኢትዮጵያዊነትን (አጽንዖት ከራሴ) እናንተ የዛሬዎቹ አዳምና ሔዋን ከእነርሱ የወረሳችሁ መሆናችሁንም ተገንዝባችኋል፡፡ እነዚያኑ ሕያዋን ቅርሶች ለተተኪው ትውልድ ታስረክቡ ዘንድ እነሆ ኃላፊነቱና ግዴታውን እናንተ ጫንቃላይ ወድቆ የሚገኝ በመሆኑም ተረድታችኋል፡፡›› (ኤርሚያስ፣ 113) አራቱም ሃይማኖቶች ዘወትር የሚያነሷትን ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት? እንዲህ ከተነሣ ሃይማኖት ምንድን? ነው የሚለውን እንይ፡፡

እነዚህ አራቱም ሃይማኖቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ነው የሚኖሩት፡፡ አራቱም የራሳቸው ሥርዓተ አምልኮና ምእመኖቻቸውን የሚይዙበት፣ የሚሰብኩበት፣ የሚያስተዳድሩበት መንፈሳዊ ሕግ አላቸው፡፡ ዓለምን የፈጠረ፣ የሚያስተዳድር፤ የሚገዛ ኃይል አምላክ እንዳለ ያምናሉ፤ በጎነትንና መልካምነት፤ ሀገርንና ሰውን መውደድን፤ ፈጣሪን መፍራትን ያስተምራሉ፡፡ ክፋትንና ምቀኝነትን፤ ሽብርና ሁከትን፣ ሌብነትን ጉቦኝነትን፣ ስግብግብነትንና ንፋግነትን፣ ዘረኝነትን እና መለያዬትን ይጸየፋሉ፡፡ በምጽአትና በመጨረሻ ፍርድ ያምናሉ፡፡ ታዲያ ሁሉንም አማኞች አንድ ያደረጋቸው ሃይማኖት ምንድነው? ስንል፡-

ሃይማኖት ውስብስብ እና ሰፊ ጽንሰ ሐሳብን የያዘ ቃል ነው፡፡ ለመበየንም አስቸጋሪ ነው፡፡[2] በማኅበራዊ ሳይንስ፣ በሥነመለኮት፣ በሥነ ሰብእ፣ በታሪክ ወዘተ አጥኝዎች ዘንድ እንደየ ዲስፒሊኑ ልዩ ልዩ ትርጓሜዎችን ይይዛል፡፡ የማኅበራዊ ሳይንስ አጥኝው Durkhim እንዲህ ይላል ‹‹Religion is something eminently social /ሃይማኖት በጣም ማኅበራዊ ጉዳይ ነው›› ይለናል፡፡ (Durkhim፣ 253)

ጠቃሚ ተግባራትን ከጎጂዎች የሚለየው ደግሞ ሃይማኖት ብቻ ነው፡፡[3] ሌላው ደግሞ "በጌታ ደም የተመሠረተች እንጂ በፍጡር ፍልስፍና የተመሠረተች አይደለችም፡፡ ይህች ሃይማኖት የመላእክት ሃይማኖት ነች …" ብርሃኑ፣ 2003፣ 13 ሃይማኖት ትርጉሙና ምሥረታው ይለያል እንጂ ተግባሩ ግን አንድ ነው፡፡

አራቱም ሃይማኖቶች በተለያየ ጊዜ በልዩ ልዩ ታሪካዊ ዳራ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ናቸው፡፡ የኦርቶዶክስ ክርስትና ቀዳሚውን ቦታ ሲይዝ እስልምና ተከታዩን ይይዛል፤ የካቶሊክ እምነት እስልምናን ተከትሎ የገባ ነው፤ የፕሮቴስታንት እምነት ደግሞ ወደ ሀገር በመግባት አራተኛ ደረጃን ይይዛል፡፡ (ብርሃኑ፣ 49)

በተለይ በእስልምና ነሽዳና መንዙማ ውስጥ በተደጋጋሚ ጎልቶ የሚነሣው ነብዩ መሐመድ ሒዱ ወደ ሐበሻ ምድር ያሉትን ተከትሎ ኢትዮጵያን ሃበሻ በሚለው ስም በመተካት በብዛት ሲጠቀሙ ይስተዋላል፡፡ ኢትዮጵያ የሚለውን ስምም እንደ ሁኔታው ይጠቀሙበታል፡፡

---

[2] *"God cannot Keep Silent'" strong religious – Natiomalism – Theory and Practice Eran tzidkiahu.Research Question /Questions de Recherche N – 47 october 2015.*

[3] *ሀሰን፣ :51*

ኢትዮጵያ በሁሉም ሃይማኖቶች ዘንድ በክርስትናውም በእስልምናውም ስሟ እየተቀያየረ ደጋግማ በእናትነት፣ በመልካምነት፣ በአቃፊነት፣ በእንግዳ ተቀባይነት፣ በፍትሐዊነት፣ በአብሮነት፣ በዓልደፈር ባይነት፣ በቃል ኪዳን ምድርነት፣ በሀገረ እግዚአብሔርነት፣ በገናና ታሪክ ባለቤትነት፣ ከዓለም ታላላቅ ክሥተቶች እና አርዓያነት ጀርባ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንዳለ በቅዱሳት እና በታሪክ መጽሐፍቶቻቸው ያነሣሉ፤ ያወሳሉ።[4]

ከላይ የጠቀስኳቸው እና የጥናቴ መሠረት የሆኑት ሃይማኖቶች በዝማሬ፣ በነሽዳና በመንዙማ ግጥሞቻቸው ውስጥ ኢትዮጵያን በልዩ ልዩ ሕብር ገልጸዋታል። ያሉባትን ሀገራዊ ሕመሞች ይሆናል ከሚሉት መፍትሔ እንዲሁም ከዘመኑ መንፈስ ጋር አዋህደው መራራውን ሀቅ በመንፈሳዊ ጥበብ በኩል አንጸባርቀዋል። ስያሜው ይለያይ እንጅ ምዕራፍ ሦስት ላይ በምንጠቅሰው ተጨባጭ አመክንዮ ተነሥተን ሁሉንም መዝሙር በሚለው ቋት ውስጥ አካትተን መጥራት እንችላለን።

ይኽ የመዝሙር ግጥም ደግሞ በፎክሎር ውስጥ የሚጠና ጉዳይ ነው። በሚያስተላልፈው መልእክት ሀገረሰባዊ እምነት፤ በግጥሙ ስነቃል፣ በአካዋወኑ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ፣ ክዋኔውን ለማጀብ በሚውሉ መሣሪያዎች ቁሳዊ ባህል ያለበት መንፈሳዊ ጥበብ ነው። ጉዳዩ ይኼ ከሆነ ፎክሎር የሚለውን ነጥብ ላንሳ፤ ፎክ እና ሎር በሚሉ ሁለት ቃላት የተመሠረተ ጥምር ቃል ሲሆን፣ ፎክ (Folk) ቡድኑን የጉዳዩ ባለቤትን ሰዎችን የሚመለከት ሲሆን፣ ሎር (lore) ደግሞ ጉዳዩን የሚባልለትን ቡድኑን ያስተሳሰረውን የጋራ የሆነው ነገር ይመለከታል። (Dandes 417)።

የፎክሎር ጥናት ሰዎች የሚያስቡትን፣ የሚጨነቁበትን፣ የሚፈልጉትን፣ የሚጠሉትን፣ የሚወዱትን ነገር ለማወቅ ለመረዳት ሁነኛ መፍትሔ ነው። ፎክሎር የሰው ልጅ ስለአካባቢውና ስለ ዓለም ያለው ዕይታና ዕይታውን የሚገልጽበት ቃላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ቁሳዊ ሀብቶች፣ የማንነቱ ማሳያ አሻራ የሆኑትን ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈ ያቆያቸውን የሕይወት ዘመን ተመክሮዎች የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው። (ሰሎሞን፣ 1)። የዝማሬ ግጥም ደግሞ ከፎክሎር ዘርፎች በስነቃል ሥር ይጠናል።

---

[4] *ሙሐመድ, 32። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ታሪክ ልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻፣ 69። መጽሐፍ ቅዱስ (480)። ቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም (241)። ኢድሪስ፣ 78*

በሃይማኖት ስር ያሉ ምእመናን አምልኮታዊ ተግባራቸውን፣ ተስፋ ምኞታቸውን ኀዘን ደስታቸውን፣ ልመና ጸሎታቸውን የሚገልጡበት መግባቢያ አላቸው፡፡ ያ መግባቢያ መዝሙር ነው፡፡ ‹‹ መዝሙር መግባቢያ ቋንቋ ነው" (ያሬድ፣ 8)

እነዚህ የመዝሙር የነሽዳና የመንዙማ ግጥሞች ሃይማኖታዊ መልካቸውን እና እይታቸውን እንደጠበቁ በሥነ ቃል ጥላ ሥር ሲጠኑ ተግባራቸው ተግባሩ ስለሆነ ነው፡፡ ስነቃል የመግለጥ፣ የማጠናከር፣የመትከል፣ የማምለጥ፣ የማስተማር፣ የመቆጣጠር ተግባር አለው፡፡ (ፈቃደ፣ 42) እነዚህ ሁነቶች በሃይማቶቹ የዝማሬ ግጥሞች ውስጥ ታይተዋልና የባህሪ ውርርስ አላቸው፤ የተግባር አንድነት አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ በኦርቶዶክስ፣ በእስልምና፣ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ ዶግማና ቀኖናውን፣ ቁርዓኑንና ሀዲሱን ሳይጥሱ፤ መሠረታዊ የእምነት ምሰሶዎችን ሳይበጥሱ እና ሳይሸራረፉ፤ በሃይማኖታቸው ሕግና ደንብ መሠረት ሃይማኖታዊ ተልእኮውን ለማሳለጥ፣ግብ ለመምታት፤ አንድም ከመደበኛው ሥርዓት ጋር ተዋሕደው፤ ሁለትም ጎን ለጎን የሚካሔዱ አያሌ ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ መኖራቸው የታወቀ ነው፡፡

ይኸ ጥናት ደግሞ በአራቱ ሃይማኖቶች ስር በሚከናወኑ ፎልኮራዊ ጉዳዮች በአንዱ በመዝሙር ግጥሞች ውስጥ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንዴት እንደቀረበ የሚፈተሸበት ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊነት ሐበሻ፣ አቢሲኒያ፣ ሀገሬ የሚሉ ስሞች በተለያየ አውድ ውስጥ ሲነሡ ከራስጠጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ ይነዝረኛል፡፡ ኢትዮጵያ በደሜ የተዋሐደች፤ በአጥንቴ የቀለጠች፤ በሥጋዬ የሠረጸች ያህል ይሰማኛል፡፡ ወጣት እንደመሆኔ መጠን ሁለት መንግሥታትን አይቻለሁ፡፡ ዘመነ ኢህአዴግን እና ዘመነ ብልጽግናን፣ ሁለቱም መንግሥታት ኢትዮጵያ ውስጥ ነበሩ፤ አሉ፡፡ አንዱ በሐልዮ ሌላው በገቢር፡፡ እርሷ ግን በእነርሱ ውስጥ ትኑር አትኑር ሰፊ ጥናት ይፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያን ሀገሯን፣ ዳርደንበሯን፣ ሕዝቧን፣ ጋራ ሸንተራሯን፣ ሰላምና ጸጥታዋን፣ ርሃብና ጥጋቧን፣ ብልጽግናና ችግሯን በሚመለከት የተለያዩ ዓለማዊ አቀንቃኞች (secular musicians) ፣ድምጻዊያን፣ ሙዚቀኞች በተለያየ ብዙኃን መገናኛ ቀርበው ሲዘፍኑ፣ ሲያቅራሩ፣ ሲፎክሩ

ሲሽልሉ በስሜት ሲያለቅሱ በአርምሞ ተመልክቻለሁ፡፡ ጥናቱን እንዳደርግ ያነሣሱኝ አራት ምክንያቶች ናቸው እነሱም፡-

- አንደኛ የሀገሪቱን 96.7% ሕዝብሃይማኖተኛ በሆነበት ሀገር ውስጥ ኦርቶዶክስ፣ እስልምና፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት በመዝሙራት እንዴት ነው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እየተቀነቀነ ያለው? ምን ዐይነትተደጋጋሚ ትርክት አለ? የሚለው ጥያቄ ጉዳዩን በጥልቀት ለመመርመር ከፍተኛ ተነሣሽነት ፈጥሮብኛል፡፡
- ሁለተኛው ጉዳዩ ሰፊ ትኩረትና ከፍተኛ ርብርብ የሚያስፈልገው ጉዳይ ሆኖ እያለ፤ በዚህ ርእስ ጉዳይ ላይ ምንም ዐይነት ጥናት አለማግኘቴና አለመደረጉ ክፍተቱን ለመሙላት ያለኝ ፍላጎት ሌላው የተነሣሽነት ምክንያቴ ነው፡፡
- ሦስተኛው በእነዚህ ሃይማኖቶች ውስጥ ዕለት ተዕለት በሚቀርቡ መዝሙሮቻቸው ውስጥ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከቀዳሚ ጉዳዮቻቸው አንዱ ነው? ወይስ የእግረ መንገድ ሥራ ነው? የሚለውም ሌላ ምክንያቴ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደተጽእኖ ፈጣሪነታቸው ኢትዮጵያን በእያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ ለመቅረጽ የሔዱበትን ርቀት ያሳያልና፡፡
- አራተኛው ሁሌም በየዘመኑ ከውስጥም ከውጭም ፈተና የማያጣቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በመዝሙር ግጥሞቹ ውስጥ በመፈለግ ስለ ሀገር መቆርቆርን፣ ህልም መተግበርን፣ ስለሀገር መሞትን፣ሀገር ማገልገልን፣ከእኔ በፊት እኛ ማለትን፣ በትውልዱ አእምሮ ውስጥ ለመትከል ካለኝ ፍላጎት የመነጨ ነው፡፡

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

- በሀገሪቱ የተከሠቱ ፖለቲካዊ፣ ሀገራዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ክሥተቶችና ለውጦች ምንድን ናቸው?
- ይዘቱ በዘመን መንፈስ ውስጥ በምን ዐይነት ድምጸት የቀረበ ነው?
- በመዝሙር ግጥሞች በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ማእቀፍ ውስጥ ተደጋግመው የተነሡ መባያ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

በዚህ ርእሰ ሥር የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማና ንዑሳን ዓላማዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1.4.1. አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓለማ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአራቱ ሃይማኖቶች የአማርኛ የመዝሙር ግጥሞች ውስጥ እንዴት እንደቀረበ መፈተሽ ነው፡፡ እነዚህ ሃይማኖቶች በዓለም ሀገራት ላይ ያሉ ናቸው፡፡ ዝማሬውም እንደየሀገሩ እምነትና ትውፊት የተለያየ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የኦርቶዶክስ፣ የእስልምና፣ የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንት መዝሙራት ነሺዳና መንዙማዎች ላይ ነው፡፡

### 1.4.2. ንዑሳን ዓላማዎች

- ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሠቱ ፖለቲካዊ፣ ሀገራዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ክስተቶችና ለውጦች በመዝሙረኞቹ እይታ ምን እንደሚመስል መገምገም፤
- ✓ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ማሕቀፍ ውስጥ ተደጋግመው የተነሡ መባያ ጉዳዮችን መፈተሽ፤
- ✓ የመዝሙራቱ ነሺዳና መንዙማዎች በምን ዐይነት ድምጸት እንደቀረቡ መተንተን፤

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የትኛውም ጥናትና ምርምር ያለ ፋይዳ ወይንም ያለ ጠቀሜታ አይሠራም፡፡ ይሄ ጥናትም ለተለያዩ አካላት ልዩ ልዩ ጥቅም ይሰጣል፡፡ ከእነዚህ ጥቅሞች መካከል፦

1. በእምነቱ ውስጥ ላሉ አገልጋዮች የሚሰጠው ረብ ነው፡፡ አገልጋዮች በዝማሬያቸው በነሽዳቸው በመንዙማቸው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በምእመናን ልብ ውስጥ ተክሎ በማሳደር ረገድ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ እንደመሆናቸው መጠን ቢያንስ በእያንዳንዱ አልበማቸው ውስጥ ያነሡትን ጉዳይ በተመለከተ አንድ ሥራ እንዲያካትቱና በሀገር ጉዳይ ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሐሳብ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፤
2. ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠውና አሁንም ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ በመሆኑ ቀጣይ፣ ሰፊ እና ጥልቅ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች የመነሻ ሐሳብ በመሆን ክፍተቱን ይሞላል፤

3. ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊያንን በተመለከተ በመዝሙር ግጥሞቻቸው ውስጥ አካትተው የተሠሩትን የሃይማኖቶቹ ዘማሪያንና እና ሥራዎቻቸውን በመሰነድ ተተኪ ትውልድ የእነሱን ሥራ አይቶ ተጨማሪ ሥራዎችን እንዲያበረክት ተነሣሽነት ይፈጥራል፡፡
4. በሀገር ደረጃ መናናቅን፣ ጥርጣሬን፣ እኔ ብቻነትን መንቅሮ ጥሎ፣ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን በተመለከተ ሁሉም ሃይማኖት ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ክብር፣ ብልጽግና፣ ሰላም፣ በጸሎቱ፣ በዝማሬው፣ በሥርዓተ አምልኮው ውስጥ ምን ያህል እየደከመ መሆኑን በማሳየት እርስ በእርስ ተከባብሮ፣ አንዱ የአንዱን ሥራ እና ልፋት አውቆና ተረድቶ፣ ለእሴቱ ዋጋ በመስጠት በሰላም እና በፍቅር እንዲኖር ያግዛል፡፡ ምክንያቱም መተዋወቅ መከባበርን ያመጣልና፡፡ በመከባበር ውስጥ ሀገር ይቀጥላል፡፡
5. መንግሥት፤ ሃይማኖቶች የሀገር ፍቅርን እና አንድነትን፣ ተቆርቋሪነትን እና አብሮ መኖርን፣ ፈጣሪ ከሀገራቸው ጋር እንዲሆን ቀን እና ሌሊት መለመንን፣ በተከታዮቻቸው ልብ ውስጥ ለመቅረጽ ያለመታከት ዘመናቸውን ሙሉ እንደ አንድ ተግባራቸው አድርገው የሚሠሩትን የሃይማኖት ተቋማት ፖሊስ ሲቀረጽ እንዲያሳትፋቸው፣ በገንዘብ እና በቁሳቁስ እንዲያግዛቸው ለማስቻል እንደ አንድ የመነሻ ሐሳብ ያገለግላል፡፡ በዚህ ጥበብ አማካኝነት በአማኝ ልብ ውስጥ ሀገርን መትከል ዋጋው ዐለት ላይ መቅረጽ ነውና፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በአራቱ ሃይማኖቶች የአማርኛ የመዝሙር ግጥሞች ውስጥ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንዴት እንደቀረበ የሚፈተሽበት ነው፡፡ ትኩረቱም አራቱ ሃይማኖቶች ላይ ነው፡፡ ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ እስልምና እና ፕሮቴስታንት፡፡ መዝሙራቱ የተሠሩበት ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡ እነዚህ ሃይማኖቶች በዓለም ሀገራት ዘንድ ባሉ ሕዝቦች ብዙ ቢልዮን ተከታይ ያላቸው ናቸው፡፡

ታዲያ በየትኛው ሀገር ውስጥ ያሉትን ሃይማኖቶች ነው? የሚለው ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ 96.7% ሕዝብ ዘንድ ተከታይ ባላቸው የእምነት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ የመዝሙር ግጥሞች ውስጥ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን መተንተን ነው፡፡ በካሴት፣ በሲዲ፣ በቪሲዲ፣ በዩቲዉብ ላይ የተሰናዱት ላይ ነው፡፡ መነሻ ዘመኑ 1983 ይሆንና መዳረሻው 2013 ዓ.ም. ማብቂያ ድረስ የተሠሩትን ያጠቃልላል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ በዐይነታዊ የምርምር ዐይነት ሥር ያለውን ገላጭ የአቀራረብ መንገድ ተከትሏል፡፡ የመተንተኛ ስልቱ ደግሞ የይዘት ትንተና (content analysis) ነው፡፡ ዘዴው የንግግር ፍችን፣ አገባብን ለመተንተን ከማገልገሉም በላይ የሙዚቃ የግጥምን፣ የሬድዮ መልእክቶችን፣ ለመተንተን ያስችላል፡፡ ስሜታዊ የሆኑ ጉዳዮችንም ለመተንተን ያስችላል፤ (parasad፣ 8) ለመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት የተጠቀምኩት የሰነድ ፍተሻን (Textual analysis) ነው፡፡ ይኸ ማለት ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ግብዓቶች በጥልቀት ተመርምረዋል፡፡ ታላሚ ወይም ዓላማ ተኮር (purposive የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተጠቅሜያለሁ፡፡ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2013 ዓ.ም. ድረስ የተዘመሩና ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ይኖራቸዋል ብዬ የሰበሰብኳቸው 1900 መዝሙራት መካከል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ የሚያጠነጥኑ 49 መዝሙራትን ከአራቱም ሃይማኖቶች ሥር አግኝቻሁ፡፡ ይህም ያነሣሁትን ርእሰ ጉዳይ በቀጥታ ሊያገዘፉልኝ የሚችሉትን ብቻ የተመለከተ ነው፡፡

የመረጃ ምንጮቼ ሁለት ናቸው፡፡ ቀዳሚና ዳኅራይ፤ በቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ሥር የተካተቱት በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተሠሩት ሀገራዊ መዝሙራት ናቸው፡፡ እነዚህን መዝሙራት ከሲ.ዲ.፣ ከቪ.ሲ.ዲ፣ ከካሴት፣ ከዩቱብ፣ በመሰብሰብ እና በማዳመጥ ወደ ጽሑፍ ቀይሬያቸዋለሁ፡፡ ለዳኅራይ የመረጃ ምንጭነት የተጠቀምኩባቸው የጥናቱ ቀጥተኛ ጉዳዮች ያልሆኑ፣ ጥናቱ ይበለጽግ፣ ይደምቅ፣ ይገዝፍ፣ ይለምድ፣ ይዋሃድ ዘንድ ስለጽንሰ ሐሳባዊ ቅኝት፣ ስለንድፈ ሐሳባዊ ቅኝትና የመሳሰሉ ጉዳዮችን መረጃ ያገኘሁበት ምንጭ ነው፡፡

## 1.8. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

መጀመሪያ ያደረግኩት ከትምህርት ክፍሉ ለተለያዩ ተቋማት ጥናቱን አስመልክቶ ትብብር እንዲያደርጉልኝ የሚጠይቅ ደብዳቤ ማጻፍ ነበር፡፡ አጻፍኩ፤መጀመሪያ የሔድኩት ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት ነው፡፡ በዚህ ስር የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃና መምሪያ የሚባል አለ፡፡ መምሪያው ላይ ያሉ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ዐይነት የተደራጀ መዝሙራት እንደሌላቸው ገልጸው ወደ ማኅበረ ቅዱሳን መዝሙርና ኪነጥበብ አገልግሎት ማስተባበሪያ ክፍል ላኩኝ፡፡

እነዚም የክፍሉን ምክትል ኃላፊ አቶ ፍቃዱ ምሕረቴን አገኘሁት፡፡ እንደሚረዳኝ ገልጾልኝ ተለያየን፡፡ በሳምንቱ ምንም የለም፣ በወሩም ምንም የለም፡፡ ይኼን ጉዳይ የሚያደራጅ ቡድን ከመዝሙር ክፍል እንዳደራጀ ቢነግረኝም ውጤት የለም፡፡ በአካልም በስልክም ደጅ ብጠናም የተፈለገው መረጃ አልተገኘም፡፡ በመጨረሻ ከሁለት ወር ልፋት በኋላ እኔ የምፈልጋቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ የሚያቀነቅኑ አራት መዝሙራትን አገኘሁ፡፡ ተቋሙ በዚህ ደረጃ የተቀናጀ መረጃ ባለመያዙ ዐይኔን ወደ ሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ ወደ ካሴት፣ ሲዲ፣ ቪሲዲ፣ መሸጫ ሱቆች አዞርኩ፡፡

መዝሙራት ሲገኙ የዘማሪው ስም ይጠፋል፡፡ የዘማሪው ስም ሲገኝ ዓመተ ምሕረቱ አይገኝም፡፡ ይኼን ለማሟላት የተቻለችን ጥረት አድርጊያለሁ፡፡ ሀገር ውስጥ የሌሉትን ስልካቸውን እየተቀበልኩ በመደወል ጥረት አድርጊያለሁ፡፡ ከዚያም ሌሊት ሌሊት እነዚያን ሁሉ መዝሙራት በአጽንኦት ማዳመጥ ነበረብኝ፡፡ እያዳመጥኩ ከጉዳዩ ጋር የማይሔዱ መዝሙራትን መለየት ሌላው አድካሚ ሥራ ነበር፡፡ ከተለዩ በኋላ ራሴ በከፍተኛ ጥንቃቄ ወደ ወረቀት መገልበጥ አለብኝ፡፡ አልደመጥ ያሉትን ቃላት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎችን እንዲያዳምጡልኝ በመጠየቅ ሙሉውን መዝሙር ያለህጸጽ ለመገልበጥ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡

በዚህ ሂደት መዝሙረ ተዋሕዶ የሚሉት የመዝሙር መጽሐፎች ረድተውኛል፡፡ በዚህም ዘማሪት አዜብ ከበደ፣ ዘማሪት ትንቢት ቦጋለ፣ዘማሪ በርሱ ፍቃድ አንዳርጋቸው፣ ዘማሪት ለምለም ከበደ፣ መልአከ ገነት በለጠ ይረፉ (ከአሜሪካ)የሚቻላቸውን አግዘውኛል፡፡

ቀጥሎ የሔድኩት ጦር ኃይሎች ወደ ሚገኘው የኢትዮጵያ እስልምንና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ነበር፡፡ ደብዳቤዬን ለጸሐፊዋ ከሰጠሁ በኋላ ጉዳዩ ይመለከታቸዋል ወደ ተባሉት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ዘንድ ወሰደችኝ፡፡ እርሱ ደግሞ ይኼን ይዘት ይመለከተዋል ወዳለው ሰው መራኝ፡፡ አቶ ዑስማን ይባላል፡፡ አቶ ዑስማንም ብዙ እንደሚረዳኝ ቃል ገብቶልኝ ተለያየን፡፡ አልተሳካም፡፡

ስለዚህ በተቋሙ በኩል ያደረግኩት ጥረት እንዳልተሳካልኝ ሳውቅ አንዋር መስጊድ አካባቢ ያሉ የእምነቱ ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ሚገኙበት ሱቆች አመራሁ፡፡ በተደጋጋሚ ብሔድም በዚህ ጉዳይ ላይ የተሠሩ መንዙማዎችን እና ነሽዳዎችን ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ለጽንሰሐሳብ ማበልጸጊያ የሚሆኑ መጻሕፍትን ግን አግኝቻለሁ፡፡

በጣም ሲቸግረኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አረብኛ ትምህርት ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩትን ዶክተር ሀሰን ካምን አፈላልጌ አገኘኋቸው፤ እርሳቸውም ጥሩ ርእስ እንደመረጥኩ ነግረውኝ ነገር ግን መረጃ ለማግኘት እንደምቸገር በማስረዳት የት እና እንዴት መሔድ እንዳለብኝ በመምከር አስፈላጊውን ነገር ሁሉ እንደሚያግዙኝ ቃል ገብተውልኝ ተለያየን፡፡ በምክራቸው መሠረት በይዘቱ ላይ መረጃ አላቸው የተባሉትን ሰዎች ሁሉ አገኘሁ፡፡

በዚህ በነሽዳ ዘርፍ ታዋቂ የሆነውን ሰው ሙነሽድ ሙአዝ ሀቢብን፣ በዑስታዝ አቡበከር አህመድ በኩል አገኘሁት፡፡ ሙነሽድ ሙአዝ ሀቢብም የሙንሽድ አሊ አሚንን ስልክ ሰጠኝ፤ ደወልኩለት፡፡ ቀና ትብብር አድርጎልኝ የተወሰኑ ነሽዳዎችን ላከልኝ፡፡ ጋዜጠኛ ሁሴን ከድር ሦስት ነሽዳዎችን ሰጠኝ፡፡

በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ያሉትን በጉዳዩ ላይ የተባሉትን ነሽዳና መንዙማዎቸን ለማግኘት ጋዜጠኛ ሁሴን ከድርን፣ ዑስታዝ አቡበከር አህመድን፣ነቢል አቡሀሪ ኮሌክሽንን፣ሙአዝ ሀቢብን፣ ሙንሽድ ቶፊክ ዩሱፍን፣ ሙንሽድ አስማማው አህመድን፣ ሙሓመድ ፈረጅን በተለያየ መንገድ አግኝቻቸዋለሁ፡፡ አሊ አሚንና ጋዜጠኛ ሁሴን ከድር መረጃ በማቀበል ሂደቱ የአንበሳውን ድርሻ ሲይዙ ሌሎቹ የሚችሉትን ያህል ተባብረውኛል፡፡

በሃይማኖቱ ውስጥ የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት በርካታ መንዙማና ነሽዳዎችን አድምጫያለሁ፡፡ የሚሆኑትን ከማይሆኑት መለየት አድካሚ ነበር፡፡ የሙነሽዶችን ስም፣ ዓ.ም.. እና ጣልቃ የገቡ አረብኛ ቃላትን በትክክል ማስፈር፣ አድምጦ መገልበጥ ፈታኝ ነበሩ፡፡ ነገር ግን በቅኖቹ ሙነሽዶች ፣ የሃማኖቱ ተከታዮች፣ በአሚን እና በሁሴን ከድር፣ በዶክተር ሀሰን ካም ቀና ትብብር ለትንተናው የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ በመጨረሻም ፕሮፌሰር አደም ካሚል ለአንዳንድ ጥያቄዎቼ ግልጽ ማብራሪያ በመስጠት ጥናቴ ፈር እንዲይዝ ረድተውኛል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የሔድኩት የተለያዩ ቅርንጫፎች ወዳሉት የፕሮቴታንት እምነት ተቋም ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በፕሮቴስታንት እምነት ጥላ ሥር ሰባ አራት ቅርንጫፎች እንዳሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡[5] በመዝሙር ታሪክ ደግሞ ሦስቱ ተቋማት የተሻለ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ መረጃ አቀባዮቹ ገልጸውልኛል፡፡ እነሱም መሠረተ ክርስቶስ፣ ሙሉ ወንጌል፣ አማኑኤል ኅብረት

[5] አበበ፣ 146

ናቸው። ነገር ግን እኔ የምፈለገውን መረጃ በተደራጀ መንገድ ይዘው አላገኘኋቸውም።ያለኝ አማራጭ በሌሎች የእምነት ተቋማት እንዳደረግኩት ሁሉ በሃይማኖቱ መዝሙር ላይ ዕውቀት እና መረጃ ያላቸውን ሰዎች ፈልጎ ማግኘት ነበር።

መጀመሪያ ካሁን በፊት በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናትና ምርምር የሠራውን ጋዜጠኛ ዘካርያስ ብርሃኑን ማግኘት ነበር። ፋና በሚሠሩ ጋዜጠኞች በኩል አገኘሁት። እጁ ላይ ያሉትን መረጃዎች እንድጠቀምባቸው ሰጠኝ። እኔ የምፈልገውን መዝሙር ከአንድ በላይ ላገኝ አልቻልኩም። ቀጥሎ የሔድኩት በእምነቱ ትልቅ ቦታ ከሚሰጣቸው ዘማሪያን መካከል ወደ አንዷነው። ሶፊያ ሽባባውን በስልክ አገኘኋት። እርሷ ደግሞ የተሻለ ወደ ምትለው ሰው በእምነቱ ታዋቂ ወደ ሆነው ጸሐፊ ወደ ዘሪሁን ግርማ ደገፉ መራችኝ። ከስድስት ወር በላይ ደጅ ካስጠናኝ በኋላ የተወሰኑ መዝሙራትን ሰጠኝ። ቀጥሎ ያደረግኩት ሲዲዎችንና መጻሕፍትን እያፈላለግኩ መዝሙራትን ማዳመጥ ነበር። እጅግ አድካሚ ሌሊቶችና ቀኖችን አሳልፌ ያገኘሁትን ይዤ ወደ ሌላው የእምነት ተቋም ዞርኩ።

አራተኛው በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚያወሱ መዝሙራትን መፈለግ ነበር። ጋዜጠኛ ዘካሪያስ ብርሃኑ የአባ ጴጥሮስ ባርጋን ስልክ ሰጠኝ፤ እርሳቸው ደግሞ ለዚህ ቅርብ ናቸው የሚሏቸውን የአባ ዳዊት ውብሸትን ስልክ ሰጡኝ። አባ ዳዊት ደግሞ በካቶሊክ መዝሙራት ጥልቅ ዕውቀት አለው ብለው የሚያምኑበትን ዘማሪ ስልክ ሰጡኝ። ራእይ ሳሙኤል ይባላል፤ ዘማሪና የአቢይ ዘርዓ ክህነት ተማሪ ነው። እሑድእሑድ ላዛሪስት ትምህርት ቤት እየተገናኘን ከልቡ ረድቶኛል። በጽዮን ማርያም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን መዘምራን የተሰበሰበ የመዝሙር መጻሕፍትን ሰጥቶኛል። በጉዳዩ ላይ የሚያተኩሩ መዝሙራት ያሉበት ድረስ እያነፈነፈ ከነ ኦዲዮዋቸው ልኮልኛል።

የካቶሊክ መዝሙራትን ለመሰብሰብ ዘማሪ ራእይ ባይኖር የሚታሰብ አልነበረም። ነገር ግን በቂ ነው ብዬ ስላላመንኩ ብዙ ቦታ አፈላልጌ ከሻሸመኔ እስከ ናዝሬት ላገኝ አልቻልኩም። ፒያሳ ወደ ሚገኘው ዋናው ጽሕፈት ቤት ደብዳቤ ይዤ ሔድኩ። እነሱም በተቋም ደረጃ የተደራጀ እንደሌለ ነግረውኝ ወደ ራእይ ሳሙኤል ላኩኝ። እርሱን አግኝቸው ስለነበር የራሴን ጥረት አደርጌ ለትንተና የሚበቁ ዝማሬዎችን አደራጅቼ ጨረስኩ።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በዚህ ክፍል ስር ከርእስ ጉዳዩ ጋር የተያያዙ ሐሳቦች ከጉዳዩ ጋር የሚገናኙ ቀደምት ጥናታዊ ጽሑፎች ይዳሰሳሉ፡፡ በዳሰሳውም እኔ በጥናቴ ላነሣው ከፈለግሁት ርእስ ጋር የሚገናኙ ከዚህ ቀደም በፊት የተጠኑ ጥናቶች ከእኔ ጋር የሚያመሳስላቸውን እና የሚያለያያቸውን ነጥብ የሚፈተሽበት ነው፡፡

### 2.1. ጽንሰ ሐሳብ

#### 2.1.1. የመዝሙር ምንነት

እንደ አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ሐዲስ መዝገበ ቃላት አገላለጽ መዝሙር የሚለው ቃል

> ምስጋና በገና ዘምሮ ዘመረ" በማለት ይተረጉመዋል፡፡ (ኪ.ወ.ክ፣ 582)፡፡ መዝሙር ከምስጋና ከውዳሴ ከቅዳሴ ክብር ከመስጠት ጋር ተገናኝ ቃል ነው፡፡ ቃሉ የተሸከመው ጽንሰ ሐሳብ ሰፊ ነው፡፡ ‹‹መዝሙር ምስጋና ዘወትር ገንዘቡ ለሚሆነ ለልዑል እግዚአብሔር የሚቀርብ ውዳሴና ቅዳሴ፣ ስባሔና እማሔ፣ አኮቴትና ስብሐት ነው፡፡ መዝሙር በውስጡ ገጸ ንባብ፣ ኃይለ ቃል፣ ምሥጢር እንዲሁም ዜማን ይይዛል፡፡

የሚሉት ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ በመዝሙር ውስጥ ፈጣሪንን የምናመሰግንብት ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር የተለያዩ መልእክቶችን አካቶ በብዙ ምሥጢር አጅቦ መዝሙርን ማቅረብ እንደሚቻል ያስገነዝባሉ፡፡ በተቀራራቢ ሐሳብ (ሰሎሞን፣ 13) መዝሙር ምስጋና ብቻ አይደለም፤ በርካታ ጉዳዮችን የሚያስተነትን ነጥብ ነው፡፡ በመዝሙር ፈጣሪ ብቻ አይደለም የሚመሰገነው የፈጣሪ እናት ቅድስት ድንግል ማርያምን ጨምሮ ሌሎች መላእክት፣ ጻድቃንን፣ ሰማዕታትን፣ ሐዋርያትን፣ እንደክብራቸው መጠን ይሞገሱበታል፤ ይቀደሱበታል፤ ሀገርም ትመሰገንበታለች፤ ትቀደስበታለች፤ ሕዝቦቿም ከጥፋት እንዳይውሉ ፈጣሪያቸውን እንዲያመሰግኑ ይደረግበታል፡፡ ይሉናል፡፡

ስለዚህ መዝሙር ለአንድ ነገር ብቻ ማለትም ፈጣሪን ለማመስገን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ጉዳዮችንም ተሸክሞ መልእክት ማስተላለፍ የሚችል መሆኑን ያስገነዝቡናል፡፡

2.1.2. የነሽዳ ምንነት

ነሽዳ ቃሉ አረብኛ ነው፡፡ መጀመሪያ ቃሉን አረብኛ ውስጥ ሲጠቀሙት ነሽዳ ማለት ነው፡፡ የጠፉበትን ከብቶች ጠየቀ፡፡ ግመሎችን ጠየቀ፡፡ ኸረ ግመሎችን ያያችሁ ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ ነው፡፡ ነሽዳ ማለት ግመል ጠየቀ ማለት ነው፡፡ ከዚያ "ማለ" መሃላ የሚለውን ያዘ፡፡ ቀጥሎ ማስተዋወቅ የሚለውን ትርጉም ያዘ፡፡ ከዚያም ከድምፁ ጋር ማያያዝ ጀመረ፡፡ የጻፈውን ግጥም ከፍ ባለ ድምፅ አሰማው፡፡ ከዚያ ከግጥም ጋር ተያይዞ መጣ፡፡ እንደ ብሔራዊ መዝሙር ሃይማኖታዊ መዝሙር ሲጠቀሙበት እናያለን፡፡ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በተማሪዎች አካባቢ እያደገ የመጣ ነው፡፡ እኛ ሀገር ብዙ አንጠቀመውም፤ መጠቀም የጀመርነው ዘመናዊ መድረሳዎች ከተጀመሩ በኋላ ነው፡፡ መድረሳዎች የዓመት በዓል ጊዜ፣ ጠዋት በትምህርት ቤት በተለያየ ጊዜ ይሉታል፡፡ ከ1920ዎቹ ሐረር አካባቢ ተጀመረ፡፡ በአረቡ ዓለም ነሽዳ የሚለው ሃይማኖታዊ መዝሙር ወደ እስልምና ወደ መመለስ ጋር፣ እስልምናን ከማወቅ ፍላጎት ጋር፣ እስላማዊ ንቅናቄ ከመነሣት ጋር፣ ሰውን ሃይማኖቱን ለማስተማር፣ ወደ ሃይማኖቱ ለመመለስ ካለው ፍላጐት ጋር ከቅኝ ግዛት መነሣት ጋር፣ ሰውን ለመቀስቀስ ተጠቅመውታል፡፡ እኛጋ በሦስት ደረጃ አለ:-

1ኛ. በት/ቤቶች ውስጥ

2ኛ. ከውጭ የመጡ ዜማዎችን በካሴት ደረጃ በመስማት፤ ከዚያም በቻናሎች መስማት ጋር ከዘመናት ሙዚቃ ስልቶች ጋር ያንኑ ማለት ጀመሩ፣

3ኛ. ማዳቀል ጀመሩ፤ ወደ እኛው ሀገር መንዙማ፤[6]

ነሽዳ መነሻው በአረቡ ዓለም ሆኖ ወደ እኛ ሀገር የገባ ነው፡፡ ቃሉም ጠየቀ አማለ ከሚል ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ አገልግሎቱም ሃይማኖታዊ የመዝሙር ግጥም ነው፡፡ ይኼም ቀደም ብዬ ካነሣሁት የመዝሙር ግጥም ጋር አቻ ትርጓሜ፣ አገልግሎት እና ጠቀሜታ የያዘ ቃል ነው፡፡ በትርጉም ደረጃ ስናየው ዝማሬ የሚለውን አቻ ይሰጠናል፡፡ ነሽዳ አቻ ትርጉሙ ዝማሬ ማለት

[6] *ይኼን ያሉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አረብኛ ክፍል መምህሩና ተመራማሪው ዶ/ር ሀሰን ካዎ ናቸው፡፡ በ2020, May 29. በአርትስ ቴሌቪዥን ከደረጀ ኃይሌ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ፡፡*

ነው።[7] ይኼም ማለት የመዝሙር፣ነሽዳና መንዙማ ግጥሞች ተወራራሽ ትርጉም እንዳላቸው የሚያሳይ ነው።

### 2.1.3. የመንዙማ ምንነት

መንዙማ ምን ማለት እንደሆነ እንደሚከተለው ተብራርቶ እናገኘዋለን፡-

> መንዙማ ቃሉ አረብኛ ነው። ነዘመ ከሚለው የአረብኛ ስርወ ቃል የመጣ ነው። ነዘመ ማለት ገጠመ ማለት ነው። መንዙማ ዝርው ያልሆነ (ግጥም) ማለት ነው። በአረብኛ መንዙማ ትምህርታዊ ጉዳዮችን ለማስተላለፍ የሚያገለግል ግጥም ማለት ነው። በእንግሊዘኛ (deductive poetry) የሚለው ነው። (ታዛ መጽሔት፣ 30)።

በማለት የቃሉን ትርጉም ያስቀምጣሉ። በማስከተልም መንዙማ

> በሀገራችንም ለነብዩ መሐመድ ፍቅር፣ ክብር ማሳያ የሚገጠሙ ግጥሞች ናቸው፤ አላህን ለማወደስ የሚደረገውንም ያካትታል። ደጋግ ሰዎችን ለማሞገስ የሚደረገውም በዚሁ የሚካተት ነው።..... ሃይማኖታዊ ትምህርቶች፣ አፈንጋጭን ከስሑት ተግባሩ እንዲታቀብ የሚያስገድዱ ኃይለ ቃሎች፣ የማጽናኛ/ማበረታቻ ሐሳቦች ይካተቱበታል.... አጀማመሩ እስልምና በመካ ከመነሣቱ በፊት አረቦች በግጥም ችሎታቸው በጣም የተደነቁ ነበሩ። (ዝኒ ከማሁ)

በሀገራችን ደግሞ ከእስልምና ወደ ሀገራችን መግባት ጋር የሚያያዝ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ

> መንዙማ አልፎ አልፎ መዝናኛ ነው። አንዳንዴ የጸሎት ማድረሻ ነው፤ ብዙውን ጊዜ የማኅበረሰብን ሰንኮፍ ማሳያ ነው። **አንዳንዴም የሀገር ፍቅር መግለጫም**

---

[7] *ይኼንን ሀሳቤን የሚያጠናክሩልኝ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር እና ስነ ሥነጽሑፍ ት/ት ክፍል ባልደረባ እና መምህር የሆኑት መሐመድ አሊ(ዶ/ር) ናቸው። በ2020, May 31. ከፋና ቴሌቭዥን ጋር ባደረጉት ቃለምልስ ላይ "አቻ ትርጉሙ ዝማሬ ማለት" ነው ይሉናል።*

ነው። (አጽንኦት ከራሴ)…. መንዙማ በሀገራችን በዚህ ጊዜ ጀመረ የሚል መረጃ አልተገኘም። ሆኖም የተስፋፋበት ዘመን ይታወቃል ከ896-1280 (ዝኒ ከማሁ)

ልክ እንደ ነሺዳው ሁሉ የመዝሙር ግጥምን ትርጓሜ የያዘ፤ ይዘቱ ሃይማኖታዊ የሆነ፤ እንደ (ሩት፣ 167) አገላለጽ የሃይማኖት ግጥምን ባህሪ የሚያሟላ የሚል ፍች አለው። መነሻው ከአረቡ ዓለም ሆኖ ኢትዮጵያዊ ቀለም ያለው በእስልምና ውስጥ ያለ፤ ማወደሻ፣ ማዜሻ፣ መማጸኛ ተግባርን የያዘ ጥልቅ ኢስላማዊ ጥበብ ነው። የመዝሙር ግጥም፣ ነሺዳ፣ መንዙማ በተግባራቸው፣ በባህሪያቸው፣ በጠቀሜታቸው በትርጓሜያቸው አቻ ጉዳዩን የያዙ ተመሳሳይ አገልግሎት፣ ዓላማና ተልዕኮ ያላቸው የስነ ቃል ዘርፎች ናቸው።

እነዚህም በአንድ ማጥናት ምክንያታዊ መሆኑን ከተፈጥሮው ባህሪያቸው እንረዳለን። የሚለያዩት በዳራዊ ታሪካቸው እና በየሃይማኖታቸው ውስጥ በሚሰጡት አገልግሎት እና በአከዋወን ሂደታቸው እና አውዳቸው ነው።

### 2.1.4. የመዝሙር ባህሪያት

መዝሙር የሚለው ቃል በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ያለውን ነሺዳና መንዙማ እንደሚተካ ከላይ ባሰፈርኩት ሐሳብ የመሀመድ አሊን ቃለመጠይቅ ጠቅሼ ማቅረቤን ልብ ይሏል። ከዚህ በኋላም መዝሙር እያልኩ የምጠቅሰው በሁሉም ሃይማኖቶች ያለውን የመዝሙር ግጥም ነው። ይኸ እስልምንናም ክርስትናንም ሌሎች ሃይማኖታዊ የመዝሙር ግጥሞችን የሚመለከት ነው። ሁሉም ሃይማኖቶች ዓላማቸው አንድ ነው። የሰው ልጅ ፈጣሪውን ፈርቶ፣ አክብሮ፣ ለሕጉ ተገዝቶ፣ መልካም ሥራሠርቶ፣ በምላሹ ከፈጣሪው፣ በምድር በረከትን ፣ በሰማይ ከቅጣት ነጻ ወጥቶ፣ ገነትን ወይም ጀነትን እንዲወርስ ማድረግ ነው።

የዚህ ጥናት ዓላማ እንዲሳካ ከሚያደርጉ አሳላጭ መሣሪያዎች አንዱ መዝሙር ነው። ይህም በሁሉም ሃይማኖቶች ያሉ የዝማሬ ግጥሞች ምን የጋራ ባህሪያት አላቸው? ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል። በአፍሪካ የሥነ ቃል ጥናት አንቱታን ያፈራችው Ruth አንድን ግጥም ሃይማኖታዊ ነው ለማለት ሦስት ነጥቦች መሟላት አለባቸው ትላለች። ይዘቱ ሃይማኖታዊ፣ ከዋኙ የሃይማኖቱ ባለሚል ሲሆን፣ የሚከወንበት የታወቀ አጋጣሚ ሲኖረው ነው ትላለች (Ruth ፣ 167)።

### 2.1.4.1. ይዘቱ

ይዘት ስንል በውስጡ የሚይዛቸውን ነጥቦች ይመለከታል፡፡ እንደ Finnegan አገላለጽ አንድን ግጥም ሃይማኖታዊ ነው ለማለት ይዘቱ ሃይማኖታዊ መሆን አለበት፡፡ ምን ማለት ነው? ሲባል በሃይማኖቱ አስተምህሮ ውስጥ የሚዳሰሰው ማናቸውንም ነገር ያቀፈ ሲሆን ይኸን መጠሪያ ይወስዳል፡፡ ስለዚያ ሃይማኖት የሚሰብክ፣ የሚያስተምር፣ የሚያጽናና፣ የሚያሠራጭ፣ ይሆናል፡፡ ይኸውም ከሌሎች ከፉከራ፣ ከሽለላ፣ ከለቅሶ፣ ከሰርግ ወዘተ ግጥሞች የተለየ ያደርገዋል፡፡

የመዝሙር ግጥም ይዘት ከሌሎች የግጥም ዐይነቶች የተለየ የሚያደርገው ይህ ባህሪው ነው፡፡ የመዝሙር ግጥም የሚጻፈው ለትምህርት፣ ለተግሣጽ፣ ልብን ለማቅናት፣ ለማጽዳት፣ ንስሐ ለመግባት በሃይማኖት በምግባር ለመጽናት ነው፡፡ ስለዚህ የመዝሙር ግጥም በይዘቱ ከሌሎች በማኅበራዊ ጉዳዮች እንዲሁም በግል ሕይወት ዙሪያ ከሚያጠነጥኑና ከሚደርሱ… የግጥም ዐይነቶች የተለየ ነው (ሰሎሞን፣ 50-51) ይዘቱ ሃይማኖታዊ ሲባል በሃይማኖቱ ውስጥ የተካተቱ እና ሊባሉ፣ ሊደረጉ፣ ሊሆኑ የሚገባቸውን ማናቸውንም ጉዳዮች የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት ማለት ነው፡፡

### 2.1.4.2. ከዋኞቹ የሃይማኖቱ ባለሚሎች ሊሆኑ

የሃይማኖት መዝሙር ሃይማኖታዊ ከሚያሰኙት ጉዳዮች ሁለተኛው ባህሪ ከዋኙ ነው፡፡ አንድ ስነቃል የሚከወንበት አውድ፣ የሚከወነው ጉዳይ ወይም ተከዋኝ ነገር እና ተደራሲ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ከዋኙም ዋናው ነገር ነው፡፡ ‹‹ስነቃል ሕይወት ኖሮት ከነሙሉ ድምቀቱና ግብ መችነቱ ሊከሠት የሚችለው የክዋኔው አካላት በሙሉ ባንድ ሆነው ሲቀርቡ ነው›› (ዘሪሁን፣ 23) እሱ ማለት አንዱ ከጎደለ ውበቱን ያጣል ከዋኙ ደግሞ ዋነኛው አካል ነው፡፡ ክዋኔ ካለ ከዋኝ መኖሩ ግድ ነው፡፡ ያለ ከዋኝ ክዋኔ የማይታሰብ ነው፡፡ ‹‹ክዋኔ የሥነ ቃል ተቀዳሚና መሠረታዊ ባህሪ ነውና” (Finnegan፣ 2)፡፡

ታዲያ እንደ ሩት ፊኔጋን እምነት ሃይማኖታዊ ግጥም እንዲባል አቀንቃኙ፣ ከዋኙ ወይም የሃይማኖቱ አገልጋይ ባለሚል ሊሆን ይገባል፡፡ ያ ማለት ከእምነቱ አገልጋይ ወይም አማኝ ውጭ የማይባል ነገር መሆኑን ያሳያል፡፡ ይኸን ባህሪ ሲላበስ የሃይማኖት ግጥም ይባላል፡፡

### 2.1.4.3. አጋጣሚው

ሦስተኛው አንድ ግጥም ሃይማኖታዊ ነው ሊያስብለው የሚችለው ክዋኔው በከዋኙ አማካኝነት ሊባልበት፣ ሊደረግበት፣ ሊተገበርበት፣ሊዘመርበትና ሊነገርበት የሚችል የታወቀ አጋጣሚና ክብረ በዓል ሲኖረው ነው። "ምክንያቱም ስነቃሎች ከሚቀርቡበት ማኅበራዊ አጋጣሚ ተነጥለው ሊቀረቡ የማይችሉ በመሆናቸው ነው።" (ሰሎሞን፣ 148)

የመዝሙር ግጥም ደግሞ በስነ ቃል ሥር የሚጠና ዘርፍ ነው። ከሥነቃል ባህሪያት አንዱ ደግሞ አውዳዊነት ነው። ፊኔጋን እንደምትለው አንድ ግጥም ሃይማኖታዊ ለመሆኑ ማረጋገጫው የሚከወንበት አጋጣሚ ነው። (Finnegan፣ 162) የመዝሙር ግጥሞች ደግሞ በክብረ በዓላት፣ በጉባኤዎች፣ በሃማኖታዊ ሰርግ፣ የሃይማኖቱ ተከታዮች ከዚህ ዓለም በሚለዩበት ጊዜ ወዘተ አጋጣሚዎች ይከወናሉ።

እነዚህ ከላይ ያነሣናቸውን ባህሪያት የሚያሟሉ ሲሆኑ ሃይማኖታዊ ግጥሞች ያሰኛቸዋል። የመዝሙር ግጥም ደግሞ ከሃይማኖት ግጥሞች አንደኛው ስለሆነ እነዚያን ሦስት መገለጫ ባህሪያት ይወርሳል።

### 2.1.5. የመዝሙር ጠቀሜታ

> የመዝሙር ግጥም ገላጭና አስረጅ በመሆኑ በቀላል አገላለጽ ወይንም ዐረፍተ ነገር ለማሳየት ያልቻልናቸውን የማንችላቸውን ምረረ ገሃነምን፣ ጣዕመ መንግሥተ ሰማያትን፣ ውድቆ መነሣትን፣ በሃይማኖት መጽናትን፣ ሠራዊተ አጋንንትን ድል መንሳትን፣ አምልተን ለማስረዳት እንዲሁም በቀላሉ በሰማዕያን ልቦና ታትሞ እንዲቀመጥ ያስችላል። …ስነ ምግባርን በቃል ለማጥናት ያስችላል። …በጸሎትነት ያገለግላል …ለፈጣሪያቸው ምስጋና እንዲያቀርቡ …ሰላምና መረጋጋት እንዲያገኙ የሚያስችል ታላቅ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው (ሰሎሞን፣ 17)

ፈቃደም የስነ ቃልን ተግባር ሲገልጽ መትከል፣ መግለጥ፣ ማምለጥ፣ ማስተማር መግታት ናቸው ይለናል (ፈቃደ፣ 16-20)። ጠቀሜታው የሚመነጨው ከተግባሩ ነው። የሥነ ቃል ተግባር የመዝሙር ግጥምን ይሸከማል፤ የስነቃል ግብር የመዝሙር ግጥም ግብር ነው። ከዚህ የተነሣ የመዝሙር ግጥሞች ጠቀሜታ አያሌ መሆናቸውን እንረዳለን።

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርእስ ሥር ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት እና ዝምድና ያላቸው የታተሙም ሆነ ያልታተሙ ጥናቶች ተዳሰዋል፡፡ በዚህ ረገድ በ ኤም.ኤ ደረጃ ተሠርቶ ያገኘሁት አንድ ጥናት ነው፡፡

እርሱም በሁለተኛ ዲግሪ ለድህረ ምረቃ ማሟያ የቀረበ የዘካርያስ ብርሃኑ ጥናት ነው፡፡ ሁለተኛው ታትሞ በመጽሐፍ መልክ ለአንባቢ የቀረበው የመ/ር ሰሎሞን ወንድሙ መጽሐፍ ነው፡፡ የሁለቱንም ጥናት ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን፣ ከእኔ ጋር የሚያመሳስላቸውን እና የሚያለያያቸውን፣ ያነሡትን ጉዳይ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡

በቀዳሚነት የማየው፡- የዘካርያስ ብርሃኑን ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ የቀረበው ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር ነው፡፡ ርእሱም ‹‹በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና በፕሮቴስታንት እምነት በካሴት እና በሲዲ የወጡ የአማርኛ መዝሙር ግጥሞች ጥናት›› ይላል፡፡ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ዋቢ መጽሐፍቱን ጨምሮ በ89 ገጽ ተሰናድቷል፡፡

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች ተከፋፍሏል፡፡ ምዕራፍ አንድ መግቢያን ይይዝና ዳራ፣ አነሣሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ ዘዴ፣ ጠቀሜታ፣ ወሰን የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎችን ያጠቃልላል፡፡ ምዕራፍ ሁለት በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ሥር አራት የዲግሪ ማሟያ ጥናቶችን አራት የታተሙ ጥናቶችን ባጠቃላይ ስምንት ጽሑፎችን አይቷል፡፡ ጥናቶቹ ከእርሱ ጥናት ጋር በቀጥታም በተዘዋዋሪም ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡

በምዕራፍ ሦስት በመዝሙር ምንነት ሃይማኖቶች አከፋፈል ስር የመዝሙር ምንነትንና ዳራን አስረድቷል፡፡ የሁለቱንም ሃይማኖቶች አስተምህሮ፣ ታሪካዊ ሂደት፣ የእምነቱ መዝሙራት ዐበይት ባህሪያት ተገልጸውበታል፡፡ የመዝሙርን አከፋፈል ከዘመናት አኳያ ሲከፈሉ፣ በበዓላት ሲከፈሉ፣ ከይዘት አንጻር ሲከፈሉ ብሎ በሦስት ምድብ ካስቀመጠ በኂላ በይዘት ስር የምስጋና፣ የንስሐ፣ የልመና፣ የስብከት መዝሙራት ብሎ ያስቀምጣል፡፡ ሁለቱን ሃይማኖቶች የሚያመሳስላቸው የምስጋና እና የንስሐ ነው፡፡

በኦርቶዶክስ ያሉት የልመናና የስብከት መዝሙራት በፕሮቴስታንት ውስጥ በችግር ጊዜ የሚዘመሩ እና የድል መዝሙራት በሚል ተተክተዋል፡፡ በፕሮቴስታንት የወንጌል አሠራጭ የሚለው ደግሞ በጭማሬ ገብቷል፡፡ የበዓላት መዝሙራት ሁለቱም ላይ ገብተዋል፡፡የአምልኮ እና የውዳሴ መዝሙራት ሰባተኛና ስምንተኛን ደረጃ ይዘው ከፕሮቴስታንት ተቀምጠዋል፡፡ በምዕራፍ አራት መዝሙሮቹ በጭብጥ እና በዘመን ተመድበው ተተንትነዋል፡፡ እዚህ ላይ ሁሉንም ሁለቱንም ሃይማኖቶች በአራት ነጥቦች አካትቶ የምስጋና፣ የንስሐ፣ የልመና፣ የስብከት፣ በሚል ቋት ውስጥ አስገብቶ ከተነተነ በኋላ ጭብጥና ዘመናትን በመቶኛ ስሌት አቅርቧል፡፡

በምዕራፍ አምስት ዋና ዋና መባያ ጉዳዮችን እረኛ፣ ጋሻ፣ መድኃኒትና ጽዮን በሚል ንዑሳን ርእሶች አቅርቧል፡፡ ድንግል እና ተዋሕዶ የሚሉት በኦርቶዶክስ ላይ ብቻ የተገኙ ናቸው፤ በመጨረሻም የጥናቱ ግኝትና ይሁንታ የሚሉ ጉዳዮችን አትቷል፡፡ በግኝቱም በመዝሙሮቹ ይዘት እና ዘመናት ረገድ የልመና ይዘት ካላቸው መዝሙራት በስተቀር በሁለቱም ሃይማኖቶች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው መዝሙራት በተመሳሳይ ዘመናት ላይ የተዘመሩ መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ ከተሰበሰቡት 1373 መዝሙራት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጥናቱ ተለይተው ከታወቁት 11 ዘማርያን 603 መዝሙራት ሰብስቧል፡፡ በፕሮቴስታንት እምነት በኩልም ከ9 ዘማሪዎች 770 መዝሙራት ተገኝተዋል፡፡ ከፕሮቴስታንት ይልቅ በኦርቶዶክስ ዘንድ የልመና ግጥሞች መብዛታቸው የጥናቱ ግኝት ያስረዳል፡፡

መባያዎች ዘማሪያን በምእመናን ዘንድ ሊያስረዱ የሚፈልጉትን ሃይማኖታዊ ርእዮተ ዓለም በመግለጥ፣ በመትከል በማጽናት የሃይማኖቱን ሕልውና ለማስቀጠል የሚደረገውን ከፍተኛ አስተዋጽዖ ሌላው የጥናቱ ግኝት ነው፡፡ ጥናቱ ትኩረቱን አድርጎ ይኼንን ግኝት ያገኘው በኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን እና በፕሮቴስታንት እምነት ከ2000 ዓ.ም. በፊት ባሉት ዓመታት ከ5 አልበም በላይ ካሳተሙ 20 ዘማርያን 1373 የመዝሙር ግጥሞችን በመሰብሰብ ነው፡፡

የጥናቱን ጥያቄ የሚመልሱ ዓላማውን የሚያሳኩ ንዑሳን ርእሰ ጉዳዮችን መርጦ ዝርዝር ማብራሪያ መስጠቱ ለጥናቱ ስኬት ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረገ በመሆኑ እንደ አንድ ጠንካራ ጎን የሚታይ ነው፡፡ አሃዛዊ መረጃዎች በመቶኛ ስሌት በሰንጠረዥ መልክ መቅረባቸው ለአንባቢ እና ተመራማሪ ምቹ መሆኑ ሌላው ጠንካራ ጎኑ ነው፡፡

በፕሮቴስታንት በበዓላት ጊዜ የሚዘመሩ መዝሙራት ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ በተፈጸሙ ዋና ዋና ተግባራት ወቅት፣ በመታሰቢያው ቀን አልያም መታሰቢያውን በማሰብ የሚዘመሩ መዝሙራት ያመለክታል ይለናል ነገር ግን በኦርቶዶክስ በዓላት ላይ እንደተገለጸው ዝርዝር መረጃ የለም፤ ዋና ዋና ተግባራቱ፣ ለምሳሌ ያህል የትኞቹ ናቸው? በመታሰቢያው ቀን የተባሉትስ? የለም፡፡ ይኼ ለአንባቢ እና ለተመራማሪ ድፍን ነው፡፡ ንዑስ ርእሱ መሠረዝ ነበረበት፤ ወይም ተብራርቶ መቅረብ ነበረበት፤ ይኼ አንዱ ደካማ ጎን ነው፡፡

ሌላው በኦርቶዶክስ በበዓላት ሲከፈሉ ብሎ ያስቀመጠው በዋና ርእስነት ነው፡፡ ነገር ግን ከይዘት ስር ልክ እንደ ፕሮቴስታንቱ ማስቀመጥ ይቻል ነበር፡፡ በፕሮቴስታንቱ በይዘት ሥር የተቀመጡት የአምልኮና የወንጌል አሠራጭ መዝሙራት በኦርቶዶክስ ስር እንዳለው በስብከት መዝሙራት ስር ሊካተት ይችል ነበር፡፡ የድል እና የውዳሴ የተባሉትም የምስጋና መዝሙራት ውስጥ መግባት የሚችል ነበር ምክንያቱም ውዳሴና ምስጋና ልዩነት የላቸውምና፡፡ ከይዘት አኳያ ብሎ በፕቴስታንቶች የመዝሙር ውስጥ የተዘረዘሩትን ውስን ርእሶች መሰብሰብ የሚችሉ በመሆናቸው አከፋፈል ላይ ድክመቶች ይታያሉ፡፡

የእኔና የዘካርያስ ጥናት የሚያመሳስለው፣ የሁለታችንም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነው፡፡ የሁለታችንም በአማርኛ መዝሙር ግጥሞች ላይ መጠንጠኑ ነው፡፡ መዝሙራትን የከፈልንበት መንገድ ከፊል ተመሳስሎ አለው፡፡ መባያ ጉዳዮችን ማንሣታችንም ያመሳስለናል፡፡

የሚለያየን ደግሞ እርሱ በኢ.ኦ.ተ.ቤ እና በፕሮቴስታንተን እምነት ውስጥ ከአምስት አልበም በላይ ባወጡ ከ1960ዎቹ እስከ 1990 ዎቹ ከ2000 ዓ.ም. በፊት በእነዚህ ዘመናት ውስጥ መዝሙራትን መሰብሰብ ነው፡፡ እኔ ደግሞ በአራቱም ሃይማኖቶች ላይ ነው ትኩረቴን ያደረግኩት፤ ዘመኑም ከ1983-2013 ዓ.ም. ማብቂያ ድረስ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን አስመልክቶ በተዘመሩ መዝሙራት ነሽዳዎች መንዙማዎች ላይነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን፣ በፕሮቴስታንት፣ በካቶሊክ እና በእስልምና ሃይማኖቶች ላይ ነው፡፡ የእርሱ ጥናት በዘመን እና በአልበም የተገደበ ነው፡፡ የእኔ በዘመንና በይዘትየተገደበ ነው፡፡

የእርሱ ጥናት ዓላማ ያደረገው በዘመን ውስጥ የሁለቱንም ሃይማኖቶች የመዝሙር ግጥሞች በመሰብሰብ መሰነድ እና ይዘቶች ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው፡፡ የእኔ ጥናት ኢትዮጵያና

ኢትዮጵያዊነት በአራቱ ሃይማኖቶች የመዝሙር ግጥሞች ውስጥ እንዴት እንደቀረበ መፈተሽ ነው፡፡

በዚህ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በተመለከተ በቀረቡ የዝማሬ፣ የነሽዳ እና የመንዙማ ግጥሞች ውስጥ ምን ዐይነት ጉዳዮች ተነሥተዋል የሚለው የሚዳስስበት ነው፡፡

ሁለተኛ ከጥናቴ ጋር ተያያዥ ነው ብዬ ዳሰሳ ያደረግኩበት ‹‹የአማርኛ መዝሙራት ድክመቶች እና ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች›› የሚል ነው፡፡ በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃና መምሪያ ስር ባለው በማኅበረ ቅዱሳን አማካኝነት በ2010 ዓ.ም. የታተመ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ በስድስት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ መግቢያ በመግቢያው ስር የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ፣ የመዝሙር ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ አከፋፈል፣ ዐይነቶች፤ በምዕራፍ ሁለት የአማርኛ መዝሙራት ድክመቶችና ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ብሎ ይዘት በአማርኛ የመዝሙር ግጥም ምን እንደሚመስል የሚያስረዱ ነጥቦችን በዝርዝር አቅረቧል፡፡ በምዕራፍ ሦስት የአማርኛ መዝሙር ዜማ ምንነትና ምን መልክ እንዳለው የተተነተነበት ክፍል ነው፡፡

በምዕራፍ አራት መንፈሳዊ ሕዝባዊ ዜማ በሚል ርእስ አጠቃቀምን፣ ፋይዳን እና ችግርን የሚመለከቱ ሐሳቦች የተሰተናገዱበት ክፍል ነው፡፡ በምዕራፍ አምስት የያሬዳዊ ዜማ ምንነት፣ ባህሪያት፣ ያሬዳዊ ዜማን ለአማርኛ መዝሙራት መጠቀም ያለው ፋይዳ እና ለመጠቀም ምን እንደሚጠበቅብን ያብራራል፡፡ በመጨረሻም በምዕራፍ ስድስት ክፍል ውስጥ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳቦች ቀርበዋል፡፡ ጥናቱ ዓላማ አድርጎ የተነሣው ድክመቶችን በማንሣት፣ ትኩረት የሚያሻቸውን ጉዳዮች በመጥቀስ፣ የመፍትሔ ሐሳብ መለገስ ነው፡፡

ጠንካራ ጎኑ የአማርኛ መዝሙራት ምን መምሰል እንዳለባቸው ወጥነት ያላቸውን መለኪያ መሥፈርቶች ለማስቀመጥ መሞከሩ አንደኛው ጉዳይ ነው፡፡ የዝማሬ ግጥሞችን የስነ ግጥም መለኪያ መንገዶችን በመጠቀም ትንታኔ ማድረጉና በአማርኛ የመዝሙር ግጥምና ዜማዎች ላይ የሚነሡትን ተራርቆሽ ለማቀራረብ የሚችሉ የመፍትሔ ሐሳቦችን መጠቆም በጠንካራ ጎን ሊነሣለት የሚችል ሐሳብ ነው፡፡

ደካማ ጎኑ ከ1996 ዓ.ም. ለምን እንደ ጀመረ ምክንያት ቢያስቀምጥም መጨረሻ ድንበሩ ግን መቼ እንደሆነ አይገልጽም፡፡ መነሻ ካስቀመጠ መድረሻ ቢያስቀምጥ ጥሩ ነበር፡፡ ምክንያቱም ይኼ ጥናት መቼ ላይ እንዳቆመ ማወቅ ለቀጣይ ተመራማሪ ግብአት ስለሚሆን፡፡

ለጥናቱ ግብአት ይሆኑ ዘንድ የተመረጡት የዝማሬ ግጥሞች በምን መስኪያና በምን መሥፈርት እንደሆነ በግልጽ አልሠፈረም፡፡ በአማርኛ የተሠሩ የመዝሙር ግጥሞች ብሎ ከተነሣ በኋላ በአማርኛ የተሠሩት የፕሮቴስታንት እና የሌሎች ሃይማኖቶች መዝሙራት ውስጥ እንዳሉ እየታወቀ ሌሎችን ለምን መዳሰስ እንዳልፈለገ በግልጽ አለማስቀመጡ ወይንም አለመፈተሹ ሌላው ድክመቱ ነው፡፡ የሁለታችንም ጥናት የሚያመሳስለው በአማርኛ ከተሠሩ የመዝሙር ግጥሞች ላይ መሥራታችን ነው፡፡

ሌላው የመዝሙር ጠቀሜታዎችን ማንሣታችን ለመክፈያ ይሆን ዘንድ የተጠቀመንበት ዘዴ ከፊል ተመሳስሎ አለን፡፡ ልዩነቱ እርሱ በኦርቶዶክስ መዝሙራት ብቻ አተኩሯል፡፡ እኔ በኦርቶዶክስ፣ በእስልምና፣ በካቶሊክ እና በፕሮቴስታንት ላይ ትኩረቴን አድርጌአለሁ፡፡ የሰሎሞን ጥናት ዓላማ የአማርኛ መዝሙር ግጥሞች ምን መምሰል እንዳለባቸው መሥፈሪያ ሳጥኖችን አስቀምጦ መወሰን ነው፡፡ *እኔ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአራቱ ሃይማኖቶች የመዝሙር ግጥሞች እንዴት እንደቀረበ መፈተሽ ነው፡፡* ሰሎሞን ዜማንና ግጥምን ይፈትሻል፡፡ እኔ ግጥምን ብቻ ተመልክቻለሁ፡፡

## 2.3. የንድፈ ሐሳብ ማዕቀፎች

የፎክሎር ጥናት ሲደረግ የተሰበሰቡት መረጃዎች በተለያዩ መተንተኛ ቲዎሪዎች አማካኝነት ይተነተናሉ፣ ይላመዳሉ፣ ይነጸራሉ፣ ይተነተናሉ፡፡ ይህ ትንታኔ በዘፈቀደ ሳይሆን ከመረጃዎቹ ጋር በወጉ በተሸመነና በተስማማ ንድፈ ሐሳብ ሊቀርብ ይገባል፡፡ መረጃዎች በምንም ዐይነት መንገድ ይሰብሰቡ እነዚህ በሥርዓት የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎች ለአንባቢ ወይም ለተደራሲ በሚገባ መፈከር እና አሻሚ ባልሆነ መንገድ በቅጡ መቅረብ አለባቸው (Creswell፣ 68) እና (Marsh and Rossman፣ 213) ያትታሉ፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የምንመለከተው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ የተንጠለጠሉ የዝማሬ ግጥሞች በየትኞቹ ማዕቀፎች መስታወትነት ገብተው እንዲነጥሩ ነው፡፡

የተነሣው ርእሰ ጉዳይ በርካታ ንድፈሐሳበዊ ቅኝቶችን ሊጠራ ቢችልም እኔ ግን ጥቂቶችን መርጬ ተጠቅሜያለሁ፡፡ እነሱም ሁለት ናቸው፡፡ እነዚህ እኔ የመረጥኳቸው ቀጥተኛ ማንጸሪያና መፈተሻ ሆነው ስላገኘኋቸው ነው፡፡ ለሰበሰብኩት መረጃ መተንተኛ የንድፈሐሳብ ማዕቀፎች ብዬ የተጠቀምኳቸው አንደኛ ተግባራዊ ወይም ጠቀሜታዊ ሲሆን ሁለተኛው ማኅበራዊ ሂስ አንድ በአንድ እንመልከት፡፡

ተግባራዊ (ጠቀሜታዊ) ንድፈ ሐሳብ /functional approach/ ነው፡፡ እኔ ያነሣሁት ርእሰ ጉዳይ የሚጠናው በፎክሎር ሥር ነው፡፡ ፎክሎር ደግሞ ከሰው ጋር የተዛመደና የተሳሰረ ጉዳይ ነው የሚሠራው፡፡ ፎክሎርንም ፎክሎር ያደረጉት በሥሩ ያሉ ክፍሎች ተደምረው ነው፡፡ እነዚህ ናቸው የሥነቃል ባለቤቱን ማኅበረሰብ ሙሉ የሚያደርጉት፡፡ ፎክሎር የኅብረተሰቡን ሕልውና ውብ የሚያደርጉ ተግባራዊ ፋይዳዎች አሉት፡፡ ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የማስተላለፍ፣ ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር አለው (Radcliffe Brwon፣ 394)፣ ( Bascom፣ 344)::

ተግባራዊ ንድፈሐሳብ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር ያግዛል (okpewho፣ 173) ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በማኅበረሰቡ ውስጥ አፍራሽም ገንቢም ጉዳዮችን የሚይዝ ነው፡፡ እያንዳንዳቸው የፎክሎር ዘውጎች ለማኅበረሰቡ ፋይዳ ያለው ግልጋሎት ይሰጣሉ፡፡ የዚህ ንድፈ ሐሳብ ዋና ዓላማ አንድ ስነቃል የተለያየ አገልግሎት፣ ተግባር፣ ጥቅም እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፡

ጠቅለል ሲደረግም አንድ ማኅበረሰብ ባህላዊ ወጎችን የሚጠብቅበትና ማኅበራዊ ግንኙነቱን የሚያጠናክርበት ነው (Bauman፣ 66)፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ልዩ ልዩ ገጾች አሉት፡፡ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ተምሳሌታዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ባህላዊ፣ ጥቂት መገለጫዎቹ ናቸው፡፡ በዚህም የማይዳስሳቸው መስኮች የሉትም ማለት ይቻላል፡፡ የሥነቃል ሚናም በልዩ ልዩ መስኮች ከሚገለጽባቸው ጉዳዮች አንዱ ፋይዳውን ማሣየት ነው፡፡ እንስሳት ሃይማኖት የላቸውም፡፡ ሰዎች ግን አላቸው፤ እነዚህ ሰዎች ሃይማኖታቸውን ለማሳለጥ የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ዝማሬ ነው፡፡ ዝማሬው ደግሞ ዜማ፣ ግጥም፣ አልባሳት፣ መሣሪያ፣ ጊዜና ቦታ አለው፡፡

እኔ ግጥሙን ብቻ ወስጀ በነዚህ ሃይማኖቶች ውስጥ ያሉትን ማኅበረሰቦች በመዝሙሮቻቸው ውስጥ የተቃወሙትን፣ የደገፉትን፣ የተከሉትን፣ የነቀሉትን፣ የነቀፉትን፣ የወደዱትን፣ የጠሉትን፣ ያስተላለፉትን መልእክት፣ ትችት፣ ድጋፍና ቅሬታ፣ ኃዘንና ደስታ፣ ተመልክቸባቸዋለሁ፡፡ የመዝሙሮቹን ፋይዳም በሃይማኖቱ ተከታይ ማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ የተሰጠው ቦታም ተገልጦበታል፡፡ ከዚህ በመነሣት መረጃዎችን ለመተንተን ከመረጥኳቸው አንዱ የንድፈ ሐሳብ ማዕቀፍ ተግባራዊ ወይም ጠቀሜታዊ ነው፡፡

ማኅበራዊ ሂስ ንድፈ ሐሳብ/social critisism/ ሁለተኛው ማኼሻ ማዕቀፌ አድርጌ መርጨዋለሁ፡፡ ንድፈ ሐሳቡ በማኅበረሰብ ሳይንስ ጥናት ውስጥ/social science study/ የታወቀ ነው፡፡ በጀርመን ፍራንክፈርት መሠረቱን አድርጎ ፍራንክፈርት ትምህርት ቤት ውስጥ የበቀለ ነው፡፡ በ1923 ተቋሙ ተመሥርቶ በ1937 ክርቲካል ቲዎሪ የሚለው እሳቤ ብቅ አለ ከዚሁ ጋር ተያይዘው ከመጡ ንድፈ ሐሳቦች መካከል የማኅበራዊ ሂስ ንድፈ ሐሳብ አንዱ ነው፡፡ ማኅበራዊ ሂስ ማኅበረሰቡ አሁን ያሉበትን ማኅበራዊ ሥርዓት በፊት ከነበሩበት አንጻር የመፈተሻ ልማድ ነው፡፡ ይኽን ዐይነቱን የመመርመሪያ መንገድ ለመጠቀምና ለመስጠት የማኅበረሰቡን እሴት በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል (Fletcher፣ 75)፡፡

ሥነ ጽሑፋዊ ንድፈ ሐሳብ ያለሂስና ታሪክ፣ ታሪክ ያለ ንድፈ ሐሳብና ሂስ፣ ሂስም ያለታሪክና ንድፈ ሐሳብ ሕልውና የላቸውም (Wellek and warren፣ 30)፡፡

ማኅበራዊ ሂስ ከራሱ የሚመነጩ ዓላማዎችና ሊያነሣቸው የሚፈልጋቸው ጥያቄዎችን በውስጡ ይዟል፡፡ ከማኅበረሰቡ ታሪክ በመነሣት ሂስ መስጠትና በሚገባ መመርመር እንደሚያስፈልግ በዚህ ውስጥ የተጠቀሰው ዓላማው ነው፡፡ በዝማሬዎች ውስጥ ያሉት ግጥሞች ደግሞ ከዘመን መንፈስ የራቁ አይደሉም፡፡ በአንድም በሌላም መንገድ ዘመኑን ይዋጃሉ፡፡ ግጥሞች ከተጻፉበት ወቅታዊ ክስተቶች ጋር የጠበቀ ቁርኝት አላቸው (Lucas፣ 654)፡፡

በዚህም የማኅበራዊ ሂስ ንድፈ ሐሳብ ሥር በርካታ ጉዳዮች የተነተናሉ፡፡ እነዚህም ሃይማታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ግብረገባዊ፣ ታሪካዊ፣ ሀገራዊ ጉዳዮች ይተነተናሉ፡፡ ጥቂቶችን መመልከት ይቻላል፡፡ በስሕተትና በትክክል /right and wrong/ እንደ ማኅበረሰቡ ባህል፣ እምነትና፣ አመለካከት ከጥሩና ከመጥፎው፣ ከትክክልና ከስሕተት፣ ከማድረግና ካለማድረግ እሳቤዎች ጋር የተገናኘ የምርምር ዘርፍ ነው፡፡ (ጠና፣ 365) ሥነ ምግባራዊ ሂስም በማኅበረሰቡ ዘንድ ያሉ ባህላዊ ሃይማኖታዊ የሥነ ምግባር መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በአንድ የሥነ ጽሑፍ ሥራ ላይ የሚደረግ ምዘና ነው፡፡ በዚህ ሂስ ሃያሲው የቀረበው ጽሑፍ ምንያህል ሥነ ምግባርን ሊያስተምር እንደሚችል ይፈትሻል (ባምላኩ፣ 2015)፡፡

ፖለቲካም የኅብረተሰብ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ሰው ከፖለቲካ ፖለቲካም ከሰው ሊነጠል አይችልም፡፡ በምድር ላይም ፖለቲካ ያልሆነ ጉዳይም ፈልጎ ማግኘት ከባድ ነው፡፡ ሃይማኖት

በፖለቲካ ውስጥ አለ። ፖለቲካም በሃይማኖት ውስጥ አለ። በኢኮኖሚም እንዲሁ ነው። ታዲያ ይህ ከሰው ልጅ ሕይወት የማይነጠለው ፖለቲካ ምንድን ነው? ይኽንን መልስ እናገኛለን።

‹‹ፖለቲካ ከሥልጣንና ሀገር ከማስተዳደር አኳያ፣ አንድ መንግሥት ከሚያስተዳድረው ሕዝብና ከሌሎች መንግሥት ጋር ያለው ግንኙነት ሁኔታ፣ አመለካከት እንቅስቃሴ፣ ሥነ መስተዳድር ወይም የማስተዳድር ሳይንስ ነው›› (አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 89)። ይኽንን መግፍኤ ሐሳብ ይዘን ወደ ፍልስፍናው ወይም እሳቤው ስናመራ ‹‹ፖለቲካዊ ፍልስፍና የሰዎችን ማኅበራዊ አደረጃጀት የሚያጠና በማኅበረሰብ ውስጥ የግለሰቡን ቦታ የሚጠይቅ በተገላቢጦሽም ግለሰብ ከኅብረተሰብ ጋር ሊኖረው የሚገባውን ግንኙነት የሚመረምር የፍልስፍና ዘርፍ ነው›› (ዘካርያስ፣ 17)።

ስንጨምቀው በአንድ መዝሙር ግጥም ውስጥ ታሪክን የሚፈትሹ፣ በዘመን መንፈስ ውስጥ የተከሠቱ ብርቱ ጉዳዮችን የሚመረምሩ፣ መጥፎነው የሚሉትን የሚኮንኑ፣ ሰናይ ነው የሚሉትን እሳቤ ለማስቀጠል የሚውተረተሩ ሐሳቦች በአያሌው ይገኛሉ። እነዚህ ሃይማኖታዊ፣ ግብረገባዊ፣ ታሪካዊ፣ ሀገራዊ፣ ፖለቲካዊ ወዘተ… ጉዳዮችን በሥሩ ይዞ እመረምራለሁ የሚለው የማኅበራዊ ሂስ ንድፈ ሐሳብ ለዚህ ጥናት እንደ ሁለተኛ ማዕቀፍ ተጠቅሜበታለሁ።

## 2.4. የፖለቲካ ምንነት

*ፖለቲካ "ፖሊቲ" ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ይህም የጥንታዊ ግሪክ ትናንሽ መንግሥታዊ ተቋሞች መጠሪያ ነበር። ፖለቲካ የኅብረተሰብ አደረጃጀትን፣ የመንግሥት ይዘትን፣ ዐይነትን፣ ቅርጽንና ተግባርን፣ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች መሠረታዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የሚያደርጉት ትግል፤ በመንግሥት መካከል የሚፈጥሩት ግንኙነቶች ማለትም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲንም የሚመለከት የተወሰነ መደብ የሚኖረውን ንድፈሐሳባዊ ግንዛቤና ከዚሁ የሚመነጨው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያጠቃልላል።…ፖለቲካ ታላቅ የኅብረተሰብ ለውጥ መሣሪያ የመሆኑን ያህል መልሶ በኢኮኖሚው መሠረታዊ ባሕርይ ላይ የራሱን ተፅእኖ ያደርጋል።*[8]

ድምፀት በሚቀናበረው የትኛውም ዐይነት ጽሑፍ ላይ የደራሲው አስተሳሰብ የሚገለጥበት መንፈስ ነው።

---

[8] *የማርክሲዝም ሌኒንዝም መዝገበ ቃላት፣ 311*

…Tone as the expression of a literary speker's attitude of his listener. the tone of his utternance reflects… his sense of how he stands toward those he is addressing …. The tone of a speech can be described as critical or approving formal or intimate, outspoken or heticent, solemn or play ful, arramt or plyfully angry or loving, serious or ironic conde scending or obsequious, and so on through numberless possible nuances of relationship and attitude both to object and auditor.[9]

… የትኛውም ቃል፣ ዐረፍተ ነገር፣ አንቀጽ፣ ሙሉው የፈጠራ ድርሰትና እንዲሁም ተጨባጭ ሰነድ ሁሉ የራሱ የሆነ ድምጸት አለው፡፡ በሚጽፉት የጽሑፍ ዐይነቶች ከሚስተጋቡት የድምጸት ዐይነቶች መካከል የቁጣ፣ የኃይለ ቃል፣ የመለሳለስ፣ የቁጭት፣ የትእዛዝ፣ የምፀት፣ የፌዝ፣ የአሽሙር፣ የመጠራጠርን፣ የመሰለቻቸትና የመረጋጋት ስሜቶች እንደምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ፖለቲካዊ ድምፀት ያነገቡ መዝሙራት በአራቱም ሃይማኖቶች አሉ፡፡ እነዚህም በሁለት የአገዛዝ ዘመን ውስጥ የታረቁ ናቸው፡፡ ድምፀታቸውም ሆነ ፖለቲካዊ ጉዳዮቻቸው የዘመኑን መንፈስ የዋጁ የመዝሙር ግጥሞች ናቸው፡፡ ጉዳዩን ያገዝፉ ዘንድ በናሙናነት የተመረጡ ግጥሞች ተወስደው እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

---

[9] *Abrams, .258*

# ምዕራፍ ሦስት

# የመረጃ ትንትና

## 3.1. ፖለቲካዊ ድምፀት ያላቸው መዝሙራት

### 3.1.1. ዘረኝነትን ኮናኝ መዝሙራት

ዘረኝነት[10] ዓለምን እያወከ ያለ በሽታ ነው፡፡ በአራቱም ሃይማኖቶች በኦርቶዶክስ፣ በእስልምና፣ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት አማኞች ዘንድ እጅግ ፀያፍና የተወገዘ ተግባር ነው፡፡ በኢትዮጵያ ከ97% በላይ ሕዝብ ተከታይ ያፈሩት እነዚህ ሃይማኖቶች የዕለት ተዕለት የአገልገሎት ማሳለጫ በሆነው በዝማሬዎቻቸው ውስጥ ዘረኝነትን አጥብቀው ሲፀየፉ እናያለን፡፡

ለምሌ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን እንግዳወርቅ በቀለ "መራራ ሕይወቴ" በሚለው መዝሙሩ ውስጥ ዘረኝነትን የሚያወግዝ መዝሙር አለው፡፡

*መራራ ሕይወቴ*

. . .

እኔ የኬፋ ነኝ የአጵሎስ አትበሉ

የተለያየ መንግሥት አያጠናም እንዲሉ

. . .

(ዲ/ን እንግዳወርቅ በቀለ 1997፣ 4.11)

መዝሙሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትመራበት መጽሐፍ ቅዱስ ሰማንያ አንድ መጻሕፍትን የያዘ ነው፡፡ ሰማንያ አሐዱ ይባላል፡፡ የቤተ ክርስቲያኗ ሥርዓት፣ ዶግማ፣ ቀኖና እና ትውፊት ይህንን ቅዱስ መጽሐፍ መሠረት

---

[10] *Racism is hierarchy of superiority/inferiority along the lion of human. This hierarchy can be constructed and marked in diverse ways.(JOURNAL OF WORLD-SYSTEMS RESEARCH, ISSN:1076-156X | vol, 22 Issue page 9-15 | http://dx.doi.org/10,5195/jwsr.2016.609 | jwsr.org. what is research?Roman Grosfoguel.university of California,Berkeley,p10.)*

ያደረገ ነው፡፡ ዝማሬውም ከዚህ ይቀዳል "ይኸንም እላለሁ እያንዳንዳችሁ እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ እኔ ግን የኬፋ ነኝ እኔስ የክርስቶስ ነኝ አትበሉ" 1ኛቆሮ.1÷12 ይላል፡፡ ከዚህ ይቀጥልና "ክርስቶስ ተከፍሏልን? ጳውሎስ ስለ እናንተ ተሰቀለን?" እያለ ቅዱስ ጳውሎስ ይጠይቃል፡፡ ይህንን የሚላቸው ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ነው፡፡

ዛሬም ዘማሪው ለእኛ ለኢትዮጵያዊያንና መዝሙሩን በቀጥታ ለሚያዳምጡት የእምነቱ ተከታዮች የኬፋ ወይም የአጵሎስ ነኝ አትበሉ ብሎ ዘረኝነትን ሲኰንን ልዩነትን ሲያወግዝ ይታያል፡፡ ምክንያቱም ይላል ሁለተኛው ስንኝ ከተለያየንና ዘር ከቆጠርን በአንድነት ፀንተን መኖር አንችልም፡፡ አመክንዮው ውሃ የሚያነሣ ነው፡፡

ዘረኝነት አኗኗርን ብቻ ሳይሆን አሟሟትንም ያበላሻል፡፡ ሕዝብ በዘረኝነት በሽታ ታውሮ ከዚህ ጽኑ ደዌ መፈወስ ካልቻለ ተፈረካክሶ ይወድቃል፡፡ ከላይ የተመለከትነው የመዝሙር ግጥም ቅዱሱን መጽሐፍ ሲመረኮዝ በተጠየቅ ነው፡፡ ኬፋ ስለሕዝቡ አልሞተም፤ ጳውሎስም ስለ ምእመናን አልተሰቀለም፤ ክርስቶስም ሲከፈል አላዩትም፡፡ "አንዱ ስለሁሉ ሞተ ይላል" እንጂ (2ኛ ቆሮ. 5÷14)፡፡ እንግዲህ በዚያ ዘመን የነበሩ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ይህንን እያወቁ እነርሱ ግን ዘር ቆጠሩ፤ መቧደን ጀመሩ፡፡ በዚህም ተገሠጹ፤ ይኼ መዝሙርም የዛሬዎቹን ኢትዮጵያውያን የኦርቶዶክስ አማኞችን ከትናንቶቹ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ጋር እያነጻጸረ ይወቅሳል፡፡

ከዚህ ባሻገር ይኼ መዝሙር የወጣበት ጊዜም የዘመኑን መንፈስ የሚያሳይ ነው፡፡ 1997 ዓ.ም. ሀገራዊ ምርጫ የነበረበትና የፖለቲካውን ሰማይ የታከከበት ዓመት ነበር፡፡ ወቅቱም ምን ያህል ሰው በዘረኝነት ደዌ ተለክፎና በልዩነት ገመድ ተጠፍሮ እንደነበር የሚያሳይ ነው፡፡ ድምፀቱም ግሣጼ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዘረኝነት ልክፍት ያበዱት የኢትዮጵያ ዜጎች ደግሞ የእነዚህ ሃይማኖቶች ተከታዮች መሆናቸውን ስናስብ ሃይማኖቶቹ እና ሃይማኖተኞቹ ምንያኽል እንደተራራቁ እንታዘባለን፡፡

ዘማሪት አዲስ ለማ "ተነሽ ኢትዮጵያ" የሚለው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መዝሙሮቿ ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በዚህም በዘመኑ የነበረውን የዘረኝነት ጥግ እንዲህ ታነሣዋለች፤

ተነሽ ኢትዮጵያ

. . .

ተበጣጥሰን በዘር..... ተነሽ ኢትዮጵያ

አንድነት ስናጣ... ተነሽ ኢትዮጵያ

ፍሬዋን ነሳችን.... ተነሽ ኢትዮጵያ

ምድር ተለውጣ..... ተነሽ ኢትዮጵያ

ዘራችን ክርስቶስ... ተነሽ ኢትዮጵያ

መሆኑን ዘንግተን.... ተነሽ ኢትዮጵያ

ምንጮቻችን ነጥፈው.... ተነሽ ኢትዮጵያ

አዝነን ተጠምተን.... ተነሽ ኢትዮጵያ

(ዘማሪት አዲስ ለማ፣1997፣4)

ወቅቱ 1997 ዓ.ም.ሦስተኛው ሀገራዊ ምርጫ የሚከወንበት ጊዜ ነበር፡፡ ምርጫውን ተከትሎም ብዙ ደም የፈሰሰበት፤ የሰው ሕይወት የተቀጠፈበት ወቅት ነው፡፡ ይኼም አንዱ ብሔር ሌላኛው ብሔር በድሎኛል ብሎ እንዲያስብ ተደርጓል፡፡ የመዝሙሩ ግጥምም ይህንን የዘመን መንፈስ ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡

“ተበጣጥሰን በዘር” ይላል የመጀመሪያው ስንኝ፤ ያልሆነና ያልተከሠተ ነገር አልተዘመረም፤ ተነሽ ኢትዮጵያ ይላል፤ እንደገና አይዞሽ ተስፋ አትቁረጪ ነው ነገሩ፡፡ በመዘሙሩ ውስጥ በዘር ተበጣጥሳ ያለችው ኢትዮጵያ ታሳዝናለች፡፡ ምክንያቱም በዘር መከፋፈሏ አንድነትን ነሳት፡፡ አንድነት በማጣቷ ከእግዚአብሔር የምታገኘውን በረከት፣ ምርቃት፣ የተፈጥሮ ስጦታዎች የሆኑት ሁሉ ተጣሏት፡፡ በዚህ ምክንያት ምድር ተለውጣ ቡቃያ፣ ፍሬ፣ እህል፣ ምግብ ነፈገቻት፡፡ የመንስኤና ውጤት ትስስሮሹ ኃያል አመክንዮአዊ ነው፡፡ በዘር መከፋፈል ውጤቱ

ላይ ተፈጥሮም ፊቷን ታዞራለች፡፡ ለዚህ ማረጋገጫው ምድር ፍሬ መንፈጓ ነው፡፡ ዘረኝነት እንኳን ፈጣሪን ግዑዛን ፍጡራኑን እንደሚያሳዝን የሚያረዳ ዝማሬ ነው፡፡

ዘራችን ክርስቶስ መሆኑን ስለዘነጋን ዋጋ ከፍለናል፡፡ ምንጮቻችን ነጥፈዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ ተጠማን ነው ጉዳዩ፡፡"ዘራችን ክርስቶስ ነው" ሲል መዝሙሩ በኢ.ኦ.ተ.ቤ አስተምህሮ ክርስቶስ አምላክ ነው፤ ይኸ ቅዱስ አምላክ ደግሞ ስለ ሰው ልጆች ተሰቅሎ፣ ሙቶ፣ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ ነው፤ ስለዚህ ሁሉም ከእርሱ የእርሱ ለእርሱ ነው፤ ትርጓሜው፡፡ ዘራችንን ክርስቶስን ስናደርግ ምድርም ፍሬዋን ትሰጣለች፤ ምንጮችም ውሃን ያፈልቃሉ፤ የሚል አንድምታ አለው፡፡

በዚህ ግጥም ውስጥ በዘረኝነት ሰንሰለት ታስሮ መቧደን ረሀብንም ጥምንም እንደሚያመጣና የምድር እና የሰማይ ፈጣሪ እንደሚያዝን ያሳያል፡፡ ዘረኝነትን አምርሮ የሚጠላ የዝማሬ ግጥም ነው፡፡ ድምፀቱም ቁጭት አዘል ነው፡፡ በቁጭቱ ውስጥ ሆኖ ግዴለም ተነሽ ኢትዮጵያ እያለ ተስፋን ይረጫል፡፡

ዘማሪ ጸሐፊ ትእዛዝ ዲ/ን ታዴዎስ ግርማ ምሥጢረ ኢትዮጵያ በተሰኘው መዝሙሩ ላይ የዘረኝነት ምሬት በሚያንገሽግሽ መንፈስ ውስጥ ሆኖ፡-

ምሥጢረ ኢትዮጵያ

ዘሬን አትጠይቁኝ ስለማንነቴ

ሰው መሆን በቂ ነው ኢትዮጵያዊነቴ

(ዘማሪ ፀሐፊ ትእዛዝ ዲ/ን ታዴዎስ ግርማ 2011)

ዘመኑ ዘመነ ብልጽግና ነው፡፡ ኢህአዴግ ወርዶ የመደመር መዝሙር በብዛት እና በስፋት የተቀነቀነበት ጊዜ ነው፡፡ የለውጡ መሪ አቢይ(ዶ/ር) ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በየ መድረኩ የሰበኩበት ዘመን ነው፡፡ ብቸኝነት፣ ዘረኝነት፣ ልዩነት በመሪ ደረጃ የተወገዘበት ወቅት ነው፡፡

የመዝሙሩ ግጥም ረዥም ቢሆንም ጉዳዬን እንዲያጎለብቱልኝ የቀነጨብኳቸው ሁለት መስመር ስንኞች ናቸው፡፡ ቁጥራቸው ትንሽ መልእክታቸው ጥልቅ ነው፡፡ ዘሬን አትጠይቁኝ፤ ዘር ምን

ያደርጋል፤ ኢትዮጵያዊ ካላችሁ በቂ ነው፡፡ ከሆነም ሰውነቴ ይበቃኛል፡፡ ሰው ስለሆንኩ ነው እንጂ ኢትዮጵያዊ የሆንኩት፤ ኢትዮጵያዊ ስለሆንኩ አይደለም ሰው የሆንኩት የሚል ጠንካራ ፍልስፍና የታጨቀበት የቁጣ ድምጸትን ያዘለ ግጥም ነው፡፡ ከፍ ሲል ሰውነት ዝቅ ሲል ኢትዮጵያዊነት ከዚያ ወርጄ መዋረድ አልፈልግም የሚል ነው፡፡ የዘመኑን መንፈስም ይመስላል፡፡ ዘረኝነትን የሚያቀነቅኑ ቢኖሩም እንደ ፀረ-ዘረኞች ግን ጎልተው አልተደመጡም፡፡

በሁለተኛ የምንመለከተው የኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት ተከታይ የኾኑት ሙነሽዶች በነሽዳቸውና በመንዙማቸው የዘረኝነትን ፀያፍነት የገለፁበት መንገድ ነው፡፡ በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ዘረኝነት ጥንብ ናት፡፡[11] የነብዩ መሐመድ ሰ.ዐ.ወ ቃል ነው፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች የሕይወት መመሪያ የሆነው ቅዱስ ቁርአን ስለዘረኝነት ብዙ ብሏል፡፡[12]

በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ጎንደሬ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ ሀድያ ወዘተ መሆን አያጸድቅም፡፡ ከሁሉ የሚበልጠው አላህን የሚፈራ እንደሆነ ልዩ ልዩ የቁርአን ምዕራፎች ይነግሩናል፡፡

ስለዚህም ዘረኝነት በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ እጅግ አስፀያፊ እና አስነዋሪ ድርጊት መሆኑን ተከትቦልናል፡፡[13] የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮችም ይህንን የቅዱስ ቁርአን ሐሳብ በነሽዳቸውና በመንዙማዎቻቸው ይገልጡታል፡፡ ከነዚህ መካከልም በኅብረት ነሽዳ ሠርተው ለአድማጭ ያቀረቡት ሙነሽድ አስማማው አህመድ፣ ሙነሽድ እስማኤል ተክሌና ሙነሽድ ሀሰን ዑመር ይገኙበታል፡፡ ርእሱም ታረቀን ይላል፡፡

---

[11] *Kesem media net ዘረኝነትና ዳፋው April 24,220 አህመድ ሁሴን (አቡ ቢላል) "ዘረኝነት ጥንብናት አትቅረቧት" ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ).. አንድ ሙስሊም እንደሙስሊምነቱ ሳይሆን እንደ ኦሮሞነቱ፣ አማራነቱ፣ ሶማሌነቱ፣ ትግሬነቱ፣ ስልጤነቱ፣ ጉራጌነቱ ወዘተ ብቻ ሲያስብና በዚሁ ዐሳቡም እየተነዳም ክፉ ሲደርግ ከመታዘብ የበለጠ ምን ስቃይ ይኖራል፣ እንደ ኮሶ የተጣበው ዘረኝነት መርዝ እንደቀመሰች ዐይኑ እያክለፈለፉ ቆንጨራ አስይዞ ወደ ወንድሞቹ ቀዬ ሲዶለው የማን ያለህ ይላል?*

[12] *https://am.eferrit.com ቁርአን ስለ ዘረኝነት ምን ይላል? እስላም ለሁሉም ጊዜ እምነት ነው፡፡ ሙስሊሞች ከሁሉም አህጉራት እና ዳራዎች የመጡ ናቸው፡፡ አንድ አምስተኛ የሰውን ልጅ ይሸፍናሉ፡፡ በአንድ ሙስሊም ልብ ውስጥ ለእብሪት እና ለዘረኝነት ምንም ቦታ የለም፡፡ አላህ የሚነግረን የሕይወት ብዛት እና የሰዎች የተለያዩ ቋንቋዎች እና ቀለማት የአላህ ግርማ ምልክት ነው፡፡ እና ስለ ትህትና እኩልነት እና ልዩነቶች ተረድተን እንድንማር ነው፡፡ "ሰማያት ምድርንም መፍጠሩ፣ የቋንቋዎቻችሁና የመልኮቻችሁም መለያየት፣ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው በዚህ ውስጥ ለሚታውቁ ሕዝቦች በእርግጥ ተአምር አለ" (ቁርአን 30:22)*

[13] *ቅዱስ ቁርአን "የአዳምንም ልጆች በእርግጥ ከሌላው ፍጡር አከበርናቸው፡፡ በየብስና በባህርም አሳረፍናቸው፡፡ ከመልካሞችም (ሲሳዮች) ሰጠናቸው፡፡ ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው" (17:70) "እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ አንድትተዋወቁም ጎሳዎች ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው 49:1፤*

ታረቀን

ምድርን ለፈሳድ አጭደው ሲባክኑ፤

በየአደባባዩ የሰው ዘር ሲያድኑ፡፡

የማይታይ ጁንድህ ጠላት ይዳብሳል፤

ገዳይ ሲያረፋፍድ ሟች ይገሰግሳል፡፡

በቀለም በቆዳ በዘር ሲቧደኑ፤

ነጭ ጥቁር ብለው ፍጡር ሲኮንኑ፤

ነጭ ጥቁር ብለው ፍጡር ሲኮንኑ፤

ምድራችን አነባች ህልቁም ረገፈ፤

አለሁ ያለው ስልጡን ደርሶ እየሰነፈ፡፡

(ሙነሽድ አስማማው አህመድ፣ መንሽድ ኢስማኤል ተክሌ

መንሹድ ሐሰን ዑመር 2013 ዓ.ም.)

የመዝሙር ወይም የነሻዳው ጭብጥ ታረቀን ነው፡፡ ማነው የሚታረቀን? ብለን ስንጠይቅ አላህ የሚል መልስ እናገኛለን፡፡ ምን አጥፍተን? ብለን ደግመን ስንጠይቅ ዘረኞች ሆነናል ነው የሚለው፡፡ ነሽዳው የሚኮንነው ዘረኝነት ነው፡፡ ነጭ ጥቁር እያሉ በዘር ቀለም ሰክረው ፈጣሪ የፈጠረውን ፍጡር አንዱን ሲኮንኑና ሌላውን ሲያጸድቁ የሚታይበት ነው፡፡ በዚህም የፈጣሪ የእጅ ሥራ የሆነችውን ምድር አነባች፡፡ ምድር አንድም ግዑዟ ተፈጥሯዊ ስሪት የሆነችው ናት፡፡

ተፈጥሮም ዘረኝነትን አይወድም ነው፡፡ አንድም ምድር የሰው ልጅ መኖሪያ ናት፡፡ የሰው ልጅን ትወክላለች፡፡ በስመሀዳሪ ዘይቤ ገብታለች፡፡ ማደሪያውን ጠርቶ አዳሪውን ነውና፡፡ በምድር ላይ የሚኖሩ የሰው ልጆችም በዚህ የዘረኝነት ልክፍት የተነሣ አለቀሱ አነቡ አነፈረቁ ተሰቃዩ የሚል

ጉምቱ ሐሳብን ይይዛል። ዘረኝነት በሁለት ወገን የተጠላ ነው። በፈጣሪና በፍጡራን ዘንድ፤ከዚህም የዘረኝነት ጦስ የተነሣ ህልቁም ረገፈ ይላል። ህልቁ የሚለው ሕዝቡን ነው። ዘረኝነት ጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ነው። ዘረኝነት ካንሰር ነው።

የነሽዳው ግጥም ሠለጠነ የሚባለው ፍጡርም በዘር ሕመም ተበክሏል። ደርሶ ይሰንፋል። የዘረኝነትን መርዝ ትከሻው መቋቋም አልቻለም። ራሱ ሠለጠነ የሚባለው የተማረው አካል የዘርን እሳት የሚጭረው፣ የሚያፋፍመው፣ የሚያጋድለው፣ የሚያጫርሰው እርሱ ነው። በመሠልጠንና በመሰይጠን መሐል ያለው ልዩነት በነሽዳው ውስጥ ጎልቶ ይታያል። ሰው ሲሠለጥን ዘርን ለባቂላና ለስንዴ እየሰጠ እርሱና ወገኖቹ አንድ ይሆናሉ። ምክንያቱም ሁሉም ሰው በፈጣሪው ፊት እኩል እንደሆነ ይነግረናልና።

የነሽዳው ድምፀት በሰዎች ላይ ያለው እምነት ተሟጦ አልቆ በቀቢፀ ተስፋ ወድቆ ወደ ፈጣሪው ያንጋጥጣል። እንዲሁ "ታረቀን" ይላል። ተጠየቁ ደግሞ ሀገሪቱ በዚህ ከቀጠለች የሙት እናት ትሆናለች ነው የሚለው። ለዚህም መፍትሄው ታረቀን እያለ ያለቅሳል። ለቅሶውን እንድናለቅስለት በአሳማኝ ምክንያት ይጠራናል። የዘመኑን መንፈስ ጠቋሚ ነው። ስለ አንድነት ይሰብካል ስለ ኅብረት ይጣራል በሌላ በኩል ደግሞ ስለ ዘረኝነት ይቀነቀናል፤ ስለዘር ይዜማል። በዚያ በኩል ሲወተፍ በዚህ በኩል ይቀደዳል። የዘመኑ መንፈስና ጭብጡ ተዋሕደዋል።

ሦስተኛ፤ ዘረኝነት በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ውጉዝ ከመ አርዮስ መሆኑን እናያለን። የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው መጻሕፍት ብዛቱ ሰባ ሦስት ነው። የአስተምህሮዋ መነሻ ይሄ ነው። በዚህ ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ዘረኝነት በተደጋጋሚ ተኮንኗል።[14] በቤተ ክርስቲያኗ መሪ በካርዲናሏም አማካኝነት በተለያየ ጊዜ ምእመናኗ ከዘረኝነት አስተሳሰብናተግባር እንዲቆጠቡ ታስተምራለች። [15] ለሃይማኖቷ ተከታዮችም በቋንቋቸው በሚቀርብ መዝሙር ላይ ስለ ዘረኝነት እርኩሰት ስለ ልዩነት መጥፎነት ትሰብካለች። በምሬት ትኮንናለች።

---

*[14] መጻሕፍ ቅዱስ፣ ዘፍ 3፥20 አዳምም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም አወጣ የሕያዋን ኹሉ እናት ናትና" "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ግዟትም" ዘፍ 1፡20 የጥፋት ውኃ መጥቶ የምድርን ነዋሪዎች በሙሉ ባጠፋ ጊዜ አራት ጥንዶች ማለትም ኖህና ሚስቱ ከሦስት ልጆቻቸውና ከልጆቻቸው ሚሰቶች ጋር ተረፉ። መጻሕፍ ቅዱስም ሁላችንም የኖህ ዝርያ እንደሆንን ይናገራል ዘፍ 9፡18-19*

*[15] https"://www.sbs.com.aw aug 7, 2022 ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነ ኢየሱስ በጾመ ፍልሰታ ምእመናን "ዘረኝነትንና ጥላቻን በኢትዮጵያ አብሮነት" ተክተው በፍቅር እንዲጸልዩ የመንፈሳዊ መሪ ምክራቸውን ለግሰዋል።*

ዘማሪት ሀና ዮሐንስ “አቤቱ መልሰን” በተሰኘው መዝሙሯ ስለ ልዩነት ዘር መጥፎነት እንዲህ ብላለች፡-

አቤቱ መልሰን

እኛ በኃጢአት ተዘፍቀናል፤

የሕይወት ምንጭ አንተን ረስተናል፡፡

ውሃ መቋጠር የማይችሉ

የተሸነቆሩ ጉድጓድ ሠርተን ጠፍተናል፤(2)

ወንድም በወንድሙ ላይ በክፋት ተነሣ

መለያየት ስር ሰዶ ፈጣሪውን ረሳ፡፡

(ሐና ዮሐንስ፣2013)

ዘረኝነት ኃጢአት ነው ትላለች፡፡ ኃጢአት ደግሞ እግዚአብሔርን ማጣት ነው፡፡ ፈጣሪውን ያጣ ሰው ምንም ሕይወት የለውም፡፡ እሷ በመዝሙሯ የጠቀሰችው የተሸነቆሩ ጉድጓዶች ያለቻቸው የዘረኝነት ገደሎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ጉድጓዶች ውስጥ መኖር ደግሞ መጨረሻው መጥፋት መሆኑን የዝማሬው ግጥም ይናገራል፡፡ ቃኤል በአቤል ላይ እንደተነሣ ሁሉ ወንድም በወንድሙ ላይ ተነሣ ትለናለች፡፡

ወንድም በወንድሙ ላይ በክፋት ተነሣ፤

መለያየት ስር ሰዶ ፈጣሪውን ረሳ፡፡

(ዝኒ ከማሁ)

ይህም ታሪክ በኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ አራት ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ቃኤልና አቤል የአዳምና የሔዋን ልጆች ናቸው፡፡ የአቤልን መሥዋዕት እግዚአብሔር እንደተቀበለው ያወቀው ቃኤል፤ በታናሽ ወንድሙ ላይ በቅናት ተነሥቶ ቀጥቅጦ ገደለው፡፡ በዚህም ቃኤል በእግዚአብሔር ዘንድ

ተቀጣ፡፡ ይሄ መዝሙር ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ይጣራል፡፡ ሁሉም የሰው ልጅ አባቱ አዳም እናቱ ሔዋን ናት፡፡ ፈጣሪው ደግሞ አንድ እግዚአብሔር ነው፡፡ ነገር ግን ወንድም በወንድሙ እህት በእህቷ አባት በልጅ ልጅ በእናት ላይ እየተነሡ ይገዳደላሉ፡፡ ይኼ ደግሞ ፈጣሪን መርሳት ነው፡፡

ፈጣሪው አንድ የሆነ ሕዝብ መሠረት እና ምክንያት በሌለው ሁኔታ እርስ በእርሱ ልዩነትን እያሰፋ ይገዳደላል፡፡ ይኼ የመዝሙር ግጥም ዘረኝነትን ይኮንናል፡፡ ድምፀቱ እሮሮ ነው፡፡ መብሰልሰል ነው፡፡ ኩነኔ ነው፡፡ መዝሙሩና የዘመኑ መንፈስን ተዋሕደዋል፡፡

አራተኛ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ወይም ወንጌላውያን አማኞች ዘንድ ዘረኝነት በዝማሬያቸው ያለውን ቦታ እናያለን፡፡ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ዘረኝነትን አጥብቀው ይነቅፉታል፡፡ ፍሬ እንዳያፈራም ብሎም እንዲቀነጭር ይሻሉ፡፡ ለዚህ ማረጋገጫው ከአገልግሎት መስካቸው አንዱ በሆነው የዝማሬ ሥርዓታቸው ላይ ደጋግመው ዘረኝነትን ኰንነዋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ (1980) ገላ.3፥26-29፣ “በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፡፡ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ሰብስቧችኋልና፡፡ አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፡፡ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፡፡ ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፡፡” “ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለምና በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ” 1ኛ ጴጥ. 1፥23

በተለያዩ የአገልግሎት ቦታዎችና ጊዜዎች ውስጥ ሆኖ የሚዘመረው መዝሙር የታምራት ኃይሌ ምድር ሰፊ ናት የተሰኘው የመዝሙር ግጥም ላነሣሁት ርእሰ ጉዳይ ዋቢ ይኾናል፡፡

…

ጌታ ኢየሱስ የሞተላቸው፤

በጎቹ ሁሉ የእርሱ ናቸው፤

በማን ርስት ነው የምንጣላው፡፡

ተው እንመለስ ፍርድ አለ ኋላ፤

ምድር ሰፊ ናት ምን ይገፋፋናል፤

መነካከሳችን ያጠፋፋናል።

በአንድ ቤት ማደር ቢያቅታቸው፤

አብርሃምና ሎጥ ቤተሰብ ናቸው።

ችግር የለም ወይ ግራ ቀኝ መኼድ፤

ከማን ተማር ነው ወገን ማሳደድ።

(ፓስተር ታምራት ኃይሌ ቁጥር 9 1993)

አብርሃምና ሎጥ ቤተሰብ ናቸው። ሳይጣሉ አንተ በዚህ እኔ በዚህ ተባብለው በሰላም የተለያዩበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ለማንጸሪያነት በማስገባት ልዩነትን እንተው፤ ዘረኝነትን እናግልለው፤አንነካከስ ይላል። ዘፍ. (13፥7-11) በዝህ ክፍል ያለው የኦሪት ዘፍጥረት ታሪክ ይኼንን የመዝሙር ግጥም ያገዝፈዋል።

“የአብርሃምና የሎጥ በጎች በሚጠብቁት መካከልም ጠብ ሆነ በዚያም ዘመን ከነዓናውያንና ፈሪሳውያን በዚያች ምድር ተቀምጠው ነበር። አብርሃምም ሎጥን አለው እኛ ወንድማማቾች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሀለው።

… ሎጥም በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለው ሀገር ሁሉ መረጠ ሎጥም ወደ ምሥራቅ ተጓዘ፤ አንዱ ከሌላው እርስ በእርሳቸው ተለያዩ።” ለሁላችንም የሞተው ጌታ ኢየሱስ ነው። ላንዱ ሌላ ለሌላው ሌላ የሞተ የለም። ለሁላችንም የሞተው ኢየሱስ ሆኖ ሳለ ለምን አሳዳጅ ተሳዳጅ እንሆናለን ነው? ጉዳዩ። በግ ያለው ዘማሪው ምእመናንን ነው። በደሙ የተዋጁትን ሁሉንም ክርስቲያኖች ነው። መሠረቱ ይኼ ሆኖ እያለ አንዱ አንዱን ያሣድዳል። ዘረኝነት ያስፈርዳል። መነካከሳችን ያጠፋፋናል። ተው እንመለስ እያለ እየጠየቀ ይለምናል። ይማጸናል፤ መሪር ድምፀት ነው። ዘረኝነት እና መለያየት አንገፍግፎታል። አብርሃምና ሎጥ የአንድ ቤተሰብ ልጆች ሆነው እረኞቹ ሲጣሉባቸው ችግራቸውን በሰላም ነው የፈቱት እኛም ችግሩን በዚህ መልክ

እንፍታው። ወገን ወገኑን ማሳደድ ይቅር ይላል። ዘመነኛው የዝማሬ ግጥም የዘመኑ መታያ ሠረገላ ነው።

ዘመነ ኢህአዴግና ዘጠናዎቹ ወገን በወገኑ ላይ ዘር እየቆጠረ የሚታይና የማይታይ በደል የሚደርስበት ጊዜ ነው። መዝሙሩ የመጣው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በተደረገ ማግስት ነበር ። ሁለተኛው ሀገራዊ ምርጫ የተደረገበት ጊዜም ነበር። የዚህ ሁሉ መንስኤው ልዩነት እና ዘረኝነት ነው። ስለዚህ መዝሙሩ በዙሪያው ያለውን ጊዜ የተሸከመ፤ የዘመን መንፈስ ያረገዘ፤ የመዝሙር ግጥም ነው። ከጦርነት ማግስት ከምርጫ ማግስት ከመፈናቀል ማግስት መውጣቱን ስናስብ መዝሙር የዘመኑ መስታወት ነው።

### 3.1.2. የአንድነት አናጺ መዝሙራት

ዘረኝነትን መኮነን ማለት አንድነት መስበክ ማለት አይደለም፤ ረሃብን መጥላት ማለት ጥጋብን መውደድ እንዳልሆነ ሁሉ። ስለዚህ ዘረኝነትን የሚኰንኑት በአንድ መልክ ታይተዋል። እነዚህ ደግሞ አንድነትን የሚሰብኩ ኅብረትን የሚያነሡ ዝማሬዎች ናቸው።

በአራቱም ሃይማኖቶች ዝማሬዎች ውስጥ በተለያየ መጠን እና ቅርጽ አንድነትን የሚያንጹ የአንድነት[16] አናጺ[17] መዝሙራት፣ የኅብረትን መሻል የሚሰብኩ ስንኞች በየዘመኑ በጉልህ ይገኛሉ። ለአንድነት ሰፊ ዐውደ ምሕረት፣ ለወንድማማችነት ግዙፍ መድረክ ከፍተው የሚሠሩ ሃይማኖቶች ያሉባት ሀገር መሆኗ በቀጣይነት የምንሰማቸው ዝማሬዎች፣ ነሽዳዎች፣ መንዙማዎች ምስክሮቼ ናቸው።

ከጎህ መቅደድ እስከ ጽልመት መንደድ፣ አንድነት በሚቃተትባት ሀገር አንድነት መጥፋቱ የሚያሳዝን እና አንገት የሚያስደፋ ሀገር ቢሆንም ቅሉ ዛሬም ኅብረት፣ ወንድማማችነት፣ አንድነት ይዘመራሉ። አንድነት ማለት ኅብረት ማለት ነው። በኅብረት መቆም፣ ለጋራ ዓላማ በአንድነት መነሣት፣ በመንፈሳዊ እና ቁሳዊ፣ በተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ጠላቶች ፊት እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ በመሆን በወንድማማችነት መንፈስ መነሣት ነው።

---

[16] *አንድነት ሕብረት ወይም ተመሳሳይነት የሚለውን ይይዛል፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት ገጽ 327፣*

[17] *አነፀ (አነጠ) ተጠረበ ሳገ፤2 ሰራ ገነባ፣ አናፂ ሲሆን ደግሞ ከእንጨት የሚሰሩ ቤቶችን እቃዎችን የሚሰራና የሚጠግን ባለሙያ፣ ታነፁ ሲሆን ደግሞ ተጠራበ፣ ተለገ ተሰራ፣ ተገነባ ሕንፃ ሐውል የሚለውን ይይዛል ዝኒ ከማሁ ገፅ 324*

አንድነት ሊባል አንድ ዐይነት የሚለውን መንፈስ አይደለም። በተለያየ ሃይማኖት፣ ባህል፣ እምነት፣ እሳቤ መሠረት ላይ አንድ የጋራ ማንነትን መገንባትን የሚመለከት ነው።

የመዝሙሮቹ መንፈስም አንድ ዐይነት እንሁን ሳይሆን የሚሉት አንድ እንሁን ነው። በአንድ መሆን እና በአንድ ነጻነት መካከል ያለው ልዩነት ከሀገሪቱ መሪዎች እሳቤ ተራው ዜጋ ድረስ ተደጋግሞ ይባላልና።[18]

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዝማሬዎች ስለ አንድነት ምን ይላሉ የሚለውን ላንሣ፣ መራራው ሕይወቴ በሚለው የዲያቆን እንግዳወርቅ መዝሙር ውስጥ ይኽን አንድነት የሚያንጽ ዝማሬ እናገኛለን።

****

ዳሯ እሳት መሐሏ ገነት

ለእኛም ይስጠን ፍቅር አንድነት

****

(ዲ/ን እንግዳወርቅ በቀለ፣ 1997፣ 4-1)

የሚያወራው ስለ ኢትዮጵያ ነው፤ የሚዘክረው ቅድስቲቷን ምድር ነው። "ዳሯ እሳት ነው" ይላታል፤ መሐሏ ደግሞ ገነት ነው፤ የእሳት ዳርነቷ የሚመነጨው ከፈጣሪ ጠባቂነትና ከልጆቿ አልደፈር ባይነት የጀግንነት መንፈስ ውስጥ ነው። መሐል ገነትነቷ ከፈጣሪዋ ቡራኬና ከልጆቿ ታታሪ ሠራተኝነት ይከሠታል። ይሁን እንጂ ፍቅር አንድነት መዋደድ የለም። ከመፋቀር ይልቅ መጣላት ሥራችን ነው፤ ምክንያት እየፈለጉ ከመተባበር ይልቅ ምክንያት እየፈለጉ መሰባበርን መርጠናል። ይኼ ዝማሬ እንደውሃ ፈሳሽ እንደ እንግዳ ደራሽ ዝም ብሎ ተግተልትሎ በኢ-አመክኖያዊ ፍኖት አልተንቦራጨቀም ይልቁንም በምክንያት ነው።

የአንድነት ድንጋይ ግዛው አንድነትን ከሚያንጹ ከኦርቶዶክስ ዝማሬዎች ውስጥ የዘማሪ ፀሐፊ ትእዛዝ ዲ/ን ታዴዎስ ግርማ ምሥጢር ኢትዮጵያ የተሰኘው መዝሙር ነው።

---

[18] *http://youtube/-ay1RJ61R9*

ምሥጢረ ኢትዮጵያ

****

አንድነን ልጆችሽ ኢትዮጵያ፤

ጠላት አይለየንም ኢትዮጵያ፤

ተሰባስበን በፍቅር ኢትዮጵያ።

****

(ዘማሪ ፀሐፊ ትእዛዝ ዲ/ን ታዴዎስ ግርማ 2011)

ቃልና ልብ ያልተጋመዱበት ከንፈርና ሕሊና የተኳረፉበት ጊዜ ነው። በዚህ ሰዓት አንድ ነን ልጆችሽ ኢትዮጵያ ይላል። ጠላት አይለየንም ኢትዮጵያ በማለት ይሰብካል። ከተሰበሰብን በፍቅር በማለት ይጮኻል። ግን አድማጭ ያጣ ጩኸት እንደሆነ ከዚያ በኋላ የተፈጠሩ ክሥተቶች ምስክሮች ናቸው። ዘማሪው በእንቶኔ ዘይቤ ኢትዮጵያን ያናግራታል፡ አንድነን እኮ! ማንም ጠላት አይለየንም! ልጆችሽ እንደ አህያ ጆሮ አንድ ነን! ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት! በፍቅር ተሰብስበናል ኢትዮጵያ - ኢትዮጵያ- ኢትዮጵያ እያለ አንድነትን ይቀርጻል፣ ይማጸናል፣ ያንጻል፣ ይቃትታል።

በኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮች ልብ ውስጥ አንድነት ዋጋው ትልቅ መሆኑን በዝማሬያቸው በነሻዳቸው በመንዙማቸው ገልጠውታል። ነሽዳዎችና መንዙማዎች አንድነትን በጽኑ ያስሷታል፣ አንድነትን ካለችበት ይጠሯታል፣ ወንድማማችነትን ነይ ነይ የትነሽ ይሏታል። አንድነት ግዛቷ ሰፊ ነው። ተናፋቂ ናት፤ ለዚህ ማሳያ ይኸን ዘንድ የሚከተለውን ነሺዳ እንይ፤

****

ወንድሜን ተይ በይው አይግፉኝ ከእቅፍሽ

እኔም የአንቺው ልጅ ነኝ እርሱም ካንቺ ማሕፀን

ካንቺ ሌላ የታለ አዋዶ ሚቀርጸን

ጀሊል ይስማሽ እንጂ ይይሽ በእዝነቱ፤

በደም እንዳይቆሽሽ እንዳይከፋ ቤቱ፤

እምዬ ሃገሬ ላንዱ አላደለሽም

እንዋዳድበት መልሽው ወንድሜን

በረባው ባረባው አያፍስሰው ደሜን

****

(ሀገሬ ቁ፣2 አሽርፍ ናስር፣ 2013)

ዘማሪው ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ወንድሜ ነው ይላል፡፡ ሙስሊም፣ ክርስቲያኑ፣ ዋቄፈታው፣ በተለያየ የሃይማኖት ድርጅት ውስጥ የሚገኘውን በልዩ ልዩ የጎሳ ሣጥን ውስጥ ያለውን ሁሉንም የኢትዮጵያ ልጆች አንድ መሆኑን አበክሮ ይገልጻል፡፡ በእንቶኔ ዘይቤ ኢትዮጵያን ያናግራታል፡፡ እኔ የአንቺ ልጅ ነኝ፣ እርሷም ካንች ማሕፀን፣ ካንቺ ሌላ የታል፤ አዋዶ ሚቀርጸን፣" እያለ ይጠይቃታል፡፡ እዚያው ይመልስና ጀሊል ይስማሽ ይላታል፤ ጀሊል የሚለው አምላኩን ፈጣሪውን ነው፡፡ እኛ የአንድ እናት ልጆች ሆነን ከተጣላን ካልተባበርን፣ ቤቱ ይቆሽሻል በማለት በምክንያትና ውጤት አንድ አለመሆን የሚያስከፍለውን ዋጋ ይናገራል፡፡ ኢትዮጵያ ለሁሉም የተዘረጋ እጅ እንዳላት፣ የማታዳላ ሐቀኛ እናት መኾኗን፡-

እምዬ ሀገሬ ላንዱ አላዳላሽም፤

ለግራም ለቀኝም እቅፍ አያጥርሽም፡፡

እንዋደድበት መልሺው ወንድሜን፤

በረባው ባራባው አያፍሰሰው ደሜን፡፡

(ዝኒ ከማሁ)

በማለት እናቱ ኢትዮጵያን እምዬ እያለ እየጠራ ይማጸናታል፡፡ ከኩርፊያው፣ ከጠላትነት ፍኖት፣ ከጥፋት ሀዲድ፣ ካለማተባበር ወጥመድ፣ መልሸውና አንድ እንሁን የሚል የለቅሶ እና የተማጽኖ ድምፀት የታከለበት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ልክ እንደ እናት ፍትሐዊ ናት፡፡ እናት ከአብራኳ ለተገኙት ልጆቿ በፍጹም እንደማታዳላ ኢትዮጵያም ለማንም አላዳላሽም ነው የሚለው፡፡ ያለሽ ለም መሬት፣ ያለሽ ውሃ፣ ያለሽ ሕዝብ፣ ያለሽ ድልብ ታሪክ ለሁላችን ይበቃል የሚል ነው ልመናው፡፡ ሰበብ እየጠቀስን ከምንባላ ምክንያት እየፈለግን በመዋደድ እንደ ሰም ተጣብቀን አንድ ሆነን እንቁም፡፡ ያለን ይበቃናል፡፡ ለሁላችን ይተርፋል ነው ጭብጡ፡፡

ዘመኑን የዋጀ ነሽዳ ነው፡፡ ወቅቱ ሀገራዊ እርቅ የሚፈለግበት አንድነት የሚሰበክበት በሙስሊሙም በክርስቲያኑም ኅብረት ዘንድ ከመለያየት አንድ ወደ መሆን መንፈስ የደረሰበት ጊዜ ነው፡፡ አንድ ሆኑ ሲባል ደግሞ እንደገና ለመለያየት የሚያቆበቁቡበት ሥጋት ፈተና የበዛበት ጊዜ ነው፡፡ ዘመኑን ገላጭ ተማጻኝ ዝማሬ ነው፡፡

በኢትዮጵያ እስልምና ተከታዮች ዘንድ የአንድነት ዋጋው ግዙፍ መሆኑን ሌላው ምሳሌ የብሥራት ዜና ተሰማ በሚል በኅብረት የቀረበው ነሺዳ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

የብሥራት ዜና ተሠማ

ትፈቅድ እንደሁ ልምጣ ወዳላህበት፤

ሳይገድለኝ ኅዘኑ ሳልሞት በፀፀት፡፡

የሔድንበት መንገድ ልክ አልነበረም፤

በአንድነት ለመቆም ይኼው ቃል ገብተናል፡፡

(አሊ አሚን፣ ሙአዝ ሀቢብ፣ መሐመድ አወል ሳላህ፣ ነስሩ ኸድር፣ ሙሀመድ ሰዒድ፣ አስማማው አህመድ፣ ቶፊቅ የሱፍ በኅብረት የቀረበ 2012)

የለውጡን በረከት የተቋደሰ የነሺዳ ግጥም ነው፡፡ ከለውጡ ከ2010 ዓ.ም. በፊት የሙስሊሙ ኅብረተሰብ በብዙ ፈተና ውስጥ እንደነበረ የሚታወቅም የሚነገርም ነው፡፡ የሙስሊሙን

ማኅበረሰብ ጥያቄዎች አንግበው ድምጻችን ይሰማ ብለው የተነሡትን ወጣቶች የኢህአዴግ መንግሥት አሥሯቸው ነበር፡፡ በዚህም በአማኙ ማኅበረሰብ ዘንድ መከፋፈል ነበር፤ በመጅሊሱም አመራሮች ተቋም በርካታ ጥያቄዎች ይነሡ ነበር፡፡

የለውጡ መሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር  አቢይ(ዶ/ር) አህመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን መከፋፈል በማስቀረት ረገድ ያገኙትን ስኬት [19] ፣ በእስልምና እምነት ተከታዮችና መጅሊሱ አካባቢ የነበረውን ሽካራ ግንኙነትና ልዩነት በመናድ እና በማስታረቅ አመርቂ ውጤት አምጥተዋል፡፡ [20] ይኼንን ተከትሎ የጋራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሁሉም የተስማሙበት መጅሊስ በማቋቋማቸው፣ የተለያዩት አንድ በመሆናቸው የተሰማቸውን ደስታ በሚሌኒየም አዳራሽ የገለጹበት ነሽዳ ነው፡፡ [21] ወቅቱን የጠበቀ፣ ጊዜ አሳይ፣ ክስተት ጠቋሚ፣ ውስጣዊ ሐሴት ፈንጣቂ አንድነት ሰባኪ ነሽዳ ወይም መዝሙር ነው፡፡

ከርእሱ ሲጀምር የብሥራት ዜና ተሰማ ነው የሚለው፡፡ የምን ብሥራት ሰምተው ነው? ተብሎ ሲጠየቁ፤ እርቅ ተፈጠረ፣ ከአብሮነት ብርሃን አድማሱ አንፀባራቀ፣ ሰማይ ምድሩ ደመቀ፤ ሰማይና ምድር የተባለው ግዑዛን አይደሉም፤ በሰማያት ያሉ ፈጣሪ፣ መላእክት (መላይካን) ናቸው፤ በምድር ደግሞ ሰዎች፡፡ አንድ በመሆናችን ሁሉም ደስ አለው፡፡

የአንድነት ክፍያው፣ የዋጋውን ስሌት ይጠቁማል፡፡ የሔዱበትን መንገድ ይረግማሉ፡፡ ስለ ነገው አቀበት ያስባሉ፤ ወንድም ወንድሙን እንዴት ይረሳል? ይላሉ፡፡ የእናቶችና አባቶች ልመናና ለቅሶ ያን የመለያየት ግንብ በማፍረስ ያለብንን የትውልድ አደራ ለመወጣት በአንድነት፣ በአብሮነት በጋራ መቆም አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው ይላሉ፡፡ ይኼ በእምነት አጥር ውስጥ ብቻ ተቀብሮ የሚቀመጥ ሐሳብ አይደለም፡፡ የአብሮነት ፋይዳ የትውልድን አደራ ተሸክሞ ለቀጣዩ ትውልድ ማሻገር የሚቻለው አንድ ስንሆን ነው፡፡ የአንድነት ውሉ የኅብረት ምሥጢሩ ጥልቅ ነው፡፡

የነሽዳው ድምፀት ደስታና ስብከት ነው፡ ቃል ኪዳን ማሰር ነው፡፡ ሁሉም የሆኑት በአንድነት ዐደባባይ ላይ መሆኑን ግጥሙ ይናገራል፡፡

---

[19] *Httos://youtube/H6VNX7ek1k የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሲኖዶስ በጋራ ባለመሥራታቸው ሀገሪቱ ብዙ ትርፍ አጥታለች ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ 2018jul.*

[20] *[https://youtube/50N62754hfo](https://youtube/50N62754hfo) ጠቅላይ ሚኒስትሩና የሙስሊም ኮሚቴዎችና መጅሊስ ጋር ስብሰባ 2018 July.*

[21] ዝኒ ከማሁ

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዝማሬዎች ውስጥ አንድነት አብሮ መቆሚያ ኃይል ነው። የፈጣሪ መደመጫ መንገድ ነው። የድል መወጣጫ መሰላል ነው። ይኸንንም በካቶሊክ እምነት ዘንድ ትልቅ ቦታ ባላት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናት አማካኝነት እናያለን። አንድነትን መሰብሰብን በቅድስቲቱ እናት በኩል ይፈልጉታል።

ሰላም ስጠን

****

እመቤቴ ማርያም የብርሃን መንገድ፤

<u>ሕዝብሽን ሰብስቢ</u> አድርጊያቸው በአንድ።

የሕይወት ምንጭ ኢየሱስ ሰላም ተጠምተናል፤

ሁሉንም ትተነው ዐይንህን ናፍቀናል።

***

(መስመር ከራሴ)

(የጽዮን ማርያም ካቶሊክቤተ ክርስቲያን ወጣት መዘምራን ቁ.1.1986)

ዝማሬው የወጣው ከደርግ ውድቀት በኋላ ነው። ሀገር ለሁለት ተከፍላለች፤ አንድ የነበረችው ኢትዮጵያ ኤርትራ የምትባል ሀገር አዋልዳለች። በአንድ የኢትዮጵያ ጥላ ሥር የነበረ ሕዝብ ተከፋፍሏል። ልዩነት በዝቷል። ጎሳ ሰባኪ ተጠናክሯል። እንሰብሰብ ከሚለው ይልቅ እንገንጠል እንበተን የሚለው አይሏል። ሕገ መንግሥት አልወጣም፤ ሀገራዊ ምርጫ አልተካሔደም።

ሁለቱም የሆኑት 1987 ነው። በሁለቱ ዋዜማና ከኤርትራ መኼድ ማግስት የተዘመረ ጊዜውን ገላጭ የዝማሬ ግጥም ነው። ድምፀቱ ልመናና ተማጽኖ ነው። በመላው የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ዘንድ አምላክ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ከሁሉም ፍጥረታት የከበረ ትልቅ ቦታ አላት። በእርሷ በኩል ወጣት መዘምራን የኢትዮጵያን አንድነት ይማጸናሉ። ሕዝብሽን ሰብሳቢ፤ የተለያዩትን አንድ አድርጊ፤ መበተን ጥቅም የለውም፤ የአንድነት ልዕልናው፣ በአንድ

የመሰብሰብ ከፍታው፣ ጥልቅ እና ጥብቅ የሆነበት ግጥም ነው፡፡ ከመውደቅ ይልቅ መነሣትን፣ ከመበተን ይልቅ መጠጋጋትን ይለምናል፤ ይኼ ደግሞ ውጤቱ ሰላምና ድል ነው፡፡

በኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ዕምነት ተከታዮች ተማሪዎች ዘንድ ያለው የአንድነት ናፍቆት አንድነትንና መቀነትን ያንፀባረቀ ነው፤

ኢትዮጵያ

አውቀዋል አድገዋል ያልሻቸው ልጆችሽ፤

ሁሉም እሾህ ሆነው እየወጉ አደከሙሽ፡፡

የአንድነት ማሠሪያ መቀነት ይኑርሽ፤

እግዚአብሔር ነይ ይላል ወደርሱ ተመለሽ፡፡

(ኢትዮጵያ፣ ሙሉቀን መለሰ፣ 1995፣ ቁጥር 1)

ኢትዮጵያ ይላታል እናቱን በቁጭት ድምፀትና በእልህ መንፈስ፣ ስለጠኑ፣ ዐወቁ፣ ነቁ፣ በቁ፣ ተማሩ፣ ተመራመሩ፣ ፊደል ቆጠሩ፣ ድንቁርን መነጠሩ የተባሉ ልጆቿ አሏት፡፡ ሁሉም ግን እሾህ ሆኑባት፡፡ የእናት ጡት ነካሽ፣ ወጭት ሰባሪ፣ ዘር ቆጣሪ፣ (ገበሬው ዘር ዘርቶ አላፈራ ያለውን መሬት ዘር ቆርጥም ይለዋልና)፣ በሌላት ጎኗ አስተምራ፣ ለወግ ለማእረግ አብቅታ ውለታዋ ግን ይኼ ሆነ የሚል ነው፡፡ የዘማሪው ኢትዮጵያ ሁሉም ይወዳታል፡፡ ችግሩን ብቻ ነቅሶ ገለል አይልም፡፡ መፍትሔውንም እንካችሁ ይላል፡፡ መቀነትን ነቅሶ ለግሷል፡፡[22]

መቀነት ማሰሪያ ነው፤ መቀነት ማጥበቂያ ነው፤ መቀነት በሴቶች ወገብ የሚታሰር ወገብ ማጥኛ ጽኑ ጨርቅ ነው፡፡ አንድም እንዳይደክሙ ማበርቻ መሣሪያ ነው፤ አንድም የተለበሰው ቀሚስ እንዳይዝረከረክ መሰብሰቢያ ገመድ ነው፤ አንድም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያሉ ሴቶች በመቀነታቸው ገንዘባቸውን፣ ውድ ነገራቸውን፣ ቡናቸውን፣ ጨዋቸውን፣ የሚቋጥሩበት ሙዳይ ነው፡፡

---

[22] *ቀነተ (መቀነት) ቅናት ታጠቀ፣ አሰረ፣ ጠመጠመ፣ ባህሩ፣ 32*

አንድም ዕንጨት ያሠሩበታል፤ አንድም የታመመ የቆሰለ ሰው ሲኖር ያክሙበታል፡፡ መቀነት ረቡ እልፍ ነው፡፡ የአንድነት ዋጋው የትየለሌ ነው፤ የረሃባችን መሶብ፤ የመበተኛችን፣ ገመድ፣ የድካማችን ምርኩዝ፣ የቁስላችን ፈውስ ነው፡፡ መዝሙሩ በዘመነ ኢህአዴግ የወጣ ነው፡፡ ያ ዘመን ደግሞ ኢትዮጵያዊ አንድነት የላላበት፣ ከሀገራዊ አንድነት ይልቅ፣ ሰፈራዊ ማንነት የነገሠበት ጊዜ ነው፡፡ ይኽን የሚሰብኩት ደግሞ የተማሩት ልጆቿ ናቸው፡፡ ግጥሙ እነሱን ይወቅሳል፡፡ ኢትዮጵያን የወላድ መካን ነሽ ይላታል፡፡ የአንድነትን አስፈላጊነት በመራር ድምፅ ይሰብካል፤ በኢትዮጵያውያን ልጆች ልብ እንዲተከል ያዝዛል፡፡

### 3.1.3. ሃያሲያነ መንግሥት መዝሙራት

ሃያሲያነ መንግሥት የመዝሙር ግጥሞች በዚህ ክፍል ይተነተናሉ፡፡ እዚህ ላይ ሂስ ስንል አንድም አጠቃላይ የኪነጥበብ ሥራዎችን የምንፈትሽበትንና የምንገመግምበትን ቅጥ ነው፡፡[23]አንድም በየትኛውም ጉዳይ ባሉ ነገሮች ላይ የሚሰነዘር አፍራሽም ገንቢም ገጽታ ያለው ሐሳብ ነው፡፡[24] አንድም ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎችን ብቻ የሚመለከተውን ነው፡፡[25] መንግሥት ሲባል ደግሞ አንድን ሀገር በጉልበትም ይሁን በሥርዓት፣ በምርጫም ይሁን በግልምጫ የሚመራ የኢኮኖሚ እና የሐሳብ የበላይነት ያለውን ቡድን ማለት ነው፡፡[26]

መንግሥትን የሚሄሱ፣ ሥርዓቱን የሚነቅፉ፣ መሪዎቹን የሚተቹ፣ መንግሥትን የሚገሥጹ፣ የመዝሙር የነሽዳና የመንዙማ ግጥሞች በድፍረት፣ ከሕሊናቸው ሳይጣሉ በጥብዐት ለእውነት በመቆም ብዕራቸውን አሹለው በመጻፍ በአንደበታቸው ይዘምራሉ፤ ምእመናንም ያዳምጧቸዋል፡፡ በዘመን መንኮራኩር ውስጥ ያለፉትን መንግሥታት ማንነትና ምንነት በመንፈሳዊ ሕይወት ማሳላጫ መሣሪያዎች አማካኝነት ያዩባቸዋል፡፡ ይታዘቧቸዋል፡፡ ይጸልዩላቸዋልም፤ ይጸልዩባቸዋልም፡፡ ይኼ ደግሞ ከሀገር ግንባታ አንጻር ከታዬ ለማበብም ለመርገፍም አስተዋጽኦው የላቀ ነው፡፡

---

*[23] C. Hugh Holman. 98),*

*[24] መንግሥት ኢኮኖሚያዊ የበላይነት ያለው መደብ ፖለቲካዊ ድርጅት ሲሆን አለማውና ተግባሩም በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለውን ሥርዓት ለማስጠበቅና ለማጠናከር የሌሎች መደቦችን ተቃውሞና አሻፈረኝ ባይነት ለማፈን የሚያገለግል የመጨቆኛ መመሪያ ነው፡፡ ማርክሲዝም ሌንዝም መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 61*

*[25] Criticism or more, specifically lidiey criticism... Is over all term for studies concerned with hefining, classifying, analysing, interpreting, and evaluating works of literature. M.H. Abrams Geoffrey Galf Harpham. Glossary of Literary terms*

*[26] ማርክሲዝም ሌኒንዝም መዝገበ ቃላት፣ 27*

በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን ዘንድ የየዘመኑን የሥርዓቱን ንቅዘቶች፣ ጉድፎች፣ በመንፈሳዊ ድፍረት ሲኮንኑ፣ ሲያወግዙ፣ ሲገርዙ ይታያሉ፡፡ ዲያቆን እንግዳወርቅ በቀለ የሁሉም ዐይን አንተን ተስፋ ያደርጋል በሚለው ዝማሬው እንዲህ ይላል፡፡

የሁሉም ዐይን

የሁሉም ዐይን አንተን ተስፋ አድርጓል፤

ምሕረት ቸርነት ይጠባበቃል፡፡

ሸክሙ ከብዷል አቅልለን፤

ያላንተ ጌታ ሌላ ማን አለን፡፡

ዕንጨት ለቃሚ ባልቴት ነበረች፤

በሠራፕታ በድህነት ያለች፡፡

በአክአብ ምክንያት ረሃብ ሆኗል፤

ወደሞት ልንወርድ ተዘጋጅተናል፡፡

(ዲ/ን እንግዳ ወርቅ በቀለ፣ ቁጥር5 1989 5.7)

የሁሉም ዐይን ተስፋ ያደረገው አምላክን ነው እንጂ መሪዎችን አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይላል ዘማሪው፣ ሸክሙ ከብዷል፡፡ የከበደው ደግሞ በአክአብ ምክንያት ነው፡፡ ሸክም የተባለው መከራ ችግር፣ ረሃብ፣ በሽታ ጉስቁልና ነው የዚህ መነሻ ጦስ አክአብ ነው፡፡ አክአብ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ የክፋት ታሪክ መሪ ነው፡፡

የእስራኤል መንግሥት ገዥ የነበረ የእግዚአብሔር ነቢያትን ያስጨፈጨፈ፣ በሚስቱ ኤልዛቤል ረዳትነት የናቡቴና ደም ያፈሰሰ ንጉሥ ነበር፡፡ በዚህ ሁሉ ግፍ የተነሣ በነቢዩ ኤሊያስ ጸሎት አማካኝነት ዝናብ ማፍሰስን፣ ለሦስት ዓመት ከስድስት ወር ያኽል የእስራኤል ሰማይ ተለጎመች፡፡ የሰራፕታዋ ረሃብተኛ ሴት የአክአብ የኃጢአት ገፈት ቀማሽ ናት፡፡

አክአብና ሚስቱ ኤልዛቤል በበደሉት ሕዝቦች ተቀጡ። ዜጎች አለቁ።[27] ይኼን ታሪክ በንቡር ጠቃሽ ዘይቤ ያመጣል።[28] የሥርዓቱን አስከፊነት በዝማሬው ይገሠጻል።

አክአብ፣ መዝሙሩ በወጣበት ዘመን የነበሩትን የኢትዮጵያ መሪዎች ያሣያል። ዘመኑ ዘመነ ኢህአዴግ ነበር። የኢህአዴግ መራሹን መንግሥት መሪዎች በእናንተ ምክንያት ነው ሀገሪቱ ለዚህ መከራ የበቃችው ይላቸዋል። ዘማሪው ግን የሥርዓቱን መሪዎች ከአክአብ ጋር እያነጻጸረ ለኢትዮጵያ ጉስቁልና ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። ድምፀቱ ግሣጼ ነው። ዘመኑንም የዋጀ ነው። የሚሰማ ከተገኘም ከእንቅልፉ አባንኖ ፀፀትና ንስሐ የሚያስገባ ነው። መዝሙራት፣ ሀገርን በዚህ መልኩ የመታደግ ሥልጣን እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። ትድግናቸው በማንቃት የሚገለጽ ነው።

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን ዘንድ የየዘመኑን ሥርዓት መሪዎች የሚሸነቁጥ መንስኤ ጉስቁልና እንጂ ምክንያት ዕረፍት መሆን እንዳልቻሉ የሚጠቁም የዝማሬ ስንኞች አሏቸው። የአዲስ አበባ መድኃኔዓለም ቁምስና ወጣት መዘምራን ማኅበር እንዲህ ይላሉ፤

ተመለሽ ሀገሬ ኢትዮጵያ፤

እስኪ አስተውይው ዛሬ ያለሽበትን፤

ችግር ጉስቁልና በዙሪያሽ ያለውን።

ከዚህ ሊታደግሽ ጌታ በደጅ ነው፤

በፊቱ ውደቂ ዛሬም ምሕረት አለው።

ኃያላን ነገሥታት ጠቢባን ቢሆኑም፤

ስላንቺ መፍትሔ ማምጣት ግን አልቻሉም።

****

[27] *የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 402*

[28] *ዘሪሁን፣ 127*

(የአዲስ አበባ መድኃኔዓለም ቁምስና ወጣት መዘምራን ማኅበር ቁጥር 4፣ 2000 ዓ.ም.)

ከርእሱ ጀምሮ ሲታይ “ተመለሽ ሀገሬ ኢትዮጵያ” ነው የሚለው፡፡ የሚያወራው ስለ ኢትዮጵያ ነው፡፡

ከላይ ኢትዮጵያን አንሥቶ ከሥር ወደ ፈጣሪ ተመለሽ ይላል፡፡ መሪዎችሽ መሣሪያ እስከአፍንጫው የታጠቁት ኃያላኑ ገዥዎችሽ በነገሥታት የተመሰሉት ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ሚኒስትሮቹ፣ ፕሬዝዳንቱ፣ ዐዋቂ የሚባሉት መፍትሔ አልሰጡሽም፡፡ በመንግሥት ላይ ተስፋ ቁረጭ፣ ከመሪዎቹ ላይ ዐይንሽን አንሺ እያሉ ዘማሪዎቹ የሥርዓቱን መሪዎች ይተቻሉ፡፡

መሪውን ተቹ ማለት ሥርዓቱን ነቀፉ ነው፡፡ የሥርዓቱ ቁንጮ ሹፌር ሆነው የሀገርን መኪና የሚያሽከረክሩት እነሱ ናቸው፡፡ ያውም በዘመነ ዕሥራው ምዕት (ሚሌኒየም) ላይ መንግሥት ልማት አስመዝግቤአለሁ ብሎ ለዓለም ሕዝብ ለማሳየት ሽር ጉድ በሚልበት ጊዜ መቅረቡ ሲታወስ የዝማሬው ግጥም የዘመን ማሳያ መስታወት መሆኑን ያሳያል፡፡

### 3.1.4. አጽራረ[29] ኢትዮጵያ በመዝሙራቱ

ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ግዙፉን ሃይማኖቶች ዝማሬዎቻቸው አምስት ዋና ዋና የጋራ ጠላቶች አሏቸው፡፡ እነዚህም **ጠኔ፣ ደዌ፣ ግዞት፣ ጦርነት፣ ሞት ናቸው፡፡** የዝማሬዎቹ ግጥሞች መጠኑ ይለያይ እንጂ በጋራ ጠላቶቻቸው ክንድ የተንጠለጠሉ ናቸው፡፡ በአስተምህሮቻቸውና ወደ ፈጣሪ ማድረሻ መንገዳቸው ይለያዩ እንጂ አጽራሮቻቸው በአደባባዮቻቸው አንድ ያደርጓቸዋል፡፡ መልክዐ ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ መልኮች) የኢትዮጵያ ገጾች ሆነው በእነዚህ መንፈሳዊ ዝማሬዎች የቀረቡትን ግጥሞች እንይ፡-

#### *3.1.4.1. ጠኔ*

ጠኔ ጽኑ ረሃብ ዐቅም የሚያሳጣ፣ የሚጥል ማለት ነው፡፡[30]ረሃብ በኢትዮጵያውያን የሃይማኖት መዝሙራት ውስጥ ዋነኛ ጠላት ተደርጎ ተሥሏል፡፡ ከጠላትም ጽኑ ጠላት ነው፡፡ ኢትዮጵያ የዳቦ ቅርጫት[31] ተብላ እንዳልተጠራች በትናንትም በዛሬም መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ዝማሬዎች ውስጥ የማይነቀል ጠላት ነው፡፡ ረሃብ ክፉ ነው፡፡ ልጅ ከልጅ ይለያል፡፡ እናትና አባት

---

*[29] ኪዳነ ወልድ፣ 778*
*[30] አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 549*
*[31] ድርቅና ጠኔ በኢትዮጵያ ፪ኛ ዓመት ቁ 5-7፣ ገጽ 3*

ያቆራርጣል። ወገንን ለጦርነት ይጋብዛል። አባቶችን ይኼን አይተው ይመስላል ከረሃብ ጦርነት ይሻላል ይሉናል።

ረሃብ ማሰቢያን ይዘጋል፤ ህሊናን ያውራል፤ ማሰቢያ የተዘጋ ህሊናው የታወረ፣ አእምሮውን የሳተ ዜጋ ደግሞ ለረሃቡ ምክንያት የሆኑትን ችግሮች ሁሉ ለመጋፈጥ ወደኋላ አይልም፤ መንግሥትንም ጨምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን ረሃብን በተለያየ ድምፀት በልዩ ልዩ ሕብር በየዘመኑ በተገለጠላቸው መንገድ ገልጸውታል። የሁሉም ዐይን በሚለው የዲያቆን እንግዳወርቅ መዝሙር ላይ ኢትዮጵያዊው ረሃብ እንዲህ ይገልጣል፤

የሁሉም ዐይን

. . .

ያለው ይመስላል ለብሶ ሲያዩት፤

ላይ ታች እያለ ይዞት ጭንቀት፤

የልጆቹ ዕንባ ጨኸት ሰልችቶት፤

ልመና ገባ ምሁሩ ድንገት።

ከዛሬ ነገ ይሻላል ስንል፤

እየባሰ ሔደ አለመታደል።

እምነ ረሃብ ይኼይስ ኵናት፤

ብለዋልና ደቀመዛሙርት።

አሳይተኸን ጌታ አትንሳን፤

በደል አለብን ይቅር በለን፤

. . .

(ዘማሪ ዲያቆን እንግዳወርቅ በቀለ፣1989/5.7 ከኦርቶዶክስ)

ምሁሩ ድንገት ነው ልመና የገባው፤ መማሩ ጥቅም አልነበረውም፤ የልጆቹ ዕንባና ጩኸት የረሃብ ነው፡፡ ይኸን መቋቋም አልተቻለም፡፡ ከዛሬ ነገ ይሻላል ብሎ ነበር፤ ነገር ግን አልተቻለም፡፡ መንግሥት ነው እንጂ የተለወጠው ረሃቡ ያው ባለበት ነው፡፡ ከዛሬ ነገ የሚለው የረሃብን የጊዜ ርዝመትና ጥልቀት ያሣያል፡፡ እምነ ረሃብ ይኼይስ ኵናት ይላል፤ ከረሃብ ጦርነት ይሻላል ያሉትን ሐዋርያት ይጠቅሳል፡፡

ኢትዮጵያ የተቀመጠችው ወርቅ ብር ላይ ነው፡፡ ግን ተርባለች፤ በብርድ ልብስ ውስጥ ሆኖ መበረድ፣ በውሃ ማማ ላይ ተቀምጦ መጠማት፣ በወርቅ ዙፋን ላይ ተዘርግቶ አንጀት መታሰር፣ ለሰሚው ግራ ይገባል፡፡ ግን እውነት ነው፤ ኢትዮጵያ ተርባለች፡፡

የረሃብ ምክንያት ደግሞ ፍቅር ማጣት፣ የአስተዳደር ብልሹነት ናቸው፡፡ ድምፀቱ እሮሮ ነው፡፡ ምሬት ነው፡፡ የዳቦ ቅርጫት ኢትዮጵያ፣ የውሃ ቋት ኢትዮጵያ፣ በዘመነ ኢህአዴግ እንዲህ ነበረች ይለናል፤ ዘማሪው እያለን ያለው መንፈሳዊ ረሃብ አይደለም፣ ምድራዊውን ጠኔ ነው፡፡

ረሃብ ማስታገሻ ካልተሰጠው መሪውን ይበላል፡፡ ረሃብ፣ ረሃብ ብቻ አይደለም፤ፖለቲካም ጭምር ነው፡፡ የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትን ካነቃነቁት ድጂኖዎች አንዱ ጠኔ ነው፡፡ ጠኔ ሰልፍም ሰይፍም ያስነሣል፡፡

### *3.1.4.2. ደዌ*

በሽታ ከኢትዮጵያ ጠላቶች አንዱ ነው፡፡ ደዌ፣ በሽታ ሕመም ማለት ነው፡፡[31] መንፈሳዊውን በሽታ፣ የነፍሱን ቁስል አይመለከትም፡፡ ሰውን ከሰው የሚለየውን እንጂ፣ ሰውን ከፈጣሪው የሚነጥለውን የነፍስ ሕመም አይደለም፡፡ ይኽን በኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዝማሬዎች በምሬት ይጠቅሱታል፡፡ የኢትዮጵያ መለያ መልኳ መሆንም ይነግሩናል፡፡ ዘማሪያት ይኽንን አስከፊና ቀሳፊ በሽታ ቸነፈር፣ ይሉታል፡፡ ቸነፈር በሽታ ነው፡፡ ተላላፊ በሽታ፣ መቅሠፍት፣ ተስቦ እልቂት ይለዋል፡፡[32]የኢትዮጵያ ሌላው መልክና ጠላት ደዌ ወይም ቸነፈር ነው፡፡

---

[32] አክሊሉ፣ 9

ኢትዮጵያ ትባረክ

ኢትዮጵያ ትባረክ በሽ ዓመት፤

ጌታ በሽ ዓመት፤

ምድራችን ትባረክ በሽ ዓመት፤

ጌታ በሽ ዓመት፤

አላት የተስፉ ቃል

አንተ የገባህላት፤

እንለምንሃለን እንዲፈፀምላት።

ረሃብ ቸነፈሩ ችግሩም በሽታ፤

ከምድር ተወግዶ ይሁን ሰላም ደስታ።…

(ኤደን ፍቃደ ሥላሴ፣ መዓዛ ዓለሙ፣ አሸናፊ ደበላ፣ ዘሪሁን እናውጋው፣

ዘማች ክብሩ፣ ዓለምዬ፣ በኅብረት የሠሩት 2000 ዓ.ም.) ከካቶሊክ ቤተክርሲቲያን፤

በምድረ ኢትዮጵያ የበሽታው መቅሠፍት ከፍቷል፤ ቸነፈር ከተራ ደዌ ላቅ ይላል። ዝማሬው የሚለው ጊዜ የማይሰጥ በሽታ ላይ ወድቀናል ነው። በሽታ ከፋብን፣ ከበሽታም በሽታ ጊዜ የማይሰጥ ፋታ የማያበጅ መቅሠፍት፤ ኤች አይ ቪው፣ ወባው፣ ይኼ እስከሚመጣበት ጊዜ ኢትዮጵያ በስንት የበሽታ ማዕበል፣ የቸነፈር መዝሙር ወጀብ እንዳለፈች ያሳየናል። ይህ የመዝሙር ግጥም የዘመኑን ፖለቲካዊ መልክ በቸነፈሩ መራርነት በመሪር ድምፀት ይገልጣል።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ፊት ላይ ከመጡ አስቀያሚ በሮች አንዱ ደዌ ቸነፈር መሆኑን ዘማሪያን በመዝሙራቸው በሚገባ ገልጠውታል ማለት ነው። ጊዜው ሚሌኒየም ነው። ቸነፈሩ በሽታው እንዳለ ያምናሉ። ኢትዮጵያ በዚህ የበሽታ ወጀብ እንደተከበበች ይናገራሉ። ነገር ግን ከዚህ

ከአዲሱ የሚሌኒየሙ መባቻ ጀምሮ እርሱ ተወግዶ ደስታ ሰላም ይምጣ ይላሉ፤ ዝማሬያቸው ዘመኑን ዘመነ በሽታ ይለዋል፡፡ እውነት ነው፤ ኢትዮጵያ በብዙ በሽታ፣ ደዌ፣ ቸነፈር ስትጠዘጠዝ ነበር፡፡ ምኞታቸው ግን እውን ሆኗል? ተብሎ ሲጠየቅ፤ መልሱ አልሆነም ነው፡፡ ይኼው ይኼ ጥናት እስከተሠራበት ባለው ዘመን ሌላ "ኮረና" የሚባል ወረርሽኝ መጥቶ ዓለምንም ሀገራችንንም ብዙ እነደጎዳ ተመልክተናል፡፡

*3.1.4.3. ስደት*

በእስልምና እምነት ተከታዮች መነሽዶች ዘንድ ስደት በጽኑ ይወገዛል፡፡ ለዚህ የስደትን አስከፊነት በተለያየ መንገድ ገልጸውታል፡፡ ስደት ቀዬን ጥሎ ከተወለዱበት ሥፍራ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሀገርን ጥሎ መውጣት ነው፡፡ በፖለቲካ ምክንያት፣ በረሃብ ምክንያት፣ በጦርነት ምክንያት ወዘተ. ተገፍተውና ተከፍተው ከወዳጅ ዘመድ ተነጥሎ ወደሰው ሀገር መሄድ ነው፡፡ ሙነሽድ ሙአዝ ሀቢብና አሸርፍናሰር እንዲህ ይሉናል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለነበረው የዜጎች ስደት፡-

ጠብቃት ሐበሻን

****

ዕዝነት አፈር ገባ ሰው በሰው ቆሰለ፤

የወንድምም አንጀት ለወንድም አልበጅ አለ፡፡

ሀገርስ ነበረን እንደሌላው ሀገር፤

መዋደድ ሲሳነን መረረን ቸነፈር፡፡

እናትም ስታጣ የወለደችውን፤

<u>የስደት ማእበል ነጥቆባት ልጇን፡፡</u>

ሰው ሁሉ ተከፋ በረካን በማጣት፤

ያረቢ ኑሥራህን ያዘነ ይደሰት፡፡

****

መስመር ከራሴ

(ሙነሽድ ሙአዝ ሀቢብ እና አሽርፍ ናስር 2010 (2011?)

ከእስልምና፤ መተዛዘን ቀርቷል፤ ሰውም በሰው ቆስሏል፤ ወንድም በወንድሙ ጨክኗል፡፡ ሀገርስ ነበራቸው፣ ልክ እንደ ሌሎቹ፤ ታዲያ ምን ያደርጋል ሀገራቸው ለልጆቿ አልሆን ብላ በስደት ማዕበል መመታቷን ይነግሩናል፡፡ ስደት የኢትዮጵያ ሌላው መታወቂያ ካርድ ሆኗል፤ የቀድሞ ታሪኳ የሚመሰክረው የስደተኞች መጠለያ እንደነበረች ነው፤ ነገር ተለውጦ ታሪክ ተገልብጦ የእርሷ ልጆች የሌሉበት ሀገር የለም፡፡

እንደ ጨው ዘር ተበትነዋል፡፡ ያልተሰደደ አይበለጽግም ወይም ጀነት አይገባም የተባለ ይመስል በብዙ ገፊ ምክንያት ሕዝቡ ተሰዶ አልቋል፡፡ በአረብ ሀገራት፣ በአውሮፓና፣ በአሜሪካ የነጻነት አርበኞች ልጆች ባይተዋር ኖነው በስደት ይንከራተታሉ፡፡ በግፍ ይታሠራሉ፤ የስደት ሕይወት መራራ ነው፡፡ ይኼ ደግሞ ዘመኑን ያሳያል፡፡ የፖለቲካውን አስተዳደር ይገልጣል፤ የሕዝቡን አኗኗር ያመለክታል፡፡ ሀገርስ ነበረን እንደሌላው ሀገር ሲል ተስፋ ቆራጭ ድምፀት ነው፡፡ ስደት የፈቃድ ባርነት ነው፡፡ ነሺዳው ብዙ ጓዝ ተሸክሟል፡፡ ዘመንና ኑሮን እህህ ይላል፡፡

### *3.1.4.4. ጦርነት*

እዚህ ላይ የምናየው ሰማያዊውን ወይም መንፈሳዊውን ጦርነት አይደለም የግጥሙን ምድራዊ ጦርነት እንጂ በወንድማማቾች በእኅትማማቾች፣ በአዳም ወይም በአደም፣ በሔዋን ወይም በሐዋ ልጆች መካከል የተደረገውንና የሚደረገውን መሬታዊና ሥጋዊ ጦርነት ነው፣ የምናየው በኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ዘንድ የተዘመረውን ግጥም ነው፡፡ ምን ያኽል ትኩረት ተሰጥቶታል? እንዴትስ ያለቦታ ተለግሶታል? የዘማሪ ሙሉቀን መለሰ መዝሙርን እንመልከት፤ ሙሉ መዝሙሩን ስናዳምጠው ወይም ስናነበው፤ የተለያዩ ሐሳቦችን ያነሣል የሚኰንነው የሃይማኖት ተቋም አለ፡፡ ስለ ሰላም ያነሣል፣ ስለ ፍርድ ያነሣል፣ ስለ ጦርነት ያነሣል፡፡

እዚህ ላይ ስለ ጦርነት የሚያነሣበትን ክፍል ብቻ እንይ፤

**ኢትዮጵያ**

****

ጦርነት ረሀብ ስደት ደርሶብሻል፤

ችግር በየፈርጁ ተፈራርቆብሻል።

በመከራሽ ብዛት ያፍረት ማቅ ለብሰሻል፤

የሚታደግ አዳኝ ኃያል ብርቱ አተሻል።

****

(ሙሉቀን መለሰ ቁጥር 1፣ 1995 ዓ.ም.)

ይኸ መዝሙር የወጣው ከኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በኋላ ነው። ጦርነቱ የተጀመረው በ1990 ዓ.ም. ሲኾን የተቋጨው ደግሞ በ1992 ዓ.ም. ነው። ለዚህ ጦርነት ከሰማንያ ሺህ (80,000.00) በላይ ሰዎች ሕይወታቸው ተቀጥፏል።[33]

ሀገሪቱ በጦርነት አዙሪት እንደነበረች ያሳያል፤ የጦርነት ዳፋው ደግሞ መጠነ ሰፊ ቀውስ ይዞ ይመጣል፤ የኢትዮጵያ ቁርስ ምሳና እራት እስኪመስል ለዐሥራ ሰባት ዓመታት በጦርነት ስትታመስ የነበረች ሀገር እንደገና ከሰባት ዓመት እረፍት ማግስት ተመልሳ ተማገደች፤ በመቶ ሺዎች ተፈናቀሉ፤ በሺዎች ሥጋቸው ለአሞራ ሲሳይ፣ ለጅብ እራት ሆነ፤ ዘማሪው የእናት ሀገሩን መከራ በምሬት ድምጸት ጦርነት ደርሶብሻል። ችግር በየፈርጁ ተፈራርቆብሻል፤ ጦርነትም የሚያኮራሽ ሳይሆን ያፍረት ማቅ አልብሶሻል ይላታል፤ ይኼ እውነት ነው ጦርነት የሀገር ኢኮኖሚ ያደቃል፣ ወገንን ከወገን ይነጥቃል። የሥነ ልቦና ቀውስ ያስከትላል፤ ለአካል ጉዳት ይዳርጋል፤ ልጅና ወላጅን ይነጥላል።

የሥነ ልቦና ቀውስ ያስከትላል፤ ለአካል ጉዳት ያበቃል፤ ጦርነት ጌጥ፣ ባህል፣ ኩራት፣ ሞገስ አይደለም፤ እፍረት ማቅ ውርደት ነው።

[33] አክሊሉ፣ 9

የሚታደግሽ የለም ይላታል፡፡ የዘመኑ መሪዎቻችንም፣ ሆኑ መንግሥቶቹ ከዚህ መከራ ሊታደጉን እንዳልቻሉ፤ የጊዜውን የጦርነት ድባብና ውጤት በፀፀት እና በቁጭት ይነግረናል፡፡ በጦርነት የሚጠቀሙት የጦር መሳሪያ አምራች ድርጅቶች ብቻ ናቸው፡፡ በጦርነት ደስ የሚላቸው የወታደሩን ሥጋ የሚበሉት አሞራና ጅብ ብቻ ናቸው፡፡

እናትና አባት ወገንና ዘመድ የወታደሩን አስክሬን እንኳ አያገኙትም፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ጦርነትን በፊልም አይደለም የምናውቀው በየጓዳችን እንጅ፤ የዝማሬው ግጥም ለአማኙ ይኼን መራራ ሀቅ ተጋቱት ይላል፡፡ እነዚህ ኃይሎች መሪዎቿ ናቸው፡፡ ጀግናና ስልጡን መሪ ማለት ጦርነት አድርጎ የሚያሸንፋ ሳይኾን ጦርነት እንዳይካሔድ ማድረግ የሚችል ነው፡፡ ጦርነት የከሠረ ፖለቲካ ውጤት ነው፡፡ በሚታደግ ኃይል ማጣት ውስጥ ዝማሬው የሚናገረው ይኼንን ነው፡፡

*3.1.4.5. ሞት*

ሞት ሁለት ዐይነት ትርጉም አለው፡፡ አንደኛው የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው፡፡ ሁለተኛው የነፍስ ሞት ነው፡፡ የመጀመሪያው ምድራዊ ሲሆን ሁለተኛው ግን ሰማያዊ ነው፡፡ ምድራዊው ሞት በፈጣሪ ቁጣ፣ በአስተዳደር ብልሹነት ሊመጣ ይችላል፡፡ እዚህ ላይ በዘማሪዎች ግጥሞች ላይ የሚታዩት በግዴለሽነት እና ደጎና መሪ እንዲሁም የተሻለ ፖለቲካዊ ምህዳር ባለመፈጠሩ የሚመጣውን ሞት የሚያወግዙና የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ይኸንንም ከክርስትና አንድ ከእስልምና አንድ ዋቢ አድርገን እንይ፡-

ከኦርቶዶክስ፡-

ኢትዮጵያ እጆችሽ ዘርጊ

****

ሕፃናት ወላጆች አጥተው በሜዳ ሲበታተኑ፤

ንስሮችሽ ወጣቶች አልቀው የአፈር ሲሳይ ሲሆኑ፤

የሞት መልአክ ተልኮብሽ የአፈር ሲሳይ ሲሆኑ፡፡

(ዘማሪ ቴዎድሮስ ዮሴፍ 1994)

ከሙስሊም፡-

ታረቀን

****

ሀገሬን እላለሁ ላለቅስ እየዳዳኝ

የሙት እናት ስትሆን ኃዘኗ እንዳይጎዳኝ (2ጊዜ)

(ሙነሽድ አስማማው፣ እስማኤል ተክሌ፣ ሀሰን ዑመር 2012 (2013)

በዘማሪ ቴዎድሮስ የቀረበው ሞት ከባድ ነው፣ ከሰማይ የታዘዘ ቁጡ የሞት መልአክ ነው የመጣው፤ በዚህም ሕጻናት ወላጆችን አጡ፣ ቡቃያዎች ረገፉ፣ የአፈር ሲሳይ ሆኑ፣ ወጣት አጣሽ፣ አንድም በበሽታ አንድም በጦርነት አንድም በረሃብ፤ መዝሙሩ የወጣው፣ 1994 ነው። የጦርነት ማግስት ነው። ኤች.አይ.ቪ. ወጣቱን ያረገፈበት ጊዜ ነው። ድምፀቱ መራር ነው። ጊዜውን አመላካች ነው።

በሙነሽድ አስማማውና፣ እስማኤልና ሀሰን የቀረበው ነሺዳ ደግሞ አምላክ እንዲታረቃቸው ይለምናሉ፤ ስለ ሕዝቿና ስለኢትዮጵያ ነው። የሙት እናት ሆናለችና፣ ወልዳ መካን ሆናለችና፣ ሀገሬን እላለሁ ይላሉ፣ በለቅሶ ሲቃ፤ ኃዘናቸው ከባድ ነው። የእናት ቤት ባዶ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ልጆቿን ስታጣ፣ ሞትን አምርረው ይጠሉታል፤ ሞትን ሲቃወመው መኖር ይፈልጋል፣ ሞት የሃይማኖቶቹ የዝማሬዎች መገለጫ ነው።

## 3.2. ሀገራዊ ድምፀት ያላቸው መዝሙራት

በዚህ ክፍል በጥናቱ የተመረጡት ሃይማኖቶች ዝማሬዎች የሀገራቸውን፣ የጀግኖቹን፣ የነገሥታቱን ታሪክ በአደረጉት ወይም በገጠሙት መነጽርነት ልክ ያተቱትን ይታተትበታል። የተመለከቱትን ይታይበታል። በሌላ በኩል ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር የገለጹበት ቅጥ ይመረመርበታል።

### 3.2.1. ሀገረ ታሪክ ዘካሪ መዝሙራት

ሀገር ማለት በቁሙ ሀገር፣ መንደር፣ ከተማ፣ ገጠር፣ ብዙ ቤቶች የተሠሩበት፣ ብዙ ሰዎች የሚኖሩበት፣ በያቅኚውና በየክፍሉ ገዥ አዛዥ ዳኛ መልእክተኛ ያለው ታላቁም ታናሹም..።[34] ሀገር ከደም ትስስር፣ ከቋንቋ ከባህል እና ሃይማኖት ልዩነት በላይ የሆነ ፖለቲካዊ የጋራ ማንነት ነው።[35] ታሪክ ደግሞ በዘመናት ኑባሬ ውስጥ የሰው ልጅ በማኅበራዊ ባህላዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ ፖለቲካዊ ፍልስፍና እና መሰል ሁነቶች በተለያዩ ሰፋሪ አሐዶችና ዳራዎች ያደረጋቸው ፈርጀ ብዙ መስተጋብሮችን እንዲሁም በየጊዜው አፈር ላይ ያሳረፋቸው አሻራዎች.. የሚጠናበት ጥበብ ነው።[36] ሃይማኖቶቹ ስፋቱና ቅርጹ ይለያይ እንጂ ስለ ሀገራቸው፣ ስለ መኖሪያቸው ስለሕዝባቸው ግድ እንደሚላቸው ከዚህ በታች የማነሣቸው ዝማሪዎች ዋቢዎች ናቸው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪዎች የኢትዮጵያን ታሪክ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን ታሪክ አድርገው ያቀርቡታል። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ አድርገው ይወስዳሉ። ይኸንንም በልዩ ልዩ ዝማሬዎያቸው ያመሠጥሩታል፤ ያለ ኦርቶዶክስ ኢትዮጵያ የለችም። ያለ ኦርቶዶክስ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር አትታሰብም የሚል መንፈስ ያላቸው ግጥሞች በዝማሬዎቻቸው ይደመጣሉ። ይኸንንም ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ የሀገሪቱ መሪ "ኦርቶዶክስ ሀገርናት" ብለው ሐሳባቸውን ያጠናክሩላቸዋል።[37]

ዘማሪ ዲያቆን ትዝታው ሳሙኤል "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" በሚለው ዝማሬው ታሪክን ይዘክራል፤

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ

የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ፤

የአንድ ምድር ማኅፀን መንታ፤

---

[34] አለቃ ኪዳነ፣ 365

[35] አምሃ ፣ 16

[36] ታየ ፣69

[37] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሲኖዶስ በጋራ ባለመሥራታቸው ብዙ ትርፍ አጥታለች፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ https://youtube/H6VNXQNXQTekQk

ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኢትዮጵያ፤

ኢትዮጵያ - አኵሱም ላሊበላ የታሪክ አሻራ፤

ኢትዮጵያ - የጣና ገዳማት የግሸን ተራራ።

****

(ዘማሪ ዲ/ን ትዝታው ሳሙኤል 2000 ዓ.ም.፣)

ይኽ መዝሙር የወጣው በዘመነ ኢህአዴግ ነው፣ የወቅቱን የዘመን መንፈስ ያዘለ ነው። ቤተ ክርስቲያኗን ከዘመነ ደርግ ጀምሮ የመግፋት፣ ንብረቷን የመውረስ ልክፍት የመጣባት ፍጹም ለውጥ ያልመጣላት፣ የመንግሥቱ መሪዎች ቤተ ክርስቲያኗን ሳያከብሩ ሚለኒየምን በዓል ለማክበር ተፍተፍ የሚሉበትን ጊዜ ነበር፤ የዚህ ምሬት ያንገፈገፈው ዘማሪ ታሪክ እየዘከረ ትናንትን  እየጠቀሰ ስጫት ሰገነት ይላል። ቤተ ክርስቲኗ የሀገሪቱ ታሪክ የእኔ ታሪክ ናቸው የምትላቸውን ሰበዞች እያነሣ በመጀመሪያ ስንኞቹ አዚሟል።

ዘማሪው ቤተ ክርስቲያኒቱንና ሀገሪቱን መነጠል እንደማይቻል ይነግረናል። በአንድ ሳንቲም ላይ በፊት ለፊት የሰው ጀርባው ደግሞ የአንበሳ ምስል አለ፤ አንዱን ስታነሣ ሌላውን ታነሣለህ፤ አንድ ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ መኼድ አይቻልም ነው ጭብጡ።

አኵሱምን ያነሣል፤ ላሊበላን ይዘክራል፤ የጣና ገዳማትን ያመጣል፤ ሀገሬን አላስደፍርም ያሉትን፣ በጣሊያኖች መትረየስ ሰውነታቸውን በደም አበላ አጨቅይተው በክብር የወደቁትን አቡነ ጴጥሮስን፣ ያወሳል፤ ፊደሉን፣ ቁጥሩን፣ የዘመን መቁጠሪያውንና ስነ ጽሑፍን ይዘረዝራል። ይኼ ሁሉ ታሪክ የኦርቶዶክስ ነው። የእኔ የምትዪው ሁሉ የተዋሕዶ ነው፤ ይላታል።

በመገፋት ቁዘማ ውስጥ ያለ፤ ውለታው የተዘነጋ፤ አመድ አፋሽ የሆነ ሰው መንፈስ የተጫነው ድምፀት ነው። የቤተ ክርስቲያኗንም የሀገሪቱንም ታሪክ እንድናስታውስ ያደርገናል። ታሪክ ነጋሪ ታሪክ ዘማሪ ግጥም ነው።

በኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታይ መነሽዶች ዘንድ ታሪክ ነቃሽ ታሪክ ዘካሪ ነሻዳዎች መንዙማዎች በተለያየ ጊዜ ቀርበዋል፡፡ የጥቁር ሕዝብ መኖሪያነቷን፣ የዓለም የስልጣኔ አሻራ ባለቤት መሆኗን፣ ቀደምት ምድርነቷን፣ በጥዑም ቃላት ገልጸዋል፡፡ ለዚህ ምስክር ኢትዮጵያ በሚል ርእስ ሙዐዘ ሀቢብ እና ቶፊቅ የሱፍ ያቀረቡት ነሽዳ ነው፡፡

****

የዓለም ስልጣኔ የጥበብ አሻራ፤ (ኢትዮጵያ)

የታየብሽ የነጻነት ጮራ፡፡

ቀዳማዊት እመቤት የጥቁሮች አምባ፤

አንቺ ነሽ ኢትዮጵያ የአርነት ካባ፡፡

(ቶፊቅ የሱፍ፣ ሙአዝ ሀቢብ 2011 ዓ.ም.)

ይህ ነሽዳ ዘመን አይሽረውም፣ ጊዜ አይከዳውም፣ ታሪክ ዐዋቂ አይዘነጋውም፤ ተቀዳሚ ሐሳቡ በሀቂቃ ላይ የቆመ የእውነት ሐውልት ነው፡፡ ጥንታዊት የዓለም ስልጣኔ ወጋገን የፈነጠቀባት እንደሆነች በርካታ ታሪካዊ ማስረጃዎች አሉ፡፡[38] የአክሱም ሐውልት፣ የፋሲል ግንብ፣ የነሽዳ መስጊድ፣ ላሊበላ፣ ሶፍ ዑመር ዋሻ፣ የሐረር ግንብ፣ ፊደሏ፣ ዘመን አቆጣጠሯ፣ ስነ ጽሑፏ ድንቅ ምስክሮቿ ናቸው፡፡

የጥቁር ሕዝብ መከበሪያ መሆኗን የዐድዋን ታሪክ ምሥጢር ይስባል፡፡[39] ጥቁር የተከበረው በዐድዋ ድል ማግስት ነውና፡፡ ፈጣሪ የቸራትን ተፈጥሯዊ ጸጋዋንና ታሪኳን ይስባል፡፡ አንድን ዘመን ብቻ የሚሸከም ብቻ ሳይሆን ዘመንን እየዋጀ የሚሻገር ማለፊያ ታሪክ ነቃሽ ግጥም ነው፡፡ ድምፀቱም የመዘባነን የኩራት ነው፡፡ የሙገሳ ነው፡፡ ሀገራቸውን ያወድሳሉ፡፡

የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ዘማሪ የሆነው ዘማሪ ታምራት ኃይሌ ቀደምት የኢትዮጵያን ታሪክ እንዲህ ይነቅሳል፡-

---

[38] ጌታቸው፣ 90
[39] ጳውሎስ፣ 218

የጥበብ ጌታ

****

እኔማ ኢትዮጵያ ነኝ፤

ብዙ እንቆቅልሽ ያለኝ፡፡

ጌታ አንተም ንጉሥ ነህ፤

እንቆቅልሽን መፍታት ታውቃለህ፡፡

የዕውቀት የጥበብ ጌታ፤

እንቆቅልሽን ፍታ፡፡

በዛና እንቆቅልሼ፤

ለብዙ ዘመን አልቅሼ፡፡

አንድ ቀን ዝናህን ሰማሁ፤

ልነግርህ ከሳባ መጣሁ፡፡

(ዘማሪ ታምራት ኃይሌ ቁጥር 6 1985)

ታሪኩ በንቡር ጠቃሽ ዘይቤ የደመቀ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ "የሳባም ንግሥት በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች፡፡" 1ኛ ነገ 10÷1፡፡ ይኽ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ የኢትዮጵያ ታሪክ ነው፡፡ ዘማሪው ይህንን መነሻ አድርጎ ያቀርባል፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንድ ሺ ዓመተ ዓለም ነግሣለች፡፡ ግዛቷ ሰፊ ነበር፡፡ የሰሎሞንን ጥበብ ስትሰማ ስለነበር ታምሪን በሚባለው ነጋዴ አማካይነት ብዙ ዝና አዳመጠች፡፡

ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘች። [40] ብዙ ጥበብ ተማረች። ሰሎሞንንም ፀነሰች። እንቆቅልሿንም ፈታላት።[41] ዘማሪው አንድም ጌታ የግሉን የሕይወት እንቆቅልሽ እንዲፈታለት ይጠይቃል።

አንድም ውስብስብ ችግሩን እንዲተረትርለት ይማጸናል። አንድም የኢትዮጵያን ውል የጠፋበትን የመከራ እንቆቅልሽ እንዲፈታ ፈጣሪውን ይለምናል። ሰሎሞንን በጌታ ሳባን በኢትዮጵያ እየመሰለ የጉስቁልናው ቅኔ ሰምና ወርቁ እንዲገኝለት ይቃትታል። እኔም ኢትዮጵያ ነኝ ብዙ እንቆቅልሽ ብዙ ችግር፣ እልፍ ፈተና ያለብኝ ይላል። ኢትዮጵያ በሳባ ተገብታ ትማጸናለች።

እዚህ ላይ በትኩረት የምናየው ዘማሪው ጉዳዩን ለማስረዳት የጠራውን ጥንታዊ ታሪክ ነው። ይህ ታሪክ ኢትዮጵያ ፈጣሪዋን ለማግኘት የሔደችበትን ጥበባዊ ጉዞ ያመሣጥራል። ይህ ታሪክ ኢትዮጵያ ለጥበብ እና ለሥልጣኔ የነበራትን እና ያላትን ከባድ ተምኔት ይናገራል። የመዝሙሩ ታሪክ የንግሥተ ሳባን እና የሰሎሞንን እንዲሁም የቀዳማዊ ምኒልክን ታሪክ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያዘክር ታሪክ አስታዋሽ እና ተማጻኝ ግጥም ነው።

### 3.2.2. ሀገር ፍቅር አዝማሪ

በዚህ ክፍል በሀገር ፍቅር የነደዱ ዝማሬዎች በሀገር ፍቅር የተሰቃዩ ስንኞች፣ በሀገር ፍቅር የነኾለሉ ነሸዳዎች፣ ከፍቅራቸው ብዛት የተነሣ የቃል ጎተራቸው የገዘፈ የመዝሙር ግጥሞች ከየሃይማኖቶቹ ተመርጠው ይተነተኑባቸዋል።

ፍቅር በአንድ ነገር ላይ ከፍተኛ የሆነ የመወደድ ስሜት መኖር ነው።[42] ሀገር ያደጉበት ከተማ ወይም ገጠር፣ የተወለዱበትና ያቀኑት፣ በደስታ ጊዜ የተደሰቱበት በኀዘን ጊዜ ያዘኑበት የጠጡት፣ የሚታጠቡበት ወንዝና ውኃ የተመላለሱበትአቀበት ቁልቁለት፣ መንደር ለመሥራት የገቡበት ጫካው ሳሩ፣ ዱሩ፣ ያፏጩበት ሽንተረሩ፣ አየሩ፣ እሸቱ፣ ምርቱ፣ ባህሉ፣ ሃይማኖቱ ሳቁ፣ ለቅሶው፣ እድሩ ሽምግልናው ሁሉ በነጻነት ኪራይ ዋጋ ሳይከፈልበት የሚከናወንበት ትንሹም ትልቁም መሪውም ተመሪውም የሚታወቁበት ማንነትን የሚያጎናጽፍ ጥለውት ሲሔዱበሔዱበት ሌላ ሀገር ምን ቢሳካ ቢሞላ የማይረሳ ከውስጥ የማይጠፋ ማንነት ነው።[43]

---

[40] *ሰሎሞን፣ 50-57*
[41] *ክብረ ነገሥት ግዕዝና አማርኛ፣ 17-25*
[42] *የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ፤ መዝገበ ቃላት፤ 590*
[43] *አባ ሕርያቆስ፣ 398*

ዘማሪያኑና ሙነሽዶች ትርጉም ባለው ፍቀር ከንፈው ኢትዮጵያን እናቴ፣ እምዬ፣ ሀገሬ ሲሏት እንመለከታለን፣ ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር ምእመናቸቸው ወክለው በልዩ ልዩ ኅብረ አምሳል ስኬታቸውን ይገልጻሉ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ካሴቶችን በማውጣት ከቀዳሚዎች ተርታ የሚመደበው ሊቀ መዘምራን ቴዎድሮስ ዮሴፍ እንዲህ ይላል፤

ሰላም ለኢትዮጵያ

****

ሰላም ለኢትዮጵያ ሰላም ለሀገራችን፤

ይላክልን ይላክልን ቸሩ አምላካችን፡፡

ለዓለማት ሁሉ ኢትዮጵያ ተስፋ ነሽ፤

አይደለሽም ብዙ በቁጥር አንዲት ነሽ፡፡

. . በታላቁ መዝገብ ስምሽ የሰፈረ፤

የቆየው ድንበርሽ እንደተከበረ፡፡

ያኑርሽ ፈጣሪ አንችን ከፍ አድርጎ፤

መሐልሽን ገነት ዳሩን እሳት አድርጎ፡፡

(ሊቀ መዝምራን ቴዎድሮስ ዮሴፍ፣ 2012)

በታላቁ መዝገብ ስምሽ ሰፍሯል ይላታል፡ ይህ ታላቅ መዝገብ ማነው? ቢባል በዓለም መጻሕፍት ዘንድ በሽያጩ እና በተነባቢነቱ አንቱ የተባለው ቅዱስ እና ተወዳጅ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ኢትዮጵያ የሚለው ስም በክብር በተደጋጋሚ ተጽፏል፡፡

ይህንን ዐውቆ ነው ስምሽ የከበረ ነው፤ ኢትዮጵያ የሚላት፡፡ እርሱ የሚያመልከው ፈጣሪ ሀገሩን ኢትዮጵያን ከፍ አድርጎ እንዲያኖርለት ይለምናል፡፡ ከፍቅሩ ብዛት የተነሣ ጠላቶቿ ብዙ ስለሆኑ ዳሯን እሳት መሐሏን ገነት እንዲያደርግለት ይመኛል፡፡

ማንም ሰው ለሚወደውና ለሚያፈቅረው ነገር ሁሉ ክፉውን ማየት አይፈልግምና። የዓለም ሁሉ ተስፋ ኢትዮጵያ ናት ይላል። የፍቅሩን ጥግ የገለጸበት መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። በተፈጥሮ ሀብቷ ተስፋ ናት፣ የግዮን መፍሰሻ ናት፣ በነጻነት ክብሯ፣ የጥቁሮች መመኪያ፣ በዳግም ባርነት ያለመውደቅ ተስፋ፣ የማሸነፍና የድል ምልክት ናት፣ በእግዚአብሔር ሕዝብነቷ ተስፋ ናት፤ በዚህም ይመካል። ለዘማሪው -- ኢትዮጵያ፣ ተስፋውም መመኪያውም ዳር ድንበሩም፣ ታላቅ መዝገቡም፣ አንዱም፣ ብዙውም ናት። በኢህአዴግ ውስጥ ለውጥ ከተደረገ በኋላ የተዘመረ መዝሙር ነው። ዘመኑ ስለ ኢትዮጵያዊነት ከንዳ እስከ ቤተመንግሥት ብዙ የሚባልበት የቁጭት እና የተስፋ ጊዜ ስለነበረ።

በእስልምና እምነት ተከታይ ሙነሽዶች ዘንድ የሀገር ፍቅር መገለጫው ብዙ ነው። እስከ ሞት የደረሰ ነው፤ ነፍስን አሳልፎ እስከመስጠት የሚለካ ነው። መተኪያ የሌላትን ውድ ሕይወት እስከ መገበር የደረሰ ነው። ነፍስን አሳልፎ እስከመስጠት ከዚህ ሌላ የሀገር ፍቅር የት ይገኛል? ይህንን አንኳር ሐሳብ ሀገሬ ቁጥር ሁለት በተሰኘው የአሽርፍ ነስር ነሺዳ ላይ ይገኛል።

ሀገሬ ቁጥር 2

****

ሀገሬ ሀገሬ ደረትክን ስጥ ቢለኝ ለጠላት ቀልደኛ፤

ዘብ ቁምላት ብባል ሌት ተቀን ሳልተኛ።

ለአፍ ወለምታ እንኳ ከቶ ሳላቅማማ፤

እሞትልሻለሁ ሀገሬ ለአንቺማ።

ሀገሬ (4)

****

(አሽረፍ ናስር፤2013)

ነሸዳው የወጣው፣በኢህአዴግ መቃብር ላይ ብልጽግና ፓርቲ ነፍስ በዘራበት ዘመን ነው፤ የኢህአዴግ ዋነኛውና ቀዳማዊ ግንባር ህውሓት አኩርፎ በረሃ የገባበት ጊዜ ነው። በዚህም ጦርነት ተነሥቷል። ሀገሪቱም የእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ ነበረች። በዚህ የጦርነት ቀውስ መሐል ነው ነሸዳው ለአማኙ የደረሰው። ኢትዮጵያ የተነሣባትን የውስጥ ጦርነት ለማሸነፍ ከሁሉም የኢትዮጵያ ሥፍራ ጎሳ፣ ቀለም፣ ሃይማኖት ሳይል የዘመተበት ወቅት ነው። ነሸዳው ዘመኑን ከነጽልመቱ ተሸክሟል። የጀግንነት ድምፀት ተሞልቷል።

"ሀገሬ" ይላታል እናቱ ኢትዮጵያን ደረትክን ስጥ ብባል እሰጥላታለሁ። ደረት የነፍስ ወለል ነው። ለሀገር የነፍስን ወለል መስጠት እንዴት ያለ መውደድ? እንዴት ያለ ፍቅር ነው? አጃኢብ ነው። ደረት የሕይወትመሠረት ነው። የሕይወት መሠረት ለሾለ ጦር መስጠት ምንኛ መታደል ነው። ለእናት ሀገሩ ያለው የፍቅሩ ጥልቀት ከነፍሱ በላይ ነው። እግራቸውን ለጠጠር ደረታቸውን ለጦር ሰጥተው በክብር ያቆሟትን አርበኞች አባቶቻችን ሀገር እሱም አንዳባቶቹ ለመሆን ተመኘ። ጠላትን በቁጣ የሚገላምጥ፤ ሀገርን አለሁልሽ በሚል መንፈሳዊ ጥንካሬ የሚያጀግን በሀገር ፍቅር የተቃጠለ ድምፀትን ያነገበ ነሸዳ ነው።

በዚህ ዘማች እና አዝማች ነሸዳ ውስጥ ለዘጠኝ ጊዜ ሀገሬ ምን ዐይነት የሀገር ፍቅር? እንዴት ያለ መውደድ ነው? በጥቂት መስመር ጥልቅ ፍቅር ተገልጾበታል። የሀገር ፍቅርን በጽኑ መሠረት ላይ ይተክላሉ።

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን ለሀገራቸው ባላቸው ፍቅር የተነሣ ፈጣሪቸውን ኢትዮጵያን አሰባት ተመለከታት ያላንተ ማንም የላት እያሉ ወደፈጣሪያቸው ወደፈጣሪዋ ይማጸኑላታል፤ ሰው ለወደደው ላፈቀረው ነገር መልካም ይመኛል፤ ከምኞትም አልፎ በቃልም በተግባርም ይገልጻል። ይኼ ዝማሬ ይህንን ያሳያል።

ኢትዮጵያን አስባት

****

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን አስባት፤

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን አስባት፤

በምሕረት አይኖችህ ተመልከታት፤

በምሕረት እጆችህም ዳስሳት፤

በፍቅርህ ደግፋት፡፡

(የመቂ ኪዳነ ምሕረት ወጣት መዘምራን ማኅበር፣ ቁጥ 3 አልበም፣ 2006 ዓ.ም.)

የሀገር ፍቅር መገለጫው መልኩ ብዙ ነው፡፡ ሕይወቱንና ገንዘቡን በመስጠት፣ ለሀገሩ መልካም በመመኘትና ፈጣሪ ሀገሩን ከክፉ እንዲጠብቅለት በጾም፣ በጸሎት፣ በለቅሶ በመለመን ፍቅሩን ይገልጻል፡፡ በቀንና በሌሊት ከሚታይና ከማይታይ፣ ከረቂቅ መንፈሳውያን ጠላቶች ኢትዮጵያን ፈጣሪ እንዲጠብቅላቸው በፍቅር እንዲደግፋት፣ በምሕረት እንዲጎበኛት፣ በፍቅር ያሳስባሉ፡፡

ከእነሱ ዐቅም በላይ የሆነ ችግር እንዳለ በመዝሙሩ ይታያል፡፡ የእግዚአብሔር ዐይኖች ደግሞ እንዲመለከትላቸው ይጠይቃሉ፡፡ ለሀገራቸው ፍቅር.. ደስታ መልካም ነገር ሁሉ እንዲመጣ በማሳሰብ ፍቅራቸውን አሳይተዋል፡፡ የ2007 ዓ.ም. ምርጫ ሊመጣ በዋዜማው የተዘመረ ነው፡፡ ይኼም ቀጣዩን ጊዜ የሚማጸኑ ናቸው፡፡

በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ዘንድ የሀገር ፍቅርን የሚዘክሩ፣ በተለያየ ዓመት ውስጥ ልዩ ልዩ መልክ ያላቸው ዝማሬዎች አሉ፡፡ ከእናት ጋር ያመሳስሏታል፡፡ እናት መተኪያ እንደሌላት፣ አምሳያ እንደሌላት፣ አንዲት እንደሆነች ሁሉ ሀገርም እንዲህ ናት ይሏታል፡፡ ለአብነትም የመስከረም ጌቱ ዝማሬ ቀርቧል፡፡

ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ 2 እማማ ሀገሬ ኢትዮጵያ፤ (2)

ኢትዮጵያ 2 እማማ ሀገሬ ኢትዮጵያ፤ (2)

ሰላም እፎይታሽን አድብቶ ሚናጠቅ፤

ክፉ ጨካኝ አውሬ ዲያብሎስ ደም አፍሶ ሚስቅ፡፡

ወንድም ከወንድሙ እየገፈተረ፤

በትውልዱ ልብ ውስጥ አመጽ ጥላቻን ያኖረ።

ዛሬ በአምላክ ስልጣን ትእዛዝ ከላይ ይውጣ፤

ጠላትሽ ይሰየፍ በጌታዬ ቁጣ።

ዳር ድንበር ዙሪያሽን ይጠርሽ በእሳቱ፤

የጨለማው ምክር ይሁንባት ከንቱ። (መስከረም ጌቱ 2013 ዓ.ም.)

በእነዚህ ስንኞች ውስጥ ገና በአዝማቹ ሀገሬ፣ እማማ፣ ኢትዮጵያ የሚሉ የእናት ሀገር ፍቅር መግለጫ ቃላትን በውብና ጽኑ የፍቅር ድምፀት ተሰድረው እናገኛለን። ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ስምንት ጊዜ፣ እማማ የሚለው አራት ጊዜ፣ ሀገሬ የሚለው አራት ጊዜ ተጠቅሷል። በሁለት መስመር ስንኝ ይህ በእናት ፍቅር መንደድ የተገለጠበት ለምንድን ነው? ብለን እንድንጠይቅ የሚጋብዝ ነው። ኢትዮጵያ እልፍ ጠላቶች አሉባት፤ ሰላምን የሚናጠቅ፣ ወንድም ከወንድም የሚያጋድል ክፉ መንፈስ፣ ዳር ድንበሯን ያለፈ ወራሪ ኃይል፣ ደም አፍሳሽ ጨካኝ አውሬ አለና እነዚህን እንዋጋ ነው የሚለው። ዘማሪው ይኼ ሁሉ ፈተናና ጠላት ያንዣበባትን ሀገሩን እናቱን ኢትዮጵያን የአምላክ ስልጣን መሠረት አድርጎ ከላይሽ ይውጣ ይኽ ሁሉ ጠላት ይወገድላት ሲል ይገልጻል።

ዘማሪው ሀገር ሀገር ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚባልበት ዘመን ላይ ቁሞ ነው ይኼን መዝሙር ያወጣው። ዘማሪው ኢትዮጵያ ጠላቶቿ ብዙ ናቸው በማለት ለሀገሩ ይጨነቃል፤ ለኢትዮጵያ ያስባል፤ የሚፈታተናትን ርኵስ መንፈስ በቁጣ ይገሥጻል።

## 3.3. ማኅበራዊ ድምፀት ያላቸው መዝሙራት

በዚህ ርእስ ውስጥ ነሥሣ ይቅርታና ሌብነትን ገናኘ የሆኑ ማኅበራዊ ድምፀት ያላቸው መረጃዎች ተተንትነውበታል።

### 3.3.1. ኅሠሣ ይቅርታ መዝሙራት

ኅሠሣ፣ ፍለጋ፣ ፍላጎት፣ጥያቄ፣ ጥየቃ፣ምርምር፣ምርመራ፣ፍቃድ መፈቀድ፣ ሐሳብ ምኞትን ይይዛል።[44] ይቅር ማለት ሲባል ለበደለን ሰው ይቅርታ ማድረግ ማለት ነው። ይቅርታ ተብሎ የተተረጎመው የግሪክኛ ቃል ቀጥተኛ ትርጉም መተው የሚል ነው...። ይቅርታ ውጤቱ የውስጥ፣ የቤተሰብ፣ የጎረቤት፣ የሀገር ሰላም መማጣት ነው።

ይቅርታ ከራስ ጋር ሊደረግ ይቻላል። ከተፈጥሮ ጋርም እርቅ ሊፈጸም ይችላል። እዚህ ላይ የሚፈለገው ይቅርታ፣ በፈጣሪና በሰው መካከል ስለተፈጸመው በደል የሚሆነውን የይቅርታ ካሳ አይደለም። በሰዎችና በሰዎች፣ በጎሳዎችና በጎሳዎች መካከል የተፈጸመ ጥቁር ጠባሳ መፈወሻ መድኃኒት ነው።

የሃይማኖት ፍሬዎች የሆኑት መዝሙራት ቂምን እያወገዙ ከልብ የሆነ ይቅርታ እንዲበዛ ይሰብካሉ። ይማጸናሉ። ያስተምራሉ። ሰው ሰውን ይቅር ሲል ፈጣሪ ደግሞ እርሱን ይቅር እንደሚለው የሃይማኖቶቻቸውን መጽሐፍ እየጠቀሱ ለይቅርታ የልባቸውን ደጅ የሚከረችሙትን ይገሥጻሉ።[45] ሰሚ አግኝተዋል ወይስ አላገኙም? ቃላቸው የምእመናን ልብ ላይ ሠርቷል? ወይስ አልሠራም? የሚለው ሌላ ጉዳይ ሆኖ እነርሱ ግን ለይቅርታ ቦታ እንዳላቸው ማሳያዎች ብዙ ናቸው።

የኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በጋራ ከሚቀበሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንዱ የሆነው የማቴዎስ ወንጌል "አንድን ሰው አንድ ሰው ቢበድለው በቀን ሰባት ጊዜ ሰባ 7x70=490 ጊዜ ይቅር ማለት እንደሚገባ ያስተምራል።" ማቴ. 21÷7 በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ስምና ቦታ እንዲሁም ተቀባይነት ካላቸው ዘማሪዎች አንዱ የሆነው ዘማሪ ይልማ ይቅርታን በምእመናን ልብ ውስጥ ለመትከል የሔደበት መንገድ እንዲህ ይገለጣል፤

---

[44] ኪዳነ ወልድ፣ 482

[45] ያሬድ፣ 175

## ትንሣኤሽን ያሳየን

****

ይቅርታ ታላቅ ነው ቁስልን ይሽራል፤

ጸብ ግን እስከዛሬ እነማንን ጠቅሟል?

ቂምና በቀልን ለትውልድ ያቆዩ---- ትንሣኤሽን ያሳየን፤

በማይበርድ እሳት ውስጥ ሕዝብን ያጋያሉ--- ትንሣኤሽን ያሳየን።

(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ፣ ቁጥር 2፣6-9፣ 1994)

ኢትዮጵያ ከደርግ ውድቀት በኋላ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር ከወደቀች ዐሥራ አንድ ዓመት ሆኗታል። (1994) ከኢህአዴግ መራሹ ድርጅት ከሕወሐት ጋር ሻአቢያ ቀደም ያለ የትጥቅ ጓደኝነት ነበራት። በጉዟቸው ውስጥ መቃቃርም መፈቃቀርም ውስጥ ገብተው ብዙ አሳልፈዋል። ሁለቱም ደርግን አባርረው ሀገር መግዛት ቢጀምሩም የውስጣቸውን ቅራኔና ችግር በእርቅ ከመፍታት ይልቅ ቁርሾው መርቅዞ አፈሙዝ ተሳስበዋል።

ይኽ የሆነው ግን ይቅርታን በሚሰብከው ሃይማኖት ውስጥ ባሉት ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊና በፕሬዘዳንት ኢሳይያስ መካከል ነው። ሁለቱም ክርስቲያኖች ናቸው። ክርስትና ደግሞ እርቅን እንጂ ጦርነትን አይሰብክም። ያመረቀዘውን ቁርሻቸውን በውይይትና በይቅርታ ፈትተው ያንን ዘመን መሻገር ለምን አልቻሉም? የሚል ጥያቄ ቢነሣ፣ መልሱ የሚሆነው እነሱ በሃይማኖቱ ውስጥ አሉ እንጂ ሃይማኖቱ በእነሱ ውስጥ የለም ነው፤ ድንጋይ በውሃ ውስጥ ይኖራል፤ ውሃ ግን በድንጋይ ውስጥ አይኖርም፤ ይቅርታ በሚሰብኩ ሃይማኖቶች እየኖሩ በይቅርታ ድልድይ መሻገር አለመቻል ትልቁ ስብራት ነው።

ይኼ መዝሙር ዘመኑን የዋጀ ነው። ሀገር በቂምና በበቀል የተከበበችበት ጊዜ ነበር። ምሁራን ታሪክ እየጠቀሱ፣ ጥናት እየነቀሱ፣ ጥቅስ እያወሱ ነገር የሚቆሰቁሱበት ጊዜ ነበር። የይቅርታ ድልድይ ከመዘርጋት ይልቅ የጥላቻ ሐውልት እንዲገነባ በብዙ መጠን በግራም በቀኝም ደክመዋል። ዘማሪው ግን ይሄንን ይኮንናል።

ይቅርታ ታላቅ ነው ቁስልን ይሽራል፤

ጸብ ግን እስከ ዛሬ እነማንን ጠቅሟል? ይላል፡፡

ይቅርታ ጥላቻን ግንብ ማፍረሻ ሰላማዊ ደማሚት ነው፡፡ ይቅርታ ሀገርን እግር ተወርች ላሰረው ጽኑ የቂም ደዌ ፍቱን ርጢን[46] ነው፡፡ ሀገር በዘመን ተራራነት ለገዘፈችበት የውጣ ውረድ ክብር ብቸኛው እልባት የይቅርታ መሠረት መጣል ሲቻል ብቻ ነው፡፡ ዝማሬው የሚለው ይቅር የሚሉ ሰዎች ታላቅ ናቸው፡፡ በዚህ ከላይ በተጠቀሰው ነጠላ ስንኝ ውስጥ ሁለት ግዙፋን አካላት አሉ፡፡ ይቅርታ ጠያቂና ይቅርታ ተቀባይ፣ ሁለቱም ታላቅ ናቸው፡፡ ራሱ ይቅርታም ታላቅ ነው፡፡

ሀገርን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት አንዱ ግለሰብ ሌላውን ግለሰብ ሊበድል ይችላል፡፡ አንዱ የጎሳ መሪ ወይም የብሔር መሪ ሌላውን ቡድን፣ ግለሰብ፣ ሕዝብ ሊበድል እና ሊያስቀይም ይችላል፡፡ በዚህ ወንድማዊ እኅታዊ ቤተሰባዊና ሕዝባዊ ግንኙነት ውስጥ የሚፈጠረው ቁርሾ ለማንም አይጠቅምም ነው የሚለው -- ዝማሬው፡፡ ጸብ እነማንን ጠቅሟል? ብሎ ይጠይቃል፡፡ መልስ የሚሰጠው ባያገኝም መልስ ግን አለው፤ ማንንም አልጠቀመም፤ በዓለማችን ብዙ በደሎች ተፈጽመዋል፤ ሕዝቦችና መንግሥት ግን ትውልዳቸውንም ሆነ ሀገራቸውን ያሻገሩት የቂም እና የጥላቻን ጨለማዊ አዘቅት በይቅርታ ክዳን በመድፈን ነው፡፡

የኔልሰን ማንዴላ የትልቅነት ምሥጢር ከዚህ ይቀዳል፡፡ ሃያ ሰባት ዓመት ወህኒ ያማቀቁትን ነጮች ከእስር ሲፈታ ሳይበቀላቸው ጭራሽ ስልጣን በማጋራት ለትውልዱ የፍቅር እና የሰላም ሐውልት ገነባ፤[47] በሞቱም ጊዜ ዓለም ከያለበት ተሰባስቦ በክቡር ሥጋው ላይ የአበባ ጉንጉን አስቀመጠ፡፡

የጀርመን ናዚ በአይሁዳውያን ላይ የፈጸመው ግፍ የተፋቀው በምንድን ነው? ምላሹ ይቅርታ ነው፤አሜሪካ በጃፓን ሄሮሺማና ናጋሳኪ ለፈጸመችው በደል የትኛው በቀል ተወሰደ? በመተው ተቋጨ እንጂ፤ ሁቱና ቱትሲ ተጣልተው በአንድ መቶ ቀን ከ800,000-1,000,000 ሰዎች ሲረግፉ መቋጫው ይቅርታ ነበር፡፡

---

[46] ርጢን ከሙጫ ተቀምሞ የሚዘጋጅ ልዩ ፈዋሽ ዕጣን ነው፡፡መጋቤ ሐዲስ እሸቱ፣ 14

[47] Nelson Mandela.long walk to freedom,The outo biography of nelson mandela.734.Littel,Brown

.     .     .

ቂምና በቀልን ለትውልድ ያቆዩ፤

በማይበርድ እሳት ውስጥ ሕዝብን ያጋያሉ።

ዘማሪ ይልማ ኃይሉ፣ ቁጥር 2፣ 1994

ቂምና በቀልን ለትውልድ እንደ ደኅና የአባት ርስት ተንከባክቦ ማቆየት ትርፉ ለልጅ ልጅ እርስ በእርስ መተላለቂያ መርዝ ማስቀመጥ ነው። ከዚህ የሚያተርፈው ደግሞ የሁሉም ሃይማኖቶች ጠላት ሰይጣን እና የጦር መሣሪያ ነጋዴዎች ናቸው። ዝማሬው ቂም በቀልን ነቅሎ ይቅርታን ይፈልጋል። በእስልምና ሃይማኖት ነሺዳና መንዙማ አድማጮች ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት እና ተወዳጅነት ያላቸው ቶፊቅ የሱፍ እና ሙአዝ ሀቢብ፣ የእስልምና ሃይማኖት ለይቅርታ ያለውን ቦታ በነሽዳቸው በጽኑ እንዲህ ያነሡታል። ይቅርታ በተወዳጅነት ትፈለጋለች። ይቅርታ ግዙፍ ሥፍራ ተሰጥቷታል።

ኢትዮጵያ

የልዩነት ካብ በአንድነት አፍርሰን፤

የጥላቻን አጥር በፍቅር አድሰን።

ተዋዶ መኖርን የሚያሳዩ ለዓለም፤ /2/

ሰላምን ዘማሪ ልጆች አሉሽ ዛሬም።

በይቅርታ ድልድይ ጥላቻን ተሻግረው፤

ፍቅርን ያስበለጡ ቂም በቀልን ሽረው።

እንደ አንድ ቤተሰብ ሆነው ያረፉብሽ፤

አንቺ ነሽ ኢትዮጵያ ዓለም የሚያከብርሽ

(ቶፊቅ የሱፍ ሙአዝ ሀቢብ፣2011)

እስልምና ለይቅርታ ያለው ሥፍራ ግዙፍ ነው። ይኸንን ሥፍራ በነሽዳው ውስጥ ጉልህ መልክ ኑሮት እናገኛለን፡፡ ነሺዳው የለውጡን በረከት ያረገዘ ነው። ኢትዮጵያ ላይ አቶ ኃ/ማርያም ወርደው አቢይ(ዶ/ር) ወደ ሥልጣን የመጡበት ጊዜ ነው። ቂምን መሻር፣ ጥላቻን ማጥፋት፣ ይቅርታን ማድረግ በለውጡ ጠቅላይ ሚኒስትር እና አመራሮች የሚሰበክበት ነበር። ነሺዳው የዘመኑ መንፈስ ረቦበታል። የሀገሪቱ መሪ እስረኞችን በይቅርታ ፈትተዋል። ከሀገር ውጭ ለነበሩ ተቃዋሚዎች ወደ ሀገር እንዲገቡ ጥሪ አድርገዋል። በአረብ ሀገር ተጉዘው ሁለት የተጣሉ ግለሰቦችን አስታርቀዋል። ሁለቱ የኦርቶዶክስ ሲኖዶሶች ሀገር ውስጥ ውጭ ሀገር ያሉት ታርቀው አንድ እንዲሆኑ ለፍተዋል፤ በእስልምና ውስጥ የነበረውን መከፋፈልም በይቅርታ አንድ እንዲሆኑ ለማስቻል ጥረት አድርገዋል፣ ተሳክቶላቸዋልም። ይኼ ነሺዳ ወቅታዊውን ሀገራዊ ገሀድ ያንፀባርቃል። በመንግሥትና በመሪዎች ደረጃ የይቅርታ አስፈላጊነት ታምኖበት ሰፊ ሥራ እንደተከናወነበት አለ የሚባል ሀቅ ነው።

በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ዘንድ ይቅርታ ዋጋ እንዳለው የመሰከረም ጌቱ “ኢትዮጵያ” የሚለው መዝሙሩ ምስክር መሆን ይችላል።

ኢትዮጵያ

****

እውነት ባደባባይ ይታይ በከፍታ፤

የሐሰት ምስክር የሚሰማው ይጣ።

እናቶች አባቶች ወጣት ልጆች ሁሉ፤

ከክፋት ሸፍተው ለእርቅ ያዘንብሉ። ( ሀገሬ እማማ)

እናት ሀገሬ ነሽ አምላክ የባረከሽ።

****

(መስከረም ጌቱ 2013)

እውነት አደባባይ ላይ ከቆመች፣ የሐሰት መቃብሯ ቅርብ ነው። ዘማሪው የሚለው ይኼንን ነው። ዛሬ ወንድም በወንድሙ፣ ቃኤል በአቤል አዳም በሔዋን ላይ እየተነሣ ያለውኮ በሐሰተኛ ታሪክ ትርክቶች ምክንያት ነው። ያልተገደለውን ተገድሏል። ያልሞተውን ሙቷል። ደጉን አኮስሰው፣ ክፉ ክፉውን አግዝፈው በሚተነትኑ በታሪክ ደናቁርት "ምሁራን" ነን ባዮች ዘንድ በሚቀርቡ የቅጥፈት ፕሮፖጋንዳዎች ወጣቱ ተታሎ፣ ትውልዱ በማያውቀው እና በማያገባው ሙከራ እየተቆላ ያለው ለዚህ ነው። ሐቅ በአደባባይ የማትቆመው የሐሰት ባዶነት የእውነት ትንሣኤዋ እስኪገለጥ ድረስ ነው።

በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ያውን ስንመለከት መሸፈት ማለት መራቅ መሸሽ፣ ጫካ መግባት መለየት ማለት ነው።[48] ከክፋት ሽሹ ይላቸዋል። እናቶችን፣ አባቶችን እና ወጣቶችን፣ ከዚያስ ሲባል ለእርቅ ማዘንበል፣ ለእርቅ ማድላት፣ ለእርቅ መቆም ይገባል፣ እርቅ ነው የሚያዋጣው እያለ እርቅን ይሰብካል። የስብከት ድምፁቱ በጉልህ ይሰማል።

እርቅ የቂም ማርከሻ መድኃኒት፣ የበቀል መፈወሻ ክኒን፣ የጥላቻ ማፍረሻ ወጌሻ ነው። በንጹሕ ልብ ይቅር የተባባሉት በደል አንድ ቦታ ላይ ከተቀበረ ለትውልዱ ሰላምንና ዕረፍትን ይሰጣል። ይኽ ከሆነ ምእመናን በደስታ በፍቅርታ በአንድነት እንዲኖሩ ያስችላቸዋል።

የዝማሬው ጭብጥ ይኼ ነው። የሚሸሸው ከቂም ነው፤ ከበቀል ነው፤ ከመጠፋፋት ነው፤ ከጥላቻ ነው። እነዚህን ሁሉ ጥሎ ከእርቅ ማዕድ መካፈል ለቤተሰብም ለኑሮም ለሀገሪቱም ይጠቅማል።

ከለውጡ በኋላ የተዘመረ ነው። ዘመን ጠቋሚ ነው መንግሥት ይቅርታን ባህሉ ለማድረግ እየሠራበት የነበረበት ጊዜ ነው። በመላው ኢትዮጵያ የይቅርታ መንፈስ የታወጀበት ማግስት ላይ ነው። ዝማሬው ይቅርታን ይሰብካል ይቅርታ በሰው ልብ ውስጥ የሚተክል ዝማሬ ነው በወንጌላውያን አማኞች ዘማሪያን ዘንድ ይቅርታ ከላይ ባየነው መልኩ በጽኑ ተፈልጋ፣ ተሰብካ ተቀንቅናለች።

[48] ባህሩ፣ 609

### 3.3.2. ሌብነትን ገናዥ[49]መዝሙራት

የሰው ልጅ ሙቶ ወደ መቃብር ከመውረዱ በፊት በተለይ በክርስትና አስክሬኑ ይገነዛል፡፡ ይታሠራል፡፡ አለቀ ደቀቀ የሚባልበት ነው፡፡ መዝሙራት ሌብነትን ሊገንዙኑት ይፈልጋሉ፡፡ የስርቆትን ልጓም ለመያዝ ይቃትታሉ፡፡

ሙስናን፣ ጉቦን፣ ይቃወማሉ፤ ያወግዛሉ፡፡ ይኽን ማኅበረሰባዊ በሽታ በመረረ ድምፀት በቃ ይላሉ፡፡ ይኼን ሥነ ምግባራዊ ድቀት ይጸየፉታል፡፡ የሚገርመው ሰዎችን አይደለም የሚጸየፉት ድርጊቱን ነው፡፡

ሌብነት፣ በሁሉም ሃይማኖቶች እጅግ የሚጠላ ተግባር ነው፡፡ ግን አልተገታም፡፡ ይኽን ማኅበራዊ በሽታ ለማስቆም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በመዝሙሮቻቸው፣ በነሽዳና በመንዙማዎቻቸው ይጮኻሉ፡፡ እስቲ ከጩኸቶቻቸው ጥቂት ቆንጥሬ ላሳያችሁ፡፡ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪዎች አንዱ ዘማሪ ይልማ ኃይሉ እንዲህ ይላል፡-

ክብርን ልበሽ

****

ጉቦና ፍትሕን ማጣመም እንዳንለምድ፤

ከወንጌሉ ጋራ አለብን ማዛመድ፡፡

እግዚአብሔር ያለው ሰው ለእርሱ የታመነ፤

ከግፍ ሥራ ሕመም አካላቱ ዳነ፡፡

ክርስቲያን ነኝ ብሎ ጉቦ የሚበላ፤

የሚያቃጥል እሳት ያገኘዋል ኋላ፡፡

(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ፣ ቁጥር 7 /1995)

---

[49] *ዘዳ 16፥19 ፤ ዘዳ 27፥25፣ 1ኛ ሳሙ 12፥3፤ ሚያ 3፥11*

ዘማሪው ጉቦን አምርሮ ይጠላል፡፡ መዝሙሩን ማሳሪያ አድርጎ በምሬት ገልጾታል፡፡ ጉቦና ፍትሕን አናጣምም ይለናል፡፡ በጉቦ ነው የፍትሕ ሚዛን የወደቀችው፡፡ ብዙዎቹ በእጃቸው እየሔዱ በእግራቸው የሚጓዙትን ከምድራዊው የሕይወት መዝገብ ሰርዟቸዋል፡፡ የሚሰብኩት ወንጌልና የሚሰበክላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ጉቦን ይጠላል፡፡ ሌብነትን ይጸየፋል፡፡ እነሱ ግን ወንጌላዊያን ናቸው፤ ክርስቲያኖች ናቸው፤ ይኼ ደግሞ ከክርስትና ጋር አይሔድም እያለ ያወግዛል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው አምስተኛውና ስድስተኛው ስንኝ እንደሚያስረዳን የክርስቶስን ሥራ ሳይሠሩ ክርስቲያኖች ነን የሚሉትን መጨረሻቸውን ይነግራቸዋል፡፡ ወንጀለኞች ሆነው ወንጌላውያን ነን የሚሉትን የመጨረሻውን ዘመን የእግዚአብሔርን ፍርድ ይጠቁማቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም፣ ዘማሪዎቿም፣ የምትመራበትም መጽሐፍ ቅዱስ ሌብነትን እንዲህ ነው የሚጸየፉት፡፡

ጉቦ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው፡፡ ፈጣሪ የሚጠላውን ተግባር ፍጡራን ያደርጉታል፡፡ የሚገርመው ደግሞ አማኝ ነን በሚሉት ሌብነት ሀገርን የሚያፈርስ መርዝ ነው፡፡ ሌብነት በማኅበረሰቡ ዘንድ ጽዩፍ የሆነ ቆሻሻ ተግባር ነው፡፡ ሌብነት የሀገር ነቀርሳ ነው፡፡ ሌቦችን አቅፋ የያዘች ሀገር ሁሌም ባለችበት ትጓዛለች እንጂ እድገቷ አይታሰብም፡፡ ሌቦች ልጆችን የወለደች ሀገር ያውም አማኝ ሌቦችን የያዘች ሀገር እንዴት ታሳዝናለች? ዘማሪው ግን ለሀገራችን እውነተኛ እንሁን ብሏል፡፡

## 3.4. መባያዎች[50] /Motifs/

በዚህ ክፍል በሃይማኖቶቹ መዝሙራት የሚታዩ መባያዎች ይፈተሸባቸዋል፡፡ መባያዎቹ በአራቱም ሃይማኖቶች የሚገኙ ሊሆኑ ይችላሉ፤በሦስቱ ብቻ፣ በሁለቱ ብቻ ወይም በአንዱ ብቻ ሊገኙ ይችላሉ፡፡ አከሣሠታቸው ሁለት መልክ ሊኖረው ይችላል፡፡ አንደኛው በአንዱ የሃይማኖት መዝሙራት ተደጋግሞ የሚመጣና ወይም ትዕምርታዊ ፋይዳ ያለው ሲሆን ሁለተኛው፣ በአራቱም ወይም በከፊሉ የታዩ ሊሆን ይችላል፡፡

*[50]Amotif is a conspicouous element, such as a type of event, device, reference, or formula, which occurs frequently in work of literature. Page 205 M.H. Abrams Geoffrey GoH Harham.A Glossary of literary terms.Cornell university national humanity center. Ninth edition*

የመባያ ጉዳይ (motif) የሚለው ቃል በአንድ በኩል ለሚባለው፣ ለሚመስለው ጉዳይ፤ በሌላ አንጻር ደግሞ ጉዳዩ ለሚባልበት ሁኔታና ለሚመሰልበት መንገድ በመጠሪያነት እኩል ሊያገለግል ይችላል፡፡ አንድ ጉዳይ መባያ ይሆን ዘንድ ሁለት ባሕርያትን አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡ የመጀመሪያው ባሕርይ በብዙ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ተደጋግሞ መታየት፣ አልያም ቢያንስ በአንድ ሥራ ውስጥ ተመልሶ መምጣት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ትዕምርታዊ ፋይዳ ማስገኘት ነው፡፡ (ቴዎድሮስ፣ 256) ለጥናት በተመረጡት የሃይማኖት መዝሙራት ውስጥ ልዩ ልዩ ባለሙያዎች ይገኛሉ፤ እነሱም በደርዝ በደርዛቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 3.4.1. በኦርቶዶክስ፣ በእስልምና፣ በካቶሊክ፣ በፕሮቴስታንት መዝሙራት ያሉ መባያዎች

#### *3.4.1.1. ሀገረ ፈጣሪ*

በክርስትናም በእስልምናም ሊቃውንት ዘንድ ኢትዮጵያ "የፈጣሪ ሀገር ናት" ተብላ ትጠቀሳለች፡፡ በኦርቶዶክስ፣ በካቶሊክ እና በፕሮቴስታንት ሃይማኖት አማኞች ዘንድ ሀገረ እግዚአብሔር ስትባል በእስልምና ሃይማኖት አማኞች ዘንድ ደግሞ አላህ የመረጣት ነብዩ ሰ.ዐ.ወ የወደዷት ትባላለች፡፡

ይኸች በፈጣሪ የተመረጠች በቅዱሳኑ የተወደደች ሀገር ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ከአርባ ጊዜ በላይ ተጠቅሳለች፡፡ [51] ኢትዮጵያና ሕዝቦቿም በተደጋጋሚ ጊዜ በቁርዓን ተጠቅሰዋል፡፡ [52] ምክንያቱም መነሻቸው ክፋት ተንኮል በፈጣሪ ላይ ማመፅ ሳይሆን የአምላካቸውን ትዕዛዝ በመቀበል፣ ሕጉን በማክበር፣ እሱን በመፍራት፣ በደግነት ነው፡፡ የየሃይማኖቱ ዘማሪያን በመዝሙሮቻቸው ይኽንን ደጋግመው ያነሱታል፡፡ የእግዚአብሔር ከተማ ነሽ፣ የፈጣሪ ሀገርነሽ በቀንና ሌሊት ይጠብቅሻል፡፡ አይረሳሽም፣ ፈተናሽ መከራሽ ቢበዛ አይተውሽም ይሏታል፡፡ በፈጣሪ መመረጥ እሱ በመረጣቸው ቅዱሳኑ፣ ሱሐቦቹ መወደድ እንዴት ያማረ ነው?

የፈጣሪ ሀገር መሆኗን በመረዳት በሚፈጠረው ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ አደጋ ተደናግጠው ተስፋ መቁረጥ ውስጥ በመግባት ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውንና ሀገራቸውን ችላ እንዳይሉ ያደርጋቸዋል፡፡ የፈጣሪያቸውን እና የሀገራቸውን ፍቅር ልባቸው ላይ ይተክላል፡፡ ይኼም ሀገርን

---

[51] *ሰሎሞን፣ 27*
[52] *ሀሴን፣ 23*

ከማፍረስና ራሳቸውን ከቀቢጸ ተስፋ ይሠውራል። ምክንያቱም ሀገሪቱ ሀገረ ፈጣሪ ናትና። የዚህ ውጤት የተረጋጋ ማኅበረሰብ የተረጋጋ መንግሥት እንዲፈጠር ያግዛል።

የእግዚአብሔር ሀገር

የእግዚአብሔር ሀገር ነሽ ኢትዮጵያ፤

የእግዚአብሔር ምድር ነሽ ኢትዮጵያ፤

(ዘማሪ ታዴዎስ ግርማ /ከኦርቶዶክስ 1996/3.3/)

ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ሀገር ነሽ በማለት ባለቤቷ እርሱ እንደሆነ ይናገራል። በዚህም ያንተ ሀገር በመሆንዋ እንዳትተዋት አደራህን የሚል ዐይነት ተመጽኖ ያለበት ነው።

በቀጣይ የምናገኘው የቶፊቅ ዮሱፍ ሙዐዝ ሀቢብ ዓ.ም. 2011 ሲሆን እሱም ከላይ እንደጠቀስነው መዝሙር ሁሉ ኢትዮጵያ የፈጣሪ ሀገር ነሽ፤ በዚያውም ላይ ነቢይ የወደደሽ የተመረጥሽ ነሽ ይላታል። ኢትዮጵያ

አላህ የመረጠሽ ነብይ ያወደሱሽ፤ /2 ጊዜ/

ሀገሬ እናቴ ነሽ። /2/

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ኮንሶላታ ቤተ ጸሎት ወጣት መዘምራን ቁጥር 4/2001 በመዝሙራቸው ፈጣሪ ለሕዝባችን ለኢትዮጵያ እንዲራራ ይማጸናሉ።

ጌታ ለሕዝብህ ራራ፤

ጌታ ለኢትዮጵያ ራራ።

መስመር ከራሴ

በፕሮቴስታንት ዘማሪያን ከተዘመሩት መካከል ዘማሪ ዮሴፍ ከበደ፣ ቁጥር 2፣ 2006 ኢትዮጵያን በሚያጽናና ቃል ተስፋ እንዳትቆርጥና ዓለም ሕዝቦች ሁሉ እንድትተርፊ ፈጣ ያግዝሽ በሚል ዐይነት ድምፀት የተዘመረ ሆኖ እናገኘዋለን።

ብርሃንሽ መጥቷልና ኢትዮጵያ፤

ብሎም ለአፍሪካ ደግሞም ለአውሮፓ ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ፤

ብርሃንሽ ወጣ ትንሣኤሽ መጣ ክብርሽን አዩ፤

<u>የፈጣሪሽ ፊት</u> ወዳንቺ ዞረ ልብሽ ተመልሶ፤

ሁሉም እንዲያይሽ እንድታብሪ እጅሽን ይዞ።

የኦርቶዶክሱ ዘማሪ ምድሪቷ፣ ሀገሯ የእግዚአብሔር ናት፣ መሬቷና ሕዝቦቿ የፈጣሪ ናቸው ይላል። የእስልምናው ነሺዳ ደግሞ አላህ (ሱ.ወ.) የመረጣት ናት በማለት በፈጣሪ መመረጧን የፈጣሪ ምርጫ ሀገር መሆኗን ያሳየናል። ጌታ ለሕዝብህ ራራ ሲል፣ የካቶሊክ ዘማሪ የሚያወራው ስለ ኢትዮጵያና ልጆቿ ነው።

ኢትዮጵያውያን የጌታ ሕዝቦች መሆናቸውን ይናገራል። ሰዎቹም ልጆቹ ናቸው፤ ኢትዮጵያም ሀገሩ ናት። የፕሮቴስታንቱ ዘማሪ ፈጣሪ ያላትን ሀገር ነው የሚነግረን። ከሚሌኒየም በኋላ የተዘመረ በመሆኑ በዚያ ጊዜ ደግሞ በፖለቲከኞች የኢትዮጵያ ትንሣኤ ተበሥሯል እየተባለ የሚወራበት ጊዜ ነው። ዘመኑን ይነካል። ብርሃንሽ የወጣው ትንሣኤሽ የታየው ልብሽ ስለተመለሰ፣ ፈጣሪሽ ፊቱን አዞረልሽ ነው። ፊቱ ማለት፣ ምሕረቱ፣ ይቅርታው፣ ቸርነቱ፣ ወዘተ ነው።

ፈጣሪሽ ሲል የፈጠራት፣ የሚጠብቃት፣ የሚንከባከባት፣ እንደ ዐይኑ ብሌን የሚያያትን ጌታ ነው። በመሆኑም በየትኛውም አውሎ ነፋስ፣ ወጀብና ማዕበል፣ በዋናም ያኽል መከራ ውስጥ ብትሆን የፈጠራት አምላክ፣ የሚጠብቃት ፈጣሪ፣ እንዳላት ደጋግመው በመንገር ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ እንዳይረበሹ፣ እንዳይደነግጡ፣ እንዳይፈሩ ይልቁንም እንዲጸኑ ሁሉንም በሚችለው ፈጣሪ ደስ ብሏቸው እንዲኖሩ በማድረግ በኩል የሚጫወቱት ሚና ጉልህ ነው።

### *3.4.1.2. ሀገረ ቃል ኪዳን*

ቃልኪዳን አንድን ነገር ለማድረግ የተገባ ቃል ወይም አንድነገር ለመፈጸም የተሰጠ የተስፋ ቃል ነው። ቃል ኪዳን ከሁለት ጥምር ቃል ይገኛል። ቃል ስለ አንድ ነገር የተባለ፣ የተነገረ፣ የተጻፈ

ሐሳብ፣ አስተያየት፣ መልእክት ነው፡፡ [53] ኪዳን ደግሞ መሐላ ነውና የሚለውን ሐሳብ ይሸከማል፡፡ [54] በአምስት ፊደል በሁለት ቃላት የተመሠረተ ጥልቅና ምጡቅ ማኅበራዊ ፋይዳ ያለው ሐሳብ ነው ቃል ኪዳን፡፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ሆነ ዓለም ከተፈጠረ በኋላ በፈጣሪና በፍጡር እንዲሁም በፍጡራን መካከል ቃል ኪዳን ነበረ ይላሉ የሃይማኖት ሊቃውንነት፡፡ [55] በክርስትናም በእስልምና ቃል ኪዳን ትልቅ ቦታ አለው፡፡

የሦስቱም ሃይማኖቶች አባት የሚባለው አብርሃም፣ ፈጣሪ የሰጠው ቃል ኪዳን በአይሁድ፣ በክርስትና በእስልምና እምነት የተደገፈ ነው፡፡ ሥለዚህ በፈጣሪ ዘንድ ለሰዎች ቃል መግባት ከአልማዝ የጠነከረ መንፈሳዊ ዕሴት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ኢትዮጵያ በክርስትናም በእስልምናው የቃል ኪዳን ሀገር መሆኗን በእምነት መጽሐፎችም ጭምር የተገለጠ እውነት ነው፡፡ በክርስትናው ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ሀገር መሆኗ በብዙ ተጠቅሷል፡፡[56] (ዳንኤል ክብረት 2010፤212፡፡) ቃል ኪዳኖችንም ከቀስተ ደመናው ጋር ያስተሳስሯታል፤ የተገባው ቃል ለኖኅ ቢሆንም ክርስቲያኖች በቃል ኪዳን ትዕምርትነት ይወስዱታል፤ በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ሊቃውንት ዘንድ ቀስተ ደመናውን በቀጥታ ከቃል ኪዳን ጋር ያያይዙታል፡፡

በእስልምናው ሐበሻ የሚለው ስም በቅዱስ ቁርዓን ተደጋግሞ ሲጠቀስ ሀገሪቷ ምን ያህል የቃል ኪዳን ምድር እንደሆነች የሚያሳይ ነው፡፡ [57] ከዚህ በተጨማሪ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እስካልነኳችሁ ድረስ እንዳትነኳቸው ብለው ቃል የገቡላት ሀገር ናት፡፡ ተከታዮቻቸውም የነቢዩን ቃል የመስማት ግዴታ እንዳለባቸው ያውቃሉ፡፡[58]

ከዚህ ተነሥተው ነው የኦርቶዶክስ፣ የእስልምና፣ የካቶሊክ እና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ኢትዮጵያን የቃል ኪዳን ሀገር የሚሏት፡፡ አባቶቻችን "የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ" ይላሉ፤ በባህላችን ቃል ማጠፍ ነውር ነው፡፡ የዚህ መሠረቱ ሃይማኖታቸው ነው፡፡ ፈጣሪ ደግሞ ቃሉን ያጥፍ ዘንድ ሰው አይደለም ይኽች በፈጣሪ ዘንድ ቃል የተባላት ሀገር ምንኛ የታደለች ናት?! በፈጣሪ ዘንድ በተወደዱት ቅዱሳን ዘንድ ቃል የተገባላት ኢትዮጵያ

---

*[53] አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 194/193*
*[54] ዘርጋው፣ 469፣*
*[55] ቃል ኪዳን Aiga forum http:// aigaforum.com*
*[56] መዝ. 74፥14፣ ሶፎ 3፥10*
*[57] https://am.al-ain.com/article/ethiopianbasedàquawat-of-the-prophet-smosque*
*[58] ባህሩ፣ 297*

ምነኛ የተወደደች ናት?! እነዚህ መዝሙራት፣ ነሺዳዎች፣ መንዙማዎች በፈጣሪ የተገቡትን ቃሎች ይዘክራሉ፡፡

አባሪ አንድ 22ኛ መዝሙር ዘማሪ ፀሐፊ ትእዛዝ ዲ/ን ታዴዎስ ግርማ 2011 /ኦርቶዶክስ/ ኢትዮጵያ፤ አባሪ ሦስት ሁለተኛ ተራ ቁጥር (ቶፊቅ የሱፍ እና ሙአዝ ሀቢብ ፣ 2011) /ከእስልምና/፤ አባሪ አራት አምስተኛ ተራ ቁጥር ዘማሪ ወንድማገኝ ሁሴን 2001 ቁጥር 1 /ከካቶሊክ/፤ አባሪ ሁለት አመስተኛ መዝሙር ተስፋዬ ጫላ፣ ቁጥር 4፣ 1998 /ከፕሮቴስታንት/

በአራቱም ሃይማኖት ውስጥ ያሉ ዘማሪዎች ኢትዮጵያ ወይም ሐበሻ የቃል ኪዳን ሀገር መኾኗን አስረግጠው አቀንቅነዋል፡፡ ይኼን ቃል የገባው ደግሞ ፈጣሪ ነው፡፡ የፈጣሪ ቃል ደግሞ የዘመን መቀነቶች ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ አይሽሩትም፤ ፈጣሪ ለቃሉ ታማኝ ነውና ያደርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ ከፍታ በፈጣሪ እጅ እንደሆነ ይነግሩናል፡፡ ፈጣሪ የመረጣቸው ቅዱሳንና ነቢያት በኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የገቡትን ቃልም እንዲሁ ይፈጸማል፡፡ይዘገያል እንጂ የሚቀድማት የለም፣ ትወድቃለች እንጂ መነሣቷ አይቀርም፡፡

ትራባለች እንጂ መጥገቧ አይቀርም፡፡ ኩርምት ብላ ታዝናለች እንጂ የመጨረሻውን ሳቅ የምትስቀው እሷ ናት፡፡ በክርስትናውም በእስልምናውም ያሉ ኢትዮጵያውያን ዘማሪያን መጽሐፍ ቅዱስን፣ ቅዱስ ቁርዓንን፣ አዋልድ መጻሕፍትን ሐዲሱን ሌሎች የእምነት መጻሕፍትን መሠረት አድርገው ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ሀገር ናት የሚሉን መንፈሳዊ እና ማኅበረሰባዊ መጽናናትን ለመፍጠር ነው፡፡

የታደለችና የተመረጠች ሀገር መኾኗ ለአማኙ ሕዝብም የሚሰጠው ሥነልቦናዊና ማኅበራዊ ዕረፍት ቀላል አይደለም፡፡ ሕዝብና መንግሥት ቃሉን እያሰቡ ዐይናቸውን በፈጣሪያቸው ላይ በማድረግ በቀላሉ እንዳይፈርሱ እና እንዳይረበሹ ያደርጋል፡፡ መዝሙሮቹ ዘመናቸውን ጠቋሚ ናቸው፡፡ በየዘመናቱ ቃል ኪዳኑን ሲያስታውሱ ይታያሉ፡፡

### *3.4.1.3. ናፋቂነት*

ናፋቂነት ዘመድ ወዳጅ መፈለግን፣ ፊትን ለማየት መመኘትን የሚሉትን ሐሳቦች ያዝላል፡፡ ጉጉትን ምኞትን ይሸከማል፡፡ በናፍቆት ውስጥ ዛሬ ላይ ተኹኖ ትናንት ይረገዛል፣ ነገም

ይፀነሳል፡፡ አራቱም ሃይማኖቶች ውስጥ ባሉ ዝማሬዎች ትናንትን ለዛሬና ለነገ፤ ሲናፍቁ፣ ሲመኙ፣ ሲቃትቱ ይስተዋላሉ፡፡ የመቃተታቸውና የጽኑ ናፋቂነታቸው የመሠረት ድንጋይ ደግሞ ትናንት ውስጥ ያሉ ደጋግ ምግባሮች፣ ስልጣኔዎች፣ ሰላምና ምሕረቶች ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ የተሠራችባቸው ማኅበራዊ እና መንፈሳዊ እሴቶች ትናንት ውስጥ አሉ ብለው ያምናሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ በብዙ ምክንያቶች እንደመከኑ እና እንደተቀበሩ በመግለጥ ትንሣኤዋን በጽኑ ይናፍቃሉ፡፡ መዝሙሮቹ ትናንት ውስጥ ተቀምጠዋል፡፡ ዘማሪዎቹ የየሃይማኖቱ ተከታይ ምእመናንን የስሜትም የስሌትም ወኪሎች ናቸው፡፡ ዝማሬዎቻቸው ደግሞ የመብሰልሰል፣ የመቆጨት፣ የትናንት ይሻል ነበር ዐይነት ተምኔቶች ማንፀባረቂያ ፍኖቶች ናቸው፡፡ ይኽ ናፍቆት ትውልዱ በትናንት የዘመን አሻራ ውስጥ የተከተቡ አንጡራ ሰብአዊ፣ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ሀብቶችን መለስ ብሎ እንዲቀኝ፣ እንዲጠይቅና እንዲመራመር ያስችላልል፡፡ ይኽም ማኅበረሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳው የጎላ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ይኽ ምልሰት ኢትዮጵያውያን ከትናንት በጎ ታሪክ ተነሥተው ዛሬን እንዲሠሩ፣ ነገን እንዲያልሙ ይረዳል፡፡

ናፍቆቱ ከጊዜያዊ ድባቴና ጭንቀት ትናንትን በእንዲህ ነበርን ትምክሕትመንፈሳዊ እና አዕምሯዊ እድሳትን እየሰጠ፣ የትናንቱን ስንቅ ዛሬ ላይ በማስታወስ ለነገው ስኬት እርሾ ይሆናል፡፡ በዚህ የናፍቆት ጓዳ ውስጥ ተሠርተው ያለቁ ትዕምርቶች፣ ማለትም ሀገር የምትኮራባቸው ታሪካዊ ቦታዎች፣ የሀገር ባለውለታዎች፣ የትናንት ሰላም ወዘተ የትናንት ውብ ነገሮች ሲዘክሩ ይታያል፡፡

ትናንትን ናፋቂነት በአንዳንድ የፖለቲካ ልሂቃንና ስብስቦች ዘንድ ለአንድ ሃይማኖት ተከታዮችና ወገኖች በአሉታዊ መንገድ ቢሰጥም፤ ቀጥሎ የሚቀርቡት የአራቱም ትልልቅ ሃይማኖቶች ዘማሬዎችና ነሽዶች ግን ይኽንን የተንጋደደ ፍረጃ እንደማይቀበሉት ያረጋገጡበት ነው፡፡ ዋቢዎችን በቅደም ተከተል ላቅርብ፡፡

አባሪ አንድ ሰባተኛ መዝሙር ዘማሪ ይልማ ኃይሉ፣ 6.9 /1994፤ አባሪ አንድ ሃያ ሦስተኛ መዝሙር ዲ/ን ትዝታው ሳሙኤል /2000/) ከኦርቶዶክስ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አባሪ ሦስት ሙነሽድ፡- ሁሴን ሱልጣን እና አብዱል ሰላም አበራ፣2013፤ ከካቶሊክ ደግሞ ኤደን ፈቃደ ሥላሴ፣ መዓዛ ዓለሙ፣ አሸናፊ ደበላ፣ ዘሪሁን እናውጋው፣ ዘማች ክብሩ፣ ዓለምዬ፣ በኅብረት የሠሩት 2000 ዓ.ም. ይኸንኑ ጉዳይ የሚያብራሩ ናቸው፡፡

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪዎች ሀገራቸው ትቢያዋን አራግፋ ዳግም ወደ ክብሯ እንደምትመለስ በተስፋ ትንሣኤዋን ይናፍቃሉ። የእስልምናው ሙነሽድ በልጆቿ ግጭት ልቧ የተሰበረውን ኢትዮጵያን እያሰበ በቀናት መካከል ደስታሽ ይመለሳል እያለ በጎ ነገሯን ይናፍቃል። በኅብረት መዝሙር ያቀረቡት የካቶሊክ ዘማሪያን ደግሞ መጥፎ ታሪኳ ተቀይሮ መልካም ዜናዋ የሚነገርበትን ዕለት ይመኛሉ። ዓለም ሲደነቅባት ዓለም ሊገረምባት ማየትን ይሻሉ።

የፕሮቴስታንቱ ዘማሪ ደግሞ በኃያልነትና በታላቅነት ታሪኳ ውስጥ የወንጌል ዘሯን እያሰሰ በሕዳሴ ዘመቻ ውስጥ ብልጽግናዋን፣ እድገቷን፣ ትልቅነቷን ይመኛል፣ ይናፍቃል። ከላይ ለአብነት የቀረቡት መዝሙራትና ነሺዳዎች ምን ያህል በትናንት ናፍቆት በዛሬ መብሰልሰል በነገ ምኞት ውስጥ እንዳሉ የሚያሳዩ ናቸው፤ ይኸ መብሰልሰል ደግሞ ቁጭትን ይፈጥራል፤ ያ ቁጭት ታሪክን የሚለውጡ ነገርን የሚገለብጡ፣ ኢትዮጵያን ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚያሻግሩ የቁርጥ ቀን ልጆችን ይወልዳል።

### 3.4.2.. በኦርቶዶክስና በእስልምና ብቻ ያሉ መባያዎች

#### *3.4.2.1. ሀገረ ኅሩያን*

ኅሩይ ሲል የተመረጠ ነው፤ ኅሩያን ደግሞ ለብዙ የተመረጡ ይሆናል። ተኅረየ ሲል ተመረጠ፣ ተለየ ተወደደ ይሆናል።[59] ኢትዮጵያ በፈጣሪዋ የተወደደች ሀገር ናት። በፈጣሪ ብቻ ሳትሆን ፈጣሪ በፈጠራቸው፣ ፈጥሮ ከሰው አልቆና አብልጦ በወደዳቸውና በመረጣቸው ነቢያት፣ ሱሐቦች፣ ቅዱሳን፣ ጸድቃንም የተመረጠች ምድር ናት።

መዝሙሮቹ፣ ነሺዳዎቹ፣ መንዙማዎቹ ኢትዮጵያ የእነዚህ በፈጣሪ ዘንድ የተወደዱ፣ የተመረጡና የተለዩ ሰዎች ሀገርና መኖሪያ መሆኗን በኩራት ደጋግመው ያወሳሉ። ማንሣታቸው፣ መጥራታቸው፣ መዘከራቸው እንዲሁ ለግጥም ማሚያ እንዳልሆነ ደጋግመው ያነሷቸው ስንኞች ዋቢ ናቸው።

አስቦ ማለፍ አይደለም ግባቸው፤ በታሪክና በመልክዐምድር፣ በጊዜና በቦታ የማይገደብ ኢትዮጵያዊ ማንነት መፍጠር ነው። የኢትዮጵያ መልክ የሚቆመው ሥጋዊውና ምድራዊው ዓለም (secular world) ላይ ብቻ አይደለም። ይሻገራል፤ የሚሻገረው ደግሞ በምርጦቹ ነው። ከሚያልፈው ዓለም ወደ ማያልፈው ዓለም ይምዘገዘጋል። ዘላለማዊውና መንፈሳዊው ዓለም ላይ

---

[59] *ኪዳነ ወልድ፣ 486*

(spiritual world) ላይ ኢትዮጵያን ይጽፋሉ፡፡ አምዘግዛጊዎቹ ደግሞ በሁለቱም ትልልቅ ሃይማኖቶች መጽሐፍ (በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በቅዱስ ቁርዓን፣ በገድላት፣ ድርሳናት፣ በሐዲሳት እና በሃይማኖት በታሪክ) መጻሕፍቶቻቸው ያሉ ምርጦች ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የእምነት እና የታሪክ መጻሕፍት ኢትዮጵያን የሚያስጠሩ ኢትዮጵያውያን ኀሩያን አሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ከጠቢቡ ሰሎሞን ዘንድ ንጉሥ ምኒልክን የወለደችው ንግሥተ ሳባ አዜብ፣ "ንግሥተ አዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድበታለች፣ የሰሎሞን ጥበብ ለመስማት ከምድርዳርቻ መጥታለችና፣ እነሆም ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ" ማቴ. 12÷42 የተባለላት ናት፡፡

ቅዱስ ላሊበላ ቅዱስም ንጉሥም ነው፤ የላሊበላን ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናትን አንጿል፡፡[60] አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሰማያውያን ከሃያ አራቱ ካህናተ ሰማያት ጋር ሃያ አምስተኛ ሁነው መንበሩን አጥነዋል፡፡

ቅዱስ ያሬድ ከነሞዛርት እና ቤትሆቨን በፊት የነበረ የዜማ ሊቅ ነው፡፡በእስራኤል ውስጥ ትልቅ ቦታ የነበረው አቤሜሌክ ሌላው ተጠቃሽ ነው፡፡ "ኢትዮጵያዊውአቤሜሌክም ኤርሚያስን፦ ይህን አሮጌ ጨርቅና እላቂውን ልብስ በብብትህ ከገመዱ በታች አድርግ አለው፤ ኤርሚያስም እንዲህ አደረገ" ኤር.38÷12 ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ምክንያት የሆነው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም እንዲህ ተጠቅሷል "ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ አንድ ኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር" የሐዋ. 8÷27፡፡

ጃንደረባው በሐዲስ ኪዳን ትልቅ ሥፍራ ከተሰጣቸው ኢትዮጵያውያን አንዱ ነው፡፡ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የሆነው ፊልጶስ አጥምቆታል፡፡ ክርስትናን አስተምሮታል እሱም ወደ ኢትዮጵያ ይዞ መጥቷል፡፡ እነዚህና ሌሎች ምርጦች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የእምነት መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግመው የተጠቀሱ ናቸው፡፡ ዘማሪዎችም ከዚህ ተነሥተው ኀሩያኑን ያነሣሉ ይዘክራሉ፡፡

---

[60] *ዘመድኩን፤ 1፡፡ መጽሔተ አሚን ዘደብረ አሚን፣ 13፤ ሰሎሞን፣ 10፤ ከበደ፣227፤ ምክረ ሥላሴ፣ 32*

ነቢዩ መሐመድ የመሰከሩላቸው፤ በዓረቡ ዓለም እጅግ የሚታወቁ እና የሚወደዱ በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ጉልህ ሥፍራ ያላቸው ኢትዮጵያውያን አሉ፡፡ የሃይማኖቱ ሊቃውንት ከሚጠቅሷቸው መካከል ለአብነት ጥቂቶችን ማንሣት ይቻላል፡፡

ቢላል ኢብን ረባህ በኢስላም ታሪክ የመጀመሪያው ሙዐዚን ነው፡፡ ነብዩ መሐመድ "ቢላል ጥሩ ሰው ነው፡፡ እሱን ሙዕሚን (አማኝ) ያልሆነ አይከተለውም ብለዋል" ተብሎ የተነገረለት ኢትዮጵያዊ ነው፡፡[61] ነብዩን ያሳደገች፣ ያጠባችና ያዘለች ኢትዮጵያዊቷ ኡሙ አይመን (ረዐ) ናት፡፡ በረካ አልሐበሺያ (ረዓ) ኡሙ ሐቢባ (ረዓ) ከሐበሻ ስትመለስ ተከትላት የመጣች አገልጋይዋ ነበረች፡፡

የነብዩ መሐመድ የክብር ጓደኞች በመሆን በክብር ይወሳሉ፡፡ ነብዩንና እምነቱን ለማጥፋት የተነሡ ጠላቶችን በመከልከል ረገድ፤ የነብዩ አገልጋይ በመሆን የከዳሚነት ክብር በማግኘት ወዘተ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በእስልምና ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡

ሀበሾች በቁርዓንና በሐዲስ የተሰጣቸውን ቦታ በጥቂት ይዘርዝር፤ አልበቅራ አንቀጽ 144፣ አል ኒሳዕ ምዕራፍ 51፣ አልካህፍ ምዕራፍ፣ አንቀጽ 30፣ አል ኢምራን አንቀጽ 199፣ ወዘተ፡፡[62]

ጠቢቡ ሉቅማንን እዚህ ላይ ማንሣት ይቻላል፡፡ የእምነቱ ሊቃዉንት እንደሚሉት ሉቅማን ዘኢትዮጵያ የነብዩ አሏህ ዳውድ አማካሪና የእስራኤል ዳኛ የነበረ ነው፡፡ ነብዩ መሐመድም ስለ ኢትዮጵያውያን ምርጦች ሲናገሩም የሐበሻ ምርጥ ዜጎች አራት ናቸው፡፡ እነሱም ሉቅማን ነጃሽ፣ ቢላል እና መህጃ ናቸው፡፡[63]

ነጃሽም በእምነቱ ሊቃዉንት ዘንድ ተደጋግሞ የሚነሣ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ የሙነሽዶች የነሻዳቸውና የመንዙማቸው መሠረት በእስልምና ዓለም ውስጥ ኢትዮጵያን ከፍ ያደረጉ ምርጦች ላይ ነው፡፡ እነዚህ ኅሩያን አንድም በፈጣሪ የተመረጡ አንድም በነብዩ መሐመድ የተወደዱ ናቸው፡፡ እነዚህን በቁርዓን እና ሐዲስ ተደጋገሙ የተዘረዘሩትን ዕንቁ ኢትዮጵያውያንን መንዙማው እና ነሽዳው ይዘክራቸዋል፡፡

---

[61] *ሁሴን 86*
[62] *ዐምደ ሚካኤል፣ 121፥122፣119 ፣57፣60*
[63] *ሙሐመድ፣ 22፣ 114*

ኢትዮጵያ ምን ያህል በፈጣሪም በሰውም ዘንድ የተወደደች ሀገር እንደሆነች በአማኞች ልብ ዘንድ ለመትከል ሲታትሩ ይታያል። ይኼም የሀገሪቱን ትልቅነት የሕዝቦቿን ምርጥነት በማዘከር ግዙፍነቷንና ቦታዋን ይዛ እንድትቀጥል ከክብሯ እንዳትንሸራተት በማንቃት በኩል የሚፈጥረው ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ መንፈሳዊ ሥሪት ኃያል ነው። የሁለቱንም ሃይማኖቶች ሀገረ ኅሩያን የሚዘክሩትን ዝማሬዎች እንመልከት።

አባሪ አንድ ላይ ከኦርቶዶክስ ሁለተኛው መዝሙር ተክለ ሃይማኖት ፀሐይ የአምላክ አገልጋይ፤ ዘማሪ ዲያቆን ምንዳዬ ብርሃኑ፣ቁጥር 5፣ 1991፤ በተጨማሪ አባሪ አንድ 10ኛ መዝሙር አብርሂ የሚለው እና 16ኛው መዝሙር ሰላም ለኢትዮጵያ የሚለው ሊቀ መዘምራን ቴዎድሮስ ዮሴፍ 2011 ከኦርቶዶክስ ተጠቃሽ ናቸው። በተመሳሳይ ከኦርቶዶክስ አባሪ አንድ ላይ አንደኛው መዝሙርም የኪነጥበብ ወልደ ቂርቆስ፣ ቁጥር6፣ 1984. ይጠቀሳል።

እነዚህ ከላይ ለአብነት የቀረቡት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን ያቀረቧቸው ዝማሬዎች ናቸው። ከዚህ ቀጥሎ የእስልምና ዕምነት ተከታዮች ሙነሽዶች ያቀረቧቸውን ነሺዳዎች እንመልከት። ኢትዮጵያ የሚለው በሙነሽድ ሑሰኒ ሱልጣን እና አብዱሰላም አበራ 2013 ሦስተኛው አባሪ ላይ አራተኛው ይኸንኑ ያጠናክራል።

### *3.4.2.2. አርዱል እንግዳ*

እንግዳ የሚለው ቃል ነገደ ካለው ግሥ ይመዘዛል።[64] ያልዋለ ያላደረ ወይም ያልሰነበተ ከሌላ አካባቢ ሀገር ቤት የመጣ ሰው፤ባይተዋር ባእድ አዲስ የመጣ ወይም ለአካባቢው አዲስ የሆነ ማለት ነው። አርዱል፣ አርድ ከሚለው የአረብኛ ቃል የሚመዘዝ ሲኾን ትርጉሙ መሬት ማለት ነው።[65] አርዱል እንግዳ ሲባል የእንግዶች ማረፊያ ምድር፤ እንግዳ ተቀባይ ሀገር፤ እንግዳ ወዳድ ሕዝብ የሚሉትን ሐሳቦች ይይዛል፤ ይሸከማል።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በዓለም ሕዝቦች ዘንድ በዋነኝነት ከሚታወቁባቸው ቀለሞች አንዱ እንግዳ ተቀባይ ሀገርና ሕዝብ መሆናቸው ነው። ይኽ በእስልምናም በክርስትናም የታሪክ እና የሃይማኖት መጻሕፍት የተደገፈ ጣፋጭ ሐቅ ነው። የአይሁድ፣ የክርስትና እና የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የእምነት አባት ተብሎ የሚታወቀው አብርሃም በእንግዳ ተቀባይነቱ

---

*[64] አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 286*
*[65] አብዱረሂም፣ 54*

ይታወቃል። ዘፍ18-16 በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን እንግዳን መቀበል ዋጋው ከፍ ያለ ነው። በፈጣሪ ዘንድም ትእዛዝ የተላለፈበት ነው።

እንግዳን መቀበል መንግሥተ ሰማያትን ያወርሳል። "የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ… እንግዳ ሆኘ ተቀብላችሁኛልና…" ማቴ.25፥34 ጀምሮ፤ ሎጥም እንግዳ መቀበልን ከአጎቱ ከአብርሃም ስለተማረ መላእክትን በእንግድነት ተቀበለ፤ ዘፍ 19፣1፥4። የሰራጵታዋ ባልቴት ኤሊያስን በእንግድነት በመቀበል እፍኝ ዱቄቷ እና ዘይቷ በበረከት ተሞልቶላት ዱቄቱ ከማድጋው ዘይቱ ከማሰሮው ሳይጎድል ቆይቶላታል። ልጇም ከሞት ተነሣላት፤ 1ኛ ነገ. 17፥9-17። ይኼ ሁሉ የእንግዳ መቀበል ውጤት ነው።

በሐዲስ ኪዳንም እንግዳ መቀበል ስጦታውና በረከቱ ግዙፍ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እንግዳ መቀበል መሆኑን ሲያመለክት በጊዜና በቦታ የማይናወጽ ቋሚ ክርስቲያናዊ ምግባር መሆኑን ለጢሞቲዎስ ባልቴቷን ምክንያት አድርጎ ነግሮታል። "ልጆችን በማሳደግ እንግዶችን በመቀበል፣ የቅዱሳን እግሮች በማጠብ፣ የተጨነቀችንም በመረዳት በጎ ሥራንም በመከተል ይኸን መልካም ሥራ በማድረግ የተመሰከረለት ልትሆን ይገባል" 1ኛ ጢሞ. 5፥10-11

መጽሐፍ ቅዱስ እንግዳን ከሀገር ልጅ ጋር እኩል ማየት እንደሚገባ በብሉይ ኪዳኑ ዘሌዋውያን ላይ እንዲህ ተጽፏል። "እንግዳ እንደ ሀገር ልጅ ይሁንላችሁ እርሱንም እንደራስህ ውደድ ዘሌ. 19፥33፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያን ፈጣሪ ያላቸውን ፈጣሪያቸውን" የሚፈሩ ሕዝቦች ናቸው፤ ፈጣሪውን የሚፈራ ሕዝብ ቀድሞም በኦሪት በኂላም በወንጌል የእንግድነት ጉዳይ ቦታው ትልቅ መሆኑን አውቆ እንግዶችን ሲቀበል ኑሯል።

ይኽ መንፈሳዊ እሴት በሕዝቡና በአማኙ ዘንድ በመኖሩ እንግዶችን በተለያዩ ዘመን ሲቀበል የኖረ ሕዝብ ነው። ሀገሪቱም የስደተኞች መሸሸጊያ ዋሻ፤ የእንግዶች ታዛና ወደብ ሁና አገልግላለች።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መዝሙራት ላይ እንግዳ ተቀባይነቷን በማስመልከት በተለያዩ ዘማሪዎች በተለያዩ ዓመት ይኼ ስሜት ተንፀባርቋል። ኢትዮጵያን ምርጥ እና ደግ እንግዳ ተቀባይ ሀገር አድርገው ሲሥሉ እንግዶች ደግሞ ከተለያየ ሀገር በተለያየ ዘመን የመጡትን ስደተኞችን እንግዶችን ነው።

ለአብነትም ዘጠኙ ቅዱሳንን ወይም ተሰዓቱ ቅዱሳን እየተባሉ የሚጠሩትን ማንሣት ይቻላል፡፡ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ ዘጠኝ መነኮሳት ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጡ በዚህን ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ የነበረው ዳግማዊ አልአሜዳ ነበር፡፡ እነዚህ መነኮሳት የስደታቸው ምክንያት በጉባኤ ኬልቄዶን የተከሠተውን አዲስ ትምህርት በመቃወማቸው በቢዛንታይን ነገሥታት ስቃይ ስለጸናባቸው ነው፡፡[66]

በዚህም ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ንጉሡ አቀባበል አደረገላቸው፡፡ በእንግድነት የተቀመጡት በአኩሱም ቤተቀጢን የሚባለው ሥፍራ ነው፤ ስማቸውም አቡነ አረጋዊ ዞሮም፣ አቡነ ጴንጠልዮን ዘሮም፣ አቡነ ይምአታ ዘቆስያ፣ አቡነ ገሪማ ዘሮም፣ አቡነ ጽሕማ ዘአንጾኪያ፣ አቡነ አፍጼ ዘእስያ፣ አቡነ ሊባኖስ ዘቁስጥንጥንያ፣ አቡነ አሌፍ ዘቂሳርያ እና አቡነ ጉባ ዘኪልቅያ ናቸው፡፡[67]

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን ዘንድ ስደተኞችን እና እንግዶችን በመቀበል ኢትዮጵያ የእንግዶች ማረፊያ ሀገር መሆኗን አበክረው ከሚገልጽባቸው አንዱ ቅዱሱን ቤተሰብ መቀበሏ ነው፡፡ Holy Family ወይም ቅዱሱ ቤተሰብ የሚባለው ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ዮሴፍና ሰሎሜ ናቸው፡፡ ሄሮድስ ጌታን ሊገድለው በፈለገው ጊዜ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ልጇን ይዞ ወደ ግብጽ ተሰዳለች፡፡ ከግብጽ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጣና ቂርቆስ ገዳም አርፈዋል፡፡[68]

እነዚህንና ሌሎች ወደ ኢትዮጵያ የመጡትን እንግዶችን፣ ሕዝቦቿ እቅፍ ድግፍ አድርገው በማስተናገዳቸው ዘማሪዎቹ መጠጊያና መሸሸጊያነቷን ያዘክራሉ፡፡

መራራ ሕይወቴ

. . .

[66] *ጎርጎርዮስ፣71*

[67] *ሰሎሞን፣ 82-83*

[68] *ይኩኖ አምላክ ፣ 34፤ ዳንኤል፣ 563*

ዳሯ እሳት መኃሏ ገነት፤

ለእኛም ይስጠን ፍቅር አንድነት፡፡

<u>የተሰዓቱ ቅዱሳን መሸሻ፤</u>

ኖላዊ ኄር ጠባቂሽ ነው ጋሻ፡፡

. . .

መስመር ከራሴ

(ዘማሪ ዲ/ን እንግዳወርቅ በቀለ፤ ቁጥር 4፣1991) ከኦርቶዶክስ

ኢትዮጵያ ሀገሬ

. . .

የቅዱሳን ነሽ መፍለቂያ፤

<u>የምስኪኖች መሸሸጊያ፡፡</u>

. . .

መስመር ከራሴ

(ዘማሪ ሙሉቀን ከበደ፤ 2010 ዓ.ም.) ከኦርቶዶክስ

በእስልምና የሃይማኖት እና የታሪክ መጻሕፍት ዘንድ ስደት፣ ስደተኞች እንግዶች እና እንግዳ ተቀባዮች ሰፊ ሥፍራ የተሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ የሃይማኖቱ ሊቃውንት እንደሚሉት እስልምናና ስደት እስልምናና ፈተና ያልተነጣጠሉ ነገሮች ናቸው፡፡ እንኳን ሃይማኖትን ያኽል ትልቅ ጉዳይ ይቅርና ተራ ድርጅት እንኳ ሲስፋፋ ትግል፣ ፈተና፣ መከራ፣ ስደት ይኖራሉ፡፡ ስደት ካለ ስደተኞች ይኖራሉ፡፡

ዳሩል ሂጅረተይኒ

. . .

ዳሩል ሂጂረተይኒ ሀገሬ ኢትዮጵያ፤

ለስንቱ ሱሐባ ሆነሻል መጠጊያ፡፡

ኢትዮጵያ ሀገሬ ብዙ ነው ዝናሽ፤

ታሪክሽ ቢደበቅ እኔ ላውጣልሽ፡፡

ያላህ መልእክተኛ ለይተው ከሌላ፤

ጥሩነትሽን አይተው መረጡሽ ለጥላ፡፡

. . .

(አሊ አሚን፣ ፋአድ በሽር፣ በፈረንጆቹ 2013) ከእስልምና

ስለ መሰደድ፣ በእንግድነት ወደ ማያውቁት ሥፍራ ስለመበተን፣ ቁርዓን፣ ሐዲሳቱ እና ሌሎች የእስልምና ሃይማኖት የታሪክ መጻሕፍት ስለ እንግዶች እና እንግዶችን ስለሚቀበሉ ሰዎች ብዙ ብለዋል፡፡ ዋጋቸውንም ተናግረዋል፡፡ (ጌታችሁ) "እናንተ ያመናችሁ ባሮቼ ሆይ! ጌታችሁን ፍሩ፣ ለእነዚያ በዚህች በቅርቢቱ ዓለም መልካም ለሠሩት መልካም ምንዳ አላቸው የአላህ ምድርም ሰፊ ናት፤ (ብትቸገሩ ተሰደዱ፤ ታጋሾቹ ምንዳቸውን የሚሰጡት ያለግምት ነው፤ (ይላል) ባላቸው፡፡ (ቁርዓን 39፡10)

በተለያዩ የቁርዓን አንቀጾችም የስደት ተሳታፊዎች የፈጣሪ ምሕረት እንደሚገባቸው በፈጣሪ ዘንድ ቃል ተገብቶላቸዋል፡፡ የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ አልበቀራ 218፣ ኦልኒሳዕ 100፣ አል አንፋል 72፣74፣75፤ አልተውባ 20፣110፣117 ኦልናህል 41፥1፣10 አልሀጅ 58፣ አል ሀሽር 8 የመሳሰሉትን እናገኛለን፡፡[69]

---

[69] *አደም፣ 60-61*

ኢትዮጵያም በእስልምናው ዓለም በእንግዳ ተቀባይነቷ እጅግ ትታወቃለች፤ ትደነቃለችም፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ ስደተኞችን ተቀብላ በእንክብካቤ ለዓመታት ያቆየች ሲሆን ለዚህ የታጨችው ከሌሎች ሀገራት ጋር ተወዳድራ አይደለም፡፡ በመለኮታዊ ማለትም በአላህ ውሳኔ እንጂ፡፡[70]

በነብዩ መሐመድ ተከታዮች ላይ የመካ ቁረይሾች ተቃውሞና ጭቆና አብዝተው እንዳበረቱባቸው የሃይማኖቱ ሊቃውንት ጽፈዋል፡፡ በዚህም ተከታዮቻቸውን ጠርተው ወደ ሐበሻ ምድር እንዲሰደዱ አድርገዋቸዋል፡፡ የእውነት ምድር ናት ወደ ሐበሻ ምድር ሒዱ በዚህ ክርስቲያን ንጉሥ አለ፤ በግዛቱም ፍትሕ ታገኛላችሁ፤ በአላህ እርዳታ ድል እስክናገኝ ወደዚያ ሒዱእንዳሏቸው ተዘግቧል [71] ወደሐበሻ ምድር ሁለት ጊዜ ስደት ተደርጓል፡፡ ይኼም ዳሩልሂጅረተይኒ በሚል ይታወቃል፡፡

ኢትዮጵያ

. . .

ሒዱ ወደ ሐበሻ ወደ ሰላም ሀገር፤

እዚያ ንጉሥ አለ አማኝ የሚያፈቅር፡፡

እዚያ ንጉሥ አለ ስለ እውነት የሚኖር፤

እዚያ ንጉሥ አለ ስለ እውነት የሚኖር፡፡

ተብሎ ተመስክሯል ለዓለሙ መብራት፤

ለሰው ከተላኩት ለእዝነት፡፡

. . .

---

[70] *መሐመድ፣7*
[71] *ሀሰን፣ 143*

(ሙነሽድ ሑሰኒ ሱልጣን እና አብዱል ሰላም አበራ፣ 2013) ከእስልምና

በመጀመሪያው የሐበሻ ስደት እንዲህ ነበር። በነብይነት በአምስተኛው ዓመት ረጅብ ወር ላይ የመጀመሪያ የሶሐቦች የስደተኛ ቡድን ወደ ሐበሻ ተሰደደ። ዐሥራሁለት ወንዶችንና አራት ሴቶችን የያዘ ነበር። የቡድኑ መሪ ዑስማን ቢን አፋን ሲሆን፣ ባለቤቱ የአላህ መልእክተኛ ሴት ልጁ ሩቅያ ነበረች። የአላህ መልእክተኛ እርሷንና ባሏን ዑስማንን በማስመልከት ሲናገሩ። እናንተ ከኢብራሂምና ከሎጥ በኋላ ለአላህ ብሎ በመሰደድ የመጀመሪያ ቤት ናችሁ።... ሙስሊሞች ጥሩ አቀባበል ተደረገላቸው።[72]

ሁለተኛው የሐበሻ ስደት የተደረገው ነጃሽ ስደተኛ ሙስሊሞችን በመልካም ሁኔታ ማስተናገዱን ቁረይሾች በመስማታቸው ነው። ጅዕፋርም ሙስሊሞችን ወክሎ የተጠየቀውን መለሰ። ... ነጃሽም ሙስሊሞቹ ሒዱ በአገሬ ውስጥ በሰላም ተቀመጡ። የሰደባችሁ ይቀጣል፣ የሰደባችሁ ይቀጣሉ፣ የሰደባችሁ ይቀጣል፤ ከእናንተ በአንዳችሁ ላይ ጉዳት አድርሼ ጋራ የሚያክል ወርቅ ባገኝ የምወድ አይደለሁም አሏችሁ።[73] ነሺዳዎች እና መንዙማዎችም ይኽንን ታሪክ መሠረት አድርገው ኢትዮጵያን የእውነት ምድር፣ የአማኞች መጠጊያ ሀገር፣ የፍትሕ ጀምበር ይሏታል።

ኢትዮጵያውያን ዘር፣ ሃይማኖት፣ ቆዳ እና ቀለም ሳይመርጡ የመቀበላቸው ምሥጢር ሃይማኖታዊ መሠረት፣ መንፈሳዊ ምንጭ ያለው፣ ቱባ ባህላዊና ማኅበራዊ እሴት ነው። እንግዳ አድርገው የሚቀበሉትም የውጭውን ብቻ አይደለም እርስ በእርሳቸው ጭምር እንጂ።

ከዚህ በተረፈ ማንም መንገደኛ በመሸበት ቦታ ወደ አንዱ ቤት ጎራ ብሎ "የእግዚአብሔር እንግዳነኝና አሳድሩኝ" ይላል። እንግዳ ተቀባዩም ቢሆን እንግዳውን የሚቀበለው (እንግዶችን) በደስታና በፍቅር ተቀብሎ የሚያስተናግደው በቤቴ እያለ ሳይሆን "ቤት የእግዚአብሔር ነው" በማለት ነው።[74]

ዛሬ እንኳን የውጭውን ዜጋ የሀገርን ልጅ እንግዳ አድርጎ መቀበል ሥጋት እየሆነ መጥቷል። ይኽ ጥንታዊ መሠረት ያለው ባህላችንም እየተሸረሸረ በመጣበት በዚህ ወቅት ዘማሪያኑ እና

---

[72] *ዝኒ ከማሁ ገጽ 146-147*
[73] *ዝኒ ከማሁ ገጽ 171*
[74] *ካህሳይ፣ 229*

ሙነሽዶች ታሪክን እየጠቀሱ የትናንቷን እንግዳ ተቀባይ ሀገር ታሪክ እያወሱ እንደድሮው እንዲሆን ይማጸናሉ፡፡

ይኼ የእንግዳ ተቀባይነት እሴት ፈጽሞ ጠፍቷል ማለት አይቻልም፡፡ በቅርቡ ከሶርያ የተሰዱ እንግዶች በሀገራችን ተጠልለዋል፡፡ ሕዝቡም በእንግዳ ተቀባይነት ባህሉ እያስተናገዳቸው ክፉ ቀን እያሳለፉ ነው፡፡ የእነዚህ ዘማሪዎች መዝሙራት አንዱ ውጤት ተደርጎም ሊቆጠር ይችላል፡፡ ምክንያቱም በመዝሙሩ የስደተኞች መጠጊያ የሆነችውን ሀገር በመዘከር ዛሬም እንግዳ እንድንቀበል ይሰብካሉ፡፡

ፈጣሪም እሱንና ቅዱሳኑን መልእክተኞችን በስደት የተቀበለች ሀገር መሆኗን አስቦ በምሕረት እንዲጎበኛት ይማልዳሉ፡፡ አብሮ መኖርን ያጸናሉ፡፡ መተሳሰብን በአማኝ ልብ ውስጥ ይተክላሉ፡፡ ይኼም መንፈሳዊ መጽናናትን፣ ልባዊ መረጋጋትን፣ ቱሪዝምን መሳብን፣ በመፍጠር ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢካኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ያረጋግጣሉ፡፡ ከሁለቱም ሃይማኖቶች አብነቶችን እንጥቀስ፡፡

### 3.4.3. በኦርቶዶክስ፣ በካቶሊክ፣ በፕሮቴስታንት መዝሙራት ብቻ ያለመባያ

*"እጅ መዘርጋት"*

ሦስቱም ሃይማኖቶች በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኙ በክርስትና ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ የውስጥ ብዛትና ማነስ ይለያዩ እንጂ መሠረታቸው ክርስቶስ ነው፡፡ በክርስቶስ መሠረትነት ልዩ ልዩ የአምልኮ ሥርዓት አላቸው፡፡ ቀኖናዊ እና ዶግማዊ ልዩነታቸውም እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያ እጆቿን ትዘረጋለች በሚለው በእኩል ይስማማሉ፡፡ መዝ 68፥31

ኢትዮጳያ ሲሉ ሕዝቧን ነው፡፡ እጅ ሲሉ ደግሞ እንደ ኢትዮጳያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር መዝገበ ቃላት አገላለጽ ብዙ ኃይልን ዘፍ. 9፥2፡5፤ ሉቃ.1፥66፤ ልግስናን ያመለክታል፡፡ ዘዳ. 15፥8፡፡ ቀኝ እጅ ከግራ እጅ እንደሚበልጥ ይታመናል ዘፍ.48፥13-19፤ እጅ እንደ አንደበት የንግግር ስልትን ይገልጣል፤ ሐጌ.1፥1 የሐዋ.26፥1፡፡ ክርስቶስ በእጅ ምሳሌነት እንደሚገለጥ ሊቃውንት ተርጉመዋል፤ መዝ. 144፥7፡፡[75]

---

[75] *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ 167*

ከሰውነት ክፍላችን ውስጥ ግዙፍ ተግባር የሚፈጽመው እጅ ነው። የስሜቶቻችን ሥራ አስፈጻሚ ነው። በእጅ ጽድቅ ይሠራል። ወንጀል ይፈጸማል። ሲሻን ፈጣሪን ሳይሻን ጣኦት እናመልክበታለን። የእጅ ተግባሩ ብዙ ጉልበቱም ኃያል ነው። እጅ እምነታችንን፣ ኃይላችንን፣ ማንነታችንን፣ አኗኗራችንን፣ ውሏችንን የምንመራበት ብርቱ ሥጋችን ነው።

የጥፋትም የልማትም መንገድ ነው። አእምሮ ያለባቸው በጎም ይሁን መጥፎ ዓላማዎች ከሚያስፈጽምባቸው መሣሪያዎች አንዱና ዋነኛው እጅ ነው። ሃይማኖቶች ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ሲሉ በእጅ የተመሰለውን፣ እምነቷን፣ ኃይሏን፣ ሕይወቷን፣ ማንነቷን፣ ውሎ አዳሯን፣ ውጥታ መግባቷን፣ ጠላት ወዳጇን፣ ኃዘንና ደስታዋን፣ ውድቀት እና መነሣቷን ነው። ሁለንተናዋን ለእግዚአብሔር የዘረጋችና የሰጠች፣ መመኪያዋን ፈጣሪ ያደረገች ሀገር ናት ብለው በዝማሬያቸው ያቀነቅናሉ።

ሥራዋም ሁሉ ወደ አምላኳ የተዘረጋ ለእርሱ የተሰጠ እና ከእርሱ የሚባረክ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እጅ የተባለው ሥራ ነው ይላል። Hand is a symbol of work[76] ይኼ ኢትዮጵያ ምን ያህል በፈጣሪዋ የምትተማመን ሀገር እንደሆነች፤ መነሻዋና መድረሻዋ እግዚአብሔር እንደኾነ በማዘከር፤ ልመና ጸሎቷ ወደ አምላኳ እንደሆነ በማሳሰብ አንድምየፈጣሪ ሕዝብና ሀገር መሆኗን ሲያሳይ፣ አንድም እሷን እና ሕዝቦቿን ሊነካ እና ሊደፍር የሚያስበውን ጠላት ረዳት ከላይ እንደሆነ አውቆ እንዳይሞክረው ሲያደርግ፤ ምእመናን እና ምእመናት ደግሞ ከፈጣሪያቸው ጋር ያላቸውን ቁርኝነት እንዲያጠብቁ ያግዛል።

ይኼም በአማኙ ሕዝብ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ሀገሬም የእርሱ ናት የሚል ስሜት በመፍጠር የተረጋጋ ማኅበረሰብ እንዲኖር ከማድረግ በላይ በራስና በፈጣሪ መተማመን ከፍ ያደርጋል። ዝማሬዎችም ይኼንን ደጋግመው ሲያነሡ ይታያል።

ኢትዮጵያ እጆቿን

. . .

ኢትዮጵያ እጆቿን ዘረጋች አለ ወደ እግዚአብሔር፤

---

[76] *Tadros malaty, commentary on psalm, .324*

ነብዩ ዳዊት በትንቢት አይቶ ስንፋቀር።

ዛሬ ግን ኾነን በዘር በቋንቋ የምንሰለፍ፤

የተዘረጋው የፍቅር እጆቿ እንዳይታጠፍ።

(መምህር ምሕረተ አብ አሰፋ 2013) ከኦርቶዶክስ

በተመሳሳይ መልኩ ከካቶሊክ (የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንዘማሪያን በዋሽንግተን ዲሲ ያቀረቡት 2013) ይኸንኑ ሐሳብ የሚደግፍ መዝሙር እናገኛለን።

ኢትዮጵያ እጆችሽን ዘርጊ፤

ክህደትሽ ትዕቢትሽን ከእግሩ በታች ጥለሽ፤

ታጠቢ ተመለሽ ሰላሙን ያልብስሽ።

ከፕሮቴስታንት (ተስፋዬ ጫላ ቁጥር 4 1998) ባወጣው ዝማሬ "ኢትዮጵያ ሀገሬ" በማለት እነዚህን መልእክቶች በውስጡ ይዞ ቀርቧል።. . .

ኢትዮጵያ ሀገሬ እጆችሽን የምትዘረጊበት፤

ሰዓቱ ደርሷል ዕንባ ሚደርቅበት ካፈርሽ፤

ሰላም ይታጨዳል ከወንዝሽ፤

ዓለም ይባረካል ዓለም ይባረካል። (2)

### 3.4.4. በኦርቶዶክስና በካቶሊክ ብቻ ያለ መባያ

*"ድንግል ማርያምና ርስት"*

ቅድስት ድንግል ማርያም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እና በካቶሊክዊት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ልዩ ክብር ከሚሰጣቸው ቅዱሳት አንስት ቀዳማዊዋ እናት ናት። ሁለቱም ሃይማኖቶች የመሠረተ እምነት ልዩነት /Dogmatic difference/ ቢኖራቸውም፤ ካቶሊካውያን

ድንግል ማርያምን የሰው ወገን፣ የአዳም ዘር ሳትሆን ኃይል አርአያማዊት ሰማያዊት ናት፣ ኦርቶዶክሶች ደግሞ የሰው ዘር የሆነች ኢያቄምና ሐና የሚባሉ እናትና አባት ያሏት፣ እንደ ሰው ተወልዳ ያደገች፣ እግዚአብሔር የጠበቃት፣ የአዳም ውርስ ኀጢአት የሌለባት፤ ንጽሕት ቅድስት የድኅነታችን ምክንያት ናት። ብለው አምነው ቢለያዩም የአምላክ እናት ናት፣ ንጽሕት፣ ቅድስት ናት ብለው በማመን ይገናኛሉ።

ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው የኢትዮጵያ እናት ናት። ኢትዮጵያ ለድንግል ማርያም ርስት የአደራ ሀገር ናት። ርስት ቤተ ዘመድ የሆነ እያረሰ የሚጠቀምበትና ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ መሬት ዐጽመ ርስት ይባላል። የግል ወይም የራስ ይዞታ መሬት።[77] በጸሎት በእናትነቷ ኢትዮጵያን እና ሕዝቦቿን ትጠብቃለች ብለው ያምናሉ። ይኼንንም በመዝሙሮቻቸው ደጋግመው ገልጸዋል።

በእነዚህ ዝማሬዎች ዘንድ ርስት እና ድንግል ማርያም የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ድንግል ማርያም በሁለቱ እምነት ተከታዮች ዘማሪያን ዘንድ ርኅሩኅ፣ አዛኝ፣ ዋስ፣ ጠበቃ፣ ረዳት ተደርጋ ቀርባለች። ኢትዮጵያና ሕዝቦቿም ርስቷ፣ ምድሯ፣ ስጦታዋ፣ ዐሥራቷ ተደርገው ተሥለዋል።

ይኼም ምእመናን ሲጨንቃቸው መማጸኛ፣ ሲከፋቸው መሸሸጊያ፣ መከራ ሲያዣብብባቸው ጥላ ከለላ፣ ሲርባቸው የእንጀራ መሶብ፣ ሲጠማቸው የውሃ ማሰሮ፣ ሲደክማቸው ምርኩዝ፣ በቀቢፀ ተስፋ ሲወድቁ መጽናኛ ቅድስት እናት እንዳላቸው ደጋግመው በመንገር ማኅበራዊ እና መንፈሳዊ ዕረፍት እንዲፈጠር በማድረግ የሚጫወቱት ሚና ግዙፍ የሚለግሱት ፋይዳ ጉልህ ነው።

ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በተለይ ኦርቶዶክሳዊያን ከድንግል ማርያም ጋር ያላቸው ቅርርብ እንደ እናትና ልጅ ነው። ሲምሉ ማርያምን ነው። አራስ ሴት ሲጠይቁ የማርያም አራስ፣ ማርያም በሽልም ታውጣሽ ተብላ ነው። ሰውነታቸው ላይ ጥቁር ነጥብ ሲያዩ ማርያም ስማኝ ይላሉ። ሕጻናት ሲጫወቱ ሮጠው ለማምለጥ ሲፈልጉ ትንሽ የማርያም መንገድ ስጡኝ ማለት፤ ሲጣሉ በማርያም ጣት እንታረቅ ብለው ትንሿን የጣት ክፍል ማሳየት፤ ዝናብ ሲዘንብ ሰማይ ላይ ኅብረ ቀለማት ሲያዩ የማርያም መቀነት ይላሉ።

[77] *አማርኛመዝገበ ቃላት፣ 102*

ፍቅሯ ምን ያኽል በደምና በአጥንታቸው እንደገባች የሚያሳይ ነው። ተማሪው ይቅርና መሪው ዐፄ ምኒልክ ጣሊያን ኢትዮጵያን ሲወር በመጣ ጊዜ ሕዝቡ ወደ ግንባር እንዲዘምት አዘውት ነበር። "ወስልቶ ቢቀር ግን ማርያምን አልምርህም" ብለው በመማል ቁርጠኝነታቸውን ያረጋገጡበት የመሐላቸው ሰነድ ናት።[78]

ይኽ የሚያሳየው ከሀገር መሪ እስከ ሕዝብ ከድንግል ማርያም ጋር ያላቸውን ጥብቅ ወዳጅነት ነው። ውጤቱንም ስናይ ሕዝቡ ይኼን መሐላ ሰምቶ ዐድዋ ድረስ ተዋግቶ የኢትዮጵያን ነጻነት ባንዲራ ከፍ አድርጎ አውለብልቧል።

ርስት አድርጋ የተሰጠችው ሀገር ስሟ ማሰሪያ ሆኖ ድልን አጎናጽፏል። ይኼም ከፈጣሪ ቀጥሎ በጸሎትና በምልጃዋ የምትጠብቃት ድንግል ማርያም እንዳለችው አማኙ ያለፍርሃት እንዲኖር ያደርገዋል። (ዘማሪ ዲ/ን ታዴዎስ ግርማ፣ 1996) ከኦርቶዶክስ

ኦ ድንግል- ኢትዮጵያ ርስትሽን፤

በእንግድነት - ኢትዮጵያ ርስትሽን፤

በካቶሊክ ቤተ ክስቲያን ደግሞ (የጽዮን ማርያም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መዘምራን፣ 1984) እንዲህ በማለት ሐሳቡን ያጠናክራሉ። ክብር ምስጋና

በቅድስት ሥላሴ ፍጹም የተባረክሽ፤

ቅዱሳን ስለክብርሽ በእውነት ያወደሱሽ፤

ሁሉም ስለ ፍቅርሽ የሚዘምሩልሽ፤

ለአንቺ ነው እመቤቴ ምስጋና የሚገባሽ።

ይኼ ዓመት ላንቺ ነው ደጓ እናታችን፤

[78] ተክለ ጻድቅ ፣ 226

### 3.4.5. በኦርቶዶክስ ብቻ ያሉ መባያዎች

#### *3.4.5.1. ደሴት*

ደሴት በቁሙ በባሕር ውስጥ ያለ፤ ባሕር የከበበው የብስ ሀገር ምድር ተራራ እንደ ደቅ፣ እንደ ሐይቅ፣ እንደ ዟይ፣ ያለነው።[79] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን ዘንድ በተለምዶ ዓመታት በወጡ መዝሙሮቻቸው ውስጥ ኢትዮጰያ የክርስቲያን ደሴት ናት እያሉ ሲዘምሩ ተስተውሏል።

ይኼንንም በቤተ ክርስቲያኗ ለተሰበሰቡ ምእመናን እና ምእመናት ሲያስተጋቡ ኑረዋል። በዝማሬዎቻቸው ውስጥ ያለችውን ደሴት ከማየት በፊት ደሴትን በአግባቡ መግለጽ ተገቢ ነው። ደሴት በውሃ የተከበበ ነው። ደሴት ከፍታ ያለው ምድር ነው። ደሴት ልዩ የማረፊያ ሥፍራ ነው። ደሴት ነፋስና ወጀብ የሚበዛበት ነው። ደሴት ልዩ የማረፊያ ሥፍራ ነው።

ደሴት ነፍስና ወጀብ የሚበዛበት ነው። ደሴት ከዋናው ምድር የራቀ ቦታ ነው። ደሴት የአእዋፍ ልዩ ዝምሬ የሚሰማበት ሥፍራ ነው። ወደ ደሴት ለመድረስ ባሕሩን ማለፍ ይጠይቃል።[80] ደሴት ሰዎች፣ እንስሳት፣ አእዋፋት ዕፀዋት የሚገኙበት የብዝን ሕይወት መኖሪያ ነው።

ደሴትን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን0ይን የተረዱ ጸሐፍት በልዩ ልዩ መንገድ ይገልጹታል። አንደኛው እይታ ደሴት የተባለችው ቤተ ክርስቲያን ናት። ደሴት ኃይለኛ ነፋስ እና ማዕበል እንደሚመጣበት ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁም በመከራ የተከበበች ናት። ደሴት በባሕር እንደተከበበች ቤተ ክርስቲያንም በዓለም የተከበበች ናት። ደሴት ከባሕር ወለል ከፍ ብሎ እንደሚታይ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው እምነትና ምግባርም ወደ ሰማያዊው ክብር የሚያደርስ ነው።[81] ስለዚህ የክርስቲያን ደሴት ቤተ ክርስቲያን ናት የሚል ነው።

ኢትዮጵውያን እና ጎረቤት ሀገሮቿን የሚመለከት ነው። የኢትዮጵያ አጎራባች ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት ሲባል አካባቢያዊ አውድን ብቻ የሚገልጽ ነው። ሶማሌ፣ የመን ክርስቲያኖች ነበሩ ጠፍተዋል። ኢትዮጵያ ዙሪያዋን የተከበበችው ከክርስትና እምነት ተከታይ ውጭ ባሉ ሀገራት ነው። መላው ምሥራቅ አፍሪካና በአካባቢው ይኖር የነበረው ክርስቲያን

---

[79] *ኪዳነ ወልድ ፣ 363*

[80] *የክርስቲያን ደሴት፤ አስተምህሮ ዘተዋሕዶ* [https://astemhro.com/2021/12/26islandofchrstianity](https://astemhro.com/2021/12/26islandofchrstianity)

[81] *ዝኒ ከማሁ*

በሙሉ ጠፍቶ ብቻዋን ሳትጥለቀለቅ የተረፈች የክርስቲያኖች መገኛ ማለት ነው፡፡[82] እነዚህ ከላይ የተጠቀቡትን የጸሐፍቱን ምልከታ ይዞን ወደ ዘማሪያኑ መዝሙር ስንወርድ ይኼንን እናገኛለን፡፡

ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት የሚለው አባባል በመዝሙሮቿ አሉታዊ ነገር የተሸከሙ፣ መጋፋትን፣ የእኔ ብቻ ማለትን፣ ያዘሉ ሳይሆኑ የራስ መልክን እና ክብርን አርግዞ ይታያል፡፡

ኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞች መኖሪያ ብቻ ናት አይልም፡፡ ዘማሪያኑ እንዲያውም የክርስቲያን ደሴትና የቃል ኪዳን ምድር ናት፤ ስለዚህ ዘር ቋንቋ አይለየንም ነው የሚሉት፡፡ ይኼ በአማኙ ብቻ ሳይሆን አማኝ ባልሆነው ወገን እንኳ አዎንታዊ መንፈስን የሚረጭ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሌላውን አልፈልግም ውጣልኝ ሳይል የክርስቲያን ደሴትነቷን ከተዋሕዶ ጋር በማስተሳሰር የቤተ ክርስቲያን፣ የክርስቲያኖችን እና የኢትዮጵያን አንድነት እና ክብር የገለጹበት ዝማሬ ነው፡፡ እነዚህ ዝማሬዎችም በሀገር ግንባታው ጡብ ድርደራ ላይ የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም፡፡ አብነቶችን እንይ፡-

ምሥጢረ ኢትዮጵያ

አትጠፋም ሀገሬ ኢትዮጵያ፤

ምልክቱን ይዛ ኢትዮጵያ፤

ከሰገነት ሥፍራ ኢትዮጵያ፤

በአምላኳ ታግዛ ኢትዮጵያ፤

ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ኢትዮጵያ፤

ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ምድር ኢትዮጵያ፤

አንድነን ዘር ቋንቋ አይለየንም ኢትዮጵያ፡፡ (3)

. . .

[82] *አባቶቻችን "ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት" ሲሉ ምን ማለታቸው ነበር? (አቻም የለህ ታምሩ)*
*Ethioreference https://ethioreference.com./archives/19706#*

(ዘማሪ ፀሐፊ ትእዝዛ ዲ/ን ታዴዎስ ግርማ 2011)

ኢትዮጵያ

የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ፤

የአንድ ምድር ማሕፀን መንታ፡፡

ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኢትዮጵያ፤

የክርስቲያን ደሴት ክብር ሃሌሉያ፡፡

(ዘማሪው ትዝታው ሳሙኤል 2000 ዓ.ም.)

*3.4.5.2. ነብርነት*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን መዝሙራት “ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን አይለውጥም” ኤር. 13÷23 የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ተመርኩዘው ጊዜና ቦታ ሳይገድባቸው መላልሰውና ደጋግመው ዘምረውታል፡፡ የኢትዮጵያውያን መልክ ከነብር ዥንጉርጉርነት ጋር በዘይቤ አጠናቅቀው በዜማ ቀምረው ለምእመናን ጆሮ አድርሰዋል፡፡ ነብርነትን ከኢትዮጵያዊነት ያሰናሰለውንና ያስማማውን ምንነት ለማግኘት ነብርነትን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን ይህንን የትንቢተ ኤርሚያስ ክፍል ከቋሚነት፣ ከአቋምነት ከአይለወጥነት ጋር አስተባብረው ተርጉመውታል፡፡

እንዲህ በማለት፡- ዘይት ጥመቱን ነምርም ዥንጉርጉርነቱን ይተዋልን? እናንተ በጎ ሥራ መሥራት ይቻላችኊልን? አንድም እመ የኃድግ ዘይት ጥመቱን ነምር ዥንጉርጉርነቱን ቢተው በጎ ሥራ መሥራት ይቻላችኊልን? እሱም አይተውም እናንተም አትመለሱም ሲል ነው፡፡ ይህን ባለው አብነት “ይክልኑ ነብር ኢትዮጵያዊ ወልጦ ኅበሪሁ” ይላል፡ የኢትዮጵያ አገልጋይ መልኩን መለወጥ ይቻለዋል? እናንተስ በጎ ሥራ መሥራት ይቻላችኊልን? አንድም “እመ

ይዋልጥ" አገልጋይ መልኩን ቢለውጥ በጎ መሥራት ይቻላችኋልን? እሱም አይለወጥ እናንተም አትሠሩ፤[83] ወቀሳ ነው።

በጎ ሥራ የማይሠሩትን ሰዎች ከኢትዮጵያዊው አገልጋይ የማይለወጠው መልኩ ጋር በማነፃፀር ሲወቅሳቸው ነው። የእሱ መልክ አይለወጥም እናንተም በጎነት የላችሁም ይላቸዋል። የእሱ እንኳን ቢለወጥ እናንተ መልካም ተግባር አትሠሩም እያለ ምን ያህል ደንዳኖች እንደሆኑ እያነፃፀረ መገሰጫ አድርጎታልል፡ የኢትዮጵያዊ መልክ ግን ጽኑ ነው፤ የትም ቢሔድ ይታወቃል ጊዜ፣ ቦታ፣ ሁኔታ፣ ገንዘብ፣ ኀዘን ደስታ የማይቀይረው ከጥንት እስከ ዛሬ የሚታወቅበት መለያ ማንነቱ ነው። ይኼ ነው ኢትዮጵያዊ፤ የነብር ዥንጉርጉርነት አይለወጥም፤ የኢትዮጵያ መልክም አይቀየርም።

ነብር ነብራዊ ማንነትን ይፈጥራል። ኢትዮጵያ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ማንነትን ትወልዳለች። ዋና ማነጻጸሪያ ግንድ ሆኖ የቀረበው ነብር ከሌሎች እንስሳት የሚለየው የራሱ ቀለም፣ የራስ ውበት፣ የራሱ ቅርጽ ባህሪ እና ስነ ልቦና አለው።

ነብር በጣም ፈጣን ነው፤ ነብር ካልነኩት አይነካም፤ ነብር በሁሉም አሸናፊ ነው፤ ነብር ቁጡ ነው፤ ነብር ሕመሙ ልዩ ነው፤ የዐይንሕመም ይጸናበታል፤ "የሰውነት መብራት ዐይን ነው" እንዲል ማቴ. 6÷22፤ በዚህ በሽታ ቢሰቃይም ከነብርነት ሙያው ንቅንቅ አይልም። ኢትዮጵያዊያንም እንደዚህ ናቸው። በመከራ አይነዋወጡም፤ በችግር አይብረከረኩም፤ ለጠላቶቻቸው ተርብ ናቸው፤ እንደግስላ ናቸው። ቁጡ ናቸው፤ ካልነኳቸውም ድንበር ተሻግረው ባሕር አልፈው ሰውን አይነኩም፤ ከነኳቸው ደግሞ አፈር አስግጠው ይሸኛሉ። ነብር አሸናፊ ነው እነሱም አሸናፊ ናቸው። ይህ የነብር ባህሪና ተፈጥሮ ነው።

መልኩን ደግሞ እንየው፤ መምህር በጽሐ ዓለሙ መልክአ ነብርን በዚህ መልኩ አቅርበውታል። ነብር መልኩ ዥንጉርጉር ነው። የነብርን ኅብረ መልክእ ለይቶ ማወቅ በጣም ከባድ ነው፤ ለምን? ቢባል ብዙ ዐይነት ኅብረ መልክእ ያለው ፍጡር ነውና። ይህ ማንነቱ ተለይቶ የሚታወቅበት የነብርነቱ መገለጫ ነው። አንድ መልክ ብቻ ያለው ድመት እንጂ ነብር የለም። ለዐይን ተመልካችም የሚያስፈራው እና የሚያስደነግጠው ይኸው ኅንብርብሬነቱ ነው። አንድ

---

[83] *ትንቢተ ኤርሚያስ። ከቀደምት አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባብና ትርጓሜው (በአንድምታ)፣ 103*

ኅብረ መልክአ አለመሆኑ እንደሆነ በሚገባ የታወቀ እና የተረዳ ሐቅ ነው፡፡ በዚህም የኢትዮጵያውያን ምሳሌ እንደሆነ ነብዩ ኤርሚያስ እንዲ ሲል ያስረዳል፡-

ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይለውጣልን? ኢትዮጵያዊያን ብዙ ኅብረ መልክእ ያላቸው፣ ብዙ ዐይነት ባህል ያላቸው፣ በብዙ ቋንቋ የሚናገሩ፣ ግን በአንድ ሃይማኖት ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑ ሕዝቦች ናቸው፡፡

ይህም ማለት እኛ እንጂ ሌላው አያስፈልግም ብሎ ማሰብ በጎጥ፣ በመንደር፣ በሐረግ ትውልድ በቋንቋ ለይቶ የእኔ ነው ያለውን ብቻ ለማኖር የሌላውን ለማጥፋት የሚጥር ሰው ኢትዮጵያን የመሰለች ነብር ድመት ሊያደርግ የሚጥር ነው፡፡[84]

ይኸ የነብር ማንነት ነው ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያውያን የተሰጠው፡፡ የማይልመጠመጥ፣ የራሱ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍ፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ሃይማኖት ያለው ሕዝብ፣ የነጻነት ዓርማ፣ የድል ፋና ወጊ ቁጣው አስበርጋጊ፣ በሰማይ በምድር ጀግና ተዋጊ ይኸ ነው ኢትዮጵያዊ ማንነት፡፡

እነዚህ መገለጫዎች ኢትዮጵያዊ ማንነት ናቸው፡፡ ማንነት (identity) በቀላል አማርኛ መለያ ቢባል ሳይሻል አይቀርም፡፡ የመታወቂያ መገለጫ ነው ቢባል አለቅጥ አቃለላችሁት አይባልም፡፡ የእነሱታቸው ዋነኛ መግለጫ ከሌለው ስብስብ የሚለያቸው እነሱ ለብቻቸው የሚጋሯቸውና ከሌላው ጋር የማይጋሯቸው የጋራነቶች ናቸው፤ መለያ ምልክቶቹ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ዘማሪያን በዝማሬ ግጥሞቻቸው ያነሱት ይህንን ኢትዮጵያዊ መልክ ነው፡፡ ዳር ድንበር መጠበቅን፣ ሰላም ወዳድነትን፣ በእምነት መጽናትን፣ በእምነት ቱባነት ውስጥ የሚተረተሩ አያሌ መልኮች አሉ፡፡ ይኸም በጋራ ታሪክ የተሸመነ ኢትዮጵያዊ አንድነት ነው፡፡ ከእነዚህ መልኮች ውስጥ የጋራ ስነ ልቦናዊ እሴት አንዱ ነው፡፡

የቋንቋና ባህል ልዩነት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የታሪክ ሂደት ያስገኛቸው አንዳንድ የጋራ እሴቶች ለምሳሌ ሀገራዊ ነጻነት እሙን ለማድረግ በጋራ የውጭ ጠላትን መመከታችን፣ ለሥርዓተ መንግሥታችን ህልውና መቀጠል ያለን የጋራ ፍላጎታችን፣ በአፍሪካ ብቸኛ የሆነ ሀገር ወለድ የግዕዝ ፊደላችን፣ በልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ቋንቋዎች ውስጥ የሚተረቱ ተረት ተቀራራቢነት፣ እንደ ክትፎና ጥሬ ሥጋ መብላት፣ ቡናን በጋራ መጠጣት፣ ለጠጅ አረቂና ጠላ

[84] *በጽሐ፣ 224፣225*

ያለን ተመሳሳይ ፍላጎት የጋራ የሆነ ኢትዮጵያዊ ስነ ልቦናችን እና የጋራ ባህላችን ይገልጻሉ፡፡ የጠይም የጥቁር ዳማ የሆነው ተመሳሳይ መልካችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትንቢተ ኤርሚያስ 13÷23 ላይ "በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይቻለዋልን" ሲል ያስቀመጠው፣ ኢትዮጵያውያን በመልክ ሳይቀር ተመሳሳነት ያለን መሆኑ፣ የአንድነታችን ተጨማሪ መገለጫ ነው፡፡[85]

የነብር መልክ የኢትዮጵያዊ መልክ ነው፤ የነብር ስነ ልቦና የኢትዮጵያውያን ስነ ልቦና ነው፡፡ ይኽ ውስጣዊ እና ውጫዊ ቀለም ልሙጥ ድመታዊ አድርባይነትን፣ ተልመጥማጭነትን፣ ተንበርካኪነትን አይመለክትም፡፡ ዝማሬዎቹም ኢትዮጵያዊነትን በነብር ውስጥ ያሳዩናል፡፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በዜማ አዋሕደው በልባችን ጽላት ይቀርጹታል፡፡ በአጥንታችን ግድግዳ ይቀርጹታል፡፡ በደማችን ቀለም ያዋሕዱታል፡፡

የራሳችን ማንነት ያለን ሕዝቦች እንደሆን በመንፈሳዊ ለዛ ይተርኩልናል፡፡ሰው ደግሞ በእምነት በኩል የተነገረውን በልቡ ውስጥ ይቋጥራል እና ሀገራችን እንድናፈቅር ራሳችን እንድናከብር ለውጫዊ ጠላት እጅ እንዳንሰጥ በማጀገን ኢትዮጵያዊ እሴትን በውስጣችን ያሠርጻሉ፡፡ ከዚህ የተነሣ አንዳችን ከአንዳችን የሚያስተሳስረንን ገመድ በማጥበቅ ሀገራዊ አንድነት ጽኑ መሠረት ላይ እንዲቆም ያደርጋሉ፡፡አብነት የሚሆኑ መዝሙራትንእንይ፡-

ኢትዮጵያ እጆቿን…

አይለውጥም የኢትዮጵያ መልክ እንደ ነበር ነው፤

በእምነት የጸና ሁሉን የሚወድ የሰላም ሰው ነው፡፡…

(መምህር ምሕረተ አብ አሰፋ 2013)

ጠብቅ እግዚአብሔር ሠራዊቷን

…

ሰንሰለት ሲጸና ለመከራ ፈርቶ፤

---

[85] *አማሃ ፣16 እና 17*

ኢትዮጵያዊ መልኩን አይቀይርም ከቶ፡፡

ድንቁን ብርሃን ያያል ወጥቶ ከጨለማ፤

በመንገዱ ሁሉ አዳኝ ቀኝህ ቀድማ፡፡

…

(ሊቀ መዘምራን ቴዎድሮስ ዮሴፍ 2010 ዓ.ም.)

ሰላም ለኢትዮጵያ

…

ለዓለማት ሁሉ ኢትዮጵያ ተስፋ ነሽ፤

አይደለሽም ብዙ በቁጥር አንዲት ነሽ፡፡

ዥንጉርጉርነቱን ነብር አይቀይርም፤

ኢትዮጵያዊ መልኩን ሊለውጥ አይችልም፡፡

ሰላም ለኢትዮጵያ ሰላም ለሀገራችን

(ሊቀ መዘምራን ቴዎድሮስ ዮሴፍ 2011 ዓ.ም.)

### *3.4.5.3. ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ገበዝነት*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን መዝሙራት ውስጥ ተደጋግመው ከሚታዩ እና ከሚነሡ የዝማሬ ግጥሞች መካከል ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ገበዝነት በዋነኛነት የሚጠቀስ ማሳያ ነው፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ የኢትዮጵያ ገበዝ ነው፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ የኢትዮጵያ ጠባቂ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ገበዝ፣ ዳር፣ ዳርቻ፣ ጠረፍ፣ ብርቱ ጠባቂ፣ ዘበኛ ማለት ነው፡፡[86]

---

[86] *ኪዳነ ወልድ፣ 29*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አማኞች ራሳቸውን እና ሀገራቸውን ለእግዚአብሔር፣ ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያም እንዲሁም ለቅዱሳን አደራ፣ ርስት ፣ ዐሥራት፣ ገበዝ አድርገው ሰጥተዋል፡፡ ዝማሬያቸው የሚገልጠው ይህንን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ትውልዱ ከኢትዮጵያ ውጭ ነው፡፡

ጊዮርጊስ ማለት ብሩህ ኮከብ ወይም ፀሐይ ማለት ነው፡፡ ሀገሩ ልዳ ሲሆን አባቱ ዞረንቶስ /አንስጣስዮስ/ ሲባል እናቱ ቴዎብስታ/ አቅሌስያ ትባላለች፡፡ ማርታ እና እስያ የሚባሉ እኅቶች አሉት፡፡[87] ሰማዕቱ ጊዮርጊስ የሰማዕታት አለቃ ነው፡፡ ክቡሩ ሁሉ ከሰማዕታት ይልቃል፡፡ ጣዖት ከሚያመልከው ከፋርሱ ንጉሥ ከዱድያኖስ ጋር ባደረገው ተጋድሎ ብዙ መከራን የተቀበለ፤ እግዚአብሔርም ስለተጋድሎው አክሊል ያወረደለትና በስሙ ቤተ ክርስቲያን ለሚያሠሩ፣ ለሚማጸኑ፣ ዝክሩን ለሚዘክሩ ብዙ ቃል ኪዳን የተሰጠው ሰማዕት ነው፡፡

እንደ ክብረ ነገሥት መረጃ የቅዱስ ጊዮርጊስ ጽላት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በዐፄ ዐምደጽዮን በ13ኛው ክፍለ ዘመን (1307-1336 ዓ.ም.) ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን የኦርቶዶክስ አማኞችም ቤተ ክርስቲያን ሲያንጹ፣ በቃል ኪዳኑ ሲማጸኑ ኖረዋል፡፡ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ኢትዮጵያውያንን የተዋሕዶ አማኞች በበዓሉ ያስተሳሰረ ያገናኘ ቅዱስ ነው፡፡ ከዚህ ተሻግሮ ኢትዮጵያን፣ ግብጽን፣ ሶርያን፣ ሩሲያን እና ሰርቢያን የሚያስተሳስራቸው ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው፡፡[88]

ይህ አማኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢነት እና ጠባቂነት ከማመኑ የተነሣ ሀገሩን ሲወር ሕዝቡን ለባርነት ሊዳርግ የመጣውን የጣሊያን ጦር ድል ያደረገው ቅዱስ ጊዮርጊስን ይዞ እንደሆነ ያምናል፡፡ በዚያ ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ የዐድዋ ጦርነት ላይ ያላሳፈራቸውን እና ለድል ያበቃቸውን ጊዮርጊስን ገበዛችን ነህ ጠባቂያችን ነህ ይሉታል፡፡ ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር የሀገሪቱን መሬት በረገጠ ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ የማርያምን ስም ጠርተው ዘማቹን ሰብስበዋል፡፡ የፍጻሜው ጦርነትም ዐድዋ ላይ ነው፡፡ የዐድዋ ጦርነት ከመጀመሩ ከአምስት ወር በፊት ጥቅምት ሁለት ከቅዱስ ጊዮርጊስ ዕለት ጋር ተያይዞ የሚነሣውን የጊዮርጊስ ተአምር እንዲህ ተገልጿል፦ በዚህም ዘመን በጥቅምት ሁለት ቀን ከአዲስ አበባ ከተማ ተነሥተው ወደ ትግሬ ዘመቻ ተጓዙ፡፡ በዚያም ቀን እንደቀስተ ደመና ያለ እሳት

[87] *ገድለ ጊዮርጊስ፣ 28፡፡*
[88] *ቃለ አብ፣ 6፣*

የሚመስል ከሰማይ ላይ በምዕራብ በኩል ሲሔድ በአራት ሰዓት ታዬ። ጢሱም ሳይጠፋ ብዙ ቆየ። የጢሱም መልክ አረንጓዴ ይመስል ነበር።

ድምጹም እንደ መድፍ ተኩስ ሆኖ ተሰማ። ንጉሡ እና ሕዝቡ አማኝ ስለነበሩ ወደ ዐድዋ ጦርነት ሲሔዱ አብረው ከተጓዙት ታቦታት አንዱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነበር።[89] አዲስ አበባ የሚገኘውን የአራዳውን ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የሚዘክረው ቤተ መዘክሩ የሚለው መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡- ዐፄ ምኒልክ ወደዚህ ቤተ ክርስቲያን መጥተው ጸሎት አድርሰው በድል ቢመለሱ ዋናውን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ሊሠሩ ስዕለት ተስለው ታቦቱን ይዘው ዘመቱ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት በዐድዋ ጦርነት ብቻ ሳይኾን በጥቅምት 1909 ዓ.ም.ከራስ ተፈሪ ጋር ወደ ሰገሌ ጦርነት በ1928 ዓ.ም. ደግሞ ወደ ማይጨው ጦርነት ዘምቷል።[90] የጊዮርጊስ ታቦት ጦርነት ድል ለማድረግ፣ ዳር ድንበር ለመጠበቅ ከሊቀ ጳጳሱ፣ ከመነኮሳቱ፣ ከካህናቱ፣ ከነገሥታቱ፣ ከወታደሩ ጋር ዘምቷል። እነሱም ድል አድርገዋል። በዚህም የእኛም ጠባቂ የኢትዮጵያ ገበዝ ነህ ይሉታል።

የዐድዋ ድል የአፍሪካ ኩራት፣ የጥቁር ሕዝቦች ክብር፣ የነጻነት ቀንዲል፣ የኢትዮጵያውያን ማንነት መታያ፣ የእኩልነት ሐውልት ነው። ይኼ ድል ሲነሣ፣ ጀግኖች አባቶቻችን ይነሣሉ። እነሱ ሲታወሱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ይዘከራል። ጦርነቱ የተደረገው በጊዮርጊስ ዕለት ነው። የተቋጨውም በዕለተ ቀኑ ነው። 1988 የካቲት 23፤ ታሪክ የሚነግረንም አቡነ ማቴዎስ የማርያምን ታቦት አስይዘው ከቀሳውስት እና ከመነኮሳት ጋር ነው የጊዮርጊስን ስብሐተ ፍቁር እያዜሙ ሲከተሉ ዜማው ሲያልቅ ድሉ ተፈፀመ።[91] የጊዮርጊስን ጽላት ይዘው፣ በጊዮርጊስ ዕለት፣ የጊዮርጊስ ስብሐተ ፍቁር እየደገሙ አሸነፉ።

ይኼን እየዘከሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ዘማሪያን ጊዮርጊስን የኢትዮጵያ ገበዝ ነህ ይሉታል። የኢትዮጵያ ጠበቂ፣ ተራዳዒ፣ ዋስ፣ ጠበቃ ነህ ይሉታል። በጦርነቱ ከእኛ ጋር እንደ ነበርክ አሁንም በኑሯችን፣ በጤናችን፣ በመውጣት መግባታችን ከእኛ ጋር ሁን፣ ፈጥነህ

---

*[89] ገብረ ሥላሴ፣ 230።*
*[90] ቃለ አብ፣ 11*

*[91] ተክለ ጻዲቅ፣ 368*

ድረስልን፣ ታደገን፡፡ ከመከራ አውጣን፣ ባርከን ይሉታል፡፡ የጊዮርጊስን ውለታ እያሰቡ ዛሬም ይጠሩታል፡፡ ትናንት አባቶቻቸው ያደረገላቸውን ገድል ዛሬም ለልጆቻቸው በዜማና ግጥም ይነግሯቸዋል፡፡ ይኼም አማኙን ትውልድ የሚረዳን ኃይል አለ የሚል በራስ መተማመን መንፈስን ይሠራላቸዋል፡፡

የትኛውም ምድራዊ ጦርነት ላይ ቢሳተፉ የማሸነፍ ርግጠኝነታቸውን ጽኑ ዐለት ይቀርጽላቸዋል፡፡ አንድ የሚረዳኝ ኃይል አለ ብሎ ካመነ ያሸንፋል፡፡ ጦርነት ሞራል፣ እምነት ስነ ልቦና ነው፡፡ ፈጣሪያቸውን እንዲፈሩ፣ ሰማዕቱ ጊዮርጊስን እንዲያከብሩ ያደርጋል፡፡ ይኼም ለሌላ ድል የመሸጋገሪያ ምክንያት በመሆን ያገለግላል፡፡ ዘማሪያኑ ጊዮርጊስን ከግብዝናው ጋር እንዲህ አንሥተውታል፡-

መራራው ሕይወቴ

ሀገርን አይተውም ያለአንዳች ጻድቅ፤

ሥውሩም ይታያል አይኾንም ድብቅ፡፡

የአባቶቼ ርስት ስሟ ቶኔቶር፤

ገበዟ ጊዮርጊስ ነው ዐሥራት ድንግል፡፡

(ዘማሪ ዲ/ን እንግዳወርቅ በቀለ 1997፣ 4፡11)

የኢትዮጵያ ገበዝ

የኢትዮጵያ ገበዝ ቅዱስ ጊዮርጊስ፤

ፈጥነህ ቶሎና በፈረስ፡፡

ጠላት ሰልጥኖ ዙሪያችን ሰፍሯል፤

የዐድዋን ድል ዛሬም ናፍቀናል፡፡

ቅጥሯ ሲደፈር የሀገራችን፤

ድረስ ጊዮርጊስ ትምክሕታችን፡፡

ጽላትህ ይውጣ ከመቅደስህ፤

ከእኛ ጋር ይዝመት ቅዱስ ስምህ።

(ዘማሪት ፋንቱ ወልዴ፣ 2011 ዓ.ም.)

ጊዮርጊስ

ጊዮርጊስ/3/ ነአ በፈረስ/2/

ኃያል በጉልበቱ ሲታበይ ሲመካ፤

የእግዚአብሔር እጅ ቅርበት ለኢትዮጵያ።

ታቦተ ጊዮርጊስ የአምላክ ቃል ኪዳን፤

የወራሪ መቅሠፍት ለሀገራችን መድኀን። . .

(ዘማሪ ዲ/ን ልዑል ሰገድ ጌታቸው፣ ቁ.5 2006)

# ምዕራፍ አራት

## 4.1. ማጠቃለያ

ይኽ ጥናት ትኩረቱን ያደረገው በአራቱ ሃይማኖቶች ዝማሬዎች ላይ ነው። እነሱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የእስልምና፣ የካቶሊክ እና የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች ናቸው። እነዚህ ሃይማኖቶች በመላው ዓለም የሚገኙ ሲሆን ጥናቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት ላይ ብቻ ያተኮረ ነው።

መዝሙሮቹ የተሠሩበት ቋንቋ አማርኛ ሲሆን የጥናቱ ዘመነ ክልል ከ1983-2013 የተሠሩት ላይ ብቻ ትኩረት አድርጓል። ጥናቱ ዓላማ አድርጎ የተነሣው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በእነዚህ ሃይማኖቶች የመዝሙራት ግጥሞች ውስጥ እንዴት እንደቀረቡ መፈተሽ በመሆኑ ጉዳዩን የተመለከቱ ዝማሬዎች ተሰብስበዋል።

ጥናቱ ባካለለው በሠላሳ ዓመት ውስጥ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን 23 /ሃያ ሦስት/መዝሙራት ተሰብስበዋል። ከእስልምና እምነት ሙነሽዶች 7 /ሰባት/ ነሽዳዎችና መንዙማዎች፣ ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን ዘንድ 12 /ዐሥራ ሁለት/ መዝሙራት፣ ከፕሮቴስታንት እምነት ወይም ከወንጌላዊያን አማኞች ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን 7 /ሰባት/ መዝሙራት/ ተሰብስበዋል።

እነዚህ መዝሙራት የየሃይማኖቶቹ ዘማሪያን በግልም በጋራም የዘመሯቸው ናቸው። ከጥናቱ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው የመዝሙር፣ የነሺዳ እና የመንዙማ ግጥሞችን በዓላማ ተኮር የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ለመሰብሰብ በሽዎች የሚቆጠሩ ዝማሬዎችን ማዳመጥ ግድ ብሏል።

የአራቱ ሃይማኖቶች ዘማሪያን በመዝሙሮቻቸው የምእመናኑን መሻትና ብሶት፣ ሕዝባቸው እና ሀገራቸው ከፈጣሪያቸው ጋር ያላቸውን የግንኙነት ልስላሴና ሽክረት በዘመን መንፈስ ውስጥ በልዩ ልዩ ድምፀት ያለ ፍርሃት በጥብዐት ገልጸዋል።

መዝሙሮቹ፣ ነሺዳዎቹ፣ መንዙማዎቹ በሁለቱም ሥርዓተ መንግሥት ጊዜ የቀረቡ በመሆናቸው የየዘመኑን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ክሥተቶችን ምን ነበርነትን እና ምን አለነትን ያሳዩ ጠቋሚ ቀስቶች ናቸው።

## 4.2. የጥናቱ ግኝት

ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃያ ሦስት /23/ ከኢትዮጵያ እስልምና ሰባት /7/፣ ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዐሥራ ሁለት/12/፣ ከኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት (ወንጌላዊያን አማኞች) ሰባት /7/ በድምሩ 49 መዝሙራት በሠላሳ ዓመት የጊዜ ክልል ውስጥ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያዊነትን አስመልክቶ የተሠሩ መዝሙራት፣ ነሺዳዎች እና መንዙማች ናቸው፡፡

የጥናቱ ማእከል የኾኑት ሃይማኖቶች ዘማሪያን በመዝሙሮቻቸው ውስጥ ፖለቲካዊ ድምጸት ያላቸውን መዝሙራት በሁለቱም ሥርዓተ መንግሥት ማለትም በኢህአዴግ እና በብልጽግና ጊዜ ያዩትን፣ የሰሙትን እውነት ለአማኞቻቸው አድርሰዋል፡፡ ዘረኝነትን ኰንነዋል፣ አንድነትን ሰብከዋል፤ ሥርዓቶቹ ከእኩይ ድርጊቶቻቸው እንዲታቀቡ ሐይሰዋል፤ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት የጋራ ጠላቶች የሚሏቸውን ስደት፣ ሞት፣ በሽታ፣ ረኃብ፣ ጦርነት ለይተው ከምድሯ እንዲወገዱ ተማጽነዋል፡፡ የእነዚህ ሳንካዎች መንስኤ የሆኑትን መንግሥታትና መሪዎቻቸው ወደ ሕዝባቸው፣ ወደ ልባቸው፣ ወደ ፈጣሪያቸው እንዲመለሱ ተማጽነዋል፣ ገሥጸዋል፡፡

በሀገራዊ ድምፀታቸው ውስጥ ትናንትን በጽኑ ይናፍቃሉ፡፡ የዛሬዋን ኢትዮጵያ በትናንት መነጽር እያዩ ተመለሽ ብለዋል፡፡ ይኼም በዛሬው ሕይወት እና ኑሮ ምን ያህል እንደተማረሩ ያሳየ ነው፡፡ ሀገረ ታሪክን ዘክረዋል፡፡ ቀዳምት የኢትዮጵያ ጀግኖችን በመጥራት እነሱን የመሰለ ሰው እንዲፈጠር የሚሹ ኾነው ተገኝተዋል፡፡

ምእመናን የሀገር ፍቅር እንዲኖራቸው አብነቶችን እየጠሩ በአማኙ ልብ ውስጥ የኢትዮጵያ ፍቅር እንዲተከል ሠርተዋል፡፡ ሌብነትን፣ ጉቦን፣ የሥነምግባር ድቀትን በጽኑ ኰንነዋል፡፡ በሕዝብ እና አሕዛብ በማኅበረሰብ እና በግለሰብ መካከል ያለ ቁርሾ ብቸኛው ማጠቢያ እና መንቀያ መንገድ ይቅርታ ነው ብለዋል፡፡

በአራቱ ሃይማኖቶች ዝማሬዎች ውስጥ እርስ በእርስ ተደጋግመው የመጡ እና የታዩ ወይም በአንዱ ሃይማኖት የሌሉ በሌላኛው ያሉ ያሉትም የራሱ ሃይማኖቱ መልክ እስኪመስሉ ተደጋግመው የመጡ መባያዎች መታያዎች አሉ፡፡

አራቱም ኢትዮጵያን ሀገረ ፈጣሪ ናት፤ የቃል ኪዳን ምድር ናት፣ ያለፈውን መልካም ነገር ናፋቂ ናት ማለታቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ኦርቶዶክስ እና እስልምና ውስጥ ያሉ ዘማሪያን እና ሙነሽዶች ኢትዮጵያ በፈጣሪና በወዳጆቹ የተመረጠች የተወደደች የተለየች ምድር መኾኗን፤ በክርስትናውም በእስልምናውም የታወቀች የእንግዶች ማረፊያ ወደብ እንግዳ ተቀባይ ሀገር አድርው ማቅረባቸውን በጥናቱ ታይቷል፡፡ አሁን ግን ያች እንግዳ የምትቀበል ምድር የራሷን ዜጎች ውጡልኝ እያለች እያፈናቀለች ትገኛለች የሚለውን መራር ሐቅ በአጽንዖት ተናግረዋል፡፡

በኦርቶዶክስ፣ በካቶሊክ፣ በፕሮቴስታንት መዝሙራት እጅ መዘርጋት የሚለው መባያ ተደጋግሞ ታይቷል፡፡ ኢትዮጵያ እና ሕዝቦቿ ወደ ፈጣሪያቸው እጆቻቸው የተዘረጉ ናቸው፡፡ ይኼም ከፈጣሪ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተዘረጋ እና በማይታጠፍ እጅ ወክለው ማቅረባቸው ታይቷል፡፡

በኦርቶዶክስና በካቶሊክ ብቻ የሚገኝ መባያ እንዳለ ተረጋግጧል፡፡ እሱም ድንግል ማርያምና ርስት የሚል ነው፡፡ የሁለቱም ሃይማኖቶች ዘማሪያን አስተምህሯቸውን መሠረት አድርገው ኢትዮጵያን ለድንግል ማርያም በርስትነት ሲሰጡ ተመልክቷል፡፡ ይኸም ሀገሪቱ ምን ያኽል በአምላካቸው እናት በጸሎት እና ምልጃ እንደምትጠበቅ ያሳየ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪያን መዝሙራት ደሴት፣ ነብርነት፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ገበዝነት የተሰኙ መባያዎች ተደጋግመው ሲከሠቱ ተስተውለዋል፡፡ ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት ብለዋል፡፡ ደሴትነቷ ግን አካባቢውን የሚገልጽ እንጂ ሀገሪቱን የአንድ ሃይማኖት መናኻሪያ ብቻ ናት የሚል እንዳልሆነ በዝማሬያቸው ተረጋግጧል፡፡

ኢትዮጵያን ለቅዱስ ጊዮርጊስ በገበዝነት አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ ይኸንንም ከዐድዋ ጦርነት ድል ጀርባ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢነት ለምስክርነት ይጠራሉ፤ ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን አይለውጥም የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት የጋራ መልኮች እሴቶች፣ ማንነቶች ተሸምኖ መቅረቡ ታይቷል፡፡

በአጠቃላይ የሁሉም ሃይማኖቶች ዘማሪያን ድምጸቱ ይምረርም ይለስልስም፣ የዘማሪያኑ እና የዝማሬዎቻቸው ቁጥር ይብዛም ይነስም ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ጉዳያቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የኢትዮጵያና የሕዝቦቿ ነገር ግድ እንደሚላቸው ተመልክቷል፡፡

ዘማሪያኑ ከሕዝቡ አብራክ ከምእመናን ማሕፀን የወጡ በመሆናቸው መዝሙሮቹም የበቀሉባቸው የአማኙ ማኅበረሰብ ቀለሞች መታያ ገጾች ናቸው፡፡ ግጥሞቹ የየዘመኑን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ያሳዩ ናቸው፡፡

ከደርግ መውደቅ ማግስት የነበረው ዘረኝነት፣ ረኃብ፣ ጦርነት፣ በሽታ፣ ስደት ከኢህአዴግ ውድቀት በኋላ እንደቀጠለ መዝሙሮቹ ተናግረዋል፡፡ ሀገሪቱ ተስፋዋ በፈጣሪ ላይ እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ እንደማትጠፋም ማረጋገጫ ሰጥተዋል፡፡

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት በጽኑ መሠረት ላይ የተጣለ ጥልቅ ምሥጢር ነው፡፡ የዘማሪያኑ ኢትዮጵያ አፈር ላይ ብቻ ያለች አይደለችም፤ ይልቁንም በሰማያዊው ሥፍራ ልዩ ጥበቃ ያላት ኃይለ አርያም የሚከልላት ናት፡፡

መዝሙሮቹ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ለመፍጠር ቀን ከሌት እንደሚተጉ ተስተውሏል፡፡ የጋራ ጠላት ፈልገው፣ የጋራ እሴትና የአንድነት ገመድ ለመሸመን በኢትዮጵያዊነት ጉድጓድ ውስጥ ድርና ማግ ሲፈትሉ መታየታቸው ጥናቱ ተመልክቷል፡፡

ዘረኝነትን ለመንቀል፡፡ በጉቦ የበሰበሰውን ለማውገዝ ከፊት የተሰለፉ ናቸው፡፡ በምግባር ብልሹነት አረንቋ የዘቀጠውን ሰው ሲኰንኑ መታየታቸው ጥናቱ አረጋግጧል፤ ኢትዮጵያን በአማኙ ልብ ውስጥ ለመትከል ታትረዋል፡፡

የጊዜና የቦታ ድልድይ በመዘርጋት በምርጦቹ እና በጀግኖቹ በኩል የትናንቷን ኢትዮጵያን ይቃትታሉ፤ ከዘመናቸው ያልመነኑ፤ የዘመናቸውን መንፈስ ያረገዙ፣ ሽንፈት የማይወዱ በሀገራቸው ከነቡጉሯም ቢሆን የሚኮሩ በፈጣሪያቸው የሚመኩ ናቸው፡፡

መዝሙሮቹ፣ ነሺዳዎቹ፣ መንዙማዎቹ ክፉ ምግባርን ይጸየፋሉ፣ ተስፋ የቆረጠውን ያጽናናሉ፣ የልብ መረጋጋት እንዲገኝ ያደርጋሉ፡፡ እርቅ እንዲፈጠር ይለፋሉ፤ ችግር ጉስቁልና ከምድሪቱ እንዲወገድ ይለምናሉ፤ መንግሥታት እና መሪዎች ሕዝቦቻቸውንና ፈጣሪያቸውን እንዲያዳመምጡና እንዲፈሩ ይመክራሉ፡፡

ሃይማኖተኛ ሕዝብና ሀገር ባለበት ሁኔታ ይኼ ሁሉ ዘረኝነት፣ ሰላም ማጣት፣ ጉስቁልና፣ ቂም በቀል፣ ረኃብ፣ ጦርነት፣ ስደት፣ ወዘተ ለምን የኢትዮጵያ መልኮች ኾኑ ቢባል ፣ አማኙ

ማኅበረሰብ በሃይማኖቱ ውስጥ እንዳለ እንጂ ሃይማኖቱ በአማኙ ማኅበረሰብ ልብ ውስጥ በሚገባ እንደሌለ ጥናቱ ያሳያል፡፡

የሃይማኖቶቹ መዝሙራት የተረጋጋ ማኅበረሰብ ተፈጥሮ፤ ሀገራዊ አንድነት ጠንክሮ፤ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ በሰላም፣ በደስታ፣ በፍቅር፣ እንዲኖሩ በማድረግ በኩል ያላቸውን ተጽዕኖ ፈጣሪነት ተጠቅመው ለሀገር እና ለሕዝብ ያበረከቱትና የሚያበረክቱት አስተዋጽ*ዖ* እንዳለ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

## 4.3. የይሁንታ ሐሳብ

- በየሃይማኖቶቹ ውስጥ ያሉ ዘማሪያን እና ሙነሽዶች አገልጋዮች የተጽእኖ ፈጣሪነታችሁ መጠን ኃያል በመሆኑ በእያንዳንዱ አልበማቸው ውስጥ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን በተመለከተ አንድ ዝማሬ፣ ነሺዳ፣ መንዙማ ቢያወጡ፤
- ተመራማሪዎች ለዚህ ጥናት የተሰበሰቡት መዝሙራት የማኅበረሰቡን ሁለንተናዊ መልክ ያቀፉ መሆኑን ተረድተው ከተለያየ ዲሲፕሊን አንጻር ቢያጠኗቸው፤
- መንግሥት፣ የሚመራው ሕዝብ አማኝ እና በእምነቱ ድርድር የማያውቅ መሆኑን ይረዳል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የየሃይማኖቱ አገልጋይ ዘማሪያን መዝሙራት በሥራና በዕረፍት ጊዜ፣ በአዘቦትና በበዓላት ቀናት፣ በአምልኮና ከአምልኮ ውጭ በሆኑ ቦታዎች የሚደመጡ ናቸው፡፡ በመንፈሳዊ ጥበብ እያዋዙ በምእመናን ልብ ውስጥ መልእክቶችን በማስረጽ ረገድ የሚያህላቸው እንደሌለ ተገንዝቦ ፖሊሲ ሲያወጣ ቢያሳትፉቸው፣ በገንዘብ፣ በቁስ፣ ወዘተ ቢያግዛቸው ኢትዮጵያዊነትን በጽኑ ዐለት ላይ ለመትከል ዐይነተኛ መሣሪያ ይሆናል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


ሀሰን ታጁ (ትርጉም)። አር-ረሒቁ-ል መኽቱም። የነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) የሕይወት ታሪክ በሸኽ ሶፍዩ ረሕማን አልሙባረከ ፉሪ። አዲስ አበባ፤ ነጃሺ ማተሚያ ቤት። 2009 ዓ.ም።

………………………።: ኢስላም። አዲስ አበባ፤ ነጃሺ ማተሚያ ቤት። 2002።

ሙሐመድ ዓሊ (ቡርሃን) ኢትዮጵያዊያን ሶሐቦች እና ሌሎችም። አዲስ አበባ፣ አል-ተውባ ፕሪንቲንግ ኢንተርፕራይዝ። 2008 ዓ.ም. ።

ማኅበረ ቅዱሳን። የአማርኛ መዝሙራት ድክመቶችና ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው?። አዲስ አበባ፣ ፋርኢስት ማተሚያ ቤት፣ 2003።

……………..። ገድለ ጊዮርጊስ፣ አዲስ አበባ። ማኅበረ ቅዱሳን ማተሚያ ቤት፣ 2011 ዓ.ም.።

ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል፣ (ቀሲስ ዶ/ር) የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ በምድር ላይ (ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ)። አዲስ አበባ 2005 ዓ.ም.

ሥርግው ገላው (ተርጓሚ፣ አዘጋጅና አርታዒ)። ክብረ ነገሥት ግዕዝና አማርኛ። የኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 19993 ዓ.ም.

ሰለሞን ተሾመ። 2009 ዓ. ም ፎክሎር ምንነቱ የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፤ ፋር ኢስት ትሬዱንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር፤ አዱስ አበባ።

ሰሎሞን ወንድሙ መታፈሪያ (መ/ር)። የአማርኛ መዝሙራት እና ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች። አዲስ አበባ፣ ጆጃው አታሚዎች፣ 2010ዓ.ም. ።

ሰሎሞን ዮሐንስ (ዲ/ን)። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት። አዲስ አበባ፣ ፋርኢስት ትሬዲንግ፣ 2010።

ቃለ አብ ናሁ ሰናይ፤ ቤተ መዘክሩ /The museum/ 2012፣ ሚሌኒየም ማተሚያ ቤት። አዲስ አበባ።

በጽሐ ዓለሙ (መ/ር)። ምዕላደ ጥበብ። ከኑ ማተሚያ ቤት፣ 2011ዓ.ም›።

በአምላኩ አስማረ። ሥነ ምግባራዊ ሂስ መጣጥፋ። አዲስ አበባ። ጃጃዎ ማተሚያ ቤት። 2015 ማርች 27፣

ባህሩ ዘርጋው። ዘርጋው የአማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣1994።

ብርሃኑ ጉበና፡፡ ዓምደ ሃይማኖት፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች፣ 2003፣ ዓ.ም.፡፡

ኃይለ ማርያም መለሰ (አባ ዶ/ር)፡፡ ታሪክ፣ ትምህርት እና ሥልጣኔ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ታሪክ ማተሚያ ቤት፡፡ 2013፡፡

ተሾመ ብርሃኑ፡፡ ከ1983 እስከ 1985 ዓ.ም. የመንግሥት ሽግግር ወቅት፤ የተዘፈኑ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ድምፀቶች (በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች ማሳያ)፡፡ 2015 ዓ.ም." (ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ)

ተክለ ማርያም ፋንታዬ፡፡ ጥንተ ጥበብ ዘሥነ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ስ ማተሚያ ቤት፣ 1965 ዓ.ም፡፡

ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ፤ ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት፡፡ አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡ 1983፡፡

ታሪኩ ፋንታዬ፡፡ አማርኛ ሁሉ ለሁሉ፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት፣ 2001 ዓ.ም.፡፡

ቴዎድሮስ በየነ፡፡ ኅብረ ኢትዮጵያ ቅጽ ፩፡፡ አዲስ አበባ፣ ግራፊክ ፕሪንተርስ፣ 2008 ዓ.ም. ፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ በይነዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ.፣ 2001 ዓ.ም.፡፡

ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፡፡ ትንቢተ ኤርሚያስ፡፡ ከቀደምት አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ ነጻሽ ማተሚያ ቤት፣ ቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም፡፡ አዲስ አበባ፡፡ 1961 ዓ.ል. ፡፡

ታየ ቦጋለ አረጋ (ኢልመ ደሱ ኦዳ)፡፡ መራራ እውነት በኢትዮጵያ ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፣ግራፊክ አታሚዎች፣2011ዓ.ም.፡፡

አቤል ጋሼ፡፡ ኢትዮጵያና መንፈሳዊ እሴቶች በኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ውስጥ፣" በሕግ አምላክ" ሽምግልናና ይቅርታ፣፡፡አዲስ አበባ፡፡ ተስፋ ማተሚያ ድርጅት፡፡ 2009 ዓ.ም.፡፡

አማሃ ዳኜው ተሰማ፡፡ ሀገራዊ ብሔርተኝነት እና ዘውጋዊ ብሔርተኝነት በኢትዮጵያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ግራፊክ አሳታሚ፤ 2012 ዓም.፡፡

አብዱረሂም አብዱራህማን (ዑስታዝ)፡፡ የአረብኛ እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ነጃሺ ማተሚያ ቤት፡፡ 1999፡፡

አዳም ከሚል፡፡ ሶሐቦች በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ዙሪያ፣ አዲስ አበባ፣ መርዋ ፕሪንተርስ አታሚዎች፣ 2008 ዓ.ል.፡፡

ኢድሪስ ሙሐመድ፣ ኢትዮጵያና እስልምና (ትርጉም)፡፡ አዲስ አበባ፣ ነጃሽ ማተሚያ ቤት፡፡ 1999 ዓ.ም. ፡፡

ኤርሚያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ (ንቡረ ዕድ)፡፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፡፡ ቼምበር ማተሚያ ቤት፣ 1998 ዓ.ም.፡፡

እሸቱ አለማየሁ (መጋቤ ሐዲስ)፣ ርጢን፡፡ አዲስ አበባ፣ ጃጃዎ ማተሚያ ቤት፤ 2010፡፡

ከበደ ሚካኤል፡፡ የዓለም ታሪክ 1ኛ መጽሐፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ ወገግታ አሳታሚ፣ 1952 ዓ.ም.፡፡

……………..፡፡ ተረትና ምሳሌ ፩ኛ መጽሐፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት፣ 1999 ዓ.ም.፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፡፡ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ሐዲስ መዝገበ ቃላት፡፡ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948፡፡

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡ ማርክሲዝም ሌኒንዝም መዝገብ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ 1978፡፡

………………………፡፡ አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፡፡ 1993፡፡

ካህሳይ ገብረ እግዚአብሔር፡፡ ባህልና ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ፡፡ አዲስ አበባ፣ 2010 ዓ.ም፡፡

አደም ካሚል ፋሪስ፡፡ ሐበሾች በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዙሪያ፡፡ 2008 ዓ.ል፡፡ ነጃሺ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም.፡፡

……………………………………..፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይና ሐዲስ ኪዳን፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡ 1980 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡፡ አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም.፡፡

…………………………………………………:: <u>አማርኛ መዝገበ ቃላት፣</u> አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አሳታሚ ድርጅት:: አዲስ አበባ:: 1993::

የሱፍ ያሲን:: <u>ኢትዮጵያዊነት፤ አሰባሳቢ ማንነት በአንድ ሀገር ልጅነት::</u> አዲስ አበባ፣ ሲና ማተሚያ:: 2009 ዓ.ም.::

ዮሐንስ ገ/መስቀል (ሌ/ጀኔራል):: <u>የኢትዮጵያና ኤርትራ ጦርነት ጦስና ትኩረት ያጣው በድንበር አካባቢ የሚኖር የትግራይና የአፋር ሕዝብ መከራ::</u> አዲስ አበባ:: ሰኔ 2010::

ያሬድ አደመ (ዲ/ን):: <u>መዝሙረ ተዋሕዶ:: ዘኦርቶዶክስ (ቁጥር 1)::</u> አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ 1994 ዓ.ም. ::

------------------:: <u>መዝሙረ ተዋሕዶ:: ዘኦርቶዶክስ (ቁጥር 2)::</u> አዲስአበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ 1996ዓ.ም. ::

-------------------:: <u>መዝሙረ ተዋሕዶ:: ዘኦርቶዶክስ (ቁጥር 3)::</u> አዲስ አበባ፣ አፍሮ ማተሚያ ድርጅት፣ 1998ዓ.ም. ::

--------------------:: <u>መዝሙረ ተዋሕዶ:: ዘኦርቶዶክስ (ቁጥር 4)::</u> አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ 2000 ዓ.ም. ::

ያሬድ ጥላሁን:: <u>እግዚአብሔርን መምሰል::</u> አዲስ አበባ፣ ርኆቦት ማተሚያ ቤት፣ 2000 ዓ.ም.

ይኩኖ አምላክ ታምሩ:: ኢየሱስ ክርስቶስ በኢትዮጵያ:: አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም.::

ዘመድኩን በቀለ:: <u>ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ የ54 ጥንታዊያን ገዳማት እና አድባራት ታሪክ ክፍል አንድ::</u> አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1992ዓ.ም.::

ዘካርያስ አምደ ብርሃን:: <u>እምዬ ሚኒሊክ ስብዕና እና ሥራዎቻቸው::</u> አዲስ አበባ፣ ጦቢያ መጻሕፍት መደብር፣ 2012 ዓ.ም.::

ዘሪሁን አስፋው:: <u>የስነ ጽሑፍ መሠረታውያን::</u> አዲስ አበባ:: ንግድ ማተሚያ ድርጅት:: 2009::

ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ (ጸሐፌ ትእዛዝ):: <u>ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ::</u> ብራና ሰላም ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ:: 1959 ዓ.ም::

ጌታቸው ደስታ:: <u>ቱሪዝም በኢትዮጵያ::</u> አዲስ አበባ:: 1999 ዓ.ም. ::

ጎርጎርዮስ (አባ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ):: <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ::</u> አዲስ አበባ:: 1978 ዓም

……………………………………:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ:: አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም. ::

ዳንኤል ክብረት (ዲ/ን)፣ ራእይ ዮሐንስ:: ክልስ እትም፣አዲስ አበባ፣ 2010 ዓ.ም›::

……………………..:: (መሐዘ ጥበባት ዲ/ን):: የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን ኅትመት አገልግሎት፣ 2012 ዓ.ም.::

……………………..:: የሰርቆ አደሮች ስብሰባ:: አዲስ አበባ፣ አግዮስ ኅትመትና ጠቅላላ ንግድ፣2009 ዓ.ም. ::

ጳውሎስ ኞኞ:: አጤ ሚኒልክ:: አዲስ አበባ፣ ማንኩሳ አሳታሚ፣2009ዓ.ም.::

ጠና ደዎ:: ሰው፣ ግብረ ገብና ስነ-ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች:: አዲስአበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2008 ዓ.ም.::

ፈቃደ አዘዘ:: የስነ ቃል መማሪያ:: አዲስ አበባ:: አልፋ አሳታሚዎች፣ 1991 ዓ.ም.::

ፋንታሁን እንግዳ:: ሥነ ጽሑፋዊ ሙዳዬ ቃላት ከነማብራሪያቸው፣:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት:: 2003 ዓ.ም.::

ከመጽሔት የተወሰደ

መጽሔተ አሚን ዘደብረ አሚን:: ልዩ እትም፣ 2012:: ነሐሴ 23:: ሰምና ወርቅ ፪ኛ ዓመት:: ታዛ መጽሔት:: መንዙማና ኪነ ጥበብ:: 2013::

ድርቅና ጠኔ በኢትዮጵያ ፪ኛዓመት ቁ 5-7 የጥናት ልዩ ዕትም ቁ5/6 የካቲት 1981 ዓ.ም.::

English sources

Abrams, M.H A GLOSSARY of Literary terms. 7th edn. Boston: Heinle&Heinle.

Abrams, M.H.. A Glossary of literary terms. Geoffrey GoHHarpham. Cornell university national humanity center. Ninth edition.

Bauman, W. Verbal Art as performance. Newbury House: Rowley, 1977.

Bascom, W. Four Functions of Folklore. Journal of American Folklore. Vol. 67. No. 266, 1954.

C. Hugh Holman. A handbook to literature (indianapolisi; ITT Books — Merrill education publishing Co's Ltd London:1985, P 98),

Creswell, J.W. Qualitative Inquiry Research Design: choosing among five Approaches. (2nd ed).) Thousand Oaks, London, New Delhi: Saga publications,Inc, 2007.

Dandes, A. The study of folklore. Englewood: N.J. prentice — Hall inc, 1965.

Durkhim, Emil. The elementary Forms of Religious Life, London,Hollen Street Press,1999.

Douglas Kellner. Critical Theory and the crisis of social theory. (http://www.gseis.ucla.edu/faculty/krllnerkellner.html)

Fletcher, C. Beneath the Surface: An account of three styles of sociological research, London and Bosten: Routledge& Kegan paul.1974.

Finnegan, Ruth. (1970). Oral Litrature in Africa. Nairobi: Oxford University Press.

Finnegan, Ruth. (1976). Oral Litrature in Africa. Nairobi: Oxford University Press.

Marshal, C. &Rossman, G. Designing Qualitative Research. United states of America: (4th Ed.). Saga publications Inc,2006.

Nelson Mandela.long walk to freedom,Theouto biography of nelson mandela.1994.Littel,Brown

Okpewho, Isider. African Oral Literature: Backgrounds, Character and Continity. Indian polis: Indian University Press.1992.

Prasad,B. Devi. Content Analysis A method in Social Science Research. New Delih: Rawat, 2008.

Radcliffe — Brwon, A.R. (1935). " on the concepts of function in social science," in America Anthropologist. No. 37, 1935).

Tadros Malaty, commentary on psalm, P.324
Wellek, Rene and Warren, Austin. Theory of literature. New York: Harcourt Brace and Company,1948.

## የድረ ገጽ ምንጮች

https://youtu.be/Qjr9aM4dhpo2020 jul 31.

https://youtu.be/GO33kYeEvYe. 2020,29 may.

Kesem media.net ዘረኝነትና ዳፋው April 24,220.

https://am.eferrit.com ቁርአን ስለዘረኝነት ምን ይላል?
https”://www.sbs.com.aw aug 7, 2022
http://youtube/-ay1RJ61R9
Https://youtube/H6VNX7ek1k 2018jul.

https://youtube/50N62754hfo 2018 July.
https://youtube/H6VNXQNXQTekQk
JOURNAL OF WORLD-SYSTEMS RESEARCH, ISSN:1076-156X | vol, 22 Issue page 9-15 | http://dx.doi.org/10,5195/jwsr.2016.609 | jwsr.org. What is research? Roman Grosfoguel. University of California, Berkeley, p10.)
Voice of America.https:Amharic.vonews.com//

feb 27,2014. https://ethiopanaroma.com/?p=101974

https://am.al-ain.com/article/ethiopianbasedàquawat-of-the-prophet-smosque

Aiga forum http:// aigaforum.com
https://astemhro.com/2021/12/26islandofchrstianity
https://www.org/am/

Ethioreference https://ethioreference.com./archives/19706#

### አባሪ አንድ፦የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መዝሙሮች

### 1/ ተነሽ ኢትዮጵያ

ተነሽ ኢትዮጵያ (3)

እንበል ሃሌ ሉያ በያሬድ ማኅሌት …. ተነሽ ኢትዮጵያ በጣም ተደነቂ …. ተነሽ ኢትዮጵያ መሠረት አንቺ ነሽ …. ተነሽ ኢትዮጵያ ለዜማ ፈለግ …. ተነሽ ኢትዮጵያ

ሃሌ ሉያ እያለ ዓለምን የቃኘ፤

ያሬድ ታሪክሽ ነው በረከት ያገኘ፡፡

ዕዝልና ግእዙን አራራዩን ቃኝቶ፤

ለልጆችሽ ሰጠ በመንፈስ ተሞልቶ፡፡

ድጓትና ጭረት ምልክት ምሳሌ፤

ጭረትና ደረት ታጅበው በሃሌ፤

የሚንቀረቀሩት አንብርና ርክርክ፤

ጽናጽል ከበሮው ተውበው በመድረክ፤

ድምቀትሽ በእርሱ ነው ድጓ ሲታወጅ፤

አንዱም አይጠገብ በተዋሕዶ ደጅ፡፡

በያሬድ ዝማሬ መቋሚያ ጽናጽል፤

በዜማ ተመስጢል ንጉሥ ገ/መስቀል፡፡

ጽዋትወ ዜማ ሀብትሽ ነው ኢትዮጵያ፤

ስበኪ ወንጌልን እያልሽ ያሌሉያ፡፡

(ሊቀ መዘምራን ኪነ ጥበብ ወልደ ቂርቆስ 1984 ዓ.ም. ቁጥር 6.3)

### 2/ ተክለ ሃይማኖት

ተክለሃይማኖት ፀሐይ የአምላክ አገልጋይ፤ (2)

ፀሐይ የአምላክ አገልጋይ፡፡ (2)

የኢትዮጵያን ምድር የባረካት፤ (2)

አስተማሪዋ የሆንክላት፡፡ (2)

ይኸንን አውቃ ትዘምራለች፤ (2)

ተክለ ሃይማኖት ትጠራሃለች፡፡ (2)

አልጫው ጣፍጧል በጸሎትህ፤

ብርሃን በርቷል ለልጆችህ፡፡

በቃል ኪዳንህ ፍጥረት ጸደቀ፤

ታምራትህም በዓለም ታወቀ፡፡

ያከበረህን አምላክ ያከብራል፤

የናቁህንም እርሱ ይጣላል፡፡

ፍርፋሬህን ልቤ ናፈቀች፤

ያንተን በረከት ስለወደደች፡፡

በእግዚአኅረያ በጸጋ ዘአብ ተማጽኛለሁ፤

ነፍሴን በእጅህ ሰጥቼሃለሁ፡፡

ከአንተ ጋር ልኑር ለዘለዓለም፤

የሚለያየን ማንም የለም፡፡

(ዲ/ን ምንዳዬ ብርሃኑ 1991 ቁጥር 5.8)

### 3/ መራራ ሕይወቴ

መራራ ሕይወቴ ጣፈጠ በማርያም፤

ማዘን ስደት ይቅር እስከ ዘለዓለም፡፡

ተፈውሷልና በእመቤታችን፤

የመሪባ ውሃ ተባረከልን፤

በእግዝትነ ማርያም እንድናለን፡፡

ሀገሪቱ መልካም ኑሮዋ መራራ፤

በስደት አለቀ ወገኔ በተራ፡፡

ሽማግሌ እንዲጦር ሕፃናት እንዲያድጉ፤

ኤልሳዕን የሚተካ አባት ሰው ፈልጉ።

ማሰሮ አምጡ ጨውም ጨምራችሁ፤

ሞት እንዳይነግሥ በመካከላችሁ።

ማረን እንበል ኤሎሄ ብለን፤

እንዋደድ እንዲሠምርልን።

ትውልድ ሁሉ ብፅዕት የሚሉሽ፤

ኢትዮጵያን ፅንባዋን አብሽ።

ታለቅሣለችና እማማ ኢትዮጵያ፤

የወላዶች መካን አድርገዋት ልጆችዋ።

ዓለሙም ንብረቱም ሁሉም ያልፋልና፤
ይበቃናል እንበል በቀና ልቦና።

የሕፃናት ድምጽ ተሰማ በራማ፤

ስለሆነች ምድራቱ አኬልዳማ።

የዘገዬ ቢመስል እግዚአብሔር፤

ቀድሞ ይፈርዳል ሳለ በምድር።

የአቤል ድምጽ ጸባኦት ደረሰ፤

ቃየልስ ወዴት ገሰገሰ።

ለአዛኝቷ ሁሉ ይሆናልና፤

ንገሯት በጽኑ ልመና።

እኔ የኬፋ ነኝ የአጵሎስ አትበሉ፤

የተለያዬ መንግሥት አይጠናም እንዲሉ።

የኢትዮጵያ ልጆች አንድነን ሁላችን፤

ልዩነት እናጥፋ ከመካከላችን።

ስንዴ መሐል እንክርዳድ አንዝራ፤

ተደምስሷል የዲያብሎስ ሴራ።

በአስጨናቂዎች እጅ አትጣለን፤

ፍረድልን እናነባለን።

ለልጁ አባት ይገደዋልና፤

አምላክ ሆይ ተመልከተን ናና።

ስለማርያም ብለን ለምነን፤

አልፈናል ያን ክፉ ዘመን።

ሀገርን አይተውም ያለአንዳች ጻድቅ፤

ሥውሩንም ይታያል አይሆንም ድብቅ።

የአባቶቼን ርስት ስም ቶኔቶር፤

ገበዟ ጊዮርጊስ ነው ዐሥራቷ ድንግል።

ዳሯ እሳት መኃኒ ገነት፤

ለእኛም ይሰጠን ፍቅር አንድነት።

የተሰዓቱ ቅዱሳን መሸሻ፤

ኖላዊ ጌር ጠባቂሽ ነው ጋሻ።

ትውልድ ሁሉ ብፅዕት የሚሉሽ፤

ኢትዮጵያን እንባዋን አብሺ።

ሀገሬን እንባዋን አብሽ፤

ኢትዮጵን እንባዋን አብሺ።

(ዘማሪ ዲ/ን እንግዳ ወርቅ በቀለ 1997 ቁጥር 4.11)

## 4/ የሁሉም ዐይን

የሁሉም ዐይን አንተን ተስፋ አድርጓል፤

ምሕረት ቸርነት ይጠባበቃል።

ሸክሙ ከብዷል አቅልልን፤

ያላንተ ጌታ ሌላ ማን አለን።

ያለው ይመስላል ለብሶ ሲያዩት፤

ላይ ታች እያለ ይዞት ጭንቀት፤

የልጆቹ እንባ ጨኸት ሰልችቶት፤

ልመና ገባ ምሁሩ ድንገት፡፡

ከዛሬ ነገ ይሻላል ስንል፤

እየባሰ ሔደ አለመታደል፡፡

እምነ ረሃብ ይጌይስ ኰናት፤

ብለዋልና ደቀ መዛሙርት፡፡

አሳይተኸን ጌታ አትንሳን፤

በደል አለብን ይቅር በለን፤

ወርቅ ብር ላይ ተቀምጠን፤

እንራባለን ፍቅር አጥተን፡፡

ዕንጨት ለቃሚ ባልቴት ነበረች፤

በሰራጽታ በድህነት ያለች፡፡

በአክአብ ምክንያት ረሃብ ሆኗል፤

ወደሞት ልንወርድ ተዘጋጅተናል፡፡

(ዘማሪ ዲ/ን እንግዳወርቅ በቀለ 1989 ዓ.ም. ቁጥር 5.7)

**5/ ቅያሜው ይቅርና**

ቅያሜው ይቅርና አምላክ ሆይ ታረቀን፤

አንተ ስለራቅከን ሞት ነው የከበበን፡፡

እስከመቼ ድረስ ሕዝብህ ተጎሳቅሎ፤

ለረከሰ መንፈስ በርኩሰት ተጥሎ፡፡

ምድር እያለቀሰች ደም እየሸተታት፤

እባክህ አምላኬ ኢትዮጵያን ታረቃት፤

እባክህ አምላኬ ሀገሬን ታረቃት፡፡

የዘመኑ ጣኦት ገንዘብ እያሳተን፤

ይኼ ደካማ ሥጋ አምላክን አስተወን፡፡

ግብዝነት ሞልቶት ፈራሹ አካል፤

በነፋስ በሽታ ሕዝባችን ታሟል፡፡

አዝ

ክንፋችን ተመቶ መብረር አቅቶናል፤

በመንፈስ በሽታ ሕዝባችን ታውኳል፡፡

ራእይ የሌለው ተራ ሰው ስለሆን፤

እባክህ ጌታችን በፍጥነት ታረቀን፡፡

አዝ

ጸጋ የተለየን ባዶነት የሞላን፤

ፍቅር የተነፈገ ሰላም የጎደለን፡፡

ሆነን ስለቀረን እግዚአብሔር ታረቀን፤

ጽድቅህን አድለን ጽድቅን ለተመኘን፡፡

(ዘማሪ ይልማ ሃይሉ 1989 ቁጥር 5.7)

**6/ ኢትዮጵያ ሆይ**

ኢትዮጵያ ሆይ እግዚአብሔርን አመሰግኚ፤ (2)

ከሕዝብሽ ጋር እልል በይ፡፡ (2)

እጆችሽን በበረከት ስለሞላ፤ (2)

ስላዳንሽ በጭንቅ ቀን ከሞት ጥላ፡፡ (2)

እግዚአብሔር ብርሃንሽ ስለሆነ፤

ካስፈሪው ቀን ልጆችሽን ስላዳነ፡፡ (2)

በሽብሸባ እልል በይ፤ (2)

በሽብሸባ ለአምላክሽ ዘምሪለት፤

ስብራትሽን ይጠግናል በምሕረት፡፡(2)

ለሕዝብሽም እግዚአብሔር ኃይላቸው ነው፤(2)

በስቃይሽ የጎበኘ መመኪያቸው፡፡ (2)

ኢትዮጵያ ሆይ እግዚብሔርን አመስግኚ፤(2)

ከሕዝብሽ ጋር እልል በይ፡፡ (2)

ሕዝብህን ባርክ ለዘላለም ጠብቃቸው፤ (2)

በጽድቅህም ከፍ አድርጋቸው፡፡ (2)

የምስጋና ነጎድጓድ ካፍሽ ይውጣ፤

ድሮም ቢሆነ እግዚአብሔር ነው ያንቺ ዕጣ፡፡(2)

(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ 1989 ቁጥር 2.6)

**7/ ትንሣኤሽን ያሳየን**

ትንሣኤሽ ያሳየን፤ (2)

ውዲቷ ኢትዮጵያ፤

ሀገረ እግዚአብሔር ትንሣኤሽን ያሳየን፡፡

የአባቶችን ዘመን ተመልሶ እንድናይ፤

አለን ኢትዮጵያኖች የፍቅር ራእይ፡፡ /ትንሣኤሽ ያሳየን/

ትቢያሽን አራግፈሽ ኀዘንሽን ትተሽ፤

ደግሞ ትገኛለሽ ሀገሬ እንደድሮሽ፡፡ /ትንሣኤሽን ያሳየን/

ያልታዘዘች ሀገር ለእግዚብሔር ሥርዓት፤

አያጣትምና ዘወትር ፍርሐት፡፡ /ትንሣኤሽን ያሳየን/

ከቁጣው አምልጣ ሰላም እንድታገኝ፤

ውብና ድንቅ አድርገህ ስለሠራሃቸው፤

አንተን ተስፋ አድርጎ ይሄ ሁሉ ፍጥረት፤

ምግቡን ይጠብቃል የእጅህን በረከት፡፡

ፊትህን ስትሠውር ይደነግጣሉ፤

ፍጥረትህን አትዘንጋ አስታውሰን እያሉ፡፡

ጨረቃን ፀሐይን በጊዜ አሰልጥነህ፤

አንዱን እያስገባህ አንዱን ታወጣለህ፡፡

ሐሩሩን ቁሩን በሚዛን ለክተህ፤ --ትንሣኤሽን ያሳየን

ይቅርታ ታላቅ ነው ቁስልን ይሽራል፤

ፀብ ግን እስከዛሬ እነማንን ጠቅሟል?

ቂምና በቀልን ለትውልድ ያቆዩ፤ ትንሣኤሽ ያሳየን

በማይበርድ እሳት ውስጥ ሕዝቡን ያጋያሉ፡፡ ትንሣኤሽን ያሳየን

(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ 1994 ቁጥር 6.9)

**8/ ክብርን ልበሽ**

ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ ክብርንም ልበሽ፤

በአዲስ ምስጋና ይሞላ ልብሽ፤

የተወደደ ነው በእግዚአብሔር ሕዝብሽ፡፡

ንብረቱ ጠፊ ነው ከንቱ የማይረባ፤

በግፍ በቅሚያ ባመጽ ሲገነባ፡፡

ሲሳይሽ ብዙ ነው ባምላክ የተሰጠሽ፤

በረከት ለማግኘት መሥራት ነው ጠንክረሽ፤

ለሀገር ብልፅግና መስራት ነው ጠንክረሽ፡፡

ኃላፊ ጠፊ ነው ምኞቱም ዓለሙም፤

ደመና ነውና ይበናል በቅፅበት፤

በግፍ የተገኘ የተከማቸ ሀብት፡፡

ይልቅ በቅንነት በሰላም <u>እንሥራ?</u>

ሲሳዩ ብዙ ነው ክብርም እያበራ፡፡

ጉቦና ፍትህን ማጣመም እንዳንለምድ፤

ከወንጌሉ ጋራ አለብን መዛመድ፡፡

እግዚአብሔር ያለው ሰው ለእርሱ የታመነ፤

ከግፍ ስራ ሕመም አካላቱ ዳነ፡፡

ክርስቲያን ነኝ ብሎ ጉቦ የሚበላ፤

የሚያቃጥል እሳት ያገኘዋል ኂላ፡፡

በመታመን ጸጋ ይጠራ ስማችን፤

እውነተኛ እንሁን ለውድ ሀገራችን፡፡

የራሱን ሳይሻ ለሀገር የሚያስብ ሰው፤

በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው፡፡

(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ 1995 ቁጥር 7.1)

### 9/ ኢትዮጵያ እጆችሽን ዘረጊ

ኢትዮጵያ እጆችሽን ዘርጊ ወደ አምላክ ወደ አዶናይ፤(2)

ሕዝብሽ ከሞት የሚያድን ይውጣልሽ የምሕረት ፀሐይ፡፡

ሕፃናት ወላጆች አጥተው በሜዳ ሲበታትኑ፤

ንስሮችሽ ወጣቶች አልቀው የአፈር ሲሳይ ሲሆኑ፤

የሞት መልአክ ተልኮብሽ የአፈር ሲሳይ ሲሆኑ፤

ቁጣውን እንዲመልሰው ለምኚ ለሰማይ ጌታ፡፡

ታማሚው እያጣጠረ ጤነኛው ቆሞ ሲፈራ፤

አምላክሽ ይኑር ይበልሽ ይለፍሽ ይኼ መከራ፡፡

አበውን ይዘሽ ተነሽ ጸሎትሽን ቆመሽ አድርሽ፤

ያብርደው እሳት ንዳዱን በምልጃሽ በልመናሽ፡፡

ልጆችሽ ቅጣት ገብቷቸው እንዲያዩ ወደ አምላካቸው፤

መከራቸው ትምህርት ሆኖአቸው ይመለስ ታካች ልባቸው፡፡

የበደልነውን ታግሶ ቁጣውን እርሱ መልሶ፤

ይማረን ይቅር ይበለን ጽኑ ምሕረቱን አስታውሶ፡፡

አሕዛብ ተነጋገሩ አምላክሽ ረሳሽ ብለው፤

ልጆችሽ ሞት ሲፈጃቸው እያዩ እጅግ፤

ጉልበትሽ እንዳይሰበር ምርኩዝሽ እርሱ ነውና፤

ደዌ ቸነፈሩን ያርቅ አቅርቢ ጽኑ ልመና፡፡

(ዘማሪ ቴዎድሮስ ዮሴፍ 1994 ቁጥር 4.7

### 10/ አብርሂ

አብርሂ ኢትዮጵያ (2)

ሃሌሃሌ ሉያ (2) አብርሂ ኢትዮጵያ

ዘላለም ይኖራል ጸንቶ ምሰሶሽ፤

በዓለም ያበራል ሕያው ታሪክሽ፡፡

ድንግል ጠበቃሽ፤

አምላክ ጠባቂሽ፤

የጽድቅ ነው ያንቺማ ደጅሽ፡፡

በወንጌል መንግሥት ጉባኤሽ ተከብሮ፤

ያሬዳዊ መዝሙር አብሮ ተዘምሮ፤

ጸበልሽን እምነትሽን፤

ተቀብተን በእምነት እንድናለን፡፡

ኢየሩሳሌም ነሽ ዳግማዊት ሀገር፤

የተቀመጠብሽ የአምላክ መንበር፡፡

በረድኤት በቸርነት

እንኖራለን በዚች ምድር ቅድስት፡፡

እጆሽን ዘርግተሽ ወደ ሰማይ ጌታ፤

ደጅሽ ተጠበቀች በእሳት ተዘግታ።

የአባቶችሽ አምላክ አይረሳሽም ከቶ፤

ታድነሻል እጆችሽ ዘርግቶ።

እስከ ዓለም ዳርቻ ምስክር ሆነሻል፤

አምላክ የሰጠሽን አጥብቀሽ ይዘሻል።

ሰሎሞንን አይተሽ አምላኩን አምልከሽ፤

በሐዲስ ኪዳን ቀድመሻል ተጠምቀሽ።

አዜብ ተብለሻል በጌታ አንደበት፤

የእምነት ምስክር ሆነሽ አብነት።

የገዳምሽን ዕጣን ምሕላሽን ይዞ፤

አቀናልሽ የእምነትሽን ጉዞ።

(መልአከ ገነት በለጠ ይረፉ አብርሂ ቁጥር 5 1994)

**11/ ተክለሃይማኖት**

ተክለሃ ይማኖት ፀሐዩ ጽድቅ፤ (2)

ያዘላትና? ለነፍሴ ስንቅ። (2)

ተክለሃይማኖት እንዳትጠፋ ነፍሴ፤

አንተው አማልዳት ቀርበህ ከሥላሴ።

ተክለሃይማኖት ድካሜን ሳስበው፤

ተክለሃይማኖት ታውኳል መንፈሴ፤

ተክለሃይማኖት ጦርነት ገጥመዋል፤

ተክለሃይማኖት ሥጋዬና ነፍሴ፤

ተክለሃይማኖት ሥጋዬን ሲደላው፤

ተክለሃይማኖት ነፍሴ እንዳትቆም ከስታ፤

ተክለሃይማኖት ተክልዬ አንተ ሁናት፤

ተክለሃይማኖት ስንቅና መከታ።

ተክለሃይማኖት በበረከት ታጭዶ፤

የእምነትህ አዝመራ፤

አየነው ተክልዬ፤

ከመላእክት ጋራ።

እንኳንና ገድለህ፤

ለሰማው በእርጋታ፤

በረከት ያስገኛል፤

የቆምክበት ቦታ።

ተክለሃይማኖት የእምነትን ሰንሰለት፤

ተክለሃይማኖት ታጥቀህ በወገብህ፤

ተክለሃይማኖት የጌታ ቃል ፍቅር፤

ተክለሃይማኖት ጽናቱ ነው ምግብህ።

ተክለሃይማኖት ፀሐይ ተክለሃይማኖት፤

ተክለሃይማኖት ኢትዮጵያን አስባት።

ተክለሃይማኖት ትጋ በጸሎትህ፤

ተክለሃይማኖት ችግር እንዳይገባት።

(ዘማሪት አዜብ ከበደ 1993 ቁጥር 2፤6)

**12/ ተክለ ሃይማኖት ጻድቅ**

በኢትዮጵያ ምድር ክብሩ ታላቅ ሆነ፤

በኢትዮጵያ ምድር ሰሙ ታላቅ ሆነ።

ተክለሃይማኖት ጻድቅ /2/ ተክለሃይማኖት አቡነ

በኢትዮጵያ ምድር ዝናህም ተሰምቷል፤

ተክልዬ ጸሎትህ ከአርያም ደርሷል፤

የሚሰማህ ሁሉ እጅግ ያደንቅሀል፤

የመዳንን ዝናር ወንጌልን ታጥቀሀል፡፡
መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ጽድቅን ስለሠራ፤
የሰማዩ ብርሃን በምድራችን በራ፡፡
ብትማርካቸው አርአያ ክህነቱ፤
ወጡ ለምነና ደቀ መዛሙርቱ፡፡
በስመአብ ብሎ ሲያነሣ መስቀሉን፤
ያስጨንቃቸዋል ምድረ አጋንንትን፡፡
ከአፉ ሲወረወር መልእክተ ወንጌሉ፤
ለእግዚአብሔር ተገዙ ነገሥታቱ ሁሉ፡፡
ቅድስና ክብሩ ያበራል ለዛሬም፤
ምሳሌ ሆኗል ለጨለማው ዓለም፡፡
ምድርን ይባርካል ተክልዬ ጸሎቱ፤
እኛም ተጠቅመናል በአማላጅነቱ፡፡

(ቸርነት ሠናይ 1995 ቁጥር 4.4)

**13/ የእግዚአብሔር ሀገር**

የእግዚአብሔር ሀገር ነሽ ኢትዮጵያ፤
የእግዚአብሔር ምድር ነሽ ኢትዮጵያ፤
ዐሥራት የተሰጠሽ ኢትዮጵያ የድንግል ርስቷነሽ
ላንቺ የሚበጀው መፍትሔው አንድ ነው፤
ሰላም የሚሰጥሽ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡
የቅዱሳን ጸሎት ኢትዮጵያን ይባርካት፤
ከረኃብ ከርዛት ከጦርነት ያውጣት፡፡
ኦ ድንግል ኢትዮጵያ ርስትሽን፤
በእንግድነት ኢትዮጵያ ርስትሽን፤
ያረፍሽባትን ኢትዮጵያ ርስትሽን፤
ጠብቂልን ኢትዮጵያ ርስትሽን፤
ሀገርሽን ኢትዮጵያ ርስትሽን፤
ኦ ድንግል /2/ ኢትዮጵያ ርስትሽን፤
በተሰጠሽ ኢትዮጵያ ርስትሽን፤
ቃል ኪዳን ኢትዮጵያ ርስትሽን፤
ጠብቂልን ኢትዮጵያ ርስትሽን፤
ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ርስትሽን፤
ከመረጥካቸው ከቅዱን ጋራ፤
ቃልኪዳን አደረግህ፤
ለባሪያህ ለዳዊት ማልህ፤
ጌታ ሆይ ኢትዮጵያን በነርሱ ታረቅህ፤
የቅዱን ክብር በቤተህ ድንቅ ነው፤
ከወንዶች ከሴቶች ሚበልጥ ቃል ነው፡፡
በቤትህ በቅጥርህ ቃል ኪዳን ገብተሃል፤
የማይጠፋ ስምህ ለእነርሱ ሰጥተሃል፡፡
ድንቅ የሆነው ስምህ ተገልጧል በነሱ፤
በተጋድሎ ጽናት ጽድቅን እዲለብሱ፡፡
በቅዱሱ ቅባት ለክብርህ አተምካቸው፤
በጸጋ ስጦታህ አማልክቱ አልካቸው፡፡
የነፃነት አርማ የበጎ ምልክት፤
ሲያበራ ይኖራል በቅዱሳን ሕይወት፡፡
ቅዱሳን ከበዋል በደመና አምሳል፤
የእግዚአብሔርን ሀገር ቅድስት ኢትዮጵያን፡፡
(ዘማሪ ዲ/ን ታዲዎስ ግርማ 1996 ቁጥር 3.3)

### 14/ አባ ተክለሃይማኖት

አባ ተክለ ሃይማኖት ጻድቁ አባት፤

ኢትዮጵያን አስባት በምልጃህ ጸሎት።

አባ ተክለሃይማት የዚጋ ዘ አብ ፍሬ የእግዚእ ኀረያ፤

የእግዚአብሔር አገልጋይ ሐዲስ ሐዋርያ፤

ክንፍህን ታድለሃል እንደ መላእክት፤

ከልስህ ሠውረን ከክፉ ጥፋት።

ይራዳሉ አጋንንት ሲጠራ ስሞህ፤

ይፈጸማል ተአምር ሲነበብ ገድልህ፤

ተምሮ ላመነህ ለተማፀነህ፤

ሁሉን ይፈውሳል ጸበል እምነትህ።

ኀዘን የከበበው ተስፋ የቆረጠ፤

በጻድቁ ምልጃ ኑሮው ተለወጠ።

ኃይልን ታደርጋለች የጻድቅ ጸሎት፤

ለምንልን ዘወትር አሰጠን ምሕረት።

(ዲ/ን ወንደሰን መገርሳ ቁጥር 1 ዓ.ም)

### 15/ ተነሽ ኢትዮጵያ

ተነሽ ኢትዮጵያ ከረከሰው ምድር፤

ደም ከፈሰሰበት ከጎደለው ክብር፤

ይሰማ ጩኸትሽ ተነሥተው እጆችሽ፤

ይፈጸም ኪዳኑ አምላክ የገባልሽ። /2/

ማቃሰትሽ በዝቷል----- ተነሽ ኢትዮጵያ

ሰቀቀንሽ ረዝሞ ------- ተነሽ ኢትዮጵያ

ልጆችሽ አዝነዋል ----- ተነሽ ኢትዮጵያ

ከምድር አይንጠፍ ----- ተነሽ ኢትዮጵያ

የረጨነው እንባ --------ተነሽ ኢትዮጵያ

አምላክ ይራራልሽ-------- ተነሽ ኢትዮጵያ

ባፈሰስነው እንባ -----------ተነሽ ኢትዮጵያ

ፍርድ ተጓድሎብሽ ---- ተነሽ ኢትዮጵያ

ደሀ ተበድሏል---- ተነሽ ኢትዮጵያ

ቅዱሳን አልቅሰው---- ተነሽ ኢትዮጵያ

ክፉዎች ስቀዋል -----ተነሽ ኢትዮጵያ

ከመሶብሽ ረድኤት----- ተነሽ ኢትዮጵያ

ርቆሻልና --------- ተነሽ ኢትዮጵያ

አልቅሽ ለአምላክሽ ------ ተነሽ ኢትዮጵያ

ንስሐ ግቢና------- ተነሽ ኢትዮጵያ

ደሀ አደጎች ሆነን----- ተነሽ ኢትዮጵያ

በገዛ ምድራችን ------ተነሽ ኢትዮጵያ

በዋጋችን ጠጣን----- ተነሽ ኢትዮጵያ

ገዝተን ውኃችንን----- ተነሽ ኢትዮጵያ

ተሰዷል ልባችን ------- ተነሽ ኢትዮጵያ

ካለንበት ሀገር ---------ተነሽ ኢትዮጵያ

እንጀራ ልመና --------ተነሽ ኢትዮጵያ

ከባዕዳን መንደር --------ተነሽ ኢትዮጵያ

ተበጣጥሰን በዘር---- ተነሽ ኢትዮጵያ

አንድነት ስናጣ----- ተነሽ ኢትዮጵያ

ፍሬዋን ነሳችን----- ተነሽ ኢትዮጵያ

ምድር ተለውጣ----- ተነሽ ኢትዮጵያ

ዘራችን ክርስቶስ----- ተነሽ ኢትዮጵያ

መሆኑን ዘንግተን -------ተነሽ ኢትዮጵያ

ምንጮቻችን ነጥፈው ------ተነሽ ኢትዮጵያ

አዝነን ተጠምተን------- ተነሽ ኢትዮጵያ

(ዘማሪት ዘዲስ ለማ 1997 ዓ.ም ቁጥር 4፤6)

**16/ ሰላም ለኢትዮጵያ**

ሰላም ለኢትዮጵያ ሰላም ለሀገራችን፤

ይላክልን ይላክልን ቸሩ አምላካችን፡፡

አዝ

ለዓለማት ሁሉ ኢትዮጵያ ተስፋ ነሽ፤

አይደለሽም ብዙ በቁጥር አንዲት ነሽ፡፡

ዥንጉርጉርነቱን ነብር አይቀይርም፤

ኢትዮጵያዊ መልኩን ሲለውጥ አይችልም፡፡

ሰላም ለኢትዮጵያ ሰላም ለሀገራችን፤

አዝ

በታላቁ መዝገብ ስምሽ የሰፈረ፤

የቆየው ድንበርሽ እንደተከበረ፡፡

ያኑርሽ ፈጣሪ አንቺን ከፍ አድርጎ፤

መሐልሽን ገነት ዳሩን እሳት አድርጎ፡፡

አዝ

አንች ቅድስት እናት የአቤሜሌክ ሀገር፤

የግዮን መፍሰሻ የተመረጥሽ ምድር፡፡

ክብርና ሞገስሽ ይመለስልሻል፤

ቀድሞ ያከበረሽ መቼ ይተውሻል፡፡

አዝ

ከምድር ነገሥታት አንዳች አትጓጊ፤

ኢትዮጵያ እጆችሽን ወደ እግዚአብሔር ዘርጊ፡፡

ምግብሽ የሚሰጥ አምላክሽ ታማኝ ነው፤

ሰላምሽ እግዚአብሔር እግዚብሔር ብቻ ነው፡፡

(ሊቀ መዘምራት ቴዎድሮስ ዮሴፍ 2011)

**17/ ኢትዮጵያ ሰላምሽ ይብዛ**

ኢትዮጵያ ሰላምሽ ይብዛ፤

ተጠለይ በእግዚብሔር ታዛ፡፡

አዝ

ከሚራራልን ፍቅር ከሆነው፤

ዘላቂ ሰላም ከእግዚአብሔር ነው፡፡

ይኸንን ዕወቂ ይሄን ተረጂ፤

በልብሽ ጉልበት ለርሱ ስገጅ፡፡

አዝ

በሰይፉ ያልቃሉ ሰልፉ የሚያነሡ፤

የሚራራልን ሲፈርድ ንጉሡ፡፡

በቀል የእርሱ ነው አይደለም ያንቺ፤

በጸጋው ታጥረሽ በጸሎት በርቺ፡፡

አዝ

የውጣ ውረድ የጉስቁልናው፤

በእግዚአብሔር ነው መከራ ማብቂያው፡፡

ሰላም ይሁን ሲል ይሆናል ሰላም፤

ያሳየሽን ፍቅር አይረሳም፡፡

አዝ

ማራት ኢትዮጵያን ማራት ሀገሬን፤

በየሔድኩበት መጠሪያ ስሜን፡፡

ይብቃት ሌሊቱ ይውጣላት ፀሐይ፤

አሁን ይዘርጋ እጅህ ከሰማይ፡፡

አዝ

እንድትፈራርስ ጠላት ሽምቋል፤

ብርቱውን ጉልበት ካፊር ደባልቋል፡፡

ይኸን ግፍ አስብ ዘንበል በልላት፤

ካንተ በስተቀር መሄጃ የላት፡፡

አዝ

ማራት ኢትዮጵያን ማራት ሀገሬን፤

በየሔድኩበት መጠሪያ ስሜን፡፡

ይብቃት ሌሊቱ ይውጣላት ፀሐይ፤

አሁን ይዘርጋ እጅህ ከሰማይ፡፡

(ሊቀ መዘምራን ቴዎድሮስ ዮሴፍ 2012)

## 18/ ኢትየጵያ እጇቿን

ኢትዮጵያ እጇቿን ዘረጋች አለ ወደ እግዚአብሔር፤

ነብዩ ዳዊት በትንቢት አይቶ ስንፋቀር፡፡

ዛሬ ግን ሆነን በዘር በቋንቋ የምንሰለፍ፤

የተዘረጋው የፍቅር እጆቿ እንዳይታጠፍ፡፡

አዝ

አምላክ አዘነ ከሰማይ ሆኖ ሲመለከታት፤

ሲያጣት ኢትዮጵያን አክብሮ ትናንት እንዳስቀመጣት፡፡

ቅዱስ መጽሐፍ ወዶ የጠራትን በመደጋገም፤

ቅድስት ኢትዮጵያን ከማፍረስ በላይ ኃጢአት የለም፡፡

አዝ

አይለወጥም የኢትዮጵያዊው መልክ እንደነበር ነው፤

በእምነት የጸና ሁሉን የሚወድ የሰላም ሰው ነው፡፡

እርሷን የሠራ የእግዚአብሔር ጣት ነው የሚጠብቃት፤

ዘር መቁጠር አይደል እናት ሀገርን የሚያስገድላት፡፡

የነኳት ሁሉ መጥፋታቸውን ታሪክ ሰምተናል፤

በክፉ ያዩዋት በረቂቅ ሰይፍ ሲወድቁ አይተናል፡፡

በአምላኳ ታምና ራስ ነው እንጂ አትሆንም ጅረት፤

ተው አትድከሙ አትችሏትም እግዚአብሔር አላት፡፡

አዝ

ሚፈታተናት የዘንዶው ራስ ይቀጠቀጣል፤

እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ምግቧን ይሰጣል፡፡

ተስፋ ናትና ቅድስቷ ሀገር ለዓለም ሁሉ፤

የማትፈርሰውን ለማፈራረስ አትታገሉ፡፡

(መምህር ምሕረተአብ አሰፋ 2013)

## 19/ ባደረብሽ ሕመም

ባደረብሽ ሕመም ሞተሽ አናይሽም፤

ኢትዮጵያ ስላንቺ ከቶ ዝም አንልም፡፡

ወደ ፈጣሪያችን ወዳንቺ ፈጣሪ፤

እንጸልያለን ኢትዮጵያ እንድትኖሪ፡፡

አዝ

አላዛር ኢትዮጵያ ከመቃብር ውጪ፤

መግነዝሽ ይፈታ ከጠላት አምልጪ፡፡

ትንሣኤሽ ይሆናል እንቅልፍሽ አብቅቶ፤
ንጉሥሽ ለአጥፊው አይተውሽም ከቶ።
አዝ
ሰማይሽ ቢጠቁርም ፀሐይ አዘቅዝቃ፤
ንጋት ይወርስሻል እግዚአብሔር ሲል በቃ።
እየተገዳደልን አለን ተጨካክነን፤
ተፈጸመ በለን ይሄ የጭንቅ ዘመን።
አዝ
ያደረብሽ ሕመም ለሞት አይሰጥሽም፤
ትንሣኤሽን እንጂ ሞትሽን አናይም።
እግዚብሔር ያኑርሽ ክፋትን አሻግሮ፤
ጥፋትሽን የሚመኝ ይታይ አቀርቅሮ።
አዝ
ሀገርን ያገዙ ዛሬ ይታገዙ፤
በጥላቻ አዚም ይብቃ መደንዘዙ።
ለሀገር የሚያድጉ በሰላም ይደጉ፤
ሰላምን አጽናልን እግዚአብሔር ደጉ።
(ሊቀ መዘምራን ቴዎድሮስ ዮሴፍ 2013)

**20/ ኢትዮጵያ ናት ሀገሬ**

ኢትዮጵያ ናት ሀገሬ፤ (2)
ተዋሕዶ ናት ክብሬ።
ያደኩብሽ መሠረቴ/ ተዋሕዶ ነሽ እናቴ፤
የአፊ መፍቻ ንግግሬ/ ያሳደግሽኝ (2) በዝማሬ
አዝ
የፍቅር ሀገር ኢትዮጵያ፤
ዘወትር ምትይ ሃሌሉያ።
አይበተን ሰላምሽ፤
አይታጎል /2/ ጸሎትሽ።
አዝ
ቃል ገባሁኝ ላልክድሽ፤
እንዳልለይ ከእቅፍሽ።
ደጅሽ ልኑር ጠዋት ማታ፤
ተዋሕዶ /፪/ የኔ አለኝታ።
አዝ
አለሽ ታሪክ የሚነገር፤
በትውልዱ የሚዘከር።
ትውፊትሽን ጠብቀሻል፤
ስሙን ይዘሽ /2/ አጊጠሻል።
አዝ
አይበጠስ ማዕተቤ፤
የታተመ ነው በልቤ።
አልፈልግም ሌላ ጥላ፤
እኖራለሁ /2/ ባንቺ ጥላ።
አዝ
የቅዱሳን ነሽ መፍለቂያ፤
የምስኪኖች መሸሸጊያ። (2)
እጆችሽን ወደ ጌታ፤
በርቺ ዘርጊ /2/ ጠዋት ማታ።
አዝ
ከቶ እንዴት ይሆናል አንቺን ምከዳሽ፤

ቀኜ ትክዳኝ ብዬ ቃል ገባሁልሽ፡፡

ከደጄ ሰላምሽ ከቤትሽ አድጌ፤

አንቺማ ክብሬ ነሽ ሞገስ ማዕረጌ፡፡ /2/

አዝ

በባእድ ሀገር እንኳን ቢሆንም ስደቴ፤

መቼ ይለዩኛል ማዕተቤ ካንገቴ፡፡

የክብርሽን እራስ ጌታዬን አምኜ፤

ላልተውሽ ቃል አለኝ፡፡ /በነብሴ ጨክኜ/2/

(ዘማሪ ሙሉቀን ከበደ 2010 ቁ.1፤2)

**21/ ጠብቅ እግዚአብሔር ሠራዊቷን**

እግዚኦ ሰላመ አባ ለሀገር፤

ጽድቀከኒ ለሕዝበ ክርስቲያን፡፡

አግርር ጸርአ ታሕተ እገሪሃ እቀብ ሕዝባ፤

ወሠራዊታ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ፡፡

(2) ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ድንበር የሚጠብቁትን፤

(2) ጠብቅ እግዚአብሔር ሰራዊቷን፡፡

አዝ

የደም መሬት አትሁን ደም አይፍሰስባት፤

ካንተ የመነጨ ሰላም ይስፈንባት፡፡

አሸናፊ እንድትሆን ለስምህ ተገዝታ፤

ዐይንህን ሳትመልስ እያት ጠዋት ማታ፡፡

አዝ

ሰንሰለት ሲጸና ለመከራ ፈርቶ፤

ኢትዮጵያዊ መልኩን አይቀርም ከቶ፡፡

ድንቁን ብርሃን ያያል ወቶ ከጨለማ፤

በመንገዱ ሁሉ አዳኝ ቀኝህ ቀድማ፡፡

አዝ

እጅግ የፈተናት ተነቅሎላት መርዙ፤

ከእግሮቿ በታች ጠላቶች ይገዙ፡፡

ደጅ ስትጠና እጆቿን ዘርግታ፤

ጠብቅ ሠራዊቱን ዳሩ እንዳይፈታ፡፡

አዝ

ከራሳቸው ይልቅ ኢትዮጵያን ወደዱ፤

ደም ከፍለው ሊያቆዩዋት በዱር ተሰደዱ፡፡

በሀሩር በውርጩ የሆኗትን አጥር፤

በማይፍቅ ቀለም ፃፏቸው ለክብር፡፡

(ሊቀ መዘምራን ቴዎድሮስ ዮሴፍ 2010)

**22/ ምሥጢረ ኢትዮጵያ**

የእግዚአብሔር የምሥጢሩ ሀገር ኢትዮጵያ (4)

አዝ

የታሪክ መገኛ የዕውቀት ማኅደር፤

የጥቁር ሕዝብ ክብር፡፡

ሀገሩ የእግዚአብሔር፤

ይመስለኝና የምንፈርስ ኢትዮጵያ፤

ቃኤል በርትቶ የሚነግሥ ኢትዮጵያ፤

አኬልዳማ እንዳይሆን ምድርሽ ኢትዮጵያ፤

ለዓለም ሕዝብ ጠፍተሽ ምድርሽ ኢትዮጵያ፤

አንቺ ሀገር የሚመራሽ አንድ ኃይል አለ ኢትዮጵያ፤

አንቺ ሀገር የሚረዳሽ አንድ ኃይል አለ ኢትዮጵያ፤

የአቡነ ጴጥሮስ የደም አሻራ፤

ኢትዮጵያን አኮራ ታፈራና ተከብራ።

ጴጥሮስ ያችን ሰዓት ኢትዮጵያ፤

በጭንቅ ውስጥ እያለ ኢትዮጵያ፤

ምነው እመብርሃን ኢትዮጵያ፤

ሀገሬን እንዳለ ኢትዮጵያ፤

ሞተልሽ ጴጥሮስ ተሠዋልሽ ኢትዮጵያ፤

ለእምነቱ ሕይወቱን የሰጠሽ ኢትዮጵያ፤

እመብርሃን ሀገሬን አትርሻት ኢትዮጵያን፤ (2)

እመብርሃን ሀገሬን አትርሻት ይህች ሀገር ማን አላት።

አንቺ ሀገር አረንጓዴ ቀይ ባንዲራሽ፤

የኪዳን ስጦታሽ፤

የቀስተ ደመና የኖህ ርግብ ምሥጢር፤

ኢትዮጵያ ልዩ ናት የቃል ኪዳን ምድር።

አትጠፋም ሀገሬ ኢትዮጵያ፤

ምልክቱን ይዛ ኢትዮጵያ፤

ከሰገነት ሰፍራ ኢትዮጵያ፤

በአምላኳ ታግዛ ኢትዮጵያ፤

ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ኢትዮጵያ፤

ኢትዮጵያ የቃልኪዳን ምድር ኢትዮጵያ፤

አንድ ነን ዘር ቋንቋ አይለየንም ኢትዮጵያ፤ (3)

ዘሬን አትጠይቁኝ ስለማንነቴ፤

ሰው መሆን በቂ ነው ኢትዮጵያዊነቴ፤

አንድነን ልጆችሽ ኢትዮጵያ፤

ጠላት አይለየንም ኢትዮጵያ፤

ተሳስበን በፍቅር ኢትዮጵያ፤

እንኖራለን በሰላም ኢትዮጵያ፤

አንድነን ዘር ቋንቋ አይለየንም ኢትዮጵያ፤ (2)

ኢትዮጵያ (2) የክርስቲያን ደሴት ኢትዮጵያ፤

የጽዮን ማደሪያ ኢትዮጵያ፤

ኢትዮጵያ (2) ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ፤

ኢትዮጵያ (2) እግዚአብሔር ኢትዮጵያ (2)

(ዘማሪ ፀሐፊ ትእዛዝ ዲ/ን ታዲዎስ ግርማ 2011)

## 23. ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ

ምንባብ

ኢትዮጵያ የጥቁር ሕዝቦች ምድር፤

ነፃነት ያላቸው ሕዝቦች መኖሪያ፤

በእግዚአብሔር የተወደደች ሀገር ኢትዮጵያ፤

.....

የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ፤

የአንድ ምድር ማኅፀን መንታ።

ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኢትዮጵያ፤

የክርስቲያን ደሴት ክብር ሃሌ ሉያ።

ኢትዮጰያ እድለኛ ሆነሽ እንዴት ይከፋሻል፤

ኢትዮጵያ ከተዋሕዶ ጋር በደም ተሳስረሻል።

ኢትዮጵያ ሥጋሽን አራግፈሽ በአጥንትሽ አትቆሚም፤

ኢትዮጵያ ያየሁትን አይተሽ የምልሽን ስሚ፤

ምህዋሩ ሲዞር የታሪክ ዙረቱ፤

ማንም አይደብቀው ይኸው ነው እውነቱ።

በስሟ ተበልቶ ሞገሷ አይቀበር፤

አይወጣም ተዝካሯ ባወጣቻት ሀገር።

ስጫት ሰገነት ያንሳታል ገና፤

ለውለታዋ ይቁም በገና።

ተዋሕዶ ናት ክብርሽ ዘላለም፤

የገለጠችሽ ለመላው ዓለም።

ኢትዮጵያ - አክሱም ላሊበላ የታሪክ አሻራ፤

ኢትዮጵያ - የጣና ገዳማት የግሽን ተራራ፤

ኢትዮጵያ - የአቡነ ጴጥሮስ የሃይማኖት ጀግንነት፤

ኢትዮጵያ - ንፁሑ ደም ክፍለዋል ዛሬ ላለሽበት።

የብሉይ የሐዲስ ባለቤት አድርጋሽ፤

የጸሎቷ ጉልበት እየጋረደሽ።

የነገሥታቱን ክብር ቅርስሽን ታቅፋ፤

ጠንካራዋ እመቤት ቆመች ላንችም ተርፋ።

ስጫት ሰገነት ያንሳታል ገና፤

ለውለታዋ ይቁም በገና።

ተዋሕዶ ናት ክብርሽ ዘላለም፤

የገለጠችሽ ለመላው ዓለም።

አዝ

ኢትዮጵያ ይጻፍ አቡጊዳ የፊደል ገበታ፤

ኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ጥበብ የቁጥር አንደምታ።

ኢትዮጵያ ከተዋሕዶ ነው የያሬዳው ዜማ፤

የሥልጣኔሽ ቀንድ የአንችነታሽ ግርማ።

ብራና ወጥራ ታሪክ ከትባለች፤

እጅሽን ኅትታ አስተምራሻለች።

የዘመን መቁጠሪያ ቀምራ ሰጣሽ፤

ዛሬም ይከበራል አዲስ ዓመትሽ።

ስጫት ሰገነት ያንሳታል ገና፤

ለውለታዋ ይቁም በገና።

ተዋሕዶ ናት ክብርሽ ዘላለም፤

የገለጠችሽ ለመላው ዓለም።

(ዘማሪ ዲ/ን ትዝታው ሳሙኤል 2000 ዓ.ም)

**አባሪ ሁለት፡- የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን መዝሙሮች**

**1/ ኢትዮጵያን አስባት**

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን አስባት፤

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን አስባት።

በምሕረት ዐይኖችህ ተመልከታት፤

በምሕረት እጆችህም ዳስሳት፤

በፍቅርህ ደግፋት።

1. ቸርነት የለንም በደላችን በዝቶ፤

ልባችን ደንድኖ በኀ ስራ ትቶ።

አንተን ከቶ መፍራት በእኛ ውስጥ አልታይም፤

ማስተዋልን ስጠን ማስተዋል የለንም።

2. ኃጢአትና በደል ሰፍኖ በምድሪቱ

ምሕረትህን ላክላት ይታጠብ ኃጢአት፤

እስኪ ቀና ትበል በእጆችህ ደግፋት፤

ሕዝብህም ይጥለቅለቅ በመንፈስህ ሙላት።

3. ማለዳ ማለዳ አዲስን ምሕረትህ፤

ርህራሔ ደግሞ ከቶ አያልቅብህ።

አንዴ ዘንበል በል ሕዝብህም ይፈታ።

(የመቂ ኪዳነ ምሕረት ወጣት መዘምራን ማኅበር ቁጥር 3 አልበም 2006 ዓ.ም)

**2/ ተመለሽ ሀገሬ ኢትዮጵያ**

ተመለሽ ሀገሬ ኢተዮጵያ ፊትሽን አዙሪ፤

ከማንም ከምንም በላይ እግዚአብሔርን ፍሪ።

አዝ

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤

ወንዱ ሴቱ ወጣቱ አዛውንቱ፤

ይንበርከክ በፊቱ ምሕረቱ ዘለዓለም ነውና። (4)

1. እስኪ አስተውይው ዛሬ ያለሽበትን፤

ችግር ጉስቁልና በዙሪያሽ ያላውን።

ከዚህ ሊታደግሽ ጌታ በደጅ ነው፤

በፊቱ ውደቂ ዛሬም ምሕረት አለው።

2. ኃያላን ነገሥታት ጠቢባን ቢሆኑ፤

ስላንቺ መፍትሔ ማጣት ግን አልቻሉም።

መሮጥ መቅበዝበዙ ዛሬስ ይበቃሻል፤

ንቂ ኢትዮጵያ ጌታ ይሻልሻል።

3. የተስፋ ቃል ያለሽ ኢትዮጵያ አድምጪ፤

የልብሽን ጆሮ ለእግዚአብሔር ስጪ።

የምትኅበኝበት ዘመኑ ቅርብ ነው፤

ቃሉን የሚረሳ ጌታ ሰው አይደለም።

(የአዲስ አበባ መድኃኔ ዓለም ቁምሰና ወጣት መዘምራን ማኅበር ቁጥር አራት አልበም 2000 ዓ.ም)

**3/ ሰላምህ ይምጣ**

ሰላምህ ይምጣ ለሀገራችን፤

ሰላምህ ይምጣ ለምድራችን፤

እግዚአብሔር ነኝ ያለኸን የምትሰማን፤

እግዚአብሔር ነኝ ያለኸን የምትረዳን፤

ኢየሱስ ነህ ያለኸን የምትወደን፤

መንፈስ ቅዱስ ሰላምህ ይምጣልን።

1 ስትፈጥረን አንተ በአምሳልህ፤

ልንመስልህ ባህሪህን ልንካፈል፤

እኛ ግን አሻፈረን ብለን፤

በደልንህ በፍቅርህ ባኖርከን፤

ዛሬ ግን በቃን በቃን መልሰን፤

በአንተ ቤት ልንኖር ይኸው እንመርጣለን።

2 ልጅህን ለኛ ስትል ላከው፤

ፍቅርህን ይቅርታን ልትሰጠን፤

ስንጠፋ የምትፈልግ አንተ፤

የምትራራ ልጆችህን የማትጥል ነህ፤

የፍቅርህ ብዛት እጅግ ያስገርማል፤

በዛ ውስጥ መኖር ለእኛ እጅግ ይበጃል።

3 ሰላምህ ለሰው ልጅ ያደልከው፤

የሚያሳርፍ ሁሉን የሞላው ነው።

መች ገባን እንደተራ ቆጠርነው፤

የሚያዋጣን የሚበጀን እርሱ ነው።

መንፈስህ ይምጣ ይህን ያስረዳን፤

ወደአንተ ሰላም ጌታ እንመለስ።

(በመድኃኔ ዓለም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ወጣት መዘምራን ዘማሪያን ሀብታሙ ደጉ፣ አቤል ኦብሳ፣ ስምኦን ኃይሉ፣ ገብሬልዋ ቴውድሮስ፣ ሳሬም ሀብቴ 2013)

### 4/ ጌታ ለሕዝብህ ራራ

በፊትህ ወድቀናል ምሕረት ፈልገን፤

ልባችን ቀደን ከምር ተጸጸተን።

አቤቱ አስበን ይቅር በለንና፤

በምሕረትህ ጎብኘን ፊትህን መልስና።

ጌታ ለሕዝብህ ራራ፤

ጌታ ለኢትዮጵያ ራራ።

1. ኃጢአታችን በዝቶ አንተን አሳዝኗል፤

በምድር ተቅበዝባዦች ባዛኞች ሆነናል።

ደከመን ሰለቸን እንዲህ ያለ ሕይወት፤

በቃ በለንና ጎብኘን በምሕረት።

2. የሠራነው በደል ቁጥር ስፍር የለው፤

እባክህን ጌታ እርሳው አትቁጠረው።

የኃጢአታችን ጉድፍ በደምህ አንጻና፤

ዳግም ሰው አድርገን ይቅር በለንና።

3. የምሕረት አምላክ መማር አይሰለችህ፤

ዛሬም ኢትዮጵያን እያት በምሕረትህ።

ተስፋዋ አንተ ነህ እፎይ የምትልባት፤

ችግር መከራዋን የምትረሳበት።

(የአዲስ አበባ ኮንስላታ ቤተ ጸሎት ወጣት መዘምራን ቁጥር አራት አልበም 2001)

### 5/ አደራ ኢትዮጵያ

አደራ አምላኬ ኢትዮጵያን ሀገሬን አደራ፤

እባክህ ጠብቃት ከልጆቿ ጋራ።

ትማፀንሀለች ቀና ብላ ዛሬ፤

ያላንተ የላትም እርዳት መድኃኔ ዓለም

ሁናት መድኃኔ ዓለም።

1 የክርስቲያን ሀገር የእምነት መጀመሪያ፤

የአበው ማረፊያ የቅዱሳን መኩሪያ።

ተብሎ በታሪክ ስሟ የገነነው፤

ኢትዮጵያ ናት ርሷ ባርከኝ የምትለው።

2. ያለፈውን ዘመን በምስጋና አስታውሳ፤

መጪውን ዘመን በአንተ ተንተርሳ።

ልታድስ ቃልኪዳን ይኼው ፊትኽ አለች፤

ከሕዝቦቿ ጋር አንተኑ ትሻለች።

3. በአንተ ታምና ዛሬ በአንተ ሁሉን ጥላ፤

ተስፋዋ ከአንተ ውጭ የላት ሌላ መላ።

ነገንም አንተነህ አልፋና ኦሜጋ፤

እባክህ አትለያት ሕዝቧን አረጋጋ።

4 የጀመርከው ሥራ በእርሷ የወጠንከው፤

ሕዝቦቿን ለማዳን ቃል እንደገባኸው።

የፍቅር የሰላም የጸጋም ሁንላት፤

መጪውን ዘማኗን አንተ ክበርባት።

5 ትላንት የረዳሃት ሆነህ ለእርሷ ጋሻ፤

በከፋትም ጊዜ የሆንካት መሸሻ።

አንተ ብቻ ነበርክ ሌላ ማንም የለም፤

ኃያሉ እግዚአብሔር ግዛት ለዘለዓለም፡፡

(ዘማሪ ወንድማገኝ ሁሴን 2001 ቁጥር 1 አልበም)

## 6/ የምታምሪ ንግሥት

በጨለማው ዓለም ፋናሽ እንዲበራ፤

ወዳንቺ ስናዘግም ጠብቂን አደራ፡፡

ለእናት ሀገራችን ሁኚያት ባልደረባ፤

ጥላለች እምነቷን ቃልኪዳን ስትገባ፡፡

እጇን ዘርግታለች ያንቺ ርስት ኢትዮጵያ፤

ጠባቂያት እንዳትርቅ ከውድ ልጅሽ መንጋ፡፡

እጆቿን ዘርጊልን ነፍሳችን ስትወጣ፤

ቆመሽ ከእኛ ወገን ሁኚልን ጠበቃ፡፡

(የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤ/ን ዘማሪያን በዋሽንግተን ዲሲ ላይብ ያቀረቡት 2013)

## 7/ ኢትዮጵያ እጆቿን ዘርጊ

1. ዲያቢሎስ ተመቶ መጥመዱ ተሰብሮ፤

አንቺ ተፈወስሽ ቢቀርብሽ ኑሮ፡፡

ያለቀስሽው እንባ በደስታ ይለወጣል፤

አንቺ ተመለሽ እርሱ ያደርገዋል፡፡

ኢትዮጵያ እጆችሽ ዘርጊ ወደ ልዑል ጌታ፤

ይጎብኝሽ ያሰብሽ በምሕረት ዐይን ይይሽ፤

ክህደትሽ ትዕቢትሽን ከእግሩ በታች ጥለሽ፤

ታጠቢ ተመለሽ ሰላሙን ያልብስሽ፤

እንደ ነነዌ ሕዝብ አንች ተመለሽ፤

የናፈቀሽው ሰላም እንዲያጥለቀልቅሽ፡፡

እኔን ብቻ እይ ፈጣሪሽ የሚለው፤

ግራ ቀኝ አትበይ ቀናተኛ አምላክ ነው፡፡

(የአዲስ አበባ ቀርሜሎስ ቤተ ጸሎት መዘምራን ማኅበር ቁጥር ሁለት 1989)

## 8/ ኢትዮጵያ ትባረክ

ኢትዮጵያ ትባረክ በሽ ዓመት፤

ጌታ በሽ ዓመት፡፡

ምድራችን ትባረክ በሽ ዓመት፤

ጌታ በሽ ዓመት፡፡

አላት የተስፋ ቃል አንተ የገባህላት፤

እንለምንሃለን እንዲፈጸምላት፡፡

ረሃብ ቸነፈሩ ችግርም በሽታ፤

ከምድር ተወግዶ ይሁን ሰላም ደስታ፤

አሜን ይሁንላት ደስታ፡፡

ይስፈን ሰላምና ፍቅር፤

አይኑር መከራና ችግር፡፡

1 ፊትህን መልስ ኢትዮጵያን ጎብኛት፤

ተስፋ ረዳቷ አንተ ሁንላት፡፡

ጭንቀት መከራዋን ሁሉን ትረሳና፤

ስላንተ ክብር ታምጣ ምስጋና፡፡

አሜን…

2 ይነገር በዓለም መልካም ዜናዋ፤

ይቀየርና መጥፎ ታሪኳ፤

ዓለም ይደነቅ ይገረምባት፤

ክብርና ሞገስ አንተ ሁነኻት፡፡

3 ቃልህ እውነት ነው እናምንሃለን፤

አንተን በተስፋ እንጠብቃለን፡፡

ምድራችን ጌታ ሆይ እንድታስባት፤

እንደቸርነትህ እባክህ ጎብኛት።

4 ከአንተ የሆነ በረከትማ፤

እንዴት ልዩ ነው አቤት ሲስማማ።

መቼም አይደርቅም የዘላለም ነው፤

ይሁን ለኢትዮጵያ ይኸ ነው የምንመኘው።

(ኤደን ፍቃደ ሥላሴ፣ መዓዛ ዓለሙ፣ አሸናፊ ደበላ፣ ዘሪሁን እናውጋው፣ ዘማች ክብሩ፣ ዓለምዬ በሕብርት የሰሩት 2000 ዓ.ም.)

### 9/ አይበቃኝም

አይበቃኝም አመስግኜም አልጠግብም፤

አልረካሁም በዚህም አልተደሰትኩም።

ሲወዳደር ከሆንክልኝ ጋራ፤ (2)

ሲነጻጸር ከሠራኸው ጋራ። (2)

ያንሳሃል የኔ ተመስገኔ፤

ቃል አጣሁ ምን ልበል ጌታዬ፤

ሰው ሆነህ መምጣትህ ለኔ ለኔ።

መስቀል መሸከምህ ለኔ ለኔ፤

ሕይወትን መስጠትህ ለኔ ለኔ፤

በእንግልት መሞትህ ለኔ ለኔ። (2)

ለኔ ነው ይህንን የሆንከው፤ (2)

ለኔ ነው ይህንን ሞት የሞትከው፤

ዐይኖቹን አሳየኸው ለእርሱ ለእርሱ፤

ብርሃን ያሳየኸው ለእርሱ።

ኃጢአቷን ምረሐት ለእሷ ለእርሷ፤

ነፃ ያወጣሀት ለእርሷ ለእርሷ።

ለእርሱ ነው ብርሃን የሆንክለት፤ (2)

ለእርሷ ነው ነጻነት የሆንካት፤ (2)

ጎዘና ..ስምዓ ውብካያ፤

ለብሔርነ ኢትዮጵያ።

ድንጋይ ተንተርሶ ምሽቱን ሲያነጋ፤

ምኞት አጥታ ነፋሱ ሕይወቱ ሲናጋ።

አንተን መመኘትን አንተን መናፈቅን፤

የሕይወቱ ማዕዘን <u>እንዲሆን አሳስበው።</u> 2

እሷም ክብሯን ሽጣ ኑሮዋን ስትገፋ፤

ሕይወቷን ለማርዘም ስትሮጥ ስትለፋ።

ጌታ ሆይ መንፈስክ ከእርሷ ጋር በመሆን፤

መንገድ አቅጣጫዋን <u>ይምራት እባክህን።</u> 2

ኢትዮጵያ እጆቿን ዘርግታ፤

አንተን በመታመን ወዳንተ አቅንታ፤

ትማጸንሃለች እባክህ ታደጋት፤

በእቅፍህ ውስጥ አርገህ ዘወትር ጠብቃት።

(ዘማሪ ፋሲካ ተስፋዬ አጃቢ ዘማሪት ቤተልሔም ኃ/ማርያም 2013)

### 10/ ሰላምን ስጠን

እግዚአብሔር አባት ሆይ ፍጡርህን አትዘንጋ፤

በጨለማ የሚጓዝ የሕዝብህን መንጋ።

ሰላምን ተጠምቶ እጆቹን ሲያነሣ፤

ልቤ ተስፋ ቆርጦ ተከቦ በአበሳ።

ተሰማ ወይ ድምፄ ከጨለማው ጉድጓድ፤

ቆጠርከኝ ወይ እኔን ከበጎችህ እንደ አንድ።

ሰላምህን ለኔ ልታፈስ መጣህ ወይ፤

ፈቀድክ ወይ እንደዚህ በእውነት ጌታዬ ሆይ።

2 ዓለም ተሸብሯል በጦርነት መቅሰፍት፤

ፍቅርን ሰላምን ላክ ኢየሱስ የኛ አባት።

አማኑኤል ሆይ ና ግዛትህን ጎብኘው፤

የጠማውን ሰላም ሕዝብህን አጥግበው።

3 እመቤቴ ማርያም የብርሃን መንገድ፤

ሕዝብሽን ሰብስቢ አድርጊያቸው በአንድ።

የሕይወት ምንጭ ኢየሱስ ሰላም ተጠምተናል፤

ሁሉንም ትተነው አይነህል ናፍቀናል።

4 ዙሪያችን አየን በሙሉ ጨልሟል፤

ፈተናም በኛ ላይ ድልን ተመኝቷል።

የኛ አባት እግዚአብሔር ድልድዩን አሻግረን፤

ከወንድሞቻችን ባንድ ላይ ደባልቀን።

5 ለሀገራችን ኢትዮጵያ ሰላም ስለምንህ፤

ገናናው አባት ሆይ እንዳይርቀን ፍቅርህ፤

ሕዝቧን ፍሬዋንም ባርክልን በክንድህ፤

ዛሬም ለዘላለም ክበር እንበልልህ።

(የጽዮን ማርያም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ወጣት መዘምራን ቁ. 1 1986)

**11/ ክብር ምስጋና**

ክብር ምስጋና ማርያም ይድረስሽ፤

የዘወትር ተስፋችን አንቺ ስለሆንሽ።

1 በሰማይ ከዋክብት በፍጹም ታጅበሽ፤

በመላእክት ፊት ከብረሽ ተመሰገንሽ።

በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ክብር ያለሽ፤

ለኛ ለሁላችን እመቤታችን ነሽ።

2 መላእክት አወደሱሽ በአንች ስላለ ክብር፤

ስላንቺ ምስጋና እኛም እንዘምር።

ወድቀን ተንበርክከን ከመንበርሽ ስር፤

በአንቺ ይታደለን የሰማያት ክብር።

3 ፍልሰታ ማርያም መላእክት የከበቡሽ፤

ሊቃውንት በሕብረት ለአንቺ የዘመሩልሽ፤

የዓለም ኃጢአት ከቶ ያልዳሰሰሽ፤

በረቂቅ ውበትሽ ከእንቁ የነጠርሽ።

4 በቅድስት ሥላሴ ፍጹም የተባረክሽ፤

ቅዱን ስለክብርሽ በእውነት ያወደሱሽ፤

ሁሉም ስለ ፍቅርሽ የሚዘምሩልሽ፤

ለአንቺ ነው እመቤቴ ምስጋና የሚገባሽ።

5 ይሄ ዓመት ላንቺ ነው ደጓ እናታችን፤

ረሀብ ጦርነት እንዲርቅ ከሀገራችን።

ኢትዮጵያ ርስትሽ ናት የልጅሽ ስጦታ፤

ሕዝቧን ጠብቂላት ሁኝላት መከታ።

(የጽዮን ማርያም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ወጣት መዘምራን ዓ.ም.1984 ዓ.ም.)

**12/ ምሕረትን ላክልን**

ጌታ ሆይ ኃጢአት ሠርተናል፤

ስለዚህ ልባችን ታሟል።

ስለዚህ ነገር ዐይናችን ታሟል፤

ስለዚህ ነገር ልባችን ፈዟል።

አቤቱ መልሰን እኛም ወዳንተ እንመለሳለን፤

ዘመናችንን እንደቀድሞው አዲስ።

አቤቱ እንደቸርነትህ ማረን፤

እንደምሕረትህም ብዛት።

መተላለፋችንን ደምስስ አሜን፡፡

አዝ

ምሕረትን፤12 x

ምሕረት ላክል ለምድራችን፡፡

ከአመጽ ከጥፋት አድናት፤

ምሕረት ላክልን ለሕይወታችን፤

ምሕረት ላክልን ለቤታችን፡፡

ምሕረት ላክልን ለሀገራችን፤

ምሕረት ላክልን ለዓለማችን ምሕረትህን፡፡

1 ኦ የምሕረት አምላክ ነህና፤

በሥራህ ትክክል ቅን ነህና፡፡

በሃሳብህም ሁሌ ትክክል ነህ፤

ጌታ ሆይ እንደሰው አይደለህ፡፡ 4X

4 ብዙ ኃጢአት ሠርተናል፤

ምሕረት ያሻናል፡፡

በደላችን አንተን በጣም አሳዝኗል፤

ይቅር በለን ጌታ በፊትህ ወድቀናል፤

ማረን የኛ ኢየሱስ ሁሉ ይቻልሃል፤

ይቅር በለን ጌታ በፊት ወድቀናል፤

ማረን የኛ ኢየሱስ ሁሉ ይቻልሃል፡፡

ምሕረትን ለምድራችን ምሕረትን፤ (2)

ምሕረትን ለፍጥረታት ምሕረትን (2)

ምሕረትን ለሕይወታችን ምሕረትን፤ (2)

(የሻሸመኔ ጽዮን ማርያም መዘምራን 2007 ዓ.ም.)

**አባሪ ሦስት- የኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት ነሽዳዎችና መንዙማዎች**

**1/ ሀገሬ ቁ 2**

ሀገሬ ሀገሬ ደረትክን ስጥ ቢሉኝ ለጠላት ቀልደኛ፤

ዘብ ቁምለት ብባል ሌት ተቀን ሳልተኛ፡፡

ለአፍ ወለምታ እንኳ ከቶ ሳላቅማማ፤

እሞትልሻለሁ ሀገሬ ሀገሬ ለአንቺማ፡፡

ሀገሬ (4)

ሀገሬ ደስታዬ እማማ ብርቱዋ፤

አንቺ ለኔ ኑሪ እኔ ላንቺ ልሠዋ፡፡

የጥቁርነት ልክ የቢላሉ እናት፤

የፍትሐዊው መሪ የነጃሽ እኮ ናት፡፡

ለክብሯ ለስሟ ሞተው እንዳኖሯት፤

ዛሬም እንደ ትናንት ሀገሬ ጀግና አላት፡፡

በፍቅርሽ ቃጠሎ ንዳድ ተንገብግበው፤

በሰንደቅሽ ውበት ላይ ከታች አብበው፡፡

ለስምሽ ሀገሬ ስማቸውን ያጡ፤

የተዋደቁልሽ ቀኑ እንደወጡ፤

በሰሜን በደቡብ በምዕራብ በምሥራቅ፤

ነፋሱን የሠዋልሽ ሀገሩን ለማላቅ፡፡

እንደንጋት ፀሐይ ተስፋዬ በአንቺ ላይ፤

ለምልሚል ሀገሬ ፈክተሽ ደምቀሽ እንድናይ፡፡

እኔ በአንቺ ልታይ ልጠራ በስምሽ፤

ወንድሜን ተው በይው አይግፋኝ ከእቅፍሽ፡፡

እኔም የአንቺው ልጅ ነኝ እርሱም ካንቺ ማሕፀን፤

ካንቺ ሌላ የታለ አዋዶ ሚቀርጸን፡፡

ጀሊል ይስማሽ እንጂ ይይሽ በእዝንቱ፤

በደም እንዳይቆሽሽ እንዳይከፋ ቤቱ፡፡

እምዬ ሀገሬ ላንዱ አላዳላሽም፤

ለግራም ለቀኝም እቅፍ አያጥርሽም፡፡

እንዋደድበት መልሺ ወንድሜን፤

በረባው ባረባው አያፍስሰው ደሜን፡፡

እምዬ ኢትዮጵያ ላንዱ አላደላሽም፤

ለግራም ለቀኝም እቅፍ አያጥርሽም፡፡

እንዋደድበት መልሺው ወንድሜን፤

በረባው ባረባው አያፍስሰው ደሜን፡፡

ሀገሬ አላህ ይጠብቅሽ፡፡

(አሸርፍ ናስር 2013)

**2/ ኢትዮጵያ**

ኢትዮጵያ የአንቺ የሰላም ምድር (2)

የፍቅር የፍትሕ የአንድነት የኅብር (እማማ) (2)

ኢትዮጵያ አላህ የመረጠሽ ነብይ ያወደሱሽ፤ (2)

ሀገሬ እናቴ ነሽ፡፡ (2)

የዓለም ስልጣኔ የጥበብ አሻራ፤ (ኢትዮጵያ)

ደግም የታየብሽ የነጻነት ጮራ፡፡

ቀዳማዊ እመቤት የጥቁሮች አምባ፤

አንቺ ነሽ ኢትዮጵያ የአርነት ካባ፡፡

በረከት የሞላሽ የተፈጥሮ ጸጋ፤

የቃል ኪዳን ምድር ሰው የመሆን ዋጋ፡፡

የአምላክ ጥበቃ ዙሪያሽን ያጠረሽ፤

በነቢያት ልሳን በክብር የተወሳሽ፡፡

የፍትሐዊነት ቅርስ የእኩልነት ግርማ፤

የሰላም አብነት የጀግንት ግርማ፡፡

የጭቁኖች ጥላ ማረፊያ መሸሻ፤

የግፉአን መርጊያ ቤትሽ መዳረሺያ፡፡

አደራን ተቀባይ ከሳር ከቅጠሉ፤

በፍቅር የሚያድርባት እርሷን ያለ ሁሉ፡፡

የብዙኃን እናት መጠለያ ካሰማ፤

የአብሮነት ተምሳሌት ኢትዮጵያዬ እማማ፡፡

አዝ

የልዩነትን ካብ በአንድነት አፍርሰን፤

የጥላቻን አጥር በፍቅር አድሰን፡፡

ተዋዶ መኖርን የሚያሳዩ ለዓለም፤ (2)

ሰላምን ዘማሪ ልጆች አሉሽ ዛሬም፡፡

በይቅርታ ድልድይ ጥላቻን ተሻግረው፤

ፍቅርን ያስበለጡ ቂም በቀልን ሽረው፡፡

እንደ አንድ ቤተሰብ ሆነው ያረፉብሽ፤

አንቺ ነሽ ኢትዮጵያ ዓለም የሚያከብርሽ፡፡

(ኢትዮጵያ ቶፊቅ የሱፍ ሙዐዝ ሀቢብ ዓ.ም. 2011)

**3/ ኢትዮጵያ**

ሀገሬ ሀገሬ፤

የሰላም ምድር የፍትሕ ጀምበር፤

ጎህ እንደቀደደ ነጻ እስክንወጣ፤

ፍትሕ እስኪሰፍን ሰላም እስኪመጣ፡፡

ሒዱ ወደ ሐበሻ ወደ ሰላም ሀገር፤

እዚያ ንጉሥ አለ አማኝ የሚያፈቅር፡፡

እዚያ ንጉሥ አለ እንግዳ ሚያከብር፤

እዚያ ንጉሥ አለ ስለ እውነት የሚኖር፡፡

ተብሎ ተመስክሯል ለዓለሙ መብራት፤

ለሰው ልጅ ከተላኩት ለእዝነት፡፡

ኢትዮጵያ የሰላም ምድር፤

ኢትዮጵያ የፍትህ ጀምበር፡፡

በፈተናና በችግር፤

የአማኞች መሸሻ ሀገር፡፡

ሀገሬ ሀገሬ፤

የእኔነት ጅማሬ፤

ሀገሬ ሀገሬ፤

የፍቅር ዝማሬ፡፡

ማሕፀንሽ ለምለም፤

የእነ ቢላል እናት፤

ስምሽን የሚያስጠሩ ሐበሻዊ ኩራት፡፡

እልፍ ጀግኖች አሉሽ፤

ለዓለም ስጦታ፤

ለሰው ልጆች ሰላም፤

ለሰው ልጆች ደስታ፤

ከዘመን ጅማሬ ዘመን እስኪለወጥ፤

ገናናው ስምሽ ታሪክሽ ሲገለጥ፡፡

ቢከፈት ድርሳኑ ቢቀራ ሐዲሱ፤

ብዙ መረጃዎች አንችን ነው ሚያወሱ፡፡

አዝ

አውቃለሁ ከፍቶሻል ሰርክ እንባሽ ይፈሳል፤

ኃዘንሽ ብርቱ ነው ባዳን ያስለቅሳል፡፡

በልጆችሽ ግጭት ልብሽ ቢሰበርም፤

ደስታሽ ይመለሳል ቀን መምጣት አይቀርም፡፡(2)

ያልፋል እናት ዓለም ክብርሽ ይመለሳል፤

ያስለቀሰሽ ባዳ ራሱ ያለቅሳል፡፡

በልጆችሽ እቅፍ እንባሽ ይታበሳል፤

ሊያፈርስሽ ያሰበው ራሱ ይፈርሳል፡፡

(ሙነሽድ ሑስኒ ሱልጣን እና አብዱልሰላም
አበራ 2013)

**4/ ጠብቃት ሐበሻን**

ያረቢ ያራህማን፤

ጠብቃት ሐበሻን፤

የቢላልን ሀገር የነነጃሽን፤

በእዝነት ዐይንህ እያት አንተው **ያራህማን፡፡**

ዓለም መሽ ጨለመች ምድሪቱ፤

ደመናውም ከፋ ራደች ሰማይቱ፡፡

ባሕሩም ጠቆረ ረገፉ አበቦች፤

ፀሐይቱም በረታች በሐበሻ ልጆች፡፡

ኑሮ ልኳ ናረ ከሰው ልጅ በላይ፤

ኒዕማው እያነሰ ሲወርድ ከሰማይ፡፡

ሕይወት ጣዕሟ ጠፋ ጊዜ ሬት ሆና፤

አኺራ ተረስቶ ኪዳን ሲኮን ኦና፡፡

አዝ

ዕዝነት አፈር ገባ ሰው በሰው ቆሰለ፤

የወንድምም አንጀት ለወንድም አልበጅ አለ፡፡

ሀገርስ ነበረን እንደሌላው ሀገር፤

መዋደድ ሊሳነን መረረን ቸነፈር፡፡

እናትም ስታጣ የወለደችውን፤

የስደት ማዕበል ነጥቆባት ልጇን፡፡

ሰው ሁሉ ተከፋ በረካን በማጣት፤

ያረቢ ኑስራህን ያዘነ ይደሰት፡፡

አዝ

ባርካት ሐበሻን የነጃሽን መንደር፤

እርቅ በል ያአላህ የቢላልን ሀገር፡፡

ቁጣህም ይብቃና እባክህ **ያርህማን**፤

ዕዝነት ተራው ይሁን ታርቀህ ሐበሻን፡፡

መዋደዱ ሰፍኖ ፍቅር ከላይ ይሁን፤

አደራ የአላህ ሩሀማን አልብሰን፡፡

ማጣት ተወግዶ ጭካኔ እና ምሬት፤

የሳቅ ዘመን አድርገው የሰላም **የዕዝነት**፡፡

አዝ

ሰላም ካንተ ሆኖ እምነት እና ፍትሕ፤

ሁሉም ሀቅ ይዳኘው ያጀሊል ኑስራህ፡፡

ከሰማዩ ይውረድ የራህመት ዝናም፤

ኢማን እና ደስታ ከጅህልና ቋጥኙ፡፡

ከሽርክ አላቀኸን ------------------

በሐበሻ ምድር በረካን ወፍቀን፤

የበሰለ ዕውቀት አሳውቀንና፤

እባክህ ያራህማን አውጣን ከፈተና፡፡

ለነ ቢላል ሀገር ለነ ኡሙ አይመን፤

እባክህ ያረቢ ምሕረትክን ወፍቀን፡፡

(ሙነሽድ ሙአዝ ሀቢብ እና አሽረፍ ናስር 2010 (2011))

**5/ ዳሩል <u>ሂጅረተይኒ</u>**

ዳሩል ሂጀርተይኒ ሀገሬ ኢትዮጵያ፤

ለስንቱ ሱሐባ ሆነሻል መጠጊያ፡፡

ኢትዮጵያ ሀገሬ ብዙ ነው ዝናሽ፤

ታሪክሽ ቢደበቅ እኔ ላውጣልሽ፡፡

የአላህ መልእክተኛ ለይተው ከሌላ፤

ጥሩነትሽ አይተው መረጡሽ ለጥላ፡፡

ጥንስሱ ሲጀመር በመካ ምድር፤

የአላህ መልእክተኛ በሰጡት ምክር፡፡

ለሱሀቦቻቸው **ለዲኑ ቀመር**፤

ወደ ሐበሻ ሒዱ እስኪያልፍ ችግር፤

እዚያ እነርሱ ዘንድ ማንንም ማይበድል፤

ታላቅ ንጉሥ አለ ሊረዳን የሚችል፡፡

ምክራቸውን ሰምተው ወደ ሐበሻ ሔዱ

የሰላም ሀገርን ለቀው ተሰደዱ፡፡

አዝ

ዳገት ቁልቁለቱን እያቆራረጡ፤

ወደ አርዱል ሐበሻ ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡

ንጉሡ ፊት ቀርበው ሌሎቹ ሲነሱ፤

ሱሐቦች እምቢ አሉ አንሰግድም ካለሱ፡፡

የቁረይሽ ተወካይ ጥያቄ አቀረበ፤

እነዚህ ንፁሐን ለመውሰድ ቀረበ፡፡

አመጣጣቸውን አይተው ስላዘኑ፤

የሚሉትን ነገር ለመስማት ፈጠኑ።

ሰይድና ጃፋር ካሉበት ተነሡ፤

በትህትና ቃላት ቀረቡ ለመልሱ።

እኛ የመጣነው ጉዞ የጀመርነው፤

የመካ ቁርይሾ ስላስቸገሩን ነው፤

በአላህ እመኑ ስላልን ብቻ ነው።

አዝ

ያታዊ ጭቆና ገኖ በወጣበት፤

የእጆቻችን ውጤት አምላክ በሆኑበት።

ታላቅ ብሥራት መጣ በዚህ ክፉ ዘመን፤

አላህ ነብይ ላከ ከመሀከላችን፤

እንደ ኢሳ ሙሳ ያኽያ ዘካሪያ፤

አስጠንቃቂ ቢላክ ምን ይገርማል ታዲያ።

ፍትሓዊው መሪ ዐሳብ ሰነዘሩ፤

ስለ ኢሳ ጉዳይ መጠየቅ ጀመሩ።

ሱረትል መርየምን ጃፈር አነበቡ፤

አህመዲን ነጃሽ ወዲያውኑ አነቡ።

የታሪኩ ይዘት እጅግ ማረካቸው፤

ቃላቸውን ሰጡ ለአገልጋዮቻቸው፤

እውነተኛነቱን ስለተረዷቸው።

ከምግብም አብሏቸው ከመጠጥም አጠጧቸው፤

ከለላዬንም ስጧቸው መንገዳቸው መንገዴ ነው።

(አሊ አሚን፣ ፉአድ በሽር በፈረንጆቹ 2013)

**6/ የብሥራት ዜና ተሰማ**

ለጀሰድ የሚመች ለሩህ የሚስማማ፤

ቢይዙት ሰንሰለት ቢገደፉት ካስማ፤

እንደህል የሚርብ እንደውሃ ሚጠማ፤

ወንድም አይደለም ወይ የወንድሙ ሸማ።

ልክ ሆኖ ባይገጥም መክደኛው ተዛንፎ፤

ቢያስተካክል እንጂ ቀድሞ ተሰልፎ፤

ይቅር ሳይባባል ወንድም ተኮራርፎ፤

ለአንድ ቀን ይጨንቃል እንኳን ዓመት አልፎ። (2 ጊዜ)

አዝ

የብሥራት ዜና ተሰማ ሰማያት ምድሩ ደመቀ፤

በአብሮነታችን ብርሃን አድማሱ አንፀባረቀ።

በአዲስ ምዕራፍ ጉዞ በአብሮነት ታሪክ ልንሠራ፤

እጅ ለእጅ ተያይዘን ቆመናል ዛሬ በጋራ።

አዝ

እንዴት ልብ አስቻለው አንጀትስ ደነደነ፤

ወንድም ያላመሉ በወንድሙ ጨከነ?

ምነው ምላሽ ጠፋ አኺራን አስታዋሽ፤

ወንድም ከዐይን ሲርቅ ሲነጠል ሲሸሽ።

መች እረፍት አገኘሁ ርቄ ከወንድሜ፤

ቆየሁ ስንከራተት ጠንቶብኝ ሕመሜ።

ተቆጥሮ አይዘለቅ የጎደለብኝ፤

እንዴት አርጎህ ይሆን እኔን ሆድ ባሰኝ።

አዝ

የሐበሻ ምርኩዜ ጋሻ መከታዬ፤

ተለየሁ ከደስታ አላውራ አልሳቅ።

ባይተዋር አረገኝ ከእቅፍህ መራቅ፤

ስንት ጉዳይ አለኝ ያላንተ ማይሞላ፤

ዛሬ በዱንያ ላይ ነገ በአርሽ ጥላ፡፡

የሔድኩበት መንገድ የቀና መስሎኝ፤

ስጠፋ ሚመልስ ወንድም አሳጣኝ፡፡

አዝ

ትፈቅድ እንደሁ ልምጣ ወዳለህበት፤

ሳይገለኝ ኀዘኑ ሳልሞት በፀፀት፡፡

አሳርፋት ነፍሴን ይቅርበለኝና፤

የነገው አቀበት ዛሬ እንዲቀና፡፡

የሔድንበት መንገድ ልክ አልነበረም፤

ወንድም አስረስቶ ለነፍስ ያደለው፤

በእናቶች ለቅሶ በአባቶች ልመና፤

ታሪክ ሊሆን በቃ ያ ሁሉ አለፈና፡፡

አዝ

የተሸከምነውን የትውልድ አደራ፤

ከስኬት ለማድረስ በአብሮነት በጋራ፡፡

ቂም በቀልን ሽረን ይቅርታን መርጠናል፤

በአንድነት ለመቆም ይሄው ቃል ገብተናል፡፡

በጽናት በተስፋ አልፈናል ያን መከራ፤

ነፍስያን ረግጠን ለመጓዝ በጋራ፡፡

ጥላቻን በፍቅር ዛሬ ድል ነስተን፤

እኛ ተሸንፈን እኛ አሸነፍን፡፡

በሙሀባ ሙላት የዘጋው ልባችን፤

አደራ ነውና የቃል ኪዳናችን፡፡

ብሩህ ነገን ማየት በውስጣችን ነግሦ፤

ዳግም ተቃቀፍን በናፍቆት በለቅሶ፡፡

(በሕብረት የቀረበ  አሊ አሚን  ሙአዝ ሀቢብ ሙሀመድ አወል ሳላህ. ነስሩ ኸድር. ሙሀመድ ሰዒድ አስማማው አህመድ ቶፊቅ የሱፍ 2012)

7/ ታረቀን

ከክልከላ መንደር ስኳትን ከርሜ፤

ባዘዝከው መደብ ላይ ሳይታወቅ ስሜ፡፡

የወንጀሌ ብዛት ከቅዱሱ ስፍራ ከቤትህ ካራቀኝ፤

አዛኙ ጌታዬ በእዝነት በራህመትህ ሳልጠፋ ታረቀኝ፡፡

አዝ

ወለምታ ማያጣው ቅጥ ቢያጣ ምላሴ፤

ሐሜት መዝናኛዬ ነገር መውሰድ ሱሴ፡፡

ሆኖ ስኖር ኖሬ እጄ ደም አፍስሶ፤

አመድ አፋሽ ግብሬ ጎዳኝ ተመልሶ፡፡

መጥፎ ነገር ያዬ ሔዶ ያስቁመው፤

በልቦናው ይጥላ ሌላ ሰው ያልቻለው፡፡

ዓለም ተመልክቼ በጄ ሳልጠላው፤

የስራ አቂባዬ? ደረሰ በኔው፡፡

ኪታቤ ሲሞላ በሰው ሀቅ ናዳ፤

መጥፎ ምትክ ይገፔ በስሜት ስነዳ፡፡

ሲጎድል ሲቀንስ የአኺራ ወራቴ፤

ሳይሰማ ቀረ ልመና ጸሎቴ፡፡

አዝ

የበላው? ንፋስ የያዘን ሸፍኖ፤

መድረሻ ሳናጣ ሳያበስለን ከድኖ፡፡

የእዝንቱ ንፋስ ሰላም ያደረገ፤

አምጣልን ጀሊሉ የተሸለ ነገ፡፡

ምድርን ለፈሳድ አጭተው ሲባክኑ፤

በየአደባባዩ የሰው ዘር ሲያድኑ፡፡

የማይታይ ጁንድህ ጥላት ይዳብሳል፤

ገዳይ ሲያረፋፍድ ሟች ይገሰግሳል፡፡

በቀለም በቆዳ በዘር ሲቧደኑ፤

ነጭ ጥቁር ብለው ፍጡር ሲኮንኑ፡፡

ምድራችን አነባችን ህልቁም ረገፈ፤

አለሁ ያለው ስልጡን ደርሶ እየሰነፈ፡፡

ታረቀን ታረቀን እንዲሁ ታረቀን፤

ያመሰኩህን ያህል በቂል ተደግፌ፤

ማልቀስ ጀምሬያለሁ ደግ ተሰልፌ፡፡

ሀገሬን እላለሁ ላለቅስ እዳዳኝ፤

የሙት እናት ስትሆን ኀዘኗ እንዳይጎዳኝ፡፡ (2 ጊዜ)

(**የኅብረት ነሽዳ** ሙንሺድ አስማማው አህመድ፤ ሙንሺድ ኢስማኤል ተክሌ ሙንሺድ ሐሰን ዑመር ዓ.ም.2012 (2013))

## አባሪ አራት፡- የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት መዝሙሮች

### 1/ የጥበብ ጌታ

እኔም ኢትዮጵያ ነኝ፤

ብዙ እንቆቅልሽ አለኝ፡፡

ጌታ አንተም ንጉስ ነህ፤

እንቆቅልሽን መፍታት ታውቃለህ፡፡

የዕውቀት የጥበብ ጌታ፤

እንቆቅልሼን ፍታ፡፡

በዛና እንቆቅልሼ፤

ለብዙ ዘመን አልቅሼ፡፡

አንድ ቀን ዝናህን ሰማሁ፤

ልንገርህ ከሳባ መጣሁ፡፡

ተቀመጥ በዙፋንህ፤

የልቤን እድነግርህ፡፡

እኔም.....

በግመል ሽቱ ጭኛለሁ፤

ወርቅና እንቁም ይዤአለሁ፡፡

ደክሞኛል ጓዜ ብዙ ነው፤

አድምጠኝ ያኔ አርፋለሁ፡፡

ሀገሬን ሕዝቤን ወክዬ፤

እኖራለሁ ቃሌን አክብሬ፤

ከእግርህ ስር ልውደቅ ጌታዬ፡፡

እኔም...

ሰማይን ምድርን ፈጥረሃል፤

በጥበብ ሁሉን አርገሃል፡፡

ከዐይንህ የተሠወረ፤

አሸንፎህስ የኖረ፡፡

ንጉሥ ሆይ ኧረ ምን ነበር፤

ፍታልኝ የኔንም ነገር፡፡

እኔም....

ገና ጥንት ሳለሁ ባገሬ፤

ስላንተ ብሰማም ወሬ፡፡

ማመን ግን አቅቶኝ ነበር፤

ልክ የሰው የእውቀትህ ነገር፡፡

ጥበብን አዕምሮን ያልፋል፤

ከሰማሁት ዝና ይበልጣል፡፡

እኔም…

(ዘማሪ ታምራት ኃይሌ ቁጥር 6 1985)

**2/ እየመሸ ነጋ እየነጋም መሼ**

እየመሸ ነጋ እየነጋም መሸ፤

ዛሬም ጉስቁልና ከምድራቱ አልሸሸ፡፡

የነገዋ ፀሐይ ሙቀት ይዛ ትምጣ፤

የሀገር ልጅ በርዶታል ድሪቶም ስላጣ፡፡

አዝ

ከትናንት ዛሬ ይሻል ይሆን ብለን፤

የበጎ ቀን ያልንህ አልመጣም ጠብቀን፡፡

በደረቀ ላንቃ ውኃ እያረረበት፤

አየን በአደባባይ ፍጥረት ሲንከራተት፡፡

አዝ

ገና ነው ምሕረቱ አልወረደም፤

የሀገሬ ንዳድ ዛሬም አልበረደም፡፡

ገና ነው ቁጣው መቸ ሰከነ፤

በሽታና ረሀብ በሀገሬ ገነነ፡፡

አዝ

በረሀብ ጉስቁልና በጥማት ተቃጥሎ፤

በብርድ ተጠብሶ በፀሐይ ከሳስሎ፡፡

ኑሮ እንዴት መሮት ለሞቱ የሚጎመጅ፤

በጎዳናው ከፈፍ ተዘርግቷል እደጅ፡፡

አዝ

እየመሸ ነጋ እየነጋም መሸ፤

ዛሬም ጉስቁልና ከምድራቱ አልሸሸ፡፡

የነገዋ ፀሐይ ሙቀት ይዛ ትምጣ፤

የሀገር ልጅ በርዶታል ድሪቶም ስላጣ፡፡

አዝ

ማረን ጌታችን ፈጽመህ አትቅጣን፤

ጠበልክን እርጬን ጠምቶናል አጠጣን፡፡

ታማሚው ይፈወስ የራበው ሰው ይጥገብ፤

የፍርድ ዐዋጅ በቅቶ ምሕረቱ ይነበብ፡፡

**ክራላይሶ** (2) **እግዚኦ መሐረነ** ክርስቶስ

(ዘማሪ ዶክተር ደረጀ ከበደ ቁጥረ 8 2005)

**3/ ብርሃንሽ ወጥቷልና ኢትዮጵያ**

አዝ፡- ተነሽና አብሪ (8)

የኃያላን የታላቅ ሀገር ታሪክሽ፤

የተስፋ ቃል የወንጌልም ዘር ያለብሽ፡፡

ሰላምሽ ርቆ ብዙ ደም ፈሶብሻል፤

የስልጣኔ መጨረሻ ተብለሻል፡፡

የመከራ ሌሊትሽ ነጋ በርሱ ጊዜ፤

የምታብሪበት ዘመን ነው የሕዳሴ፡፡

ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ፤

የከፍታ ዘመንሽ ሆነልሽ፤ (2)

አዝ፡- ተነሽና አብሪ፤ (8)

ብሎም ለአፍሪካ ደግሞም ለአውሮፓ ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ፤

ብርሃንሽ ወጣ ትንሣኤሽ መጣ ክብርሽን አዩ።

የፈጣሪሽ ፊት ወዳንቺ ዞረ ልብሽ ተመልሶ፤

ሁሉም እዲያይሽ እንድታበሪ እጅሽን ይዞ።

አዝ፦ ተነሽና አብሪ (8)

የፖለቲካ የኢኮኖሚ ቀውስ ሁሉ፤

ከሰማይ ትእዛዝ ሲወጣ ሰላም ሆኑ።

ዘረኝነትና ጥላቻ ቦታ አጣ፤

የፍቅር መንፈስ ሕዝቡን ሁሉ ይዞ መጣ።

የዘንዶውን ራስ አምላክሽ ቀጥቅጦታል፤

አዝመራሽ ሁሉ ተባርኳል ፈውሶሻል።

ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ፤

የከፍታ ዘመንሽ ሆነልሽ፤ (2)

አዝ፦ ተነሽና አብሪ፤ (8)

ብሎም ለአፍሪካ ደግሞም ለአውሮፓ፤

ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ፤

ብርሃን ወጣ ትነሣኤሽ መጣ ክብርሽን አዩ፤

የፈጣሪሽ ፊት ወዳንቺ ዞረ ልብሽ ተመልሶ፤

ሁሉም እንዲያይሽ እንድታበሪ እጅሽን ይዞ።

አዝ፦ ተነሺ አብሪ (8)

በረሀብ በስደት ሕዝብሽ ተበትኖ፤

ሲናቅ ሰው ሀገር የሰቀቀን ኑሮ።

የናቁሽ ሁሉ የተጠየፉሽ፤

ጊዜው ሲመጣ ይኼው ሰገዱልሽ።

ቀና በይ ከእንግዲህ፤

ቀና በይ ጊዜሽ ነው፤

ቀና በይ አትፍሪ፤

ቀና በይ አብሪ።

(ዘማሪ ዮሴፍ ከበደ ቁጥር 2 2006 ተነሽና አብሪ)

**4/ ሰላም**

አዝ ሰላም (3) ሰላም ኢየሱስ ነው፤(2)

ደጁ ሳይከፈት ግድግዳው ሳይፈርስ፤

የሰላሙ ጌታ ገባ ኢየሱስ።

ለተጨነቁት ግራ ለገባቸው፤

ሰላም ለእናንተ ይሁን ብሎ አሳፈራቸው።

አዝ፦ ሰላም (3) ሰላም ኢየሱስ ነው (2)

የሀገር መሪዎች ክብር ስልጣናችሁ፤

የውክልና ነው ወዶ የሰጣችሁ፤

ሞኝነት ቢመስልም ጌታን ተቀበሉ፤

ሕዝቡን እንድመራ እኔን ምራ በሉ።

አዝ፦ ሰላም (3) ሰላም ኢየሱስ ነው፤ (2)

አውራጃው ወረዳው ቀበሌም መንደሩ፤

ንግዱም ሃይማኖቱም እድር ማኀበሩ፤

ምድር እንዲፈወስ አየር እንዲጠራ፤

ሁሉም እጁን ያንሳ ኢየሱስን ይጥራ።

አዝ፦ ሰላም (3) ሰላም ኢየሱስ ነው፤(2)

ምሁር ነህ ተማሪ ሐኪም ገበሬው፤

ኢየሱስ ያድናል ጥሪው ላንተም ነው።

የትዳርህ ኪዳን ጎጆህ አይፍረስ፤

የሰላሙ ልዑል በቤትህ ይንገሥ።

አዝ፦ ሰላም (3) ሰላም ኢየሱስ ነው፡፡(2)

መጠጥና ዘፈን ኀበዝና ቆንጆው፤

አቃወሰህ ጤናህ አፈረሰ ጎጆው፤

ደግሞ የእሳት ፍርድ አለ ከዚህ የባሰው፤

የአምላክ ጥሪ ሰምቶ ላልተመለሰው፤

አዝ፦ ሰላም (3) ሰላም ኢየሱ ነው፡፡ (2)

(ፓስተር ታምራት ኃይሌ ቁጥር 12 2009)

**5/ ኢትዮጵያ ሃገሬ**

አዝ፦ ኢትዮጵያ ሀገሬ እጆችሽን የምትዘረጊበት፤

ሰዓቱ ደርሷል እንባ ሚደርቅበት ካፈርሽ፤

ሰላም ይታጨዳል ከወንዝሽ፡፡

ዓለም ይባረካል ዓለም ይባረካል፤(2)

አዝ

አያለሁ አዲስ ቀን ከደመናው ማዶ፤

ብርሃን ሲወጣልሽ ጨለማውን ቀዶ፡፡

የራቁት ልጆቹሽ ይሰበሰባሉ፤

እውነትም እግዚአብሔር ኃያል ነው እያሉ፡፡

ባማሩት መቅደሶች ወንጌል ይሰበካል፤

ሕፃን ሽማግሌው ለአምላክ ክብር ያመጣል፡፡

እግዚአብሔርም ቃሉን በተአምር ያጸናል፤

ሊሠራ ሲወጣ ማን ይቃወመዋል ማን ይከለክላል፡፡

አዝ

ዕውቀትና ጥበብ ከአምላክ የተሞሉ፤

ኃጢአትን ጠልተው ለጽድቅ የሚኖሩ፤

አዋይና ዝና ከቶ ማይገዛቸው፤

ለፍርድና ለእውነት ቅናት የበላቸው፡፡

ልጆች አሉሽ ገና ተግተው የሚነሡ፤

ለምስኪኑ መውደቅ ከልብ የሚሳሱ፡፡

የተገባልሽ ቃል በእርግጥ ይፈጸማል፤

አምላክሽ ሊያድንሽ ሊታደግሽ ወጥቷል፡፡ (2)

(ተስፋዬ ጫላ ቁጥር 4 1998)

**6/ ኢትዮጵያ**

ኢትዮጵያ 2 እማማ ሀገሬ ኢትዮጵያ፤ (2)

ኢትዮጵያ 2 እማማ ሀገሬ ኢትዮጵያ፡፡ (2)

አዝ

ሰላም እፎይታሽን አድብቶ ሚናጠቅ፤

ክፉ ጨካኝ አውሬ ዲያቢሎስ ደም አፍሶ ሚስቅ፡፡

ወንድም ከወንድሙ እያገፋተረ፤

በትውልዱ ልብ ውስጥ አመጻን ጥላቻን ያኖረ፡፡

አዝ

ዛሬ በአምላክ ስልጣን ትእዛዝ ከላይ ይውጣ፤

ጠላትሽ ይሰየፍ በጌታዬ ቁጣ፡፡

ዳር ድንበር ዙሪያሽን ይጠርሽ በእሳቱ፤

የጨለማው ምክር ይሁንባት ከንቱ፡፡

አዝ

(ኢትዮጵያ) ሀገሬ

እናት እናት ሀገሬ እጆችሽን ዘርጊ፤

እናት እናት ኢትዮጵያ…ኦሆሆ

አዝ

በምሥራቅ በደቡብ በምዕራብ በሰሜኑ፤

ልጆችሽ ጥላቸውን አዋድቀው በኅብረት ያብሩ።

በሕዝብሽ ላይ ይታይ ይቅርታ ውሕደቱ፤

ለቂም እምቢ ብለው በአንድነት ለፍቅር ይዘመቱ።

አዝ

እውነት በአደባባይ ይታይ በከፍታ፤

የሐሰት ምስክር የሚሰማው ይጣ።

እናቶች አባቶች ወጣት ልጆች ሁሉ፤

ከክፋት ሸፍተው ለእርቅ ያዘንብሉ። (ሀገሬ እማማ)

…እናት ሀገሬ ነሽ አምላክ የባረከሽ፤

አዝ

ተስፋ ያደረግነው መጣልን ማለዳ፤

ፍርዱ አልዘገየም ወረደ በቁጣ፤

የአምላክ ፍርዱ ወጣ ወረደ በቁጣ። 2

(ወረደ…ሆ)4

አዝ

የሀገሬ ልጆች ቀና በሉ፤

የደስታ ቀን ነው አትዘኑ።

የጸለይነው አግኝተናል፤

ለአስጨናቂያችን፤

መርዶ ሆኗል።

ለቅሶ ሆኗል።

መርዶ ሆኗል።

አዝ

ሰላም ይፋሰስ ይብዛ ይብዛ… አሀሀ፤

ንጋት ሆኗል አልፏል ማታ.. አሀሀ፤

ለአማኑኤል ለንጉሡ…አሀሀ፤

የምስጋና ከበሮ አንሡ…አሀሀ፤

አመስግኑ….አሀሀ፤

ከበሮ. አንሡ….አሀሀ፤

አመስግኑ…

(መስከረም ጌቱ 2013 ልዩ እትም)

**7/ ኢትዮጵያ**

ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ፈጥነሽ፤

**እጆችሽን ወደ እግዚብሔር ዘርጊ፤**

በመከራሽ ዘመን የሚረዳሽ።

አምላክሽ ነውና ወደ እርሱ ተጠጊ።

አዝ

የሃይማኖት ትምክሕት የነጻነት ኩራት፤

ከእምነት የተለየ የሞተ ሥርዓት።

ለበአል አምልኮ ተስሎ ሩቅ ሔዶ፤

የማያድን ስግደት ከእምነት ተዋሕዶ።

አዝ

በተባረክሽበት በመልካሙ ዘመን፤

ጣኦት አስተናግደሽ ከፋፍተሽ በርሽን።

ከጥንት በአላማው ያወቀሽን ጌታ፤

ማረኝ በዓላማው ያወቀሽን ጌታ።

ማረኝ በዪው ፈጥነሽ ዛሬም በይቅርታ፤

ኢትዮጵያ…

ጌጥ የሆነልሽን ለማይረባ ነገር፤

ዕንቁሽን በድንጋይ ወርቅሽ በጠጠር።

የነገድሽላቸው ውድሽን በርካሽ፤

ሽንኮራ አገዳዬ አጋድመው መጠጡሽ።

የታመንሽባቸው ቀኝ እጅሽን ሰተሽ፤

ተገን ያደረግሻቸው ሲሸሹሽ እያየሽ።

እጆችሽ ዘርጊ አሁንስ ይበቃል፤

አለሁ በይ ሲጠራሽ ኢየሱስ ይበጅሻል።

ኢትዮጵያ…

**አውቀዋል አድገዋል ያልሻቸው ልጆችሽ፤**

**ሁሉም እሾህ ሆነው እየወጉ አደከሙሽ፤**

**የአንድነት ማሰሪያ መቀነት ይኑርሽ፤**

**እግዚአብሔር ነይ ይላል ወደ እርሱ ተመለሽ።**

**ጦርነት ረሀብ ስደት ደርሶብሻል፤**

ችግር በየፈርጁ ተፈራርቆብሻል፤

በመከራሽ ብዛት ያፍረት ማቅ ለብሰሻል፤

የሚታደግ አዳኝ ኃያል ብርቱ አጥተሻል።

(ሙሉቀን መለሰ ቁጥር 1 1995)